# ፍሬ ሊቃውንት

## ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት
## እና
## ስብከቶች


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማ/መምሪያ
በማኅበረ ቅዱሳን
የመጻሕፍት ዝግጅት ክፍል



አዲስ አበባ
፲፱፻፺፱ ዓ.ም


www.ethiopianorthodox.org

©ማኅበረ ቅዱሳን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

ALL RIGHTS RESERVED

ይህ መጽሐፍ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
በማኅበረ ቅዱሳን
ኤዲቶሪያል ቦርድ ታርሞ ተስተካክሎ የተፈቀደ ነው።

__አድራሻ__:-

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ
በሰ/ት/ቤቶች ማ/መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
ፖ.ሳ.ቁ 80078
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Email:- lemat@eotc-mkidusan.org
Website;-www.eotc-mkidusan.org

የኮምፒውተር ጽሑፍና ቅንብር
የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት ዋና ክፍል

ፍሬ ሊቃውንት

## ማውጫ

ገጽ

መግቢያ ........ I

ክፍል አንድ

፩. የኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ታሪክ
- ፩.፩. መምህር አካለወልድ፤ «የቀለም ቀንድ» ........ 1
- ፩.፪. አለቃ ዶ/ር አየለ ዓለሙ፤ አራት ዓይና ዶክተር ........ 13
- ፩.፫. ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ........ 22
- ፩.፬. አፈሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ ........ 31
- ፩.፭. እማሆይ ገላነሽ አዲስ ........ 42
- ፩.፮. ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ገብረ ማርያም ........ 49
- ፩.፯. መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ........ 61
- ፩.፰. መምህር ገብረ ሕይወት ሰይፉ ........ 86
- ፩.፱. መምህር ጥበቡ አስናቀ ........ 99
- ፩.፲. ሊቀ ምሁራን ሙሉ ገላው ........ 109

ክፍል ሁለት

፪. ስብከቶች
- ፪.፩. ፍቅር ........ 119
- ፪.፪. «ሰው ዝም ብሎ የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ ቢያደርግ መልካም ነው» ........ 126
- ፪.፫. «የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ» ........ 132
- ፪.፬. ምጽዋት ........ 140
- ፪.፭. «የተባረክሽ ነሽ» ........ 147
- ፪.፮. «ጸሎትህ ተሰምቶልሃል» ........ 156
- ፪.፯. የሚጉድለን ምንድነው? ........ 170
- ፪.፰. «እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው» ........ 177
- ፪.፱. ልጆቻችንን እንዴት እናሳድጋቸው ከክፉ ነገርስ እንዴት እንጠብቃቸው? ........ 182
- ፪.፲. ፍቅር፣ ወጣትነት፣ መንፈሳዊነት ........ 197

www.ethiopianorthodox.org

# መግቢያ

ከዚህ ቀደም ከ«ስምዐ ጽድቅ» ጋዜጣችን ለምእመናን ሕይወት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ይኖራቸዋል ተብለው የታሰቡ ጉዳዮችን «ምሥጢሬን ላካፍላችሁ» ከተባለው ዓምድ ላይ በማሰባሰብ በተለያዩ ክፍሎች በመጽሐፍ መልክ መዘጋጀቱ ይታወቃል። የዚህ ዓይነቱ አሠራር በርካታ አንባብያንን እንደጠቀመና እንደሚጠቅም ብዙዎች ከሚሰጡት አስተያየት ለመረዳት ተችሏል። በዚህ ልምድ ተመሥርተን በ«ሐመር» መጽሔትና በ«ስምዐ ጽድቅ» ጋዜጣ ሲታወሱ የነበሩ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትን ታሪክና በጋዜጣና በመጽሔቱ የስብከት ዓምዶች ቀርበው የሰውን ልብ ለመማረክ የቻሉ ስብከቶችን በማጣመር በመጽሐፍ መልክ አዘጋጅተን አቅርበናል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባሳለፈችው ረጅም የታሪክ ዘመን እንደ ኮከብ የሚያበሩ ከሥራቸው የተነሣ ስማቸው በዓለማችን የክርስትና ጉዞ ውስጥ እጅግ የገነነ እና የተከበሩ ብዙ ሊቃውንት ነበሯት። ከእነዚህ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ቅድስናቸው የተመሰከረላቸው ጥቂቶች ገድልና ተአምራታቸው ተጽፎ ሲዘከሩ ይኖራሉ።

በእርግጥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስተያን ሊቃውንት ሥራና ሕይወት በሚፈለገው ዓይነትና ደረጃ ተጠንቶ ለአንባብያን አለመቅረቡ እንዳለ ሆኖ በዘመነ መሳፍንትና ከዚያ በኋላ የነበሩና ካለፉት ወርቃማ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ዘመናት የተሳለፈውን በረከት ዛሬ ላለነው ያሻገሩ ብርቅዬ የቤተ ክርስቲያኒቱ መምህራን ሕይወትና ታሪክ በአግባቡ ለምእመናን እንዲታወቁ አልተደረገም።

ማኅበረ ቅዱሳን ይህን ክፍተት ለመሙላት በጋዜጣና በመጽሔት ሲቀርቡ የነበሩ የሊቃውንት ታሪኮችን በመጽሐፍ መልክ ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን በማመን ይህን ሥራ ለምእመናን ሲያበረክት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዙሪያ ግን ሰፊና ጥልቅ ጥናት እንደሚያስፈልግ ሳይዘነጋ ነው።

መጽሐፉ በሁለት ክፍሎች የተዘጋጀ ሲሆን በመጀመሪያው ክፍል የተዘጋጁት የሊቃውንት ታሪኮች በተቻለ መጠን በመጽሔቱና በጋዜጣው ከተቀመጡበት መንገድ በይዘት ሳይለይ በቅርጽ ግን መጽሐፍ ሆኖ እንዲቀርብ ተደርጓል። ታሪካቸው ተመርጦ የቀረቡት ሊቃውንት





ዛሬ በሕይወተ ሥጋ ከተለዩን ጥቂቶቹን ነው። እነዚህ ተመርጠው የቀረቡ ሊቃውንት በቤተ ክርስቲያናችን ታላላቅ የአብነት ት/ቤቶች ተምረው አስተምረው አጠናክረው ትውፊቱና ትምህርቱን ትርጉም ባለው መንገድ ጠብቀው ያስተላለፉልን ከምንም በላይ ደግሞ በአገር አስተዳደርና እድገትም መሻሻልና ለውጥ /አዎንታዊ/ እንዲመጣ ሚና የነበራቸው ናቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ ሊቃውንት፣ መምህራንና ባሕታውያን ብቻ ሳይሆን የስብከት ታሪክም ያላት ሆና ስብከት ግን ያላጠራቀመች ቤተ ክርስቲያን ብትኖር የእኛ ቤተ ክርስቲያን ናት ማለት ይቻላል። የአቡነ ሰላማ ስብከቶች የት አሉ? የአቡነ ተክለ ሃይማኖትስ? የአቡነ ዜና ማርቆስ፣ የዘጠኙ ቅዱሳን፣ የዐሥራ ሁለቱ ንቡራነ ዕዶች፣ የሰባቱ ከዋክብት፣ የአምስቱ ከዋክብት፣ የሌሎች ባሕታውያን፣ የመምህራንና የሊቃውንት ትምህርታቸው የት አለ? የለንም። በገድላቸው ውስጥ የተጠቀሱ ጥቂቶች ቢኖሩም እነዚያውም ተአምራቱን ለመናገር የተገለጹ እንጂ ስብከታቸውን ለማስቀመጥ ተብሎ የተገለጹ አይደሉም። እነርሱ ያላቆዩን ምንአልባት በትሕትና ሊሆን ይችላል። የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅና የምሥራቃውያን አባቶች ስብከቶችንስናይም የእኛስ አባቶች የሚል ጥያቄ ይፈጠርብናል።

የቀረቡት እነዚህ ስብከቶች በተቻለ መጠን የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች /ወላጆችን፣ ልጆችን.../ በመንፈስ እንዲያድጉ የሚያግዙ ለማድረግ ተሞክሯል። የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚያግዙ ከመሆናቸው ባሻገር በያዟቸው ጉዳዮች የተለያዩ ሆነው የምእመናንን ልብ በማቅናት ያላቸው አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው የሚል እምነት አለን።

መጽሐፉ የተለያዩ ጉዳዮችን በሁለት ክፍሎች ያቀረበ ቢመስልም ስብከቱን የሊቃውንቱ ፍሬና በረከት እንደሆነ አድርገው አንባብያን ይጠቀሙበታል በሚል እምነትና ለጊዜው ብዙ ምእመናን የተለያየ ፍላጎት ስለሚኖራቸው በዓይነት መለያየታቸው ጠቃሚ ይሆናል ብለን በማመን ነው። በአጠቃላይ ይህን መጽሐፍ ስናዘጋጅ የሊቃውንት ታሪኮችና ስብከቶች ከዚህ በተሻለ አደራጅቶ ማቅረብ የሚቻልበትን መንገድ ከአንባብያን በሚሰነዘሩ ገንቢ አስተያየቶች እንደምናገኝ በማመን ሲሆን ለዚህም ረድኤተ እግዚአብሔር ከሁላችን አይለይ እንላለን።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



www.ethiopianorthodox.org


# መምህር አካለ ወልድ

/፲፰፻፹፬ – ፲፱፻፲፪/

## «የቀለም ቀንድ»

በአሥራት ከበደ

አፈር መልሱ እንጂ ድንጋይ ለምናችሁ፣
የቀለም ቀንድ ነው ትሰብሩ ታላችሁ::
መምህር አካለ ወልድ ቋሱ የት ደረሱ፣
ጎንደር ወረዱ ወይ ሥልጣን ሊመልሱ::
እስቲ በፊድ ስጡኝ አፈሩን ላንፍሰው፣
ያንን ሁሉ ቀለም ወዴት አፈሰሰው::



«ይማሯል እንደ አካልዬ
ይዋጓል እንደ ገብርዬ»

በንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት ነው፣ በወቅቱ አልጋ ወራሽ የነበሩት ልዑል ራስ ተፈሪ መኰንን በተገኙበት በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የነበረን ውሎ የተደረገው:: ውሎውን ያስዋሉት አለቃ እስጢፋኖስ የተባሉ ወንድማቸው ሲሆኑ በወቅቱ የአዲስ አበባ አድባራት አለቆች ካህናት ሁሉ በእነ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅና መምህር የነበረን ውሎ ላይ ተገኝተዋል:: ሊቀ ሊቃውንት አካለ ወልድ ታላቁ መምህር «የቀለም ቀንድ» ይባሉ ነበር:: ከላይ የዚህ ጽሑፍ መንደርደሪያ ሆኖ የተጠቀሰው ግጥም በውሎው ላይ በለቅሶ ታጅበው ከቀረቡት እጅግ ብዙ



www.ethiopianorthodox.org

ግጥሞች ተቆንጥሮ ከወንድማቸው የልጅ ልጅ ከወይዘሮ ትርሲት ትውስታ የተገኘ ነው።

መምህር አካለ ወልድ - «የቀለም ቀንድ»ን ከእሳቸው ዘንድ የተማሩ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና በቅርበት የሚያውቋቸው ሁሉ ዕውቀታቸው ምሉዕ በኩለሄ ነበር ይላሉ። በዚህም የተደነቁና የተከበሩ እስከ ዛሬም በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በትውልድ ዘንድ ሲታወሱ የሚኖሩ ታላቅ መምህር ናቸው። በዕውቀታቸው ስፋት፣ በምሥጢራቸው ርቀት፣ በጥበባቸው ምልዐት፣ በአስተሳሰባቸው ምጥቀት፣ በበሳል አስተያየታቸውና ምክራቸው ያደነቋቸው ዐፄ ቴዎድሮስ «ይማሯል እንደ አካልዬ፣ ይዋጓል እንደ ገብርዬ» ብለውላቸዋል። ይኸው አባባላቸው የዘመናትን ድንበር ተሻግሮ ካለንበት ዘመን ደርሷል።

ታላቁን የቤተ ክርስቲያን ሊቅ መምህር አካለ ወልድን ዐፄ ዮሐንስም ሆኑ ዐፄ ምኒልክ በዕውቀታቸው፣ በምክራቸውና በሚያቀርቡላቸው አስተያየት ሁሉ ያደንቋቸው ያከብሯቸው ነበር።

እኚህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ የታላላቅ ሊቃውንት መፍለቂያ የሆነውን ዛሬም የማንንታቸው ቋሚ መጠሪያ መታሰቢያቸው የሆነ የአብነት ትምህርት ቤት በቦሩ ሜዳ ያቋቋሙ ታላቅ አባት ናቸው።

ሊቁ አካለ ወልድ አባታቸው መምህር ሠርፀ ወልድ እናታቸው እመት ወለተ ኪሮስ /ሙትክ/፣ /በኋላ እማሆይ/ ይባላሉ። የተወለዱት ሰሜን ሸዋ መንዝ ውስጥ ውቢት ዓምባ አቦ በሚባለው ቀበሌ በ፲፰፻፷፬ ዓ.ም ነው። እስከ አሥራ ሁለት ዓመታቸው ድረስ በወላጆቻቸው ቤት ሆነው እየተማሩ አድገው ንባብና ዳዊትን አጠናቀቁ። ከዚያም ትምህርታቸውን ለመቀጠል ከወላጆቻቸው ተለይተው አንድ መነኩሴ ተከትለው ወደ ዋድላና ደላንታ ሔዱ። መነኩሴው ዋድላ ላይ ደጊት ማርያም በምትባል ቤተ ክርስቲያን አባ ጫልቲ ከሚባሉ የቅኔ መምህር ዘንድ እንዲማሩ አስቀመጧቸው። እዚያ ቅኔ ከነ አገባቡ ተማሩ። የቅኔ ትምህርታቸውን አገባቡን ለማስፋፋት የታወቁ የቅኔ መምህራን አሉበት በየተባለበት ቦታ ሁሉ በመቆት፣ በላስታ በኋላም በጐንደር ሲሄዱ የአባ ጫልቲ ተማሪዎች ጥቂቶች ብቻ ሲቀሩ





ተከተሏቸው። ጐንደር ገብተው በቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ደብር ቅኔ እያጠኑ እያስፋፉ ተቀመጡ። ሙሉው አድሪው በቅኔ ብቻ ተወስነው ለመቅረት አልፈለጉም። ጐንደር የቅኔ ጉባኤ ዘርግተው እያስተማሩ ከቅዱስ ዮሐንስ ወደ በኣታ ለማርያም ደብር እየተመላለሱ በኣታ ቤተ ክርስቲያን ከሚገኙት የብሉያት መጻሕፍት ሊቃውንት ዘንድ የደቂቀ ነቢያትን ትርጓሜ ማጥናት ቀጠሉ። መምህር አካለ ወልድ የቀለም ቀንድ ትምህርት አይጠግቡም ነበር። ታላላቅ ሊቃውንት የታወቁ መምህራን አሉበት በተባለበት ቦታ ይሔዳሉ። ጉባኤው እንደተዘረጋ ጐንደር አጣጣሚ ሚካኤልና እልፍኝ ጊዮርጊስ እየተመሳለሱ የመጻሕፍተ አዲሳት ትርጓሜ መማር ጀመሩ። መንገዱ ራቅ ያለ ነበረና መመላለሱ ቢደክማቸው ሐመረ ኖኅ ሥላሴ ምእት ደብር ወጥተው ተቀመጡ። ቅኔ ማስተማርና የመጻሕፍት ቤት ቅጸላው የማይመች ሆኖ ሲያገኙት ቅኔ ማስተማሩን ትተው የጉባኤ ትምህርታቸውን በአንድ ልብ መቀጸል ጀመሩ። በዚህ ሁኔታ ጎንደር በወቅቱ ከነበሩት ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና መምህራን ዘንድ አራቱን ጉባኤያት፣ መጻሕፍተ ብሉያት፣ መጻሕፍተ ሐዲሳት፣ መጻሕፍተ መነኮሳትና መጻሕፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ ጠንቀቁ።

በዚያን ጊዜ ዐፄ ምኒልክ ከሸዋ ተወስደው ጐንደር ከዐፄ ቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት ተቀምጠው በነበሩበት ወቅት መምህር አካለ ወልድ እየሔዱ ይጠይቋቸው ነበር። የጐንደር ሊቃውንት ደብረ ታቦር እየሔዱ ዐፄ ቴዎድሮስን በሚገናኙበት ጊዜ መምህር አካለ ወልድም አብረው እየሄዱ በመጠየቅ ተዋውቀዋል። ዐፄ ቴዎድሮስም ለምደዋቸው ብዙ ጊዜ ስለመጻሕፍት ምሥጢር ይጠይቋቸው ነበር። ሊቁ አካለ ወልድም ትምህርት የተከተተላቸው አንቀጹና ክፍሉ በአእምሯቸው ታትሞ የማይጠፋቸው ነበሩ። ንጉሡ የጠየቋቸውንም ወዲያው ገልጠው በሚገባ እያብራሩ ያስረዷቸው ነበር። ዐፄ ቴዎድሮስም በትምህርታቸው ይደነቁ ይደሰቱ ነበር። ለዚህም ነው ዐፄ ቴዎድሮስ ዘወትር ከሚያደንቋቸውና ከሚመኩባቸው ጀግና የጦር አዛዣቸው ከፊታውራሪ ገብርዬ ጋር እያነጻጸሩ፣



www.ethiopianorthodox.org

*«ይማሯል እንደ አካልዩ*
*ይዋጋል እንደ ገብርዬ»* ብለው የተናገሩት::

ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ መቅደላ ሲሔዱ መምህር አካለ ወልድም በጊዜው የነበሩትን ጳጳስ አቡነ ሰላማን ተከትለው መቅደላ ሔዱ:: ዐፄ ተዎድሮስ በወቅቱ አገርን አንድ ለማድረግ ሲደክሙ፣ ሲወጡ ሲወርዱ፣ የግል ክብርና ዝና የበለጠባቸው ደግሞ እሳቸው የካቡትን ሲንዱ የጭካኔ ሰይፋቸውን ይመዙ ነበር:: በዚህ ጊዜ አካለ ወልድ ለንጉሡ የምክር አሳብ ከማቅረብ ወደ ኋላ አላሉም:: በኋላም በመቅደላ ዐፄ ቴዎድሮስ እየተበሳጩ ሲሄዱ «ከገሞራ ኃይል የበለጠ ኃይል ያለህ እግዚአብሔር ለቴዎድሮስ በጎ ልብ ለሕዝቡም ሰላም ሰጥተህ ይህቺን አገር ጠብቅ» የሚለውን መወድስ ተቀኝተው በሌሊት የመቅደላ ዓምባን ለቀው ወደ ጐጃም ሄደዋል:: በጐጃም ዲማ ጊዮርጊስ ደብር ቆይተው ዐፄ ምኒልክ ሸዋ ገብተው መደላደላቸውን ሲሰሙ ወደ ሸዋ ሔደው ተገናኙ:: ዐፄ ምኒልክም አንኮበር ቁንዲ ጊዮርጊስ ደብርን በአለቅነት ሰጧቸውና ጉባኤያቸውን ጀመሩ:: ቀጥሎም በትውልድ ቦታቸው የምትገኘውን ፍርኩታ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ተሾሙ:: በዚያ ቅኔ እና አራቱን ጉባኤያት /መጻሕፍተ ሐዲሳት፣ መጻሕፍተ ብሉያት፣ መጻሕፍተ መነኮሳትና መጻሕፍተ ሊቃውንት/ ማስተማር ጀመሩ::

ከዚያ በኋላ ዐፄ ዮሐንስንና ዐፄ ምኒልክን ለማስታረቅ ምኒልክን ተከትለው ወደ ቦሩ ሜዳ ከሔዱት ታላላቅ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና መምህራን መካከል መምህር አካለ ወልድ አንዱ ነበሩ:: ሁለቱ ነገሥታት ከተስማሙ በኋላ የወሎን ባላባቶች ክርስትና አንሥተን መምህራን ሾመንላቸው እንሒድ ብለው አሳብ አደረጉ:: ዐፄ ዮሐንስ መሐመድ አባ ሻንቆን /በኋላ ንጉሥ ሚካኤልን/ ክርስትና አንሥተው አጠገባቸው ሆነው የሚያስተምሯቸው መምህር ግርማ የተባሉ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ሀገረ ስብከታቸውን ወረሂመኑ፣ ዓባይ ቤት፣ አሊ ቤት አድርገው መደቡ:: ዐፄ ምኒልክም ይማሙ አባ ዋጠው የሚባሉትን ባላባት /በኋላ ራስ ኃይለ ማርያም/ ክርስትና አንሥተው ለእሳቸው መምህር ሊቁ አካለ ወልድን መድበው ሀገረ ስብከታቸውን ተሁለ ደሬ፣ ቃሉ፣ አጋርፋ፣ አልቡኮ፣ ለጋምቦ ቦረና እንዲሆን ተደረገ::





የይማሙ አባ ዋጠው /በኋላ ራስ ኃይለ ማርያም/ ከተማ ደሴ ነበረና መምህር አካለ ወልድም ደሴ ዛሬ ስልክ አምባ እየተባለ ከሚጠራው ቦታ ታቦተ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ጉባኤ ተክለው ማስተማር ጀመሩ:: ከደቀ መዛሙርታቸው ሁለት ሁለቱን እያደረጉ በሀገረ ስብከታቸው ባሉ የተለያዩ ወረዳዎች ሕዝቡን ወንጌል እንዲያስተምሩ አሠማሩዋቸው:: ጥንትም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት በአካባቢው መሠረቱን ጥሎ ነበር:: በዚህ ትምህርት የእስልምና ተከታዮች የነበሩት በየዕለቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየመጡ ይጠመቁ ጀመር:: በወቅቱ የነበሩት ብዙ ሸሆች የክርስቲያን ሃይማኖት እንዳይስፋፋና እምነታችን እንዳይጠፋ ይህን ቄስ መግደል አለብን እያሉ ተማከሩ:: ከዚያም መምህር አካለ ወልድ አንድ ቀን ወደ ሐይቅ ሲወርዱ ቁልቢ ከምትባል ቦታ እንደ ደረሱ ከተቀመጡበት በቅሎ ጐትተው አውርደው በዱላ ደበደቧቸው:: አንደኛው መምህር አካለ ወልድን ለመግደል ጐራዴውን ሲሰነዝር መሪጌታ ተክለ ዮሐንስ የተባሉትን ደቀ መዝሙራቸውን እጃቸውን አድቋቸው እጅ ሰባራ ሆነው ቀርተዋል:: መምህር አካለ ወልድ እንዲህ ባሉና ሌሎችም በርካታ ፈተናዎች ውስጥ በእግዚአብሔር ጥበቃና ቸርነት አልፈዋል::

ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለሃይማኖት የእምባቦ ጦርነት ባደረጉ ጊዜ ዮሐንስ እጅግ አዘኑ:: ምኒልክ ተክለሃይማኖትን ድል አድርገው ማርከው ሲመለሱ፣ «በቶሎ ይፍቱ በዋስ ተከባችሁ ቦሩ ሜዳ እንድትመጡ» ብለው ላኩባቸው:: ሁለቱም ንጉሦች ዐፄ ዮሐንስ ወዳሉበት ቦሩ ሜዳ ሄደው ከረሙ::

የዐፄ ዮሐንስ ቤተመንግሥት ቦሩ ሜዳ በስተምሥራቅ ከሚገኘው ቁንዲ ከሚባለው ተራራ ላይ ተሠርቶ ነበር:: ዐፄ ምኒልክም ሶስ ገደል ከሚባለው ተራራ ላይ ሠፍረው ነበር:: መስከረም ፲ ቀን ፲፰፻፸፮ ዓ.ም ከሌሊቱ በአምስት ሰዓት በዐፄ ዮሐንስ ቤት ላይ ብርሃን ሰፎበት ታየ:: በዙሪያው የሚገኘው ሕዝብ የንጉሡ ቤት ተቃጠለ እያለ ከየአለበት በመውጣት በዙሪያው ተሰበሰበ:: ከነገሥታቱ ጋር አብረው እጨጌ ቴዎፍሎስም ነበሩ:: ነገር ግን የተቃጠለው የንጉሡ ቤት ሳይሆን በቤቱ ላይ ዙሪያውን የሚያበራው የተለየ ብርሃን ሆኖ አገኙት::



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ነገር ዐፄ ዮሐንስ ተደነቁ። ከእንግዲህ ወዲህ ይህ ቤት ለእኔ አይገባም። የአንድነትና ሦስትነት መናገሪያ የሥላሴ ምስጋና የሚደርስበት፣ ሥጋውና ደሙ የሚፈተትበት ይሁን አሉ። ወዲያውኑ ብርሃኑ እንጻለ ባርኩት ብለው እጨጌ ቴዎፍሎስ ቆመው ባረኩት። ይህ ሁሉ ሲሆን ብርሃኑ እየጨመረ እየፈካ ይሄድ ነበር። እንዲህ ሆኖ አድሮ ሲነጋ ከፀሐይ ብርሃን ጋር ተቀላቀለ። ዐፄ ዮሐንስ ወዲያው ግምጃ ድንኳን ከውስጡ አስተክለው፤ በስመ ሥላሴ ብለው ደብር አደረጉት። ቦታውን በዚህ ሁኔታ ካከበሩት በኋላ ወሎን በማስተማር አምስት ዓመት ያህል የቆዩትን መምህር አካለ ወልድን «ቦሩ ሜዳ ለእርስዎ ይገባል» ብለው ሾሟቸው። ለደብሩ መተዳደሪያም ሰፊ መሬትና ገንዘብ ሰጡ። መምህር አካለ ወልድ የቅድስት ሥላሴ ስም በአንድ ቦታ ብቻ ከሚጠራ በየቦታው ይመስገኑ በማለት ለቦሩ ሥላሴ ብቻ ተሰጥቶ የነበረውን በርካታ መሬት በማከፋፈል በተሁለደሬ ወረዳ ውስጥ ብቻ በተለያዩ አጥቢያዎች አሥራ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት አሠርተዋል። እነሱም ሞፋ ኪዳነ ምሕረት፣ ቁባፍታ ቶማስ፣ ገደራ ጊዮርጊስ፣ ቀጠማዬ ተክለ ሃይማኖት፣ ቡቂ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ፣ ሱሉሳ ተክለ ሃይማኖት፣ ዘንጊታ ሚካኤል፣ ሐራ ማርያም፣ ሐራ መድኃኔዓለም፣ ዋሄሉ ተክለ ሃይማኖት፣ ቀጋ ዓምባ ጊዮርጊስ፣ አዱምባዣ ጊዮርጊስ ናቸው።

ከዚህ በኋላ የቦሩ ሥላሴ ደብር አዲስ በመሆኑ በየቦታው የተማሩ ካህናትና ዲያቆናት መምጣት ጀመሩ። በተለይም መምህር አካለ ወልድ መኖራቸው ሲሰማ ትምህርት ፈላጊው ተሰበሰበ። በዘመኑ ረሃብ በሆነ ጊዜ /፲፰፻፹፪ - ፲፰፻፺፬ ዓ.ም/ ዐፄ ምኒልክ ሶስ ገደል ከሚገኘው መሬታቸው የሚመረተውን እህል ተማሪዎቻቸው እንዳይቸገሩ በማለት ለመምህር አካለ ወልድ ሰጥተዋቸው ነበር። በዚህ የተነሣ ብዙ ሕዝብ በየጊዜው ወደ ቦሩ ሥላሴ እየመጣ ድርጎ በመቀበል ይማር ነበር።

ታላቁ ሊቅ መምህር አካለ ወልድ - የቀለም ቀንድ ድንግላዊ መነኩሴ ነበሩ። የግሌ የሚሉት የገንዘብ ወይም ቁሳዊ ሀብት አልነበራቸውም። ከንጉሥታቱ በየጊዜው ከተሰጣቸው መሬት ሰፊ ግቢ ማግኘት ቢችሉም አይፈልጉም ነበር። ገንዘብ ሳጠራቅም ሀብት ሳከማች ሳይሉ በደብሩ አካባቢ ላለውም ሆነ ከሩቅ ቦታ ለሚመጣው ሰው ሁሉ ልብስ ለቸገረው ልብስ፣ ለተራበው እህል መስጠት አቅመ ደካማ ድሆች እንዲረዱ ማድረግ የዘወትር ተግባራቸው ነበር።

የመምህር አካለ ወልድን ቅድስናና ደግነታቸውን በተመለከተ አባ ገብረማርያም የሚባሉ የዋልድባ መነኩሴ የተናገሩት እንደ ምሳሌ ሲጠቀስ ይኖራል። አባ ገብረ ማርያም የተባሉት መነኩሴ መጽሐፈ መነኮሳትን ከሊሳው ቤት ቀጽለው ነበር። ከመምህር አካለ ወልድም ሊያደርሱ መጥተው መምህርን ብዙ ጊዜ አስተውለዋል። በኋላም በአድናቆት «እንዲያው በከንቱ ብራና እናገላብጣለን እንጂ መጽሐፈ መነኮሳት ማለት የአባቸውን ሰውነታቸውን ሁልጊዜ መመልከት ነው። አነጋገራቸው፣ አስተያየታቸው፣ አለባበሳቸው፣ አካሔዳቸው ለመነኮሳት ሌላ ትምህርት አያስፈልግም ነበር» በማለት ተናግረዋል።

ቦሩ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የተተከለበት ቦታ ከተራራ ላይ በመሆኑ እንደ ልብ አይገኝም ነበር። እንዲሁም የአካባቢው ሕዝብ የሚኖረው በገበያው ዙሪያ ስለሆነ ተራራውን በመውጣት በመውረድ ስለተቸገረ ቤተ ክርስቲያኑ አሁን ወደ ሚገኝበት ቦታ የተዛወረው በ፲፰፻፺፰ ዓ.ም ነው።

መምህር አካለ ወልድ በአበራ /ቦሩ ሜዳ/ ሥላሴ ጉባኤ ዘርግተው ተማሪዎቻቸውን የዕለት ግብር እያበሉ እያጠጡ እያለበሱ ያስተምሩ ነበር። አራቱ ጉባኤያት ሐዲሳትና ብሉያት፣ ሊቃውንትና መጻሕፍተ መነኮሳት በሰፊት ይነገሩ ነበር። የቅኔና የዜማ ጉባኤ ቤቶችም ነበሩ። በዚህ ሁኔታ ከአምስት መቶ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች ከሳቸው ጉባኤ ቀለብና ልብስ እየተሰጣቸው በአዳሪነት ይማሩ ነበር። በቦሩ ሥላሴ የነበሩት ያስተምሩ የነበሩ መምህራንም እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል።

፩. በቦሩ ሜዳ ሥላሴ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ የነበሩት ሊቃውንት የብሉያት መጻሕፍት መምህራን፤ መምህር ፊላታዎስ፣ አለቃ ወልደ ማርያም፣ አለቃ ካሣ /የአብርሃ አጽብሐ ገዳም/፣ መምህር ኪሮስና አለቃ ኢያሱ፣



www.ethiopianorthodox.org

፪. የሐዲሳት መምህራን፤ መምህር ወልደ ሚካኤል /የዜና ማርቆስ/፣ አለቃ ወልደ ማርያም የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አለቃ የነበሩ፣ መምህር ወልደ ሰማዕት፣ አቡነ አብርሃም፣ አለቃ ውቤ /የማኅደረ ማርያም/፣ መልአከ ብርሃን ጽጌ፣ መልአከ ብርሃናት ወልደ ተክሌ፣ መልአከ ብርሃን ጽጌ፣ መልአከ ገነት አፈወርቅ ናቸው።

፫. የመጻሕፍተ ሊቃውንት መምህራን፤ አለቃ ዘዮሐንስ የጉንደሩ አለቃ ወልደ ማርያም፣ መልአከ ብርሃናት ወልደ ተክሌ

፬. የመጻሕፍተ መነኰሳት መምህራን፤ መምህር ፊላታዎስ፣ መምህር ገብረ ማርያም፣ መምህር ገብረ ኢየሱስ /የጀር ገዳሙ/፣ መምህር ወልደ አማኑኤል /የደብረ ከርቤው/ ናቸው።

፭. የዜማ መምህራን፤ ሊቀ ካህናት መርሻ፣ የቤተ ልሔሙ መልአከ ፀሐይ አፈወርቅ፣ የጎንደር አቋቋም መምህር ቀኝ ጌታ ሳቀው ናቸው።

፮. የቅኔ መምህራኑ፤ አቡነ አብርሃም፣ መምህር ወልደ ሰማዕት፣ መምህር ኪሮስ፣ መምህር ኢያሱ ናቸው።

፯. መጻሕፍተ መነኰሳትንና መጻሕፍተ ሊቃውንትን መምህር አካለ ወልድ የዘወትር ጉባኤያቸው ስለሆነ ታላላቆቹ ሊቃውንት መምህር ወልደ ሚካኤል፣ አቡነ ይስሐቅ፣ አቡነ አብርሃም፣ አቡነ ጴጥሮስ፣ አለቃ ወልደ ማርያም፣ ሊቀ ካህናት መርሻ፣ መልአከ ብርሃናት ወልደ ተክሌ፣ አለቃ ገብረ መድኅን /የሐረርጌው/፣ መልአከ ብርሃን ጽጌ ሌሎችም መምህራን የመምህር አካለ ወልድን ጉባኤ ከሰሙ በኋላ የራሳቸውን ጉባኤ ለማስተማር ወደ የሥፍራቸው ይመለሱ ነበር። በሊቃውንቱ መካከል በንባብና በትርጓሜ አካሔድ የተነሣ ክርክር ሲነሣ በታመነ ምስክርነታቸው እያብራሩ ይገልጹላቸው ያስረዷቸው ነበር።

ዐፄ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ መምህር አካለ ወልድ ከዐፄ ምኒልክ ጥሪ ደርሷቸው አንኮበር ሔዱ። ዐፄ ምኒልክ አንኮበር ቅዱስ ሚካኤልን ማረፊያ ሰጥተዋቸው ጥቂት ጊዜ ቆይተዋል። እንደገና ቦሩ ሜዳ ከተመለሱ በኋላም ዐፄ ምኒልክ ለምክር እያስጠሯቸው ሁለት ሦስት ጊዜ አዲስ አበባ መጥተዋል። መምህር አካለ ወልድ በየሄዱበት ጉባኤው አይጓደልም ነበር። አዲስ አበባ መጥተው በቆዩበት ጊዜ እነ መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ ጉባኤ ቀጽለዋል። ከሊቁ አካለ ወልድ ዘንድ የተማሩትን ተማሪዎች ከብዛታቸው የተነሣ ይኸን ያህል ነው ለማለት አስቸጋሪ ነው። ከደቀ መዛሙርታቸው ውስጥ ከጳጳሳት አቡነ ይስሐቅ፣ አቡነ አብርሃም፣ አቡነ ጴጥሮስ ይገኙበታል። ሌሎቹም የታላላቅ አድባራት አለቆች፣ የገዳማት አስተዳዳሪዎች፣ ታላላቅ ሊቃውንትና መምህራን እየሆኑ ቤተ ክርስቲያንን አገልግለው ያለፉ፣ እጅግ ብዙ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትን ያፈሩ በርካታ ናቸው።

መምህር አካለወልድ ኢየሩሳሌም ሄደው ቅዱሳት መካናትን መሳለም የዘወትር ምኞታቸው ነበር። ጊዜው ሲደርስ ዐፄ ምኒልክን ተሰናብተው በምጽዋ በኩል ለመሻገር በ፲፰፻፺፩ ዓ.ም ወደ ትግራይ ሔዱ። በወቅቱ የትግራይ ገዢ የነበሩት ልዑል ራስ መኰንን «መርከብ በመጣ ጊዜ እንማርዎትና መንገድዎን ይቀጥላሉ» ብለው አባ ገሪማ የሚባለውን ገዳም ሰጥተዋቸው በዚያ ቆዩ። ልዑል መኰንን ነገ ከነገ ወዲያ ይሄዳሉ እያሉ ስድስት ወራት ያህል አቆዩዋቸው። እውነተኛው ምክንያት ግን አብዛኛውን ጊዜ ልዑል ራስ መኰንን የመጻሕፍትን ምሥጢር እየጠየቋቸው ይተረጉሙላቸው ያብራሩላቸው ነበረ። በዚህ ምክንያት በጣም ያከብሯቸውና ያፈቅሯቸው ነበረና እንዲቆዩላቸው በማሰብ ነው ይባላል። ከዚያ በኋላ የዜና ማርቆሱን መምህር ወልደ ሚካኤልን፣ የአንኮበሩን ኋላም መንነው ደብረ ዳሞ መጽሐፈ መነኰሳትን ያስተምሩ የነበሩትን መምህር ገብረ ማርያምን፣ መምህር ዓምደ ሥላሴን /የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም አበምኔትን/፣ አባ ወልደ ዮሐንስን፣ የወንድማቸውን ልጅ መልአከ ፀሐይ ተክለ አቢብንና አቶ ኃይሉ ተክለ ማርያምን ይዘው ወደ ኢየሩሳሌም አቀኑ። በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ቅዱሳት መካናትን እየዞሩ ተሳልመው ዐቢይ ጾምን በመካነ ቀራንዮ ከርመው ወደ አገራቸው ተመለሱ። ደሴ ከተማ በገቡ ጊዜ የአካባቢው ሕዝብ እስላም ክርስቲያን ሳይል በጠቅላላ በአንድነት ተሰብስበው «በክፉ ቀን ከጐተራ እህል እያወጡ እስላም ክርስቲያን ሳይሉ ለሁሉም ያከፋፈሉ ሰው እንኳን ደኅና መጡ» ብለው በደስታ ተቀበሏቸው።



www.ethiopianorthodox.org

ብዙ የእስልምና እምነት መሪዎች «ይህ ሰው የአሳህ ሰው ነው። ማተብ ይኑረው አይኑረው አናውቅም። ብቻ እሱን የሚጠላ ሐራም ነው። ቢ ሞትም ክርስቲያንና እስላም ዛንድነት ዛውያ /ጸሎት/ ሊያደርጉለት ይገባል።» ብለው የእንኳን ደኅና መጡ ምስጋና ማቅረባቸውን የሐይቁ ገዳም አበምኔት /ዓቃቤ ሰዓት/ መምህር ዓምደ ሥላሴ ስለ ጉዟቸው በጻፉት ማስታወሻ ተመዝግቦ ተገኝቷል። ከበዓታቸው ቦሩ ሜዳ ሥላሴ በገቡ ጊዜ ጉባኤው በጣም ተሰፋፍቶ ስላገኙት እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

መምህር አካለ ወልድ ከቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና ከመምህርነቱ ሥራ ጋር በንጉሥታቱና በባላባቱ መካከል አለመግባባትና ግጭት ሲፈ ጠር ሽምግልና እየተጠሩ ያስማሙ ነበር። በአንድ ወቅት ንጉሥ ሚካ ኤልና ራስ ወሌ በግዛት ወሰን ተጣልተው በነበረ ጊዜ እንዲያስማሙ ዋቸው እቴጌ ጣይቱ የጻፉላቸው ደብዳቤ፣ እንዲህ ይላል፦

*የተላከ ከእቴጌ ጣይቱ*
*ብርሃን ዘኢትዮጵያ*
*ይድረስ ለመምህር አካለ ወልድ*
*ሕመምዎን እንደምን ሆነዋል ዛሬ አልተሻለዎትም?*
*እኔም በእግዚአብሔር ቸርነት ጤናዬን ደኅና ነኝ።*

*ምንም የለብኝም ነገር ግን በራስ ሚካኤልና በራስ ወሌ መካከል የገባውን ሰይጣን እንደ ወትሮው በጣም ጠንክረው ከንቱን ሰብረው እንዲያስማሙልኝ ይሁን አደራዎን አባቴ። ለሁሉም ነገር እርስዎን የሚረዱ የሚያስማሙ ሰዎች በማለዳ ሰኞ ተነሥተው ይመጣሉ።*

*ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፲፪ ዓ.ም ተጻፈ።*

መምህር አካለ ወልድም ከእጨጌው ከመምህር ወልደ ጊዮርጊስ ጋር ሆነው በሁለቱ ባላባቶች /ገዢዎች/ መካከል ግጭት እንዳይፈጠር ማድረጋቸው ይነገራል። ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ በነበሩበት ጊዜ በሰኔ ወር ፲፱፻፲፮ ዓ.ም ለመምህር አካለ ወልድ፣ «የመጻሕፍተ መነኰሳት ንባባቸው ከነትርጓሜያቸው ተዘጋጅቶ ቢመ ጣልን ይህን ለመሰለ የመንፈሳዊ ጽሑፍ ሥራ ማተሚያ እንዲሆን





ባስመጣሁት የጽሕፈት መኪና አሳትመን ለየገዳማቱ ለመስጠት ይቻል ነበር።» ብለው ደብዳቤ ላኩላቸው። እርሳቸውም «እንግዲህ እኛ ችላ ብንል እግዚአብሔር ይፈርድብናል» በማለት ትርጉሙን ለመሥራት ተነሡ። ቦሩ ሜዳ ሆነው ለመሥራት የማያመቻቸው ሲሆን ጸጥታ ወደ ሰፈነበት ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ወርደን እንጀምረውና ፈጻሚውን እግዚአብሔር ያውቃል ብለው ሊቃውንቱን አስከትለው ወረዱ።

የትርጓሜውን ሥራ በሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ሆነው እንደ ጀመ ሩት ታመሙ። ሕመማቸውም ስለ ጸናባቸው ወደቦሩ ሥላሴ ቢመለ ሱም ሊሻላቸው አልቻለም። በተወለዱ በሰማንያ ስምንት ዓመታቸው ኅዳር ፱ ቀን ፲፱፻፲፪ ዓ.ም ዐረፉ። ዐፅማቸው እያስተማሩ ሲያገለግሉ በኖሩበት ቦሩ ሜዳ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አርፎ ይገኛል።

እኚህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ፣ መምህርና አባት በቦሩ ሜዳ ሥላሴ ባቋቋሙት የአብነት አዳሪ ት/ቤት እጅግ በርካታ ሊቃውንትን አፍርተዋል። እነዚያም ታላላቅ ሊቃውንት ሌሎች በርካታ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን ተክተዋል። ሊቁ አካለ ወልድ የመሠረቱት ታላቅ የአብነት ትምህርት ቤት እስከ አለንበት ትውልድ ድረስ አእላፍ ተማ ሪዎች የቤተ ክርስቲያኒቷን ትምህርት ሲማሩበት ቆይተዋል።

መምህር አካለ ወልድ በሕይወት ዘመናቸው የጻፏቸው፣ ያጻፏቸ ውና ያሰባሰቧቸው እጅግ ብዙ ድንቅና ጥንታውያን የብራና መጻሕፍት ዛሬም በቦሩ ሥላሴ ደብር ይገኛሉ። እንዲሁም ነገሥታቱና መሳፍንቱ በየወቅቱ የሰጡት የወርቅ፣ የብር፣ የነሐስ መስቀሎች፣ ጽዋዎች ሌሎ ችም ጥንታውያን ንዋያተ ቅድሳት፣ አልባሳትና ቅርሳ ቅርሶች አሉ። እነዚህ ንዋያተ ቅድሳትና ጥንታውያን ቅርሶች እንዲሁም መጻሕፍት ተቀምጠው የሚገኙት የመምህር አካለ ወልድ ዐፅም ባረፈበትና በንግ ሥት ዘውዲቱ መልካም ፈቃድ በተሠራው መቃብር ቤት ውስጥ ነው።

ዛሬ በዚህ ትውልድ ጊዜ ለሰማንያ አራት ዓመታት ያህል ያለ ምንም ጥገና የቆየው በውስጡ የቤተ ክርስቲያንም ሆነ የአገር ቅርስ የያዘው መቃብር ቤት በአገልግሎት ዘመን ብዛት ተሰነጣጥቆ እየፈራ ረሰ ነው። እነዚያን ድንቅና ጥንታውያን ንዋያተ ቅድሳትና መጻሕፍት



www.ethiopianorthodox.org

በአስተማማኝ ሁኔታ ለመጠበቅ በማያስችል ደረጃ የመቃብር ቤቱ መዝጊያና መስኮት ተሰነጣጥቀዋል:: እኒያ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን አባት ያሰባሰቧቸው መጻሕፍት፣ ንዋያተ ቅድሳት ጥንታውያን ቅርሶች አደጋ ላይ ወድቀው የትውልዱን አፋጣኝ እርምጃ ይሻሉ::

ያ የእልፍ አእላፋት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን መፍለቂያ፤ ለአንዲት ቀን ሳያቋርጥ ከሁሉም ጉባኤ ቤቶች ምሥጢር የሚዘንብበት ከየአገሩ በአራቱም መዓዝናት የሚሰበሰቡ ደቀ መዛሙርት መናኸሪያ የነበረ ታላቅ የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ቤት፤ ዛሬ መምህራንና ተማሪዎቹ ችግር ጠንቶባቸው፣ ረዳት አስታዋሽ አጥተው፣ ጉባኤው ተበትኖ ጭር ብሏል:: ትዕግሥት በተሳበሰ ዝምታ የቦሩ ሜዳ ሥላሴ ደብር ሰበካ ጉባኤ የትውልዱን ምላሽ አፋጣኝ መፍትሔ ይጠባበቃል::

ምንጭ:-

- ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ዶ/ር፤ አማርኛ <u>የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት</u>፤ አዲስ አበባ፤ ፲፱፻፹፩ ዓ.ም::
- አለቃ ገብረ ዮሐንስ ገ/ኪዳን፤ <u>የመምህር አካለ ወልድ የሕይወት ታሪክ</u>፣ ያልታተመ እጅ ጽሑፍ::
- ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ፤ <u>ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ</u> ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፤ /አዲስ አበባ ፲፱፻፶፱ ዓ.ም/ ገጽ ፪፻፹፯::
- ዜና ቤተ ክርስቲያን ዘኢትዮጵያ፤ ሁለተኛ ዓመት ቁ. ፳፫ ኅዳር ፴ ቀን ፲፱፻፵ ዓ.ም::
- <u>የካቲት መጽሔት</u>፤ ሚያዚያ፣ ግንቦት፣ ሰኔ ፲፱፻፹፫ ዓ.ም






# አለቃ ዶ/ር አየለ ዓለሙ

/፲፰፻፺፯ – ፲፱፻፺፱/

በመሠረት ክበደ



አራት ዓይና ዶክተር

የሃምሳኛ ዓመት በዓለ ዕረፍታቸውን መታሰቢያ አስመልክቶ ጥር ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ.ም በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት የታተመው መጽሔተ ሊቃውንት «የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሊቅነታቸውን በመረዳት በ፲፱፻፺ ዓ.ም በሰኔ ወር የዶክተርነት ማዕረግ ሰጥቷቸዋል:: በዚህም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የመጀመሪያውና ብቸኛው ናቸው:: የሊቃውንት ኮከብ የተባሉትም ስለዚህ ነው» በማለት ስለእኚህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ገልጿል::

አለቃ ዶክተር አየለ ዓለሙ የክብር ዶክትሬት ከተቀበሉ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የመጀመሪያው ናቸው:: ከዚህ መዓርግ በተጨማሪ አራት ዓይና የሚል የቤተ ክርስቲያን መዓርግ አላቸው:: ይህ መዓርግ የሚሰጠው በቤተ ክርስቲያን ትምህርት የጠለቀ ዕውቀት ላላቸው አራቱን ጉባኤያት ለሚያስተምሩ ሊቃውንት ነው:: አራቱ ጉባኤያት የሚባሉት መጻሕፍተ ብሉያት፣ መጻሕፍተ ሐዲሳት፣ መጻሕፍተ ሊቃውንት እና መጻሕፍተ መነኮሳት ናቸው:: መጻሕፍተ ብሉያት አጠቃላይ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን የሚያጠቃልል ሲሆን መጻሕፍተ ሐዲሳት አራቱን ወንጌላውያንና የጳውሎስ መልእክታትና ሌሎች ይጠቃለላሉ:: መጻሕፍተ ሊቃውንት ውስጥ የሚካተቱት ፍትሐ ነገሥት፣ ቄርሎስ፣ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ሃይማኖተ አበው፣ መጻሕፍተ ቅዳሴያትና የመሳሰሉት



www.ethiopianorthodox.org

ናቸው:: መጻሕፍተ መነኩሳት የመነኩሳትን ተጋድሎና ክብር የሚ ናገሩና ማር ይስሐቅ፣ አረጋዊ መን ፈሳዊና ፊልክስዩስን ያካተተ መጽሐፍ ነው:: አለቃ ዶ/ር አየለ ዓለ ሙም የነዚህ ሁሉ ዐዋቂ ናቸው::

በይነ ምንት ዘተጎብአ ኪዳነ ማርያም ዕንቈ ባሕርይ ያበርሁኑ፣
ለምድር ውስቴታ ሥነ ጸዳሉ አእምሮ፣
ወእርድእት ኃለፍት ትርጓሜ ይክሉኑ ነጽሮ፣
ገጸ መጻሕፍት አድባር ዘሙሴ መጽሔተ ገጹ ተምህሮ፣
እስመ ለጉባኤነ ተሠወሮ፣
ወእፎመ ሞት ጎምዘ ተፅዕሮ፣
ለመዓር ልሳኑ እምረሮ::

አለቃ ዶ/ር አየለ ዓለሙ ባረፉ ጊዜ ከቀረቡት ቅኔዎች መካከል አንዱ ዶ/ር አየለ ዓለሙ የተወለዱት ጐንደር ጭልጋ አውራጃ በዳዋ ወረዳ ይተና ማርያም የተባለች ቦታ ነው:: አባታቸው አቶ ዓለሙ ኪ ዳነ ማርያም እናታቸው ደግሞ ወ/ሮ ማን አህሉሽ ወ/ጊዮርጊስ ይባ ላሉ:: ዶክተር አየለ በ፲፱፻፳፪ ዓ.ም ተወለዱ::

ሕፃን አየለ አባታቸውን ያጡት ገና በልጅነታቸው ነበር:: እናታ ቸው ወ/ሮ ማን አህሉሽ ባለቤታቸው በሞት ከተለዩዋቸው በኋላ ልጃ ቸውን አየለ ዓለሙን ይዘው ወደ ትውልድ መንደራቸው ገንደዋ ገብርኤል ሔዱ:: ጐንደር አውራጃ ከመምጣታቸው በፊት አየለ ዓለሙ እዛው የትውልድ ቦታቸው አቦ ገዳም መሪጌታ ሳህሉ ጋር ትምህርት ጀምረው ዳዊት ላይ ደርሰው ነበር:: አለቃ አጎት ነበሯቸው:: የዜማ መምህር የድጓ መምህር የሆኑት እኒሁ አጐታቸው አለቃ አበራ ይባላሉ:: አለቃ ወ/ሮ ማን አህሉሽን ያስፈቅዱና ሕፃኑን አየለን ጐን ደር አዘዞ ተክለሃይማኖት ወሰዷቸው:: አእምሯቸው በስሎ ራሳቸውንም እስኪችሉ በማለት አለቃ አበራ ከእርሳቸው ጋር እንዲኖሩ ያደርጋሉ:: ወደ ሌላ ትምህርት ቤት የሚሔዱበት ቀን እስኪደርስ በዜማ ትም ህርት እየበሰሉ ሔዱ:: እንደውም አንዳንዴ አለቃ ተማሪዎቻቸው ቀለም ሲጠፋቸው ለማትጋት አየለን እንዲጠይቁ ለተማሪዎቹ ይነግራ ሉ:: የአዘዞ ተክለሃይማኖት ደብር ታላላቅ ሊቃውንትም አየለ ዓለሙ





ሲቃኙ መስማት ይወዱ ነበር:: ዐቢይ ጾም በመጣና ጾመ ድጓ በተቆመ ቁጥር «አየለ ይቃኘው» ይሉ ነበር:: በዚህ ሁኔታ ወደ ትምህርት ዓለም የገቡት አለቃ ዶክተር አየለ ዓለሙ በአንድ ወቅት በአንድ መምህራ ቸው «ፍሳቴ» በሚል ቅፅል መጠሪያ ይጠሩ ነበር:: መምህሩ በተማሪ ያቸው የቀለም መያዝ ስጦታ በመደነቅ ነበር ይህን መጠሪያ የሰጧቸው::

## ጠባይዕ

አለቃ ዶክተር አየለ ዓለሙ በብዙዎች ዘንድ የሚታወቁት በትኅት ናቸው፣ ባላቸው ከፍተኛ ቀለም የመያዝ ስጦታ፣ በርኅሩኅነታቸውና ደከ መኝ ሰለቸኝ የማያውቁ በመሆናቸው ነው:: ስለ ትኅትናቸው የበጌ ምድርና የሰሜን ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ እን ድርያስ እንዲህ ብለው ነበር:: «ዶ/ር አለቃ አየለ ብዙ ደቀመዛሙ ርትን ተከተውልን አልፈዋል፤ ከትኅትናቸውና ከትዕግሥታቸው ግን አንድም አልተከሉልንም»:: ቀለም ቶሎ የመያዝ ብቻ ሳይሆን ያለመዘን ጋት ችሎታም ነበራቸው:: ይኸው ስጦታቸው ነበር «ፍሳቴ» የሚለውን የአድናቆት ስም ያስጣቸው:: ተከታዮቻቸውና ተማሪዎቻቸው አራቱን ጉባኤያት አለቃ በሚያስተምሩ ጊዜ ቀለም በመዘንጋት አለመቸገራ ቸውን እያዩ እንደሳቸው መሆንን እየተመኙ ችሎታቸውን ያደንቁ ነበር::

አለቃን የሚያውቁ ስለ ጠባያቸው ሲናገሩ የርኅሩኅነታቸውን ነገር ያስታውሳሉ:: ለጋስ እንደሆኑ ይነገራል:: አንድ ጊዜ ገንዘብ ያዥ ያቸውን ስንት ብር እንዳለ ይጠይቃሉ:: እሱም አንዲት አምስት ብር እንደቀረች ይነግሯቸዋል:: ይወስዱና ወደ ውጭ ወጥተው «ማን ነው ገንዘብ ያልደረሰው?» ብለው ይጠይቃሉ:: በአጋጣሚ የደረሰ ችግረኛ «እኔ አለሁ» ብሎ ብሯን ተቀብሎ ሄደ::

አለቃ አየለ ዓለሙ ታላቅ መምህር ስለነበሩ በንጉሡ ነገሥቱ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ቀለብ ይሰጣቸው ነበር:: ይህን ቀለብ ይወስ ዱና ለችግረኞች ያከፋፍላሉ:: የሚሰጣቸውንም ገንዘብ በየጉ ዳናው ላሉ ችግረኞች አከፋፍለው ወደ ቤታቸው ይገባሉ:: ይህ ዝናቸው በጐ ንደር አካባቢ ባሉ ሥፍራዎች ሁሉ ታወቀ:: ጎንደር አውራጃ በጉባኤ ማስተማር ሲጀምሩ በርካታ ተማሪዎች ወደሳቸው መጡ:: ቀለብ



www.ethiopianorthodox.org

ተካፋዩ ሲበረክት የሚያገኘውም ይበዛ ጀመር:: ስለዚህ አንድ ዘዴ
አመጡ አለቃ በገንዘብ ያገኙ በኩል ቀለባቸው ለችግረኞቹ እንዲ
ከፋፈል ተደረገ::

ይህን ተግባራቸውን መንግሥት ስላወቀ የዕለት ምግብ ከቤተ መን
ግሥት ተፈቀደላቸው:: በዚህ ጊዜ በየደጀሰላሙ ያሉ ደጅ ጠኚዎች
ነገር አሳሰባቸው:: ሊጠይቋቸው ሲመጡም ለመለመን ያፈሩ ግን በረ
ሀብ አለንጋ የሚገረፉ መሆናቸውን ስለሚያውቁ ከዕለት ድርጓቸው
ያካፍሏቸዋል:: አሁንም በምግብ እየተጐዱ መሆኑ ሲታወቅ የእንግዳ
መቀበያ ተፈቀደላቸው::

እንደዚህ አድርገው ድንገት ችግረኛ የመጣባቸው ከሆነና የሚሰ
ጡት ከሌለ ከደቀመዛሙርታቸው ይበደሩና ይሰጣሉ:: አለበለዚያ ከመ
ንግሥት ባለ ሥልጣናት የችግረኞች መርጃ እየጠየቁ ያመጡና ተማሪ
ዎቻቸውንና ድሆችን ይረዱ ነበር::

አለቃ ዶክተር አየለ ዓለሙ ወገኖቻቸውን መርዳት በጣም ይወ
ዳሉ:: ባለ ጉዳይ ሲጉላላ ደስ አይላቸውም:: እጅ ለመንሣት ባለሥል
ጣናት ጋር በሚሔዱ ጊዜ ባዶ እጃቸውን አይገቡም:: የባለ ጉዳዮችን
ደብዳቤ ይዘው ይሔዱና ሲወጡ ባለሥልጣኑ ፊት ደብዳቤዎቹን አስ
ቀምጠው ይወጣሉ:: ይህ ድርጊታቸው አንዳንድ ባለሥልጣናትን ቢያስ
ከፋም ብዙዎቹ ይወዱላቸዋል:: ባለ ሥልጣን ጋር የሚያደርሳቸው የጡ፤
ፍትሕ ርትዕ የሚሹ ወገኖችን ጉዳይ ይዘው እንደሚመጡ ያውቃሉና::
እሳቸውም ራሳቸውም ቢሆኑ ባለሥልጣናቱ እንዳይቀየሙ የድሆች ልንባ
መፍሰስና የፍትሕ ርትዕ መታጣት ሀገርን እንደሚጐዳ በመግለፅ ነገ
ሩን ያስረዷቸዋል::

አለቃ አየለ ለብዙዎች በድካማቸው ጊዜ ኃይል ናቸው:: ደከመኝ
ሰለቸኝ ብለው የሚያስታጉሉት ነገር የለም:: በጸሎትም በማስተማርም
የተጉ ናቸው:: ይህን ጠባያቸውን የሚያውቁ በ፩ኛ ጢሞ.፬÷፲፩-፲፪
የሚገኘውን «ምክር አስተምር በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በን
ጽሕናም ለሚያምኑ ሁሉ ምሳሌ ሁን እንጅ ማንም ታናሽነትህን አይና
ቀው እስከመጣ ድረስ መጽሐፍ በማንበብና በመምከር በጸሎትም ተጠ





ብቀህ ኑር:: ይህንም አዘውትር:: እንዲህ ያደረግህ እንደሆነ ራስህንም
የሚሰሙህንም ታድናለህ» የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስን ምክር በተግባር
የገለፁ ይሏቸዋል::

እኚህ ታላቅ ሊቅ ከማለዳው አሥራ አንድ ሰዓት እንሥተው እስከ
ሰባት ሰዓት ድረስ አራቱን ጉባኤያት በተራቸው ሲተረጉሙና ሲ
ያስተምሩ ይውላሉ:: እንዲህም ሆኖ የተማሪዎቻቸው ቁጥር በርካታ
ስለሆነ እያንዳንዱ ተማሪ አይደርሰውም:: ከሰዓት በኋላ ምግባቸውን
በአስቸኳይ ቀምሰው ወደ ጉባኤያቸው ተመልሰው ለነገው ጉባኤ ይዘጋ
ጃሉ:: የተነባውን ምሥጢር ለማቅናት የጐደለውን ለመሙላት መጻሕ
ፍቱን ያስነብባሉ:: አንዳንድ ጊዜ አሳልቀ ይልና ሲጨልም በመብራት
ያስነብቡና ወደ ማታ ጸሎታቸው ይገባሉ:: ጥቂት ያርፉና ደግሞ
የመንፈቀ ሌሊት ጸሎታቸውን ዝግ ባለ ሁኔታ ያደርሳሉ::

## መማር /ማስተማር

ወጣቱ ተማሪ አየለ የዜማው ትምህርት ቢስማማቸውም ቅኔ መማር
ስለፈለጉ ከዜማ መምህራቸው ከአለቃ አበራ ፈ... ...ቀው የአደራ
ደብዳቤ ጭምር ተሰጥቷቸው መምህር አባተ ዘንድ ...ቢያ ወረዳ ኣረ
ቢያ መድኃኔዓለም ተላኩ::

አየለ ቅኔ መቁጠር ጀመሩ:: ትምህርቱ በጣም ከበደባቸው:: ቢሆ
ንም ተስፋ ባለመቁረጥ ትምህርታቸውን መከታተል ቀጠሉ:: በመጨ
ረሻ ወደ ቀድሞ ትምህርት ቤታቸው ለመመለስ ይወስኑና ጓዛቸውን
ጠቅልለው መንገድ ይጀምራሉ:: ጓደኞቻቸውም እንዲቀሩ ቢለምኗቸው
በጀ ስላላሏቸው ጉዳዩን ለመምህራቸው ይናገራሉ:: መምህር አባተም
ለተማሪዎቹ መልእክት ላኩ:: በአካባቢው ድርማ የሚባል ወንዝ አለ::
«ሂዱና ድርማን ሳይሻገር ያገኛችሁት እንደሆነ እንደ ምንም ብላችሁ
ይዛችሁት ኑ:: ወንዙን ተሻግሮ ካገኛችሁት ግን ተውት» ይላቸዋል::
ደቀ መዛሙርቱም በፍጥነት ቢሔዱ አለቃ ወንዙን ሳይሻገሩ ከወንዙ
ዳር ከነበሩ ከብት ጠባቂዎች መንገድ ሲጠይቁ አገኟቸው::

በዚህ ሁኔታ ወደ ቅኔ ትምህርታቸው የተመለሱት ደቀ መዝሙሩ
አየለ በኋላ ያስቸገራቸውን ቅኔ ተካኑት:: ቅኔን እስከነ አገባቡ



www.ethiopianorthodox.org

አውቀው አሉ የተባለ ቅኔ ዘራፊ ሆኑ:: ያውም የመምህራቸው ምክትል:: በዚሁ አገልግሎት ረዘም ላለ ጊዜ ከቆዩ በኋላ ወደ አዘዞ መመለስ ግድ ሆነባቸው:: አጐታቸው አለቃ አበራ የዜማውን ትምህርት እንዲያጠናቅቁና ወደ ቤተልሔምም ሄደው ድጓውን እንዲያስመርቁ ልከውባቸው ወደ ቤተልሔም አቀኑ:: ቤተልሔም እየተማሩ ሳለ አለቃ ኀሩይ ፈንታ የተባለ የመጽሐፍ መምህር የመጻሕፍትን ትርጓሜ እንዲማሩ ጠሯቸው::

ወዲያውም የቄርሎስን ትርጓሜ አጠኑ:: ከዚያም የመጻሕፍት ትርጓሜን የበለጠ ለመማር ጎጃም ደንበጫ ቅዱስ ሚካኤል ከአለቃ ተሰፋ ዘንድ የሃይማኖተ አበውን ትርጓሜ መማር ጀመሩ:: አለቃ ተስፋ ወደ ሞጣ ጊዮርጊስ ተዛወሩ:: የደንበጫ ካህናት አለቃ አየለ በአለቃ ተስፋ ቦታ እንዲተኩ ፈልገው ነበር:: እርሳቸው ግን ሞጣ ሄደው የመጻሕፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ አውቀው መምህርነታቸውን አስመርቀው ጐንደር ተመለሱ:: እኚህ መምህራቸው አለቃ ተስፋ ነበሩ «ፍሳቴ» ብለው የሚጠሯቸው::

ከጐጃም ተመልሰው ጐንደር ግምጃ ቤት ማርያም ከታላቁ ሊቅ መምህር ተክለ ማርያም የሐዲሳትን ትርጓሜ ሲያሔዱ ቆዩ:: ቀጠሉና ሐዲሳቱን ለማጠናቀቅ ሰሜን አውራጃ ደረስጌ ማርያም ከመምህር ገብረ ማርያም ዘንድ ሔዱ::

ከሰሜን ደግሞ ወደ ጐንደር ተመለሱና ከጌታው አለቃ ዘዮሐንስ ዘንድ የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜ መማር ጀመሩ:: የሊቃውንቱን ትርጓሜ ደግሞ በጐን ያስተምሩ ነበር:: በዚህ ጊዜ መምህሮቻቸው አለቃ ኀሩይና አለቃ ተስፋ ከጌታው አለቃ ዘዮሐንስ ጋር መጡ:: ጉባኤውም ይሰፋ ጀመር:: አለቃ አየለ ለመምህሮቻቸው የማስተማሩን ሥራ ለመልቀቅና የፍትሐ ነገሥቱን ትርጓሜ ለማጠናቀቅ ወሰኑ:: እነ አለቃ ተስፋ ግን ከእንግዲህ ማስተማር የአለቃ አየለ ፈንታ መሆኑን ነግረው እነሱ ማዳመጥ አለቃ አየለ ደግሞ ጉባኤውን ማካሔድ ጀመሩ:: የፍትሐ ነገሥትን ትምህርት ከጨረሱ በኋላ የሊቃውንት ትርጓሜን በሰፊው ማስተማር ጀመሩ::





የፍትሐ ነገሥትን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ከሣሕሌ ወልደ ተክሌ መርሐ ዕውርንና አቡሻክርን ማለትም ምሕዋረ ከዋክብትን ሚጠተ ብርሃናትን የሚያስረዳውን የሊቃውንትን መጽሐፍ ተማሩ:: ይህ ሁሉ ትምህርታቸው የሊቃውንት ቅርስ የሆኑትንና የመምህራኑን ትምህርት የምናመሳክርባቸውን የአራቱን ጉባኤ መጻሕፍት በሙሉ ንባብ ከትርጓሜ የአቡሻሕር መጽሐፍ ከነባለ ሠንሠረዡ ለመጻፍ አስ ችሏቸዋል:: ይህ ባለ ሠንጠረዥ አቡሻሕር ለኤግዚቢሽን ሲጐስ ተልኮ ለሀገራችን አድናቆትን ስለ ከፍተኛነቱም ሰባት መቶ ሃምሳ ብር ሽልማት አግኝቷል::

## በአዲስ አበባ

ከመንግሥት በ፲፱፻፳፩ ዓ.ም ጥሪ ደረሳቸውና አዲስ አበባ መጡ:: ወደ አዲስ አበባ የመጡት ከአለቃ ኀሩይ ፈንታ ጋር ነበር:: አዲስ አበባም ሁለቱ ሊቃውንት መጻሕፍትን ማስተማርና የሚታተሙትንም መጻሕፍት ከሊቃውንት ጋር ሆኖ ማጠናቀቅ ጀመሩ:: እግረ መንገዳቸውንም አብረዋቸው ከሚሠሩት ሊቃውንት ዕውቀት ይቀስሙ ነበር:: የላሊበላ ገዳማት መምህር ከነበሩት ከመምህር ኀሩይ መጻሕፍተ መነኰሳትን፣ ከመምህር ፊላታዎስ መጻሕፍተ ብሉያትን በሙሉ አጠኑ፣፡ ከመምህር ገሪማ በኋላ ከአቡነ ሚካኤል የ፲፬ቱን ቅዳሴ አጠናቀው ተማሩ:: ለብዙ ጊዜም አዲስ አበባ አራቱን ጉባኤያት አስተማሩ::

አዲስ አበባ ያሉ ደቀ መዛሙርታቸው የሚኖሩት በየአድባራቱ ነው:: ዶክተር አለቃ አየለ ግን የሚኖሩት ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ነበር:: ስለዚህ ለማስተማር አለቃ ኀሩይ ወደነበሩበት ወደ መንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስና ወደ መታሰቢያ ቤት በኣታ ለማርያም ገዳም መመላለስ ነበረባቸው::

ዶክተር አለቃ አየለ በአዲስ አበባ ጉባኤ በሚሔዱበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ብቻ ሳይሆኑ ታላላቅ መምህራንም ሁሉ የራሳቸውን ጉባኤ አቋርጠው የእርሳቸውን ጉባኤ ተካፋይ ይሆኑ ነበር::

አዲስ አበባ እያሉ ጣሊያን ኢትዮጵያን ወረረች:: ዶክተር አለቃ አየለ ሁልጊዜ በአሥራ አንድ ሰዓት በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያን ጸሎተ ሥርክ ሲያደርሱ አንድ ፋሽስት ያያል። እዚህ እየ ቆምክ የምትጸልየው የኢትዮጵያ መንግሥት እንዲመለስልህ በማሰብ ነው» ብሎ እያዳፋ ሲወስዳቸው የሚያውቋቸው ሰዎች አድነዋቸዋል።

በየካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ.ም የፋሽስት መንግሥት የአዲስ አበ ባን ሕዝብ በጨፈጨፈ ጊዜ ከነደቀመዛሙርታቸው ለዘጠኝ ቀን አሥ ረውቸዋል። በዚህ ጊዜ አለቃ እሥረኞችን በማፅናናት ከፍ ያለ አገል ግሎት ሰጥተዋል።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ወደ ጐንደር ለመመለስ ይወስናል። አለቃ ኀሩይ በዚህ ጊዜ እየደከሙ ነበርና እኔን ሳትቀብረኝ አትሒድ ብለው ይለም ናቸዋል። «በሀገሬ ሰው ተክቼ ማለፍ አስቤአለሁና የርስዎም መልካም ፈቃድም ይሁንልኝ አሳቸው።» አለቃ ኀሩይም ፈቀዱላቸው። ከመሔ ዳቸው በፊትም የጐንደር በኣታን የእልቅና መዓርግ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መልካም ፈቃድ ተሰጣቸው። ጐንደርም ሰፊ ጉባኤ አቋቁመው አራቱን ጉባኤያት ማስተማር ጀመሩ። ብዙ ሊቃውንትም አፍርተዋል። የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲም ሰኔ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም የዶክትሬት መዓርግ ሰጣቸው። የሊቃውንት ኮከብም ተባሉ።

## የመጨረሻ ዘመን

ከ፲፱፻፷፩ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ዕረፍታቸው ድረስ በዝማሬ፣ የእግዚ አብሔርን ስም በማመስገንና ምሥጢራተ እግዚአብሔር በመናገር ቆዩ። እድሜያቸው እየገፋ በመምጣቱ በዚህ ጊዜ የጉባኤው ሥራ እንዲ ቆምላቸው ተደረገ። ዶክተር አለቃ አየለ በዘመናቸው በርካታ ሊቃ ውንትን ተክተዋል። በርካታ ቆጳሳትን ሊቃነ ቆጳሳትን እንዲሁም መም ህራንን አፍርተዋል።

በአረጋዊነታቸው ላይ ጥቂት ሕመም ተጨምሮባቸው በሕክምና ሲ ረዱ ቆይተው በአንድ መቶ ሁለት ዓመታቸው ጥር ፲፯ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። የቀብራቸው ሥነ ሥርዓትም የመን ግሥት ባለሥልጣናት፣ የጐንደር ሊቃውንትና የጎንደር ከተማ ሕዝብ በተገኙበት በመንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ተፈ ጸመ።





አስክሬናቸው ካረፈበት ቦታ ላይ ባለአንድ ድርብ የመቃብር ቤት ተሠርቷል። መቃብር ቤቱ የተሠራው ከመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲ ያን ዕቃ ቤት ጋር ተያይዞ ነው የተሠራው። ምድር ቤቱ ውስጥ የማን በር ጸሎት ጠዋትና ማታ ይደረስበታል፤ ጉባኤም ይካሔድበታል። አን ዳንዴም ለምእመናን ትምህርት ይሰጥበታል። ፎቁ ሁለት ክፍሎች አሉት። አንደኛው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውሏል። ሁለተኛው ግን የዶክተር አለቃ አየለ የአራቱ ጉባኤ መጻሕፍት በሙሉ ንባብ ከትርጓሜ የሆኑ እንዲሁም ታላቁና ሙሉው ባለሠንጠረዡ አቡሻሕር የሚባለው መጽሐፍ እንግዶች ሲመጡ እንዲያዩት፣ ለአንዳንድ አስፈ ላጊ ጉዳይ ቅርሶቹ ሲፈለጉም ከዛው በቅርብ እንዲገኙና ተጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ ለማድረግ ተቀምጠውበታል።

*ምንጭ፦ መጽሔተ ሊቃውንት ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ.ም*



www.ethiopianorthodox.org

# ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ

/፲፰፻፺፯ – ፲፱፻፸፰/



«በጠኅት ከሚኅዱ ይልቅ በጠኅት ምክንያት የሚጠቀሙ ይበዛሉ::»

በተስፋዬ ሽብሩ

"ይህ ሞገስ ነው ትሉኝ ይሆናል፤ ግን እኔ ምሳሌው /ሥዕሉ/ እንጂ ሞገስ አይደለሁም:: ሞገስ አንድ ነው:: እኔ የሞገስ ሥዕል ግን አንድም ብዙም ነኝ:: ሞገስ ከአንድ ቦታና ከአንድ ቤት ይገኛል፤ እኔ ግን ከብዙ ቦታና ከብዙ ቤት እገኛለሁ፤ ሞገስ ዛሬ አለ፤ ነገ ግን እንጃ፤ ከነገ ወዲያ ግን በርግጥ የለም:: እኔ ሥዕል ግን ዓለም እስካለ ድረስ ከእናንተ ከሕያዋን ጋር አለሁ::

ይሁን እንጂ እሱ ሲታመም የማይታመም፥ እሱ ሲሞት የማይ ሞት አንድ ነገር በአደራ ሰጥቶኛል:: ይኸውም በሦስት ቀለሞች የፀመ ስም ነው:: እስከ አሁን ድረስ ከእኔ አልለየውም"::

ይህንን ምርምራዊ የሆነ ኃይለ ቃል የተናገሩት ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ናቸው:: ሊቀ መዘምራን ሞገስ አንጋረ ፈላስፋ በሚለው ባሳተሙት መጽሐፋቸው ላይ ከሚገኘው ፎቶ ግራፋቸው ሥር ተቀምጦ ይገኛል:: በዚህ አሳባቸው ሊቀ መዘምራን ስለ ሰው ልጆች ህላዌና ኅልፈት ለማስረዳት የሞከሩበት አሳባቸው እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል::

የሃይማኖት፣ የፍልስፍና፣ የምርምር መጻሕፍት ደራሲው ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ከአቶ ዕቁበ ጊዮርጊስ ወልደ ኢየሱስና ከወ/ሮ ወለተ ትንሣኤ ኃይለ ሚካኤል በኤርትራ ክፍለ ሀገር በሐማሴን አውራጃ በለኅዬዋ ወረዳ ልዩ ስሙ ክትሞ ውሊዕ በተባለ መንደር መስከረም ፩ ቀን ፲፰፻፺፯ ዓ.ም ተወለዱ::





በ፲፪ ዓመታቸው በትምህርት ተኮትኩተው እንዲያድጉላቸው ወላጆቻቸው እምኒ ጸሊም ከነበሩት የኔታ እንድርያስ ዓብቡ ከተባሉ መምህር ዘንድ ልከዋቸው ፊደል ቆጥረው የቃል ትምህርትንና ቁም ጽሕፈትን ተማሩ:: ከዚያም ወደ ትግራይ ክፍለ ሀገር እንደርታ አውራጃ ደብረ ኃይል ገዳም ገብተው ስመ ጥር ከሆኑት ከመምህር ገብረ ሕይወት ጎምሎ ቅኔ ከነአገባቡ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል:: ከየኔታ ፈለቀ አቋቋምን ከተማሩ በኋላ ወደ ጎንደር ክፍለ ሀገር በመሻገር በደብረ ታቦር አውራጃና በዚሁ አካባቢ የጎንደርን አቋቋም የጸናጽሉን አወራረድና ይትብሃሉን አጠናቀው ከዚያም የትምህርት ፍላጎታቸው ስላልተሟላላቸው እንደገና የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ለመማር በ፲፱፻፳፬ ዓ.ም ሸዋ ክፍለ ሀገር አዲስ አበባ መጥተው በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ የመምህራንና የቀሳውስት ማሠልጠኛ ገብተው ከአለቃ ኅሩይ መጻሕፍተ ሊቃውንትን፥ አቡሻሕርን /ባሕረ ሐሳብ/ ተምረዋል:: ከታወቁት ሊቅ ከዶክተር አለቃ አየለ ዓለሙ የመጻሕፍተ ሐዲሳት ትርጓሜን ጠንቅቀዋል::

ሊቀ መዘምራን ሞገስ ታዕካ ነገሥት በኣታ ለማርያም ገዳም ወደ ቅዱስ ማርቆስ፥ ከማርቆስም ወደ ታዕካ ነገሥት በኣታ ለማርያም ገዳም እየተመላለሱ ትምህርታቸውን በመልካም ሁኔታ በማካሄድ ላይ እያሉ በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም በጣሊያን ወረራ ወቅት በመታሰራቸው ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ተገደዱ:: ከዚያም ተፈትተው ወደ ኤርትራ ክፍለ ሀገር በመሔድ ፊደል ከቆጠሩበት ቦታ ለጥቂት ቀን ሲያስተምሩ ከሰነበቱ በኋላ ወደ ደብረ ጽሟኅ ገዳም ገቡ:: በገዳሙ ቆይታቸው እያስተማሩ ብዙ ደቀመዛሙርትን አፍርተዋል:: እርሳቸውም ከገዳሙ አበምኔት ከመምህር ገብረ እግዚአብሔር ቅዳሴ ተምረዋል::

በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ጦር ከማይጨው አዲስ አበባ ሲገባ ሊቀ መዘምራን ሞገስ አዲስ አበባ ነበሩ:: የሚሰደደው ከሀገር ወጥቶ አርበኛውም በረሃ ገብቶ በነበረበት ወቅት ሊቀ መዘምራን ሞገስ ከስመ ጥሩው ሊቅ ከአለቃ ዶ/ር አየለ ጋር ሆነው ስለ ሀገራቸው ነጻ መውጣት እየጸለዩ ይጠባበቁ ነበር:: ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ



www.ethiopianorthodox.org

ጊዮርጊስ ሞገስ አስገዶምና አብርሃ ደቦጭ በግራዚያኒ ላይ በምብ ወርውረው ጉዳት ባደረሱበት ጊዜ ከአርበኝነትና ከስደት የተረፈው የአዲስ አበባ ሕዝብ በፋስ፣ በአካፋ፣ በመጥረቢያ ሲጨፈጨፍ፥ ቤት ተዘግቶበት በእሳት ሲጋይ የዐይን ምስክር ነበሩ:: ሌሊቱን በሙሉ በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን እያደሩ የሀገራቸውን ነጻነት መመለስ ተግተው በጸሎት ሲጠይቁ፤ ተይዘው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥም ታስረዋል:: አሳልፈዋል:: ነጻነት እስኪመለስ ስለ ኢትዮጵያ ነጻነት በማስተማር ሀገርና ቤተ ክርስቲያን የጣሉባቸውን አደራ ተወጥተዋል::

ሊቀ መዘምራን ሞገስ ስለዚህ ጉዳይ ሲገልጹ፦ "ለሀገሬ ብዬ ነው የትውልድ ቀዬዬን ትቼ በትግራይ፣ በጎንደርና በሸዋ ክፍላተ ሀገራት እየተዘዋወርኩ ነው የኖርኩት:: ከዚያም በኋላ "ኢትዮጵያ ወይም ሞት" ከሚሉ የሀገር ፍቅር አባላት ጐን የተሰለፍሁት:: በወቅቱ ኤርትራ ከባዕድ ቅኝ ግዛት ወጥታ ወደ እናት ሀገሯ እንድትቀላቀል ባለኝ አቅምና ጉልበት ተሳትፌያለሁ:: ይህም ሲሆን ለመመልከት ችያለሁ::" ብለዋል::

ሊቀ መዘምራን ሞገስ በስንሒት አውራጃ በከረን ከተማ በልደታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ወንበር ዘርግተው፥ ጉባኤያትን አስፋፍተው ቅኔ፣ ቅዳሴ፣ እንዲሁም መጻሕፍተ ሐዲሳትን በማስተማር ብዙ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል:: ሊቀ መዘምራን ሁሉን ሰው በሚዛናዊ ዐይን ይመለከቱ፡ ስለ ነበር ከዚህ ተግባራቸው የተነሣ "የሰላም አባት" የሚል ቅጽል ስም ነበራቸው::

ሊቀ መዘምራን ሞገስ የሃይማኖት የፍልስፍና፣ የምርምር፣ የታሪክ መጻሕፍትን በመጻፍ ለትውልድ ያስቀሩ ታላቅ ምሁር ናቸው:: በአነጋገራቸውና በጽሑፎቻቸውም ላይ አብዛኛውን ጊዜ ምርምራዊ ይዘት ይታይበታል::

*"... የልምት ሰው የሚንቀሳቀስ ሬሳ ነው::*
*/ፎቶ/ ሥዕል ግን የማይንቀሳቀስ ሕያው ነው*
*ከሰው ጉልበት የሥዕል ጉልበት ይበልጣል::*
*ሰውዬው ሲጋደም እሱ ጠጋ ብሎ ይቀመጣል::*
*ሥዕሌ ሆይ፥ ከኔ ዕድሜ ያንተ ይረዝማል::*





*እኔ ስሞት ያንተ መሰንበት ይገርማል::*
*ሰላምታዬን አቅርብልኝ ለሚከተለው ትውልድ፥*
*አንተ ሰንባቹ ነህና እኔ ወደ አፈርነት ስሄድ::*

በማለት ስለ ሞትና ሕይወት ይህንን በመሰለ አቀራረብ ይገልጹ ነበር:: ሊቀ መዘምራን ከሚጠቅሷቸውና ከጻፏቸው አሳቦች ውስጥ ከዚህ በታች የቀረቡትም የሚዘነጉ አይደሉም::

«ምሽት የቀም ሕልም ነው፤ ሕልምም በአሳብ ተቀርጾ በቅዠት የሚወለድ ነው:: ማስተዋል የራቀን ለማቅረብ የቀረበውን ለማራቅ የሚያገለግል የልብ መነጽር ነው:: መከራ የጠባይ ማረሚያ፥ የሥራ ማነቃቂያ፥ የጥበብ ማሃቋቋሚያ ነው:: ተስፋ ከማጣት ወደ ማግኘት ለመሸጋገር የሚያገለግል መሰላልና ድልድይ ነው:: ትዕግሥት አድብቶ ቆይቶ ድል የማድረግ መሣሪያ ነው:: ትንትና ምንጊዜም የበላይ ለመሆን መቆናጠጫና መወጣጫ እርከን ነው:: ፍቅር መያዣ የሌለውን የሰው ልብ አስሮ ለመሳብ የሚያገለግል የሰላም ገመድ ነው:: ቁጣ፣ ጠብ እሳትን ለማቀጣጠል የሚጫር የኩሶ ክብሪት ነው:: መከራ የሥራ ጥልቀትን መለኪያና መመጠኛ ነው:: ችኮላ የትዕግሥት ጠላት፣ የጸጸት አባት ነው:: አደገኛ ሞት ያለበትን የማያውቀው ያልተገራ እንደበት ነው:: የሰው ሰውቀቱ ፍላጎቱ፥ የሰው ጠላቱ አንደበቱ:: መስማቴን አምነዋለሁ፥ ማየቴን ግን አረጋግጥበታለሁ:: ሳይሰራ አገኛለሁ የሚል ተስፋ የሌለው ሰው ነው:: በጠላት ከሚጎዱ ይልቅ፤ በጠላት ምክንያት የሚጠቀሙ ይበዛሉ:: ሀብታምና ድሃ የሚበሉት አንድ እንጀራ ስለሆነ የሀብትና የድህነት ልዩነት "አለኝና የለኝም" ብቻ ነው:: ወልዶ የሞተ ሰው መልኩ ተለወጠ እንጂ አልሞተም::» እነዚህ ኃይለ ቃላት በጥቂት መስመሮች ይቀመጡ እንጂ እያንዳንዳቸው በውስጣቸው የያዙት እምቅ የሆነ አሳቦችን እንደ ሆነ መረዳት ለማንም የሚያዳግት አይሆንም::

ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ዘጠኝ የተለያዩ መጻሕፍትን አዘጋጅተዋል:: መጻሕፍቶቻቸው ከይዘታቸውና ከመልእክታቸው ጋር የኢትዮጵያ መለያ የሆነውን የፊደልና የጽሑፍ ባህል ተጠብቆ እንዲቆይና እንዳይበረዝ የሚያስገነዝቡ ናቸው:: ይህንንም አሳብ "የሕፃናት



www.ethiopianorthodox.org

እንደበት መፍቻ"፣ "ጥንታዊ ምሳሌ በትግርኛና በአማርኛ" በተባሉት መጻሕፍቶቻቸው ገልጠዋቸዋል። በአማርኛ ያዘጋጁት መዝገበ ቃላትም ሳይጠቀስ የማይታለፍ ሥራቸው ነው። ለኢትዮጵያዊው ባህል፣ ለታሪክ ያላቸውን መቆርቆር ጠልቆ የሚያሳይ ነው። ከሊቀ መዘምራን ሥራዎች ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጣቸው "መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት" እና "አንጋረ ፈላስፋ" ይጠቀሳሉ። "መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት"፤ ቅድስት ሥላሴ በመጽሐፍ ቅዱስ፣ ምሥጢረ ሥጋዌ፣ ስለ መላእክት አፈጣጠር፣ ስለ መስቀል፣ በምንኩስና ከዓለም ስለ መለየት፣ ስለ ገነትና ሲዖል መኖር... በአጠቃላይ ትምህርተ ሃይማኖትን፥ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ ይናገራል። ከዚህም ጋር በተያያዘ በጥያቄና መልስ የተዘጋጀ ትምህርት ተካቶበታል። አንጋረ ፈላስፋ /የፈላስፎች ንግግር ከዐረብኛና ከጽርዕ ቋንቋ በመነሣት፤ ከግእዝ ከአማርኛና ከጣልያንኛ ልሳናት በመረዳት የዓለም ፈላስፎችን ዕውቀ የጥበብ ሥራዎች በማገናዘብ የጻፉት የፍልስፍና መጽሐፍ ነው። አንጋረ ፈላስፋ የሰውን ልጅ ጠባይ ደካማና ሞገደኛ ጐኑን ገልጦ የሚያሳይ፤ ለልማትና ለዕድገት የሚሆነውን ጎዳና የሚመራ፣ የሰው ልጅ ጥፋቱና ውድቀቱ በየት በኩል እንደ ሆነ ገልጦ በምሳሌና በሰም ለበስ አነጋገር የሚያሳይ መሆኑ ከይዘቱ መረዳት ይቻላል። ሊቀ መዘምራን ሞገስ ስለ መጽሐፍ ማዘጋጀትና መጻፍ "መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት" በሚለው መጽሐፋቸው መግቢያ ላይ ምክንያተ ጽሕፈት በሚል ርእስ እንዲህ ብለዋል፤

ከባሕር የሚያሻውን ያህል ውኃ ቀድቶ እንደ መጠቀም ከመጻሕፍትም ለጊዜው የተፈለገውን ያህል በጥቅስ መልክ ወስዶ ይጠቅማል በሚል አስተሳሰብ ለአንድ አንድ አከራካሪና አጠራጣሪ ነገሮች የምንጠቀምባቸውን ኃይለ ቃሎች ከልዩ ልዩ መጻሕፍት ቀድቶ በመጽሐፍ ቅጽ ማሠራጨት የተለመደ ነው። በዚህ ጊዜ ልዩ ልዩ አዳዲስ እምነቶችና አምልኮቶች እንደ እንጉዳይ ሲፈሉና ሲበቅሉ ይታያሉና ለነሱ መከላከያ ይሆናሉ። የድርሰት መጻሕፍት ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ አብራርተው የሚያስረዱ ሲሆኑ "አዋልድ ናቸው" በሚል አስተሳሰብ አንዳንድ ተጠራጣሪዎች የማይቀበሏቸው ስለሚገኙ





እናምነዋለን እንቀበለዋለን በሚሉት መጽሐፍ ቅዱስ ለማሳመንና ለማስረዳት አብዛኞቹ መጻሕፍት መነሻቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው።

በመሠረቱ ይላሉ ሊቀ መዘምራን፤ ብሉይ ኪዳን ንባብ፣ ሐዲስ ኪዳን ምሥጢር፣ መጻሕፍተ ሊቃውንት ትርጓሜ ናቸው። ደግሞም የብሉይ ኪዳን ንባብ ምሳሌ፣ የሐዲስ ኪዳን ንባብ ትርጓሜ፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንት ንባብ የምሥጢር መፍቻና ማብራሪያ ናቸው።

እንዲሁም የቅዱሳን ሐዋርያት፥ ጻድቃን ሰማዕታት ድርሳናትና ገድላት ትሩፋታቸውን፥ ቅድስናቸውን፥ ጸጋቸውንና ከፈጣሪያቸው የተቀበሉትን ቃል ኪዳን የሚገልጡ ናቸው። ቃል ኪዳን ማለት በስማቸው ለተራቡ የሚያጎርሱ፥ ለታረዙ የሚያለብሱ፥ ለተጠሙ የሚያጠጡ፥ ሳጡ የሚሰጡ ምእመናን ዋጋቸውን እንዲያገኙ የሚያስረዳ ከፈጣሪ የተቀበሉት ቃለ ብፁዓን ማለት ነው። በማለት በአጠቃላይ ስለ አዋልድ መጻሕፍት ያላቸውን አሳብ፤ "ወታደር ጠመንጃውን አንግቦ፥ ዝናሩን ታጥቆ፥ ዘገሩን ነቅንቆ አገራዊ ግዳጁን ለመፈጸም እንደሚዘጋጅ ሁሉ ካህንም ሆነ ምእመን መጽሐፍን እንደ ሰይፍ ታጥቆ እንደ ጋሻ አንግቦ በተጠንቀቅ ሊቆም ይገባል።" በማለት አዘውትረው ይናገሩ ነበር።

ሊቀ መዘምራን አዘጋጅተው ያሳተሟቸው መጻሕፍት፡-

፩. መክሥተ ልሳን ዘሕፃናት
፪. አንጋረ ፈላስፋ
፫. ሰዓታት ምስለ ባሕረ ሐሳብ
፬. ሥነ ፍጥረትና አምስቱ አዕማደ ምሥጢር
፭. መድበል አምኀ ሰላም
፮. ጥንታዊ ምሳሌ /በአማርኛ/
፯. ጥንታዊ ምሳሌ /በትግርኛ/
፰. መዝገበ ቃላት /በአማርኛ/
፱. መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት ሲሆኑ በርካታ ያልታተሙ ጽሑፎች አሏቸው። ከእነርሱም መካከል፡-

፩. መዝገበ ቃላት ግእዝና አማርኛ
፪. ተስእሎተ አንጢያኮስ ውስጣዊ አትናሲስ /በአማርኛ/



www.ethiopianorthodox.org

፫. ዛንታ አበውና ተረታ - ተረት /በትግርኛ/
፬. መዝገበ ቃላት /በትግርኛ/
፭. ፊላልጎስ ፊላስፋ /በአማርኛ/
፮. የኢትዮጵያ ሊቃውንት ቅኔ /በግእዝ/
፯. አስተዳደግ - የሚሉ መጻሕፍት ናቸው::

እነዚህ መጻሕፍት በመላው ኢትዮጵያ ተሠራጭተው በምእመናን እጅ ውለው ጽምዓ ትምህርትን አስወግደው የቆዩ እንደ ሆኑ በርካታ ሊቃውንት ይመሰክራሉ::

ሊቀ መዘምራን ቅኔን አስመልክተው የጻፉት እዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚገባው ነው:: «እንደ ዛሬ ዘመናዊው የአማርኛ ትምህርት ሳይመዘን ወይም እንደ ድሮው የቅኔ መምህራን ያልበዙበት ተማሪዎች ያነሱበት ዘመን ሳይሆን በአንድ ቅኔ ት/ቤት ከመቶ እስከ ሁለት መቶ ተማሪዎች ይገኙ እንደ ነበር ሞቶ ያልተቀበረ የነደላንታ፥ ዋድላ፥ የነጎንጅ፥ ዋሸራ ቅርስ ይመሰክራል:: የትምህርቱ ዓይነት ስሙ ቅኔ ይባል እንጂ ቁም ነገሩ <ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲሰ፡ እግዚአብሔርን በአዲስ ምስጋና አመስግኑት> ባለው መሠረት የሚደመር ነው:: "የቅኔን አገጣጠምና አሰካክ ተምሮ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚበረከተው ቅኔ ብቻ ሳይሆን የቋንቋነቱን ስልታስልት ማለት ማሱን ከነ እርባታው ጥሬ ዘሩን ከነ አርእስቱ ነባሩን ከነ አገባቡ ለይቶ ለማወቅና ለማሳወቅ ነው" በማለት ስለ ቅኔ ያላቸውን አስተያየት አብራርተዋል::

ሊቀ መዘምራን ሞገስ "ኢትዮጵያ ጥገኛ በመሆን የፊደልና የሥነ ጽሑፍ ተመጽዋች አለመሆን፥ የራሷ ፊደልና ሥነ ጽሑፍ ያላት ሀገር ስለሆነችም ቋንቋውን በየጊዜው እየሻሻለች የነበረች፥ ያለችና የምትኖር ታሪክና የታሪክ መዝገብ የሆነች ሀገር ናት" በማለት ይህ ሁሉ በቤተ ክርስቲያኗ ብርታትና ታታሪነት የተገኘ መሆኑን ያወሳሉ::

"የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከቀድሞ ጀምሮ የአገሩን ባህልና ታሪክ አበክራ ጠብቃ የኖረች ከመሆኑም በላይ ለአሁኑም ትውልድ ዘመናዊ የአማርኛ ትምህርትና ቋንቋ መሪና በር ከፋች የሆነችው ቤተ





ክርስቲያን መሆኗን የማያምን የለም" ሲሉ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ያበረከተችውን ጉልህ ድርሻ ገልጸዋል:: አሁን ያለው የአማርኛ ስልትም ቢሆን በቅኔና በመጻሕፍት ትርጓሜ አማካይነት ሲያያዝ የመጣና አዲስ ክስተት አለመሆኑን የሥነ ጽሑፍ መገኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሆኗን መዝገበ ቃላት፣ በአማርኛ ፲፱፻፷፪ ዓ.ም በሚለው መጽሐፋቸው ገልጸውታል::

ሊቀ መዘምራን ሞገስ በይበልጥ የሚታወቁበትና ከሕዝብም ያስተዋወቃቸው መጽሐፋቸው "አንጋረ ፊላስፋ" /የፈላስፎች ንግግር/ የተባለው መጽሐፋቸው ነው:: መጽሐፉን እንዴት እንዳዘጋጁት ሲገልጹም "መጽሐፉ በአንዳንድ ታላላቅ ገዳማትና አድባራት ካልሆነ በቀር በቀሩት አብያተ ክርስቲያናት ስለ ማይገኝ ብዙዎች ተጠቃሚዎች አልነበሩም:: በአንዳንድ ቦታ ታሽጎ ጠቃሚነቱ በጥቂት ሰዎች ዘንድ ተወስኖ ሲቀር መላው ሕዝብ በተለይም የጊዜው ወጣቶች፥ አስተማሪዎችና ተማሪዎች እንዲካፈሉት እንዲጠቀሙበት በሚል ከግእዝ ወደ አማርኛ መተርጎማቸውን ገልጸዋል::

ይህንንም ሲያደርጉ በየገዳማቱ የሚገኙትን አንጋረ ፊላስፋ መጻሕፍት ቅጂዎች አስተያይተው እርስ በርሳቸው በማስተራረም እንደ ተረጎሙት ነው ሊቀ መዘምራን የገለጹት::

ሊቀ መዘምራን ሞገስ "ማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት" በመባል የሚታወቀውን ማኅበር በምክትል ሊቀ መንበርነት መርተዋል:: ይህ ማኅበር "ኮከበ ጽባሕ" የተሰኘ ማተሚያ ቤት አቋቁሞ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትን በማሳተምና ለቤተ ክርስቲያን በማቅረብ ለምእመናን እንዲሰራጩ አድርጓል:: በዚህ ሒደት ውስጥ ሊቀ መዘምራን ሞገስ ከማኅበሩ መሥራችና ሊቀ መንበር ከክቡር ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ገብረ ማርያም ጋር በመሆን ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፤ ትጋት የተሞላበት ሥራም ሠርተዋል::

ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ በአሥመራ የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር አባል ሆነው በየካቲት ፲፱፻፸፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተደረገው የደራስያን ማኅበር ጉባኤ ላይ ተሳትፈዋል::



www.ethiopianorthodox.org

ስብሰባውን አጠናቅቀው ከአዲስ አበባ ወደ አሥመራ እንደ ተመለሱ
ሰጥቂት ቀናት ታመው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

ቤተ ክርስቲያን በየዘመናቱ በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊው ዕውቀት
የበለጸጉና የደረጁ አባቶች ነበሯት፤ አሁንም አሏት። ሊቀ መዘምራን
ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ከነዚህ ስመ ጥሩ አባቶች መካከል አንዱ ነበሩ።
አሁን በአካለ ሥጋ ቢለዩም የአእምሮአቸው ውጤት የሆኑት ሥራዎ
ቻቸው ግዘፍ ነስተው፣ ዘመን ተሻግረው ዛሬም ወደ ፊትም እንዲታ
ወሱ ያደርጓቸዋል። "ስም ከመቃብር በላይ" ይሏል እንዲህ ነው።

*ምንጭ፡ ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ መስከረም ፲፱፻፺፯ ዓ.ም*






# አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ

/፲፱፻፩ - ፲፱፻፹/

## ከቤተ ክህነት እስከ ማስታወቂያ ሚኒስቴር

*በተሰፋዬ ሽዛሩ*



*«ለኢትዮጵያ ታሪኳ
ነው መልኳ»*



www.ethiopianorthodox.org

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ የልደት በዓላቸውን በየዓመቱ ሐምሌ ፲፮ ቀን ያከብሩ በነበረት ጊዜ የሚያስቀድሱት በታላቁ ቤተ መንግሥት ቅጽር ግቢ ውስጥ በምትገኘው በሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ነበር።

ንጉሡ ሥርዓተ ቅዳሴው ከተፈጸመ በኋላ ወደ ቤተ መንግሥታቸው ከመመለሳቸው በፊት፣ አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ የተባሉ ሊቅ ይህንኑ ታሪካዊ ቀን በማስመልከት ንግግር ያደርጋሉ።

እኚህ ሊቅ ሃያ አንድ ዓመት ሙሉ ያለማቋረጥ በንጉሡ ፊት ንግግር አድርገዋል። በዚህም በንጉሡ እና በቅርብ ባለሟሎቻቸው ዘንድ ሊታወቁ ችለዋል።

ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ.ም /በ፲፮ኛው ዓመት ንግግራቸው/ ግን ከሌላው ጊዜ ሁሉ ለአፈ ሊቅ የተለየ ቀን ነበር። በዕለቱ ከዐ፪ ዘርዐ ያዕቆብ የተያያዘውን የተዋሕዶ ሃይማኖት ታሪክ ጠቅሰው በንጉሡ ፊት ሰፋ ያለ ንግግር አደረጉ። በተመስጦ ሲከታተሏቸው የነበሩት ንጉሥ አንድ ነገር በልባቸው ያስቡና ወደ ቤተ መንግሥታቸው ይመለሳሉ።

ሊቁም አገር አማን ብለው ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ። አንድ ቀን ለካስ ተፈልገው ኖሮ ያን ሊቅ ጥሩ ይባልና ከቤተ መንግሥት እቤታቸው ሰው ተልኮ እንዲጠሩ ይደረጋል። ሊቁም ከዋናው የእልፍኝ አስከልካይ ከጄኔራል አሰፋ ደምሴ ዘንድ ይቀርባሉ።

«ንጉሡ ሊያነጋግሩዎት ይፈልጋሉ» ይሏቸዋል ጄኔራሉ። ንጉሡም ከእልፍኛቸው ሰገነት ላይ ሆነው ግራና ቀኝ ይንጎራደዳሉ። አልጋ ወራሽ አስፋወሰን ልዑላትና ልዑላን ሌሎችም መኳንንት የሰገነቱን መሐል ክፍት አድርገው ግራና ቀኝ ቆመዋል። አፈ ሊቅ በዋናው የእልፍኝ አስከልካይ አማካይነት ንጉሡ ፊት ሲቀርቡ ዝቅ ብለው እጅ ነሱ።

አፈሊቅ በጊዜው የሆነውን ሲያስታውሱ «ነገሩ የሆነው ሳይታሰብ ነበር እና ጎንበስ ብዬ እጅ ነሥቼ ቀና ለማለት እስከ መቸገር ደርሼ ነበር። ከድንጋጤዬ የተነሳ እንደምንም ቀና ብዬ ንጉሡን አየኋቸው። እጃቸውን ወደ ኋላ አድርገው ይንጎራደዳሉ። ግርማ ሞገሳቸው ያስፈራል፤ ያስደነግጣል። ግራ ቀኙን በዐይኔ ሳማትር ደግሞ ከዚያ ሁሉ ታላላቅ





ባለ ሥልጣን መሐል ካባ የለበስኩትና የጠመጠምኩት እኔ ብቻ ነበርኩ። ጃንሆይ ወዲያውኑ ሊቁን መጠየቅ ጀመሩ።

*ጃንሆይ፦* በየጊዜው የምታደርጋቸው ታሪካዊ ንግግሮች ሁሉ አንድ ከፍ ያለ መጽሐፍ ሊወጣው የሚችል ይመስለናል። ለመሆኑ ልታሳትመው ታስባለህ?

*አፈሊቅ፦* ግርማዊ ሆይ ማሰቤስ አልቀረም። የማሳተሚያው አቅም ስለሌለኝ ብቻ ነው።

*ጃንሆይ፦* አንተ አዘጋጅተህ አቅርበው እንጂ የማሳተሚያውን ዋጋ እኛ እንረዳሃለን። /ከዚህ በኋላ ነው አፈ ሊቅ «ለኢትዮጵያ ታሪኳ ነው መልኳ» የተሰኘውን ድርሰታቸውን ማዘጋጀት የጀመሩት/

*ጃንሆይ፦* ለመሆኑ ይህንን ሁሉ ዕውቀት የገበየኸው የት ነው?

*አፈ ሊቅ፦* ለቅኔ ትምህርት ወደ ዝቋላ ሄጃለሁ እንጂ በሙሉ የተማርኩት እዚሁ ነው። በተለይ የሐዲስን ትርጓሜ ከሊቁ ቀጸላ ዘንድ በምማርበት ጊዜ /በ፲፱፻፲፱ ዓ.ም ግርማዊነትዎ አልጋ ወራሽ ሳሉ/ ለእኔና ለሌሎች አራት ደቀ መዛሙርት በወር ቀለብ ቆርጠውልን የሁሉንም ተማሪዎች ደመወዝ እኔ እየተቀበልኩ ነው የተማርኩት።

*ጃንሆይ፦* ጊዜው ምንም ቢቆይ ትዝ ይለናል። ለመሆኑ ስለ እመቤታችንና ስለ ዮሴፍ አንድ ላይ መኖር የእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል መርምረኸዋል?

*አፈ ሊቅ፦* ዕድሜ ለግርማዊነትዎ የዘመኑን ትምህርት /በተለይ እንግሊዝኛን/ በመጠኑም ቢሆን ተከታትየዋለሁ። በዚህ ምክንያት የአማርኛውንና የእንግሊዝኛውን መጽሐፍ ቅዱስ ለማስተያየትና ለማገናዘብ አልተቸገርኩም። ግርማዊ ሆይ የእንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ እመቤታችንን ለዮሴፍ ሚስቱ ሲል፣ ግእዙ ፍህርቱ፣ አማርኛው እጮኛው ይላል።

*ጃንሆይ፦* ታዲያ የትኛው ነው ትክክል ትላለህ?

*አፈ ሊቅ፦* የአማርኛውና የግእዙ ነው ትክክሉ።

*ጃንሆይ፦* እነሱ እኮ «ኢያእመራ ዮሴፍ እስከ አመ ወለደት ወልደ ዘበኩራ...» /ልጅ እስከ ወለደች ድረስ ዮሴፍ አላወቃትም/ ያለውን ይዘው ነው።



www.ethiopianorthodox.org

***አፈ ሊቅ፡-*** ይህማ «እስከ» የሚለው ቃል ፍጻሜ የለውም። ስለዚህ ማስረጃ ይሆን ዘንድ ዮሐንስ አፈወርቅ «ኢወለደት ወልደ ሚልኮል እስከ አመ ሞተት» ብሏል። «እስከ ሞተችበት ቀን ድረስ ልጅ አል ወለደችም።» ከሞተች በኋላ ወለደች ይባላልን?» ግርማዊ ሆይ?

***ጃንሆይ፡-*** ዮሐንስ አፈወርቅንና ቄርሎስን አዋልድ ናቸው በማለት ምስክርነታቸውን አይቀበሉም እኮ...!

***አፈ ሊቅ፡-*** አዋልድ ማለት ልጆች፣ ሐዲሳት ማለት አባቶች፣ ብሉያት ነቢያት ማለት አያቶች ማለት ነው። ከነተረቱ «አባት ያበ ጀው ለልጅ ይበጀው እንዲሉ እነዚህ መንፈሳውያን አዋልድ መጻሕ ፍት የተውጣጡት ከብሉያት፣ ከነቢያትና ከሐዲሳት ነው እንጂ እንደ ሥጋዊ መጻሕፍት ያለመንፈስ ቅዱስ ተራዳኢነት በሥጋዊ የተደረሱ አይደሉም።

***ጃንሆይ፡-*** ፈገግ አሉና ረዘም ያለ ጊዜ ወስደው ጥያቄ እና መልሱን በስፋት ቀጠሉ። ወዲያው የእልፍኝ አስከልካዩ አፈሊቅን ጠጋ ብለው «ንጉሡ ደክሟቸዋል። ይበቃችኋል። ሽልማት ታዞልዎታል» ይላቸውና ወደ ውስጥ ይገባሉ። የዘውድ ምልክት ያለበት ልዩ ካባ ከጥ ንድ ድርብ እና ከሙሉ ክብሩ ጋር ለብሰው ንጉሡን እጅ ነስተው ወደ ቤታቸው ያመራሉ። ለሚቀጥለው ዓመት የሚያደርጉትን ንግግር በአእ ምሯቸው እያሰላሰሉ።

አፈ ሊቅ እንደሚወቱኝ ይላሉ ልጃቸው አቶ ንጉሤ አክሊሉ ጀን ሆይ ግእዝ በሚገባ ያውቃሉ። ትርጉሙን ብቻ ሳይሆን ግእዙን በሚገባ ይናገሩታል። «ኢያእመራ ዮሴፍ እስከ አመ ወለደት... ያለውን ይዘው ነው» ሲሉኝ... ግእዝ አዋቂነታቸውን ይበልጥ ሳረጋግጥ ችያለሁ ብለ ዋል አፈ ሊቅ።

አፈ ሊቅ አክሊሉ ገ/ኪሮስ ከወ/ሮ እንተ ማርያም ሠረቀ ብርሃንና ከመሪጌታ ገብረ ኪሮስ ኃይለ ገብርኤል መጋቢት ፳ ቀን ፲፱፻፬ ዓ.ም በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ ቀሻ ማርያም እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ተወለዱ።





በአራት ዓመታቸው በአያታቸው ቤት ትምህርት /ፊደል መቁጠር/ ይጀምሩና በተለያዩ ችግሮች የተነሣ የጀመሩትን የፊደል ትምህርት ያቋርጣሉ። ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ በ፲፱፻፲ ዓ.ም ያቋረጡትን ትምህርት ጀምረው ንባብና ዳዊት በአንድ ዓመት ውስጥ ደግመው በማጠናቀቃ ቸው ድግስ ተደግሶ ለወላጆቻቸውና ለአያቶቻቸው የምሥራች ተብሏል።

በ፲፱፻፲፬ ዓ.ም ሚያዝያ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በጊዜው ከነበሩት ሊቀ ጳጳስ ከአቡነ ማቴዎስ ማዕርገ ዲቁና ተቀብለዋል። ከዚህ በኋላ የዜማ ትምህርት ለመቀጸል እንዲችሉ አባታቸው አዲስ አበባ ጽርሐ አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ደብር ያስተምሩ ከነበሩት ከሊቀ ጠበብት ደስታ ተገኝ ዘንድ ልከዋቸው ተምረዋል። በሁለት ዓመት ከስድ ስት ወር የቆይታ ጊዜያቸው ጾመ ድጓና ምዕራፍ ካጠኑ በኋላ ወደ ዝቋላ ገዳም ተጉዘው ወንበር ማርያም ከተባለች ደብር ብሉይና ቅኔ ያስተምሩ ከነበሩት ከመምህር ደስታ ቅኔ ቀጽለዋል። በዚሁ ገዳም ቅኔ ያስተምሩ ከነበሩት ከመምህር ኮከብ ዘንድ ቅኔ እስከ ዘይእዜ ያለውን ጉዳና ተምረዋል። በመጨረሻም የሐዲስና ዜማ አቋቋም መምህር ከነበሩት ከሊቄ ቀጸላ ወልደ መድኅን ቅኔውን ከነግሡ እርባታ ካስፋፉ በኋላ ለመቀኘት ሲበቁ በጉለሌ ሩፋኤል ደብር እንዲቀኙ ተፈቅዶላ ቸው ለደብሩ አለቃ ለአለቃ ሡርጹ ኃይሌ ደብዳቤ ተጽፎ ከዝቋላ ገዳም መጥተው ተቀኝተዋል።

በ፲፱፻፲፮ ዓ.ም ወደ ዝቋላ ገዳም በመመለስ ቅኔውን በማስፋፋት ከቆዩ በኋላ በ፲፱፻፲፰ ዓ.ም መምህራቸውን ሊቄ ቀጸላን ተከትለው ወደ አዲስ አበባ መጡ። ሊቄ ቀጸላ ግቢ ሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት እንዲያገለግሉ ሲመደቡ እርሳቸውም በዚህችው ቤተ ክርስቲያን የቅ ኔውን አገባብ ቀጸሉ። ከዚህ በኋላ የታወቁት መምህር ወልደ ጊዮርጊስ እንጦጦ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን የመጻሕፍተ ሐዲሳት ትርጓሜ ያስ ተምሩ ነበር። አክሊሉ ገ/ኪሮስም ከኒሁ መምህር የግብረ ሐዋርያትን ትርጓሜ መማር ጀመሩ። ከዚያም አባታቸው በቀጨኔ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ብሉይና ቅኔ ያስተምሩ ከነበሩት ከአለቃ ገብረ ኢየሱስ ዘንድ ቅኔያቸውን እንዲያስፋፉ የብሉያትንም ታሪክ እንዲሰሙ ልከዋቸዋል።



www.ethiopianorthodox.org

የዳዊትን፡ የዳንኤልን፡ የኢሳይያስን ትርጓሜ ከአለቃ ገብረ ኢየሱስ ወልደ አማኑኤል አጥንተው የአራትን ትርጓሜ እንደ ጀመሩ አባታቸው መምህር ገብረ ኢየሱስ በ፲፱፻፲፯ ዓ.ም ኅዳር ፲፬ ቀን በማረፋቸው የትምህርት ትጋታቸው በብርቱ ኀዘን ታወከ። ኀዘኑ ቢበረታባቸውም አባ እንግዳ የሚባሉ መምህር በዚያው በቀጨኔ መድኃኔዓለም ቅኔ ያስተምሩ ስለ ነበር ቅኔውን እያስፋፉ ከቆዩ በኋላ መምህራቸው ለማስተማር የበቁ ናቸው በማለት እንዲያስተምሩ ፈቀዱላቸው።

አፈሊቅ አክሊሉ በነበራቸው የመማር የማወቅ ፍላጎት የተነሣ ወደ ተለያዩ መምህራን በመሄድ ዕውቀታቸውን ያስፋፉ ነበር። በ፲፱፻፲፯ ዓ.ም ስመ ጥሩው አለቃ ለማ ኃይሉ የቀጨኔ መድኃኔዓለምን ደብር ሰልቅና ተሹመው በመጡ ጊዜ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ የሐዲስን ትርጓሜ ከሳቸው መማር ጀመሩ። አለቃ ለማም የተዋሕዶ ሃይማኖት ዋና አብነትና ሊቅ እንደ መሆናቸው መጠን ብዙ ምሥጢር አስጠንተዋቸዋል። አለቃ ለማም የአፈ ሊቅ የቀለም አያያዝ ችሎታ ስላስደነቃቸው «የዚህን ልጅ ራትና ምሳውን ሳልችል የቀረሁ እንደ ሆነ እኔ ለማ አይደለሁም» እያሉ ለባለቤታቸው ይነግሯቸው ነበር። በኋላ ላይ ግን ለአራት ተማሪዎች ከመንግሥት ቀለብ ተሰጥቷቸው እንዲማሩ መፈቀዱን ሊቁ ቀጸላ ለአክሊሉ ይነግሯቸዋል። በዚህ ጊዜ ከቀጨኔ መድኃኔ ዓለም ወደ ሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት መዛወር ግድ ሆነባቸው። ሊቁ ቀጸላም ቀለም ይገባሃልና አንዱ ቀለብ ለአንተ እንዲሰጥ ፈቅጄ ልሃለሁ። ስምህም በጽሕፈት ሚኒስቴር እንዲገባ ተደርጓል ብለው ይነግሯቸዋል። ስለዚህ ከ፲፱፻፲፱ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ድረስ ለዘጠኝ ዓመታት የሐዲሳት ትርጓሜን በሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት ተከታትለዋል።

በመቀጠል ከቀጨኔው የድጓ መምህር ከአለቃ ወልደ ዮሐንስ፣ ከመሪጌታ መርዓዊ ከዮኔታ ዘለዓለምና ከአለቃ ሀብተ ጊዮርጊስ ዝማሬ መዋስዕትና አቋቋም፣ ከአባ ገብረ ትንሣኤ የተክሌን ዝማሜ አጥንተዋል። አለቃ ሀብተ ጊዮርጊስ ያስጠኗቸውን ዜማ ደህና አድርገው ስለ ያዙላቸው ዝማሬ መዋስዕቱን አስተምር ብለው ፈቅደውላቸው ነበር።





የሃይማኖት ጥያቄ ለመመለስ እንዲችሉ የሊቅ ትምህርት ለመማር ወደ ሊቀ ሊቃውንት ሞገስ ዘወልደ ማርያም ዘንድ በመሄድ ትምህርት ጀመሩ። ከ፲፱፻፶፬ ዓ.ም ጀምሮ ሊቀ ሊቃውንት ሞገስ እስከ ዐረፉበት ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ድረስ ለሃያ ሦስት ዓመታት የሃይማኖተ አበውን፣ የዮሐንስ አፈወርቅ የቅዱስ ቄርሎስን መጻሕፍት፣ ትርጓሜን አጥንተዋል።

አፈሊቅ አክሊሉ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ከመማር ከማንበብ አልተለዩም ነበር። ለዚህም «ሊቅ እየተማረና እያስተማረ ይሞታል»፣ «ያነበበ ዕውቀትን ጠገበ»፣ «መጠየቅ ያደርጋል ሊቅ» የሚሉ ብሂሎችን ዘወትር ይጠቀሙ ነበር።

አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ አቶ በትረ ጽድቅ ካሣ በተባሉ መምህር እንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲያጠኑ ከተመረጡት የቤተ ክህነት ሊቃውንት መካከል አንዱ በመሆን በላይኛው ቤተ መንግሥት /በአሁኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ/ ሲከታተሉ ቆይተው በቅድስት ሥላሴ ት/ቤት አባ ማርቆስ የተባሉ ግብጻዊ የቋንቋ መምህር ተሰጥቷቸው እስከ ፰ኛ ክፍል ድረስ ተምረዋል። በ፲፱፻፴፰ ዓ.ም በቤተ ክህነት የድርሰት ክፍል ሥራ በመጀመራቸው የተነሣ በቅድስት ሥላሴ ጀምረውት የነበረውን የቋንቋ ትምህርት አቋርጠው በማታው የትምህርት ክፍለ ጊዜ በአሜሪካን ኢንስቲትዩት ት/ቤት በመማር የ፪ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል።

## አፈ ሊቅ አክሊሉ በቤተ ክህነትና በመንግሥት ሥራ ላይ

ከ፲፱፻፴፰-፲፱፻፶፫ ዓ.ም ድረስ ለ፲፭ ዓመታት በጠቅላይ ቤተ ክህነት በድርሰት ክፍል በዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ በየበዓሉ የሚወጡትን ድርሰቶችና እንዲሁም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ሃይማኖታዊ ሥርዓትና እምነት የሚቃወም ጽሑፍ ሲወጣ ለዚያ መልስ የሚያዘጋጁ አፈሊቅ አክሊሉ ነበሩ። ይህም መልስ የሚሰጡበት መጽሔት «መርሐ ምእመናን» በመባል የሚታወቅ ነው።

በ፲፱፻፵፰ ዓ.ም የኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራት ንዋየ ቅድሳት ሁሉ አዲስ አበባ ላይ ተሰብስበው እንዲቆዩ ተደርጎ በነበረ ጊዜ



www.ethiopianorthodox.org

«መዘክረ ምግብ መንፈሳዊ» የተባለውን ድርሰት በትእዛዝ አዘጋጅተው ያቀረቡት አፈሊቅ አክሊሉ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም ዜና ባስልዮስ የተባለ መጽሔት አዘጋጅተው አቅርበዋል። የሃይማኖት ክርክር በተነሣ ጊዜ በልዩ ልዩ የሀገር ውስጥ ጉባኤዎች ተካፋይ ከመሆናቸውም በላይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተዘጋጀው ሦስተኛው የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ጉባኤም ላይ በመገኘት በወቅቱ ለተነሱ የሃይማኖት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ በመስጠት ተሳትፈዋል።

በቤተ ክህነት በማገልገል ላይ እያሉ በግእዙ መዝሙረ ዳዊት ውስጥ የሚገኘውን ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያምን በጽሕፈት ሚኒ ስቴር ትእዛዝ ከግእዝ ወደ አማርኛ ተርጉመው በማቅረብ እስከ አሁን ድረስ እያገለገለ ይገኛል።

አፈ ሊቅ አክሊሉ በነበራቸው ጥልቅ የሥነ ጽሑፍ ችሎታና ዝን ባሌ በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም ከቤተ ክህነት ወደ ማስታወቂያ መርሐ ብሔር ሚኒስቴር ተዛውረው እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ድረስ ለ፲፫ ዓመታት አገ ልግለዋል።

በአዲስ ዘመን ጋዜጣና በኢትዮጵያ ሬዲዮ ታሪክ ጠቀስ የሆኑ የሐ ተታ ጽሑፎችን በማዘጋጀት ይሠሩ ነበር። በተጨማሪም በኢትዮጵያ ሬድዮ «አባትህን ጠይቀው ይመልስልሃል» በሚል ርእስ ትምህርታዊ የጥያቄና መልስ ፕሮግራም እያዘጋጁ ያቀርቡ ነበር።

በዚሁ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በሥነ ጽሑፍ ምርመራ አገልግ ሎት ውስጥ ልዩ ልዩ ድርሰቶችን በማረም ሠርተዋል። በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ከማስታወቂያ ሚኒስቴር በጡረታ ከተገለሉ በኋላ በቤታቸው ጽሑፎ ችን እያዘጋጁ ቆይተዋል። የሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት በሆ ኑት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ትዕዛዝና ፈቃድ በ፲፱፻፸ ዓ.ም እንደ ገና ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ተመልሰው በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት እስከ ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ድረስ በአርማትና በመጻሕፍት ምርመራ ክፍል አገልግለዋል። በጠቅላላ ለሃምሳ አንድ ዓመታት በቤተ ክህነትና በመንግሥት ሥራ ያገለገሉ ሲሆን በመጨረሻ የሕይወት ዘመ ናቸው አካባቢ በሕመም ቢያዙም እንኳ በዜና ቤተ ክርስቲያን፣ በአዲስ





ዘመንና በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጦች ላይ ስለ ግእዝ ቋንቋና ታሪክ በተደጋጋሚ በመጻፍ፣ ስለ ኢትዮጵያ በዓላትም በሬድዮና በቴሌቪዥን ለሚቀርቡላቸው ቃለ ምልልሶች በቂ መልስ በመስጠት እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ እንደበታቸው መልስ ከመስጠት ሳይገታ ባታቸው ብዕር ከመጨበጥ ሳይረታ ቆይቷል።

አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ ይሠሩ በነበረበት ወቅት የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አዘጋጅ /አንጋፋው ጋዜጠኛ ነጋሽ ገብረ ማርያም/ ለአፈ ሊቅ «ኤዲቶሪያል ለሚለው የእንግሊዘኛ ቃል ምን አማርኛ ትርጓሜ እንስጠው?» ሲል ይጠይቃቸዋል። ሊቁም፣ በሐዲስ ትምህርት፤ አንቀጸ-ትምህርት፣ አንቀጸ-ጾም፣ አንቀጸ-ምጽዋት አንቀጸ-መስዋዕት የሚል መኖሩን ለጋዜጣው ዋና አዘጋጅ በአስረጅነት ከገለጹላቸው በኋላ፣ ርእሰ-አንቀጽ ቢባል የሚስማማ መሆኑን ይገል ጹላቸዋል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ርእሰ አንቀጽ የሚለው ጸድቆ እስከ ዛሬም ድረስ እየገለገለ ይገኛል።

በዚሁ መሥሪያ ቤት ይሠሩ በነበሩበት ጊዜ በመንግሥት ትእዛዝ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ግማደ መስቀል ወደ ኢትዮጵያ አመ ጣጥ ታሪክ እንዲመረምሩ ለተላኩት የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ የጋ ዜጠኞች ቡድን መሪ በመሆን ግሼን ደብረ ከርቤ ማርያም ቡድኑን በመምራት ሄደው «ጤፉት» ከተባለው መጽሐፍ የመስቀሉን አመጣጥ ታሪክ ከግእዝ ወደ አማርኛና እንግሊዝኛ እንዲተረጎም በማድረግ ታሪኩን በመጽሔት ጽፈው በማቅረብ ከፍተኛ ተግባር ፈጽመዋል።

በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም ከሊቀ ሊቃውንት መሐሪ ትርፌ /በኋላ በብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ/ አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ ተብለው ተሹመዋል። ይህም ሹመታቸው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተመክሮ የጸደቀ ነው።

አቶ ንጉሤ አክሊሉ የአፈ ሊቅ አክሊሉ ገ/ኪሮስ ልጅ ናቸው። በአ ንድ ወቅት የእሑድ ፕሮግራም የሬዲዮ ጋዜጠኛ በነበሩበት ጊዜ ከአ ባታቸው ጋር ቃለ ምልልስ የማድረግ አጋጣሚ አግኝተው ነበር። በዚያ ወቅት የነበረውን ሁኔታ ጋዜጠኛ ንጉሤ አክሊሉ እንዲህ ያስታው ሱታል።



www.ethiopianorthodox.org

በወርኃ ግንቦት ጋብቻ ለምን አይፈጸምም? ቤተ ክርስቲያንስ በዚህ ላይ ያላት አቋም ምንድን ነው? የሚለውንና የኅዳር በሽታንና የኅዳር መታጠንን አስመልክተን ለእሑድ ጠዋት የሬዲዮ ፕሮግራም አንድ ዝግጅት እንድናቀርብ እኔና የሥራ ባልደረባዬ እና ጓደኛዬ አዲሱ አበበ /ዛሬ የአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ ጋዜጠኛ/ በአለቃችንና በመምህራችን በጋዜጠኛ አቶ ሙሉጌታ ሉሌ እንታዘዛለን። «ይሄ የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ስለሆነ ንጉሤ ቢሠራው ይሻላል ይላል አዲሱ። እሱ በደጁ ያላለፈ ይመስል...። መሥራቱንስ ልሥራ ለመሆኑ ማነው ተጠያቂው?» አልኩ። አፈሊቅ ናቸው አባትህ...» አለኝ አለቃዬ። «አባቴን ኢንተርቪው ሳደርግ ሰው ጉድ አይልም?» በማለት መከራከር ጀመርኩ። በብዙ ክርክር ሐሳቡን ተቀበልኩ። ዝግጅቱንም ሠራሁት። አፈ ሊቅ ኅዳር ለምን እንደ ሚታጠን ዘረዘሩ የኅዳር በሽታ መንሥኤን ዘከሩ.... በግንቦት መጋባትም ክልክል እንዳልሆነ ነውርም እንደሌለበት አስረዱ።... አባትህን ጠይቀው ይነግርሃል የሚለው ቃልም በዚህ መልኩ ተፈጸመ።

አቶ ንጉሤ ከአባታቸው ከአፈሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ ጋር ስለነበረው ሁኔታ ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ። «ጊዜው በ፲፱፻፶ዎቹ መጨረሻ ላይ ነው። በየዓመቱ ጥር ፳፩ የምትውለውን የአስተርእዮ ማርያምን በዓል ለማክበር ቀደም ብለን ተዘጋጅተን ከአባቴ ጋር አገራችን ተጉለት እንገባለን። ላይ ዋሻ ማርያም ከመግባታችን በፊት እግረ መንገዳችንን ከአያቶቻችን አገር ከዘንደጉር ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ጎራ እንላለን። ጥር ፳፫ ቀን የሚውለውን የጊዮርጊስን «የሰባረአጽሙን» በዓል በዚያ እናከብራለንና «የዘንድሮው እጣን ሞገር /ቅኔ/ ያንተ ነው» አሉኝ አፈ ሊቅ በጉዞ ላይ እያለን። አባቴ ባዘዙኝ መሠረት ቅኔውን አዘጋጅቼ ክብር ይእቲውን ከሙሁሩ በኋላ እጣነ ሞገሩን የሚመራ ሰው ጠፋ- የሚያዜም። አፈሊቅ ተመሪ ሆነው ጠጋ አሉ!! እኔ በጆሮአቸው ቅኔውን ስነግራቸው እሳቸው በዜማ ሲያንቆረቁሩት... አንድ ቦታ ላይ ዜማ ስበርኩ መሰለኝ «ሸሽሽ» አሉ ቀስ ብለው። ወዲያው ነገሩ ወደ ሌሎች ካህናት ጆሮ ሳይደርስ የተሰበረውን አስተካከሉትና መሪና ተመሪነቱን ቀጠልን።.... ምልጣኑ ላይ ደግሞ እሳቸው መስቀሉን





ይዘው ይመራሉ እኔ እመራለሁ ይሄ ሁልጊዜ ሳስታውሰው የምኖረው ገጠመኝ ነው። አባትና ልጅ መሪና ተመሪ ሆነን አሳለፍን።»

አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ ለዛን ከቁም ነገር ጋር አዋዝተው የመናገር ችሎታም ነበራቸው። ልጃቸው አቶ ንጉሤ የገጠሙትን እንዲህ ያስታውሱታል። «አንድ ቀን መንገድ ላይ ተገናኘንና ገበሬ «ማኅበራት» የሚለው ለሴቶች ነው። ዜና ስታነቡ ብዙ ጊዜ እንደዚያ እያላችሁ ትሳሳታላችሁ። ወይ ደረቁን «ገበሬ ማኅበሮች» በሉት። ካልሆነም «ክቡራትና ክቡራን» እንደሚለው «ማኅበራት-ማኅበራን» በሉት ብለውኝ ከሄዱ በኋላ እንደ ገና ጠሩኝና «ተወው ልጄ! ተወው! ዛሬ ወንዱ ሁሉ ሴት ስለሆነ እንዳሉህ አንብብ» አሉኝና ጉዟቸውን ቀጠሉ።»

አንድ ጊዜ ደግሞ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ባስልዮስ «አራዳ ጊዮርጊስን እልቅና ልሹምህ» ይሏቸዋል። አባታቸው አባ ገብረ ኪሮስ እዚያ ያገለግሉ ነበር። ያን ጊዜ ገዳማትና አድባራት የሚተዳደሩት በገጠር ርስት እና በከተማ ቦታ ነበር። አፈ ሊቅ ደግሞ የመጻሕፍተ ሊቃውንት ትርጓሜን በትርፍ ጊዜአቸው ከሊቀ ሊቃውንት ሞገስ ዘንድ ይማሩ ነበርና «አባታችን ... አመሰግናለሁ። ነገር ግን እኔ የቤተ ክርስቲያኑ ርስት ቀረ ብዬ ስሟገት ዋናው እና ትልቁ ቁም ነገር ቃለ እግዚአብሔሩ ይቀራል፤ ትምህርቱም ይረሳል።» ብለው በትኅትና መልሰውላቸዋል።

አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ ሀገራቸውንና ቤተ ክርስቲያንን ያለመታከት ሲያገለግሉ ቆይተው ኅዳር ፲፮ ቀን ፲፱፻፹ ዓ.ም ዐርፈዋል። የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ኅዳር ፲፯ ቀን ፲፰፻፺፮ ዓ.ም በአደጉበትና በተማሩበት በአዲስ አበባ ጽርሐ አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል።

*ምንጭ፦ የሰባት ዓመት ማስታወሻ ለአፈ ሊቅ አክሊሉ ገ/ኪሮስ /ምሉዕ በኩልሄ/ ከንጉሤ አክሊሉ። ፲፱፻፹፯*

- *ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ፣ ኅዳር ፴ ቀን ፲፱፻፹ ዓ.ም*
- *ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ፣ ታኅሣሥ ፲፱፻፹ ዓ.ም*



www.ethiopianorthodox.org

# እማሆይ ገላነሽ አዲስ

## /፲፰፻፹፱ - ፲፱፻፸፭/

*በተስፋዬ ሽብሩ*

ስለ አንዲት ስመ ጥሩ ኢትዮጵያዊት መምህርትና ባለ ቅኔ ታሪክና ማንነት ለመጻፍ ስናስብ ስናወጣና ስናወርድ አንዲት አሜሪካዊት ወደ አእምሮአችን መጣች፡፡ ሄለን ኬለር፡፡ ይህቺ ወጣት ዓለማችን ካፈራቻቸው አስደናቂና አስገራሚ ሰዎች አንዷ ነበረች፡፡ ማየትም፣ መስማትም መናገርም ፈጽሞ አትችልም፡፡ ዓይነ ሥውር ብትሆንም በርኪታ መጻሕፍት ከማንበብ አልተገታችም፡፡ ማንበብ ብቻም ሳይሆን ሰባት



*የደብረ ጽጋሉዋ የአገቢያ ኮከብ*

መጻሕፍትንም ለመጻፍ ችላለች፡፡ ከዚህም ያለፈ በርካታ ቁም ነገሮችንም ሠርታለች፡፡ ሄለን ኬለር ስማቸው ዝንተ ዓለም ገንኖ ከሚነገርላቸው ጥቂት ጠንካራ ሰዎች ተርታ የምትመደብ ሥራዋ ጥረቷ ከማንም ሰው አእምሮ የማይደበዝዝ ታላቅ ሴት ናት፡፡

አገር አቋርጠው ውቅያኖስ ከፍለን ተጉዘን ስለ አንዲት ባዕድ ሴት እንድናስታውስ ያደረጉን

*ጉንጅና ጽላሉ አንድ ነው መሬቱ፤*

*ጽላሉ ይበልጣል አንቺ ያለሽበቱ* የተባለላቸውና ማር ቀጠሉ አድናቆቱን የቸራቸው እማሆይ ገላነሽ አዲስ /ዘጽላሉ አማኑኤል/ ናቸው፡፡ ከቄስ ገበዝ ሐዲስ ኪዳናትና ከወ/ሮ ወርቅነሽ እንግዳ በምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት በይልማና ዴንሳ ወረዳ በሚገኘው ደብረ ጽላሉ





አማኑኤል በ፲፰፻፹፱ ዓ.ም ተወለዱ፡፡ በእናት አባታቸው ቤትም በክብካቤ አደጉ፡፡ አባታቸው የሚያስተምሩትንም ቅኔ ሥራዬ ብለው ይከታተሉ ነበር፡፡

የስምንት ዓመት ልጅ እያሉ አንድ ቀን ከእናታቸው ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ፡፡ በሴቶች መቆሚያ ከእናታቸው ፊት ተቀምጠው እንዳሉ በዚያው ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉት አባታቸው ከሥርዓተ ቅዳሴው በኋላ ቅኔ ይዘርፋሉ፡፡

«በታቦርሂ አመ ቀነጸ መለኮትከ ፈረስ» ማለትም መለኮትህ ፈረስ በደብረ ታቦር ተራራ በዘለለ ጊዜ ብለው ቄስ ገበዝ ለዓለሙን ሲጀምሩ፤ ገላነሽ ሐዲስ ባልታሰበና ባልተጠበቀ ሁኔታ ከተቀመጡበት ተነሥተው «ኢክህሉ ስሂቦቶ ሙሴ ወኤልያስ» አሉና ነጥቀው እርፉ፡፡ ትርጉሙም ሙሴና ኤልያስ ሊስቡት አልቻሉም ብለው አባታቸውን በጉባኤ መካከል ነጥቀዋቸው መወድሱን ጨርሰውታል፡፡ አባታቸውም እዚያው ጉባኤ መካከል አዚምሳት በማለት ተናግረዋል ይባላል፡፡ በኋላም መልሰው እንዲህ አሏቸው፡፡ «ወእንዘ ትትናገሪ ዘንተ በአድኅኖ ክሳድ ወርእስ በከመ አነ ሰማዕኩኪ ኢይሰማዕኪ ጳውሎስ፡፡»

ይህ ጳውሎስ በመልእክቱ ሴቶች በጉባኤ መካከል ገብተው እንዳያስተምሩ የተናገረውን ቃል በማስታወስ እኔ እንደ ሰማሁሽ ይህንን ስትናገሪ ጳውሎስ እንዳይሰማሽ ለማለት ነው፡፡

ከዚህ በኋላ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የተሰባሰቡት ሊቃውንትና ሕዝብ ይህ ምሥጢር እንደተገለጸላቸው ባዩ ጊዜ፤ በሁኔታው በመገረምና በመደነቅ ካህናቱ በወረብ፣ ኅብዛዙ በሆታ ሴቱ በእልልታ ገላነሽን እያመሰገኑ መንገድ ጀመሩ፡፡ እንደ ንግሥት ጉዞ በእልልታ ሆነው መጋረጃ ተጋርደላቸው እቤታቸው ደረሱ፡፡ ሕዝቡም ከፍ ያለ የደስታ ግብዣ አድርጎ ሰነበተ፡፡

ይህ ደስታ ብዙም ሳይቆይና ስሜቱ ሳይደበዝዝ ገላነሽ ሕይወት ላይ አስደንጋጭ ክስተት ተፈጠረ፡፡ በሊጋ ዕድሜያቸው ኩፍኝ በተባለ በሽታ ይያዙና ዓይኖቻቸው የማየት ብርሃናቸውን ያጣሉ፡፡ ይሄን ጊዜ አባታቸው የቤተ ክህነት ትምህርት እንዲጀምሩ በማድረግ ዳዊትን፣



www.ethiopianorthodox.org

ውዳሴ ማርያምን፣ ቅዳሴ ማርያምን፣ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜን እንዲሁም ለዘመናት ሲያስተምሩት /ከሃምሳ ዓመታት በላይ/ የኖሩትን ቅኔን ከነ አገባቡ በሚገባ እንዲያጠናቅቁ ያደርጋሉ። ለካ የዚያን ጊዜዋ ገላነሽ ሐዲስ ዐይናቸው እንጂ ልባቸው ብርሃን ነበረ።

ገላነሽ አባታቸው ካስተማሯቸው በኋላ በመምህርነት ይመርቋቸውና በአባታቸው ጉባኤ ውስጥ ተቀምጠው በየተራ ሲያስተምሩ ቆይተዋል:: ለአካለ መጠን ሲደርሱ ወላጆቻቸው «እኛ ከሞትን ማን አላት? ባል ታግባና ልጅ ትውለድልን» ብለው በማሰብ በዚሁ ገዳም ጽላሎ አማኑኤል አካባቢ ተወልደው ያደጉ ነገር ግን የቤተ ክህነት ትምህርት ያልተማሩ አቶ ጥሩነህ በላይ የተባሉትን ሰው አጋቧቸው:: ባል ያግቡ እንጂ ከወላጆቻቸው ቤት ሳይወጡ አብረው እየኖሩ ሲያስተምሩና አባታቸውን ሲረዱ በማኅበራዊ ክንዋኔዎችም ሲሳተፉ ኖረዋል። በዚህ ትዳራቸው አዳም ጥሩነህና መሠረት ጥሩነህ የተባሉ ወንድና ሴት ልጆች አፍርተዋል:: ሦስተኛ ልጃቸው ግን በሕፃንነቱ ሞቶባቸዋል::

ገላነሽ በዚህ ሁኔታ ኑሯቸውን እየገፉ ባሉበት ጊዜ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም የጣልያን ፋሽስት መንግሥት ሀገራችንን ኢትዮጵያን ወረረ:: የጽላሎ ሕዝብ ገዳሙን ትቶ በመሸሽ ጫካ ገባ:: ቄስ ገበዝ ሐዲስ፣ ባለቤታቸው፣ ልጃቸው ገላነሽ ከሊቃውንቱም ከመነኩሳቱም የተወሰኑት «ቤተ ክርስቲያናችንን እንዴት ትተን እንሄዳለን» በማለት በዚያው በገዳሙ ቀሩ:: የጣልያን ጦርም በሚያሳዝን ሁኔታ እዚያ ያገኛቸውን ሊቃውንትና መነኩሳት የገላነሽን ወላጆች ጨምሮ በግፍ ገደላቸው:: ገላነሽ ሀይነ ሥውር ስለ ነበሩ ሳይገድሏቸው ከሞት አመለጡ:: ወላጆቻቸውን በሞት በመነጠቃቸው ግን ሕይወታቸው ጎደሎ ሆኖ ነበር::

ገላነሽ የገጠማቸውን መከራ ተቀብለው በመመንኮስ ሀገር ሰላም ሲሆን ከዚያው ከአባታቸው ቦታ ላይ ጉባኤያቸውን አጠናክረውና አስፍተው የተጠሩበትን የቅኔ መምህርነት በመቀጠል ማስተማሩን ተያያዙት:: ተማሪው ዝናቸውን ከየሀገሩ እየሰማ በእርሳቸው እየተደነቀ





ለመማር ይጎርፍ ነበር:: በቅኔ መምህርነት በቆዩባቸው ኀምሳ ዓመታት ውስጥ ከጎጃም፣ ከጎንደር፣ ከትግራይ፣ ከኤርትራና ከሸዋ ክፍላተ ሀገራት እንዲሁም ከላስታና ከላሊበላ የተሰበሰቡትን አንድ ሺ ሰባት መቶ ሃምሳ ተማሪዎች አስተምረዋል:: ከኢትዮጵያ የተለያዩ ክፍላተ ሀገር የመጡ ሠላሳ ስድስት መሪጌቶችን በቅኔ መምህርነት አስተምረው ብቁ መሆናቸውን በመመስከር አረጋግጠዋል::

እማሆይ በመማር ማስተማር ሥራ ላይ ሴቶች ከወንዶች እኩል መሆናቸውን ሁልጊዜ ይናገሩ ነበር:: ይህንንም ቀሲስ ከፍያለው መራሒ «ሴቶች በኢትዮጵያ» በሚለው መጽሐፋቸው ገልጸውት ይገኛል:: እማሆይ «መማርም ሆነ ማስተማር ብርታትን እንጂ ጾታን አይመለከትም:: ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል ተሰልፈው መሥራት የኖረ እንጂ እንደ እንግዳ ደራሽ አይደለም» ይሉ ነበር:: ለዚህም ማስረጃ ሲጠቅሱ መምህራችን ክርስቶስ ሴቶች ደቀ መዛሙርቱን ሂዱና ትንሣኤዬን ንገሩ ብሏቸዋልና ልዩነት የለም ይላሉ::

እማሆይ ገላነሽ አዲስ በጠባያቸው አስተዋይ ብልህና ንቁ እንዲሁም ቅን አሳቢ ሰው እንደነበሩ የሚያውቋቸው ሰዎች ይናገራሉ:: ችኩልነትን'ንና ሽንፈትን የማይወዱ የማስተማር ፍቅር የተሰጣቸው የዘመናችን ታላቅ ሴት ናቸው:: እማሆይ ዐይነ ሥውር ይሁኑ እንጂ ዐይነ ሥውርነታቸው ሴቶች ከሚያከናውኗቸው ድርጊቶች አልገታቸውም:: ልጅ ወልደው ያሳደጉ፣ በቀለም ያጌጡና የተሸለሙ ስፌቶችን ይሰፉ፣ ከዐይናማዎች እኩልም ፈትል ይፈትሉ ነበር:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ለሌሎች ከብደው እንዳይገኙ በዚህ ሞያቸው በሚያገኙት ገቢ ራሳቸውን ያስተዳድሩ ነበር::

ለብዙ ሰዎች ዐይነ ሥውር መሆን ድቅድቅ ጨለማን ያህል ከባድ ነው:: አንድ ጊዜ ሄለን ኬለር «እኔን እዩ የዐይን ብርሃን የለኝም ግን አያለሁ፣ ጆሮዬ አይሰማም ግን አዳምጣለሁ:: አንደበቴ ተዘግቷል:: ግን ዲዳ አይደለሁም» ያለችውን ስናስታውስ እማሆይ ገላነሽም ዐይነ ሥውርነታቸው ከማየት ከመመራመር ከማስተማር አልከለከላቸውም::

እማሆይ ገላነሽ ለብዙ ዘመናት ሊቃውንት በማፍራትና በጥሩ ሥነ ምግባር ያሳለፉ፣ በአካባቢያቸው ሕዝብ ዘንድም ዝናን ያተረፉ ሊቅ እናት እንደሆኑ ታሪካቸው ምስክር ነው::



www.ethiopianorthodox.org

እማሆይ ገላነሽ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በባሕር ማዶ ማይቀር ዝናቸው የታወቀ በመሆኑ ከውጭ ድረስ እየመጡ የተለያዩ ግለሰቦች ይጠይቋቸው እንደነበር ይነገራል።

የእማሆይ ገላነሽ ሐዲስ ሥራዎች ለግእዝና ለአማርኛ ቅኔዎች ዕድገት አስተዋጽዖ አበርክተዋል። ለምሳሌ ያህል የአማርኛና የግእዝ ሁለት ቅኔ ዎቻቸውን ወስደን ብንመለከት የእማሆይ ገላነሽ ቅኔዎችን የምሥጢር ጥልቀትና ርቀት የቋንቋ ምጥቀት መገንዘብ ያስችለናል።

፩. ተርቢኖስ በኩር
እመ ኢበልዐ በልዐ
ምግበ ገድል ጸገብኩ
ኢይቤ ቤተ ሃይማኖት ጽኑዐ

**ትርጉም**

ተርቢኖስ በኩር የተባለ አለቃ ጽኑ ከሆነ የሃይማኖት ቤት የተጋድ ሎን ምግብ ቢበላም ባይበላም በቃኝ ጠገብኩ አይልም።

**ሰም**

ስስት ያለበት አለቃ ሰው እንጀራን ቢበላም ባይበላም ጠገብኩ አይልም።

**ምሥጢር**

ተርቢኖስ ማለት ጊዮርጊስ ነው። እሱም ሰማዕት ነው፤ የሰማዕታት አለቃ ነው። ስለዚህ ከሰባ ነገሥታት ጋር ሰባት ዓመት ተጋድሎ ሲያ ደርግ ከሃይማኖቱ ጽናት የተነሣ ደከመኝ ሰለቸኝ፤ ጠገብኩ ሳይል መከ ራን ስቃይን ተቀብሏል ሲሉ ነው።

**የአማርኛ መወድስ ቅኔ**
የአንተ ስጦታ ዓባይ
ዲካ የሌለው
ስለማይደርስበት ይብሰት
ሞልቶ ፈሰሰ በዓለም
የልብሀ ጥበብ ፈለግ
እየፈለቀ ከጎጃም





ማዕከለ ባሕር አልቆመ
ድልድይ ስመ እንቲአከ
ዘበየማን ወጸጋም
ይሻገሩ ዘንድ ወዳጆችህ
ሊቃውንተ ሥርዓት ወሕግ
የመረጥካቸው ቀደም
ለዓለም ወለዓለም
ጥበብሰ እመ ተከልኮ
በማይናወጽ ገዳም
የፍሬ ምስጋናን አፈራልን ሁሉን የሚጠቅም
ቀርበን ብናየው በዓይን
እስከ ሥሩ ነው ለምለም
በቅዱስ እጅህ ተባርኳልና የእርሱ ልምላሜ አይጠወልግም።

ለአብነት ያህል ይህንን ጠቀስን እንጂ መምህርቷ በቅኔዎቻቸው ውስጥ ብዙ ጉዳዮችን አመስጥረው ይገኛሉ። በተቀኟቸው ቅኔዎች ሃይ ማኖታዊ ይዘት ያላቸውን ቅኔዎች አመስጥረዋል። ከዚህ በመነሳት እማሆይ ሃይማኖተኛና መንፈሳዊነትን የተላበሱ እንደነበሩ እንዲሁም ሃይማኖታቸውን ጠንቅቀው በጥልቀት የተረዱ እናት እንደነበሩ ለማየት ይቻላል።

እማሆይ ገላነሽ እርጅና እየተጫናቸው ሲመጣ ቀድሞ የሚሠሩትን የእጅ ሥራ ለመሥራት ባለመቻላቸውና የምትረዳቸው ሴት ልጃቸው ትዳር በመያዟ የደረሰባቸውን ችግር በመስማት የካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም በባሳምባራስ ዘገየ ገብረ ወልድ አሳሳቢነት በሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ሕንፃ በአንድ ጽ/ቤት ውስጥ ጊዜያዊ የርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ ተቋቁሞ የበኩሉን ወገናዊ አስተዋጽዖ ተወጥቷል። እርሳቸውም በአንድ ወቅት «ከቤተ ክህነት ወይም ከሌላ የሚሰፈርልኝ ቀለብ የለም። በሥጋ የሚዛመዱኝ ጉልማ ያርሱልኛል። ተማሪዎቼም ተቀኝተው ለመምህ ርነት በቅተው ሲሄዱ የሰሌን ጥላና ምንጣፍ ሠርተው ያን ሸጠው ላበረከት ይሰጡኛል። የኔ ሕይወት ቅኔ ነው የቅኔ ዓይነት መዝረፍ፣



www.ethiopianorthodox.org

ሴላ ሕይወት የለኝም:: ከተማሪዎቼ የተለየ ምቾት አላገኘሁም:: በዚህም አላዝንም» በማለት በህልውናቸው በኑሯቸው በኩል ያለውን ጉዳይ በማቃለል ዘወትር ይናገሩ ነበር::

በዚህ ሁኔታ ከኖሩ በኋላ በተወለዱ በሰማንያ ዓመታቸው ባደረባቸው ሕመም ምክንያት የቅኔዋ ምንጭ እማሆይ ገላነሽ ሐዲስ ከነማ ይጠገብ ለዛቸው ሐምሌ ፲፪ ቀን ፲፱፻፸፰ ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: የቀብር ሥነ ሥርዓታቸውም ባደጉበትና ባስተማሩበት በደብረ ጽላሎ አማኑኤል ገዳም ተፈጽሟል::

እማሆይ ገላነሽ አዲስ ቤተ ክርስቲያንና ታሪክ ሊዘክራቸው የሚገቡ የዘመናችን የአጥቢያ ኮከብ ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም:: ሴቶች ቦታ ባላገኙበት በገጠራቱ ኢትዮጵያ በቅለው ለዚያውም ዐይነ ሥውርነት ተጨምሮበት ነጥረው የወጡ ስመ ጥሩ ሴት ናቸው:: ለዚህም ነው ዓለም የሃያኛው ክፍለ ዘመን አስገራሚ ሴቶች ካላቸው አንዷ ከሆነችው ሄለን ኬለር ጋር የእማሆይን ስም ለማንሳት የተሞከረው::

በአሁኑ ሰዓት በባሕር ዳር ከተማ በእኅት ልጃቸው በአቶ ተሾመ አዲስ እማካይነት መታሰቢያ ሙዝየም ተዘጋጅቶላቸው ሥዕላቸው በትልቁ ተሰሎና አንዳንድ ቅኔዎቻቸው ተሰብስበው ተቀምጠዋል:: ሙዝየሙን የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የሆኑት ብፁዕ አቡነ በርናባስ ጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም መርቀው ከፍተውታል::

እማሆይ ገላነሽ ሐዲስ ሕይወታቸውና ቅኔዎቻቸው /ሥራዎቻቸው/ ሊጠኑ ከሚገባቸው የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አንዷ መሆናቸውን ማስታወሱ ተገቢ ይሆናል::

<u>ምንጭ</u>:- ሰሎሞን ሐዲስ፣ የእማሆይ ገላነሽ ሐዲስ ዘጽላሎ አማኑኤል የሕይወት ታሪክና ሥራዎቻቸው፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል አ.አ.ዩ ፲፱፻፺ ዓ.ም

- ቀሲስ ከፍያለው መራሒ፣ የሴቶች መንፈሳዊ ሕይወት፣ ፲፱፻፷፫ ዓ.ም
- አዲስ ዘመን፣ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ.ም





# ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ገብረማርያም

/፲፰፻፹፰ – ፲፱፻፹፩/

በተስፋዬ ሽብሩ

⇒ በ፲፱፻፳ ዓ.ም ወደ ምድረ ግብፅ ተጉዘው መዓርገ ክህነት ተቀበሉ፤

⇒ በ፲፱፻፳፩ ዓ.ም የራስ ኪዳነ ማርያም ገበረ መስቀል ጸሐፊ ሆኑ፤

⇒ በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም መልአከ ሰላም ተብለው የሠራዊቱ አውራጃ ሊቀ ካህናት ሆኑ፤

⇒ በ፲፱፻፴፬ ዓ.ም የአገር ፍቅር ማኅበርን መሠረቱ፤

⇒ በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም ማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖትን አቋቋሙ፤

⇒ በ፲፱፻፶፭ ዓ.ም የሠራዊቱ አውራጃ የአገር ፍቅር ማኅበር ፕሬዚዳንት ሆነው ተመረጡ፤



በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር መዓርግ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበሩ



www.ethiopianorthodox.org

⇒ በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም ከከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤትን መሠረቱ፣
⇒ በ፲፱፻፵፰ ዓ.ም የኤርትራ ምክር ቤት አባል ሆነው ተመረጡ፣
⇒ በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም የኤርትራ ምክር ቤት ም/ፕሬዘዳንት ሆነው ተሾሙ፤
⇒ በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ም/ፕሬዚዳንት ሆነው ተሾሙ፣
⇒ በ፲፱፻፶፬ ዓ.ም ንቡረ እድ ተብለው የአክሱም ጽዮንና አውራጃዎዋ አስተዳዳሪነት ተሾሙ፣
⇒ ፲፱፻፷፩ ዓ.ም ጡረታ እስከ ወጡበት ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ድረስ በሚኒስትር ማዕርግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅ ላይ ቤተ ክህነት የቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ በመሆን አገል ግለዋል።

«ከ፲፱፻፶፯ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ድረስ የኤርትራ የፕሬስ ኃላፊና ጋዜጠኛም ሆኜ በቆየሁባቸው ዓመታት በቅርበት ካወቅኋቸው ታላላቅ ሰዎች አንዱ ክቡር ንቡረ እድ ድሜጥሮስ ገብረ ማርያም ናቸው። ገጸ አረጋዊነታቸው አለባበሳቸውና አነጋገራቸው ለየት ያለ ግርማ ሞገሳዊነትን አልብሷቸዋል። በቀረብኳቸው ቁጥር እየወደ ድኳቸውና ከልቤ እያከበርኳቸው ሄድኩ።»

ክቡር ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ገብረ ማርያም ታሪካቸው ሲዘከር ላቸው ከሚገባቸው ጥቂት ኢትዮጵያውያን አንዱ ናቸው። ባላቸው የሀገር ፍቅር ስሜት የኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ኤርትራን ከኢትዮጵያ ነጥሎ ይገዛ በነበረበት ዘመን ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ እንድትቀላቀል ሕይወታቸውን እንኳን መሥዋዕት ለማድረግ የደፈሩ የአባቶቻቸውን የአቡነ ጴጥሮስንና የአቡነ ሚካኤልን መንገድ ለመከተል ያላንገራገሩ የሀገርም የቤተ ክርስቲያንም መኩሪያ ነበሩ።

መንፈሳዊነታቸው፣ ለሰዎች ኑሮ መበልጸግ ማሰባቸው፣ ለሕዝቦች አንድነትና ሰላማዊነት መታገላቸው፣ ለዕውቀትና ልማት ዘወትር የሚ ጥሩ መሆናቸው ሁልጊዜ ይታወሰኛል። አሥመራም ሆነ አዲስ አበባ በነበሩበት ጊዜ ሁሉ እጠይቃቸው ስለነበር እጅግ ብዙ ብዙ ጉዳዮችን አጫውተውኛል።





ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሚያዝያ ወር ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ከስደት እንደ ተመለሱ ክቡር ንቡረ እድ ድሜጥሮስ በሐምሌ ወር ፲፱፻፴፫ ዓ.ም በምሥጢር ከኤርትራ አዲስ አበባ መጥተው ከግርማዊነታቸው ዘንድ ቀርበው "ኤርትራ አገርም ናት፣ ከቅኝ ገዥዎዎች ቀንበር ፈልቅቀው ወደ እናት አገርዋ እንዲቀላቀሏት አደራ" ባሏቸው ጊዜ "እኛም ይህንኑ ስለምናምንበት ነው፤ ገና ካርቱም እያለን በዐዋጃችን ያስታወቅነው" ስላሉኝ ነው ጥረቱን የጀመርነው ብለውኛል።

በኤርትራ ጀምረውት የነበረው የመንፈሳዊ ትምህርትና ጥበበ እድ በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ ብርቱ ጥረት አድርገዋል። ሁሉንም አሟልቶ የሰጣቸው የሀገርና የሃይማኖት ተቆርቋሪ፣ የአስተዳደር መሪ ነበሩ። እኝህን የሀገር ባለውለታ በማወቁ ክብር ይሰማኛል።» በማለት የንቡ ረ ዕድ ድሜጥሮስን ማንነት የተናገሩት ታዋቂው ጋዜጠኛና ደራሲ አቶ ማሞ ውድነህ ናቸው።

በዚህ ዙሪያ ስለ ንቡረ እድ ድሜጥሮስ ብዙ ሊባል የሚችል ነገር ቢኖርም ለዚህ ጽሑፍ አስፈላጊ የሚሆነውን ሐሳብ ብቻ ለማንሣት ተ ሞክሯል። በዚህ ረገድ ሌሎች ብዙ ሊሉበት ይችላሉ የሚል እምነት አለን።

## ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ገብረ ማርያም

ከመምህር ገብረ ማርያም ፍሥሓና ከወ/ሮ ወለተ አብ ማዕቀብ መስከረም ፲፮ ቀን ፲፰፻፹፮ ዓ.ም በቀድሞው የኤርትራ ክፍለ ሀገር በሠራዬ አውራጃ በዓረዛ ወረዳ ምድረ ወዲ ሰበራ ማይጨው ማይድማ ከተባለው ሥፍራ ተወለዱ። ወላጆቻቸው ያወጡላቸው ስም ኪነ ሥላሴ (የሥላሴ ጥበብ) የሚል ነበር። ዕድሜያቸው ለትምህርት በደረሰ ጊዜ ከወላጅ አባታቸው ፊደል ቆጥረው ዳዊት በመድገም መዓርገ ዲቁና ተቀበሉ። በመቀጠል ከመምህር ገ/ሚካኤል ዜማ፣ ጾመ ድጓና ምዕራፍ በመማር የዕውቀት አድማሳቸውን ማስፋት ቻሉ። ንቡረ እድ ድሜጥሮስ ለትምህርት በነበራቸው ጥልቅ ፍቅር የተነሣ የትውልድ መንደራቸውን ጥለው ለመሄድ ተገደዱ። ወደ ጎንደር ክፍለ ሃገር በመ ሄድ በደብረ ሚካኤል ወንበር ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት ከጌቴ ገሞ ራው ዘንድ ቅኔን ከነአገባቡ ተማሩ። ከዚያም ወደ ጭልጋ አውራጃ



www.ethiopianorthodox.org

በመሄድ ከመምህር መርሻ ለሁለተኛ ጊዜ ቅኔን አስፋፍተዋል። በመ- ቀጠል ወደ ጎንደር ከተማ ተመልሰው አደባባይ ኢየሱስ አቋቋምን ያስተምሩ ከነበሩት ከመምህር መኰንን ዘንድ አቋቋምን ተማሩ። ወደ ደብረ ዓባይ ተሻግረውም መዝገበ ቅዳሴን ተምረው አስመስክረዋል።

የወጣትነት ጊዜያቸውን ትምህርት በመቅሰም ያሳለፉት ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ወደ ትውልድ ሀገራቸው በመመለስ አገልግሎት ጀመሩ። አስተዋይነታቸውና ብልህነታቸው በሁሉም ዘንድ ይታወቅ ስለነበር ራስ ኪዳነ ማርያምም ይህንኑ ተረድተው ጸሐፊያቸው አድርገዋቸው ነበር። እርሳቸው በሌሉበትም እንዲያስተዳድሩ ወክለው ሲልኳቸው የተናገር ከው ቀለም /የተናገርከው የሚደመጥ/፣ የረገጥከው ለምለም ይሁንልህ፣ እሾህ አይውጋህ፣ እጥር አያግድህ እያሉ ይመርቋቸው ነበር። ንቡ ረ እድም የተላኩበትን ሥራ አጠናቀውና አስፈጽመው ይመጡ እንደ ነበር ይነገርላቸዋል። አቡነ ማቴዎስ በ፲፱፻፲፱ ዓ.ም ከሞቱ በኋላ በኢ ትዮጵያ ጳጳስ አልነበረም። ቢኖርም ኤርትራ በጊዜው በኢጣሊያ ሥር ስለነበረች መንፈሳዊ ግንኙነትም ከመሐል ሀገር ጋር እንዳይኖር ይከለ- ከል ነበር። በዚህ የተነሣ በ፲፱፻፳፫ ዓ.ም ከብዙ ሰዎች ጋር በመሆን ምድረ ግብፅ ተጉዘው ከሊቀ ጳጳሳት አባ ዮሐንስ እጅ መዓርገ ቅስ ናንና ድሜጥሮስ የሚለውን ስያሜ ተቀብለው ተመለሱ። /በቤተ ክርስ ቲያን ሥርዓት ርእሰ አድባራት የሚል መጠሪያ ላላቸው አብያተ ክርስ ቲያናት አለቆች የሚሰጥ ሹመት ነው።/

በወቅቱ የግብፅ (የምስር) እና የኢትዮጵያን የጥንት ወዳጅነትን አስመልክተው ወደፊትም በፍቅርና በአንድነት እንዲቀጥሉ "ዮም አሐደ መርዔተ ኮኑ መላእክት ወሰብእ ከመ ይሰብሕዎ ለክርስቶስ በቃለ አሚን" በልደት መላእክትና እረኞች አንድ ሆነው ለእግዚአብሔር ምስጋና እንዳቀረቡ እኛም መንፈሳዊ አንድነት እና አፍሪካዊ ወንድማማ ችነታችን ማደ ለማደ ቢሆንም በዚህ ዕለት ከፓትርያርኩ እና ከሊቃነ ጳጳሳቱ እንዲሁም ከግብፅ ሕዝብ ጋር አንድ እንድንሆን ያደረገ እግዚ አብሔር ይመስገን በማለት የተናገሩት ንግግር በዚያ የተገኙትን ሁሉ ያስደመመ ነበር።





ንቡረ እድ ድሜጥሮስ ክህነት ከተቀበሉ በኋላ ግብፃውያን ጳጳሳትና መኳንንት በተሰበሰቡበት ስለ ኢትዮጵያና ግብፅ ግንኙነት ተናግረው ሰማዕያኑን እንዳስደሰቷቸው ይነገራል። ወደ ሠራዩ ከተመለሱ በኋላ የአውራጃው ሊቀ ካህናት ተብለው ለ፲፩ ዓመታት ቤተ ክርስቲያንን አገ ልግለዋል። በ፲፱፻፴፪ ዓ.ም የኤርትራው ጳጳስ አቡነ ማርቆስ መልአከ ምሕረት ብለው ሾመዋቸዋል። በኋላም መልአከ ሰላም ተብለዋል።

በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም የኢትዮጵያ ነፃነት ከተመለሰ በኋላ ኤርትራም ነፃነ ቷን አግኝታ ከእናት ሀገሯ እንድትቀላቀል ጽኑ ፍላጎት ስለነበረ ሀገር ፍቅር የሚባል ማኅበር በ፲፱፻፴፮ ዓ.ም ተመሠረተ። ንቡረ እድ ድሜጥሮስም ከመሥራቾች አንዱ በመሆን ሕዝቡን ለነፃነት ያነሳሱ፣ ስለ ሐቀኛ የኢትዮጵያዊነት ታሪክ ያስተምሩ የነበሩ ሀገር ወዳድ ናቸው። የደቂ ወረዳ ወኪል ሆነው ቅስቀሳ በሚያካሂዱበት ጊዜ በእንግሊዞች እጅ ወድቀው አንድ ዓመት ታስረዋል። በነበራቸው የሀገር ፍቅር ስሜት የተነሣ በቆራጥነት በመቆማቸው በማይደግፉ ኃይሎች ሁለት ጊዜ በምብ ተወርውሮባቸው ከአንደኛው ሲያመልጡ በአንዱ ቆስለዋል። በዚሁ የተነሣ ሆስፒታል ተኝተው በነበረበት ጊዜ ግርማዊ ንጉሠ ነገ ሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሊጠይቋቸው ሄደው "የፈሰሰው ደምም የኢት ዮጵያን አንድነት ያጠነክራል" በማለት አጽናንተዋቸዋል።

ጣልያናውያን የኤርትራን ሕዝብ ከኢትዮጵያዊ ባህሉና ሃይማኖቱ በመለያየትና የራሳቸውን ፍላጎት በመጫን እንቅስቃሴያቸውን አጠናክ ረው እንደ ነበር ይታወቃል። ሚስዮናውያኑ በዚህ ሁኔታ ሲንቀሳቀሱ በገበያ የሚታየው መጽሐፍ በአብዛኛው የካቶሊክና የፕሮቴስታንት ብቻ ነበር። ንቡረ እድም ይህንን በመረዳት በእኛ ስንፍና ሚሲዮናውያኑ ወጣቶቻችንን ከጕያችን እየነጠቁ ይወስዱብናል። ሃይማኖታችንም ይበ ረዛል በማለት ተነሣሥተው በ፲፱፻፵፫ ዓ.ም ማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት የተባለ ማኅበር አቋቋሙ። ይህ ማኅበር ወንጌልን በማስፋ ፋትም ሆነ ሕዝበ ክርስቲያኑን በትምህርት በማነፅ ከፍ ያለ አገልግሎት ፈጽሟል። ይህ ማኅበር በወቅቱ የባህል ወረራውንና የሃይማኖት ቅስ ጣውን የሚከላከልበትና ምእመናንን የሚያስተምርበት «ዜና ሐዋር ያት» የተባለ በየወሩ እየታተመ የሚወጣ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ



www.ethiopianorthodox.org

ሃይማኖትን እምነትና ሥርዓት ጠብቆ የሚወጣ ጋዜጣ ነበር። ማኅበሩ «ኮከበ ጽባሕ» በሚል ማተሚያ ቤት አቋቁሞ አርባ ስድስት መጻሕፍተ ብሉያትን በግእዝና በአማርኛ፣ ሃያ ስድስት መጻሕፍተ ሐዲሳትን በግእዝና በአማርኛ፣ መጽሐፈ ሰዓታትን ዳዊትና ሌሎችንም በርካታ መጻሕፍት እያሳተመ ለቤተ ክርስቲያናችን በማቅረብ ለምእመናን እንዲሠራጭ አድርገዋል። የመጻሕፍት ኅትመት ነገር ሲነሣ ንቡረ እድ ድሜጥሮስ ያሳተሙት የብሉያትና የሐዲሳት መጻሕፍት ከአማርኛ ትርጓሜ ጋር መታተሙ ቀዳሚ ቦታ የሚሰጠው ይሆናል። ብሉዩ በሦስት ቅጽ ሐዲሱ በአንድ ቅጽ ተጠናቆ ቀርቧል። "እንዲህ የመሰለው ሥራ ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ አልነበረም" ሲሉ ዶ/ር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ የቤተ ክርስቲያን የአማርኛ መዝገበ ቃላት በተባለው መጽሐፋቸው ጠቅሰውት ይገኛል።

ንቡረ እድ በማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት ቅዱሳት መጻሕፍትን በማሳተም ብቻ አልተገቱም። በርካታ ትምህርት ቤቶችን በማሳነፅ ለዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት የበኩላቸውን ድርሻ የተወጡ ታላቅ አባት ነበሩ። በአሥመራ ከተማ ደብረ ቤቴል አዳሪ ት/ቤት፣ ማኅደረ ብርሃን፣ ቀራንዮ ት/ቤት፣ ማኅደረ ማርያም፣ መካነ ሕይወት ትምህርት ቤት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚሁ ጎን ለጎን መንፈሳዊ ትምህርቶችን በደብረ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ጾዋትወ ዜማ፣ መዝገበ ቅዳሴ፣ ቅኔ፣ በደብረ ማዕዘን መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቅዳሴና ትርጓሜ መጻሕፍት እንዲሰጥ አድርገዋል። በቀድሞዋ የኤርትራ ክፍለ ሀገር የተለያዩ አውራጃዎችና በሌሎችም ቦታዎች ቤተ ክርስቲያን ሊያሠሩ ዘመናዊ ት/ቤቶችም ለማቋቋም የበቁ የዘመኑ የሥልጣኔ መሠረት የገባቸው የቤተ ክርስቲያን ዓምድ ነበሩ ለማለት ያስችላል።

በአሥመራ ከተማ፣ በምጽዋ፣ በምዕራብ ኤርትራ ከዘጠኝ በላይ የሆኑ አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነፅ የየአካባቢውን ምእመን ችግር ለማቃለል የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል። መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም፣ መርሶ እስሚር ቅዱስ ሚካኤል፣ ገሊላ ማርያምና ደብረ ኢየሱስ ዋና ዋናዎቹ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው።





ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት ረገድ ያበረከቱት አስተዋፅዖ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ኢ-አማንያንን በማስተማር አጥምቀው ወደ ክርስትና መልሰዋል። እነሱንም ለመንከባከብና በእምነታቸው ለማጽናት ቤተ ክርስቲያንና ትምህርት ቤት ከፍተውላቸዋል።

ቤተ ክርስቲያን ከመንፈሳዊ ተግባሯ በተጨማሪ በልማት ሥራዎች መሳተፍና ራሷን መቻል እንዳለባት ከዘመናቸው ቀድመው የተረዱ የቤተ ክርስቲያን ፈርጥ ነበሩ። ለዚህ ደግሞ ማስረጃ መጥቀስ የሚያስቸግር አይሆንም። በ1961 ዓ.ም የቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽ/ቤት በሚኒስቴር ደረጃ ሥራ እስኪያጅ ተብለው በተሾሙ ጊዜ የሠሯቸው ተግባራት ምስክሮች ይሆናሉ። በመንበረ ፓትርያርክ ግቢ ለ14ቱ አህጉረ ስብከት ጳጳሳት ማረፊያ ቤቶች፣ በአዲስ አበባ ከተማ በተሰምዶ ኩልፌ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ዳቦ መጋገሪያና የሻማ ፋብሪካ፣ አቋቁመዋል። እነስተኛ ደመወዝ ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ለመርዳት በማሰብ የማረሻ መኪና ከውጪ በማስመጣት እርሻ ማሳረስ ጀምረው እንደነበር የሚያውቋቸው ሰዎች ያስታውሳሉ። በጉደርና በባኮ የወይን ተክልን በማልማት ቤተ ክርስቲያን እንድት ጠቀም ሥራውን ወጥነው እንደነበር የሚያውቋቸው ሰዎች ያስታውሳሉ። ከዚሁም ጋር በተያያዘ በመናገሻ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚውል የንጹሕ ስንዴ እርሻ ልማት ዕቅድ ዘርግተዋል። የቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ትምህርት ቤትን አሳድሰዋል። ለተማሪዎቹና ለአካባቢው ሕዝብ የሚያገለግል የዳቦ መጋገሪያ አቋቁመዋል።

እስከ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ድረስ መልአከ ሰላም ተብለው ሲያገለግሉ ቆይተው በዚሁ ዓመት የርእሰ አድባራት ወገዳማት የአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ንቡረ እድ ተብለው በግርማዊ ጃንሆይ መልካም ፈቃድ ይሾማሉ። በዚህ ጊዜ በመጀመሪያ የወሰዱት እርምጃ የሕዝቡን ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት የአክሱም ነዋሪ ለብዙ ጊዜያት አብሮት የኖረው የውኃ ችግር እንዲቃለል ማይሹም በተባለው የውኃ ማጠራቀሚያ ላይ መጠኑን በማሳደግ አሠርተው ሕዝቡ ውኃ ሳይቸገር እንዲያገኝ ማድረጋቸው በአካባቢው ሕዝብ ሲታወስ የሚኖር ተግባር ነው።

ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ አክሱም ጽዮንን ያስተዳድሩ በነበረ ጊዜ ለአካባቢው ሕዝብ በርካታ ጠቃሚ ተግባራትን አከናውነዋል። ቀደም ሲል



www.ethiopianorthodox.org

በአክሱም ጽዮን የኅዳር ጽዮንና የሆሳዕና በዓል ሲከበር ድል ያለ ድግስ ይደገሳል:: የአካባቢው ሕዝብም ይህንን ለማድረግ ሲል ከአቅሙ በላይ የሆነ ከፍተኛ ወጪ ያወጣል:: የድግሱንም መጠን "ኀምሳ ጋን ጠላ እንበለ አተላ፤ ኀምሳ ጋን ጠጅ እንበለ አንቡላ፤ ኀምሳ ፍሪዳ ቀርኑ ሰማይ ጠቀስ ጅራቱ ምድር አበስ (መሬት የሚጠረግ)":: በማለት ይገልጹት ነበር:: ንቡረ እድ ድሜጥሮስም እንዲህ ያለውን ሸክም ከድሃው ሕዝብ ላይ በማንሣት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እንዲቆም አድርገዋል::

ንቡረ ዕድ ጌታ መከየ እግዚእ በተባለ ቦታ የሕዝቡን የውኃ ችግር እጦት ተመልክተው በድማሚት ሰፊ ቦታ ማስቆፈር ጀምረው ገንዘብ አሰባስበው ለሥራ ሲንቀሳቀሱ በወቅቱ የትግራይ ገዢ ከነበሩት ራስ መንገሻ ሥዩም ጋር በአንዳንድ የአፈጻጸም ሂደቶች ሳይስማሙ በመቅ ረታቸው ተቀይረው ወደ አዲስ አበባ ሊመጡ ችለዋል::

የአክሱም ሊቃውንት ሲታመሙ በግል ገንዘባቸው አሥመራ ድረስ በመውሰድ ያሳክሟሉ፤ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ ሊቃውንት ሊደ ረግላቸው የሚገባውንና ማግኘት የሚገባቸውን እንዲያገኙ፣ ጉባኤያቸ ውም እንዲስፋ፣ ተተኪ ሊቃውንት እንዲያፈሩ የበኩላቸውን ጥረት አድርገዋል::

በሠሩበት ቦታ ሁሉ ባለጉዳይ በክርክርና በመመላለስ ጊዜውንና ጉልበቱን እንዳያባክን ጠዋት ወደ ቢሯቸው ከመግባታቸው በፊት ባለ ጉዳዮች መካከል ገብተው አቤቱታዎችንና ቅሬታዎችን በመስማት ለባለ ጉዳዮች የሚፈልጉት እንዲፈጸምላቸው ፍትሐዊ ውሳኔ ይሰጣሉ:: በዚህም ማንኛውም ባለጉዳይ የመጣበት ተፈጽሞለትና ሠምሮለት ይመ ለስ እንደነበር ዛሬም ድረስ ይነገራል::

በ፲፱፻፶፩ ዓ.ም በሚኒስትር መዓርግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው በተሾሙበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ከቀድሞ ጀምሮ ትጠብቀው የነበረውን የራስዋን ፓትርያርክ መርጣ ለመሾም የቻለችበት ጊዜ ነበር:: ይህም ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጋር በመተባበር ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ የሰጡት ጥበብ የተሞላበት የአመራር ችሎታ ውጤት ነው ለማለት ይቻላል::





ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ኢትዮጵያ ሀገራቸውን ተዋሕዶ ሃይማኖታ ቸውን እጅግ አድርገው የሚወዱ ታላቅ አባት መሆናቸውን ከተ ግባራቸው መረዳት ይቻላል:: ስለዚሁ ጉዳይ በአንድ ወቅት ሲናገሩ "ሁላችሁም እንደምታስታውሱት 'ኢትዮጵያ ወይም ሞት' ብለን ከተነ ሣንበት ከ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁኑ ሰዓት ስለ ኢትዮጵያ አገሬና ስለ ተዋሕዶ ሃይማኖቴ፤ የኢትዮጵያ አገሬ ጉሮሮ የሆኑት የምጽዋና አሰብ ወደቦች ከዐረቦች እጅ ላይ እንዳይወድቁ እጨነቅ ነበር:: ይህ ከነበረኝ የሀገር ፍቅር ተነሣሥቼ ከምጽዋ እስከ ተሰነይ፤ ከሐ ማሴን እስከ ዓዲግራት እየተንቀሳቀስኩ ሕዝቡን በመቀስቀስ አራራጥ በነበረ ጊዜ ጠላቶች በየጊዜው የኔን ሕይወት ከማጥፋት የተቆጠቡበት አንዳችም ቀንና ሰዓት የለም:: . . . ስለዚህ ለእውነተኛው ዓላማ ለኢ ትዮጵያ የምናፈሰው ደም የምንከፍለው የሕይወት መሥዋዕትነት የተ ቀደሰ ነው» ይሉ ነበር::

ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንደተ ቀላቀለች መጀመሪያ የኤርትራ ምክር ቤት አባል በመቀጠል የምክር ቤቱ ምክትል ፕሬዝዳንት ሆነው አገልግለዋል::

ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ የንግግር ተሰጥኦ የታደሉ ቀልጣፋና አንደ በተ ርቱዕ ሲሆኑ ተናግረው የማሳመንና ሰዎችን ወደ ራሳቸው አቀርቦ የማምጣት ልዩ ችሎታ ነበራቸው::

ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ከወ/ሮ ምዕራፍ ኣርዓዶም ጋር ጋብቻ ፈጽ መው ሰባት ወንዶችንና ሁለት ሴት ልጆችን አፍርተዋል:: በ1966 ዓ.ም በጡረታ ተገልለው ማኅበረ ሐዋርያትን በመምራት ላይ እንዳሉ በተ ወለዱ በዘጠና አምስት ዓመታቸው መስከረም ፳ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም አዲስ አበባ ዐርፈው ሥርዓተ ቀብራቸው መስከረም ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ራሳቸው ባሳነፁት በአሥመራው ደብረ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል::

ወ/ሮ ግደይ ድሜጥሮስ የንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ሁለተኛ ልጅ ሲሆኑ ስለአባታቸው ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡን ጠይቀናቸው:- የሚከተለውን እጫውተውናል::

አባታችን ብዙውን ጊዜውን የሚያሳልፈው በሥራ ነው:: ሃገሩንም በጣም ይወዳል:: ለሃይማኖቱ ያለው ፍቅርና ጽናት ዛሬም ድረስ



www.ethiopianorthodox.org

ሳስታውሰው ያስደንቀኛል፡፡ ሁላችንም ልክ እንደሱ እንድንሆን ይፈልጋል፡፡ የዘወትር ንግግሩ በሃይማኖታችሁ ጠንካራ ሁኑ ሀገራችሁን ውደዱ የሚል ነበር፡፡ እኛም የሱን ያህል ባይሆንም አቅማችን የፈቀደውን ያህል የሚለንን ለመፈጸም እንሞክራለን፡፡ እርሱ በፍጹም የዓለም ነገር አያምረውም ስለ ኑሮውም ብዙም የሚጨነቅ አልነበረም፡፡ ዘወትር የሚያስበው ስለ ቤተክርስቲያን ዕድገትና ስለ ሀገር ደኅንነት ነው፡፡

አንድ ጊዜ አስታውሳለሁ አሥመራ እያለን እርሱ የምክር ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት በነበረ ጊዜ እናታችን 'ቤታችን ሳሎናችን ምን እንደሚመስል እዩት፣ የእርስዎ ጓደኞች ሚኒስትሮች ከእርስዎ የተሻለ ኑሮ ነው የሚኖሩት፣ ለልጆችዎስ እንዴት አንድ ነገር አይሠሩም' ትለዋለች፡፡ እርሱም 'እኔ ግን ቅድሚያ ለቤተ ክርስቲያን (ለሃይማኖቴ) እና ለሀገሬ እንጂ ለራሴ ኑሮና ብልጽግና ብቻ የምሮጥ አይደለሁም፡፡ ልጆቼንም ቢሆን ትምህርታቸውን አስተምሬ ራሳቸውን እንዲችሉ አደርጋለሁ እንጂ ሌላ የምሰጣቸው ነገር የለም' ብሎ መልሶላታል፡፡ ይህንንም ብዙ ሰው ያውቃል፡፡ አባታችን ምንም ነገር ለራሴ ለልጆቼ የሚለው አይደለም፡፡ አቅሙ በፈቀደ መጠን ለሀገሬና ለቤተ ክርስቲያኔ ነው የሚለው፡፡ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ለዚሁ ሲወጣ ሲወርድ ነው የኖረው፡፡

በአስተዳደግ በኩልም ቢሆን በጥሩ ሁኔታ ነው ያሳደገን፡፡ ሁላችንንም አስተምሮ ለጥሩ ደረጃ አብቅቶናል፡፡ ሁልጊዜ ማታ ከሥራ ስንመለስ ሰብስቦ ይመክረናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሁላችንም በተራ እናነባለን እንወያያለን፡፡ የሃይማኖትና የሀገር ፍቅር በውስጣችን እንዲኖር አድርጎ ነው ያለፈው፡፡ በዚህም በጣም እናከብረዋለን፡፡

አሥመራ በነበርንበት ጊዜ ትምህርት ቤት ለመሄድ ፈልጌ ሹፌሩ በመኪና እንዲያደርሰኝ ነገርልኝ አልኩት፡፡ እርሱም 'ግደይ ይህቺ መኪና ለእኔ ሥራ እንጂ አንቺን ት/ቤት ለማድረስ አይደለም የተሰጠችኝ፡፡ የመንግሥት መኪና ስለሆነ አይቻልም በእግርሽ እየሄድሽ ተማሪ' ብሎ ከለከለኝ፡፡ እኔም በእግሬ ተመላልሼ ተምሬ ትምህርቴን ጨረስኩ፡፡ ይህንን የጠቀስኩት በትንሹ ምን ያህል አነስተኛ መስላ ለምትታይ ነገር ሁሉ ያደረግ የነበረው ጥንቃቄ ነው፡፡





ከማስታውሰው ጠባዩ አንዱ ምግብ ለብቻው መብላት አይወድም፡፡ የሚቀምሳትም ትንሽ ብትሆን ጠረጴዛው በሰው እንዲሞላ ይፈልጋል፡፡ አንድ ጊዜ ምሳ ተሰናድቶ እንዲበላ ጠራሁት፡፡ ማዕድ የቀረብነው እርሱ እንዲሁም እኔና ባለቤቴ ነበርን፡፡ ማዕዱ በየዓይነቱ ሞልቷል፡፡ እርሱ ግን ጠራኝና 'ምነው ጠረጴዛው ባዶ ሆነ ድኻ ሆነ' አለኝ፡፡ እኔም ሁሉም በየዓይነቱ ቀርቦ እንዴት እንዲህ አልክ አባባ ስለው 'ልጄ ሰው የሌለበት ጠረጴዛ ድኻ ነው' አለኝ፡፡ እኔም በጎረቤት ያሉትን ጓደኞቼን ሁሉ ጠርቼ ማዕዱን አብረን ተካፈልን፡፡ ለሰዎች የተለየ ፍቅርና አክብሮት አለው፡፡ ብቻውን መብላትና ብቻውን ማግኘትን አይደሰትበትም፡፡

እናታችን አንድም ቀን የእርሱን ደመወዝ አታውቅም፡፡ በእርግጥ በቤታችን ውስጥ ሁሉም ነገር አለ፡፡ የምትቸገረው ነገር የለም፡፡ እርሱ ደመወዙን በውጭ ነው የሚጨርሰው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ያሠራል፣ ድኻ ይረዳል፣ የልማት ተቋማት ያቋቁማል፡፡ ለቤተ ክርስቲያንም ለሀገርም ጠቃሚ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

በየቀኑ ለድኾች ሳይመጸውት የሚውልበት ቀን አልነበረም፡፡ የሰበሰውን ጋቢ /ኩታ/ አውልቆ የሰጠበት አጋጣሚ አለ፡፡ አባታችን በጠባዩም የተለየ ሰው ነበር፡፡ መጠጥ አይጠጣም፡፡ ሁልጊዜ በለውጥ ያምናል፡፡ ካላመነበት በስተቀር በይሉኝታ የሚያልፈው አንዳችም ነገር የለውም፡፡ ቤተ ክርስቲያን አሳንፃ በምረቃው ሥነ ሥርዓት ግቢው በምእመናን ተሞልቶ ዝማሬው በዐውደ ምሕረት ሲቀርብ መመልከት እጅግ ያስደስተዋል፡፡ በኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት መጽሐፍ ታትሞ ሲወጣና ሥርጭት ላይ ሲውል የሚታይበት ስሜት ዛሬም ድረስ አይረሳኝም፡፡ ይህንን የምለው አባቴ ስለሆነ ሳይሆን የሚያውቁት ሁሉ የሚመሰክሩት እውነት ስለሆነ ነው፡፡

ሌላው ስለ አባታችን የማስታውሰው ከ፲፱፻፶፭ ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞቱ ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም እየሄደ ይሳለም ነበር፡፡ መጽሐፍ ማንበብ በጣም ይወዳል፡፡ በተለይ ትንቢተ ነቢያትንና የቅዱስ ጳውሎስን መልእክታት አዘውትሮ ያነባል፡፡ ሲያነብ እያለቀሰ በኀዘን ስሜት ነበር ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

አባታችን ወንድሜ ጌዴዎን (የመጀመሪያ ልጁ ነው) ከሞተ በኋላ ብዙም ደስተኛ አልነበረም። አንድ ቀን መኝታ ቤቱ ሻይ ይዤለት ስሄድ 'ሻዩን መልሺው አልጠጣም ጌዴዎን ልጄ ሞቷል' አለኝ። በዚህ ጊዜ የጌታችን ሥነ ሥዕል ሥር ቆሞ እንደ ሰው ይነጋገር ነበር። በጣም ይወደዋል። እንደ ጓደኛ ነበር የሚተያዩት። እርሱ ከሞተ በኋላ በቃ መንፈሱ ሁሉ ተሰበረ። ብዙም አልቆየ እርሱም ልጁን ተከትሎ ዐረፈ።

በሕይወተ ሥጋ እያለ «ልጆቼ እኔንም ሆነ እናታችሁን እግዚአብሔር በሞት በጠራን ጊዜ ነፍስ ከሥጋ ስትለይና በርደተ መቃብር ወቅት ልጆች ስለ መሆናችሁ እንዳታለቅሱ አልከለክልም። በተረፈ ግን ቀብር ብላችሁ ወደ ወዳጅ ቤተ ዘመድ ፍጹም እንዳትልኩ። ከመጠን በላይም እንዳታለቅሱ እማፀናችኋለሁ» የሚል ትእዛዝ ሰጥቶናል። እኛም ለእርሱ ማድረግ የሚገባን ማልቀስና ማዘን ባለመሆኑ ወደፊት ውጭ ያሉት ወንድሞቼ ሲሰባሰቡ ለመታሰቢያነት በእርሱ ስም ሙዚየም ለማሠራት ዕቅድ አለን።» በማለት ወ/ሮ ግደይ ድሜጥሮስ ይገልጻሉ።

ስለ ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሀገር ወዳድና የሃይማኖት አባት ስለ ክቡር ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ገብረ ማርያም ማንነት የሀገራችን ታዋቂ ሰዎች እንደሚከተለው ያስቀምጣሉ።

"ንቡረ እድ በሀገራቸው አንድነትና ሃይማኖት ላይ ቀጥተኛ አቋም የነበራቸው፤ በቀላሉ ሊተኩ የማይችሉ ኢትዮጵያዊ ናቸው።»

*አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ*
*የታሪክ ጸሐፊና ተመራማሪ*
*መስከረም ፳፪ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም*

*"ንቡረ እድ ድሜጥሮስ የአገር አንድነትና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ትጉህ ሐዋርያ ነበሩ።"*

*ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ*
*የትግራይ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩ*

*ምንጭ፡- ሥርግው ሐብለ ሥላሴ (ዶ/ር)*
- *አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት*
- *ትንሣኤ መጽሔት ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ቁጥር ፩፻፴፫*
- *ዜና ሐዋርያት የካቲት ፲፱፻፶፱ ቁ.፳፫ ትግርኛ እትም*
- *ፎኖት ብርሃን ኅዳር ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ቁ.፫፻፵፩ ትግርኛ እትም*
- *አዲስ ዘመን መስከረም ፳፬ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም*






# መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ

/፲፰፻፺፭ – ፲፱፻፷፪/

*በአሥራት ከበደ*

ቤተ ክርስቲያን ሆይ ኦርቶዶክሳዊት፣
ጠበቃሽ ተረታ ሐምሌ ሃያ አራት፣
መጋቤ ምሥጢራት የሊቆቹ ዋልታ፣
መልአከ ብርሃን መሃርገ ጌታ፣
ትምህርትን ጋባገቡ በሰፊ ገበታ፤
የመጻሕፍት ምንጭ ማፍለቅ እማይገታ፣
እንደበተ ሰንቁ አፈ ወርቅ አለኝታ፣
የሕግ መሐንዲስ ለሃይማኖት ካርታ፣
ለተጋፊው ሁሉ መናፍቅ ወስላታ፣
በሚያስደንቅ ትግል እንዲያ ሲበረታ፤
በሐምሌ ሃያ አራት ደከመው ተረታ።

*አለቃ ተገኝ ታምሩ*
*ጉጃም ዘደብረ ኤልያስ*



ትልቅ እምነት ከሊቅነት ጋር አጣምረው የኖሩት መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ

ከአርባ ቀን መታሰቢያ ከቀረበ ግጥም የተወሰደ ነው።

በ፲፱፻፴፮ ዓ.ም ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብት ለተደረገው ክርክር የጉጃምን ሊቃውንት ከወከሉት አንዱ ነበሩ። በዚህም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ሊቃነ ጳጳሳት እንድትሾም በተደረገው ትግል የመከራከሪያ አሳብ ከማመንጨት ጀምሮ ቀዳሚውን ቦታ ይዘው የሚገኙ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ናቸው። «በመንፈሳዊ ሕይወት ገዥና ተጣዘ ወይም ለአንዱ የማስተ



www.ethiopianorthodox.org

ለሌላው የሚነፈግ ክብር የሌለ በመሆኑ የኢትዮጵያ ሰዎች ከዐዋቂዎ ቻቸው ሊቃነ ጳጳሳት አይሹሙ ተብሎ በሥርዋጽ /በጣልቃ ገብነት/ በፍትሐ ነገሥት የተጻፈው ተሠርዞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብ ቷን ማግኘት አለባት» የሚል ነበር ያቀረቡት አሳብ:: ይኸንን አሳ ባቸውን በወቅቱ የደገፋቸው አልነበረም:: ተቃውሞ ብቻ ነበር የገጠ ማቸው:: ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ሊቃውንቱ መከሩ:: ዐዋቂዎች በማስተዋል ተነጋገሩበት እናም ይኸን ታላቅ አሳብ ደገፉት:: ይኸው ዛሬ የእኒህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ አሳብ ፍሬ አፍርቶ የኢት ዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ጳጳሳት፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ፓትር ያርኮችን ለመሾም በቅታለች::

እኚህ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ይባላሉ:: የተወለዱት ነሐሴ ፩ ቀን ፲፰፻፹፰ ዓ.ም በጐጃም ዲማ ጊ ዮርጊስ ነው:: ወላጆቻቸው አቶ ጀንበሬ አዲሱ እና ወ/ሮ ወለተ ማርያም ኃይሉ ይባላሉ:: እናታቸው ገና በአራስ ቤት እንዳሉ አንድ የእግዚአብሔር ሰው ወደ ቤታቸው መጣ:: እናም «ይህ ሕፃን እግዚ አብሔርን እንዲያገለግለው የመረጠው ነውና በጥንቃቄ አሳድጊው፤ በሰዓቱም ወደ ትምህርት ቤት አስገቢው» አላቸውና ሄደ:: እናታች ውም እንደተባሉት አደረጉ:: በዚህም የተነሣ የሕፃኑን ስም «ያለው» በማለት ሰየሙት:: «እግዚአብሔር ያለው ይሁን» ለማለት ነው:: አባታቸው ግን አድማሱ ይሏቸው ነበር:: ሆኖም ከትውልድ አገራቸው በአሥራ ዘጠኝ ዓመታቸው እስከ ወጡበት ፲፱፻፩ ዓ.ም ድረስ እና ታቸው ባወጡላቸው «ያለው» በሚባለው ስማቸው ነበር የተጠሩት:: ከዚያ በኋላ ግን አድማሱ የሚባለው ስማቸው ጎልቶ በሕይወት በነበ ሩበት ዘመን ሁሉ ሲጠሩበት ቆይተ ዋል::

ትምህርታቸውን የጀመሩት በተወለዱበት አገር ዲማ ጊዮርጊስ ነው:: አባ ወንድሙ የተባሉ ባሕታዊ ከፊደል ጀምሮ እስከ መዝሙረ ዳዊት አስተማሯቸው:: ቀጥሎ በፊት መሪጌታ በኋላ ሊቀ ጠበብት ክንፉ ከተባሉት አጐታቸው ዘንድ፤ ጾመ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ድጓ፣ ዝማሬ መዋሥዕትና ቅኔ ተማሩ:: ከዚያም በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ በዲቁና፣





ማኅሌትና ስብሐተ ነግህ በመቆም እያገለገሉ በዚያው ካሉ ልዩ ልዩ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን /መምህራን/ ቅኔና ትርጓሜ መጻሕፍትን ሲቀጽሉ ቆዩ::

ዕድሜያቸው ከፍ እያለ በአካል እየጠነከሩ በአእምሮ እየጎለመሱ መጡ:: የአርባዕቱ ወንጌላትን ንባብ ጽፈው በየዓመቱ ግንቦት ፲፪ ቀን የሚከበረውን የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን በዓል ለማክበር በ፲፱፻፬ ዓ.ም ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም መጡ:: ለመልአከ ብርሃን አድማሱ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአገራቸው የወጡበት ነው:: በዚያ የጻፉትን መጽሐ ፍ ሸጠው ለስንቃቸው የሚሆናቸውን ገንዘብ ያዙና ወደ አዲስ አበባ አቀኑ::

አዲስ አበባ ገብተው ለጥቂት ቀናት የቆዩት በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ነው:: ከዚያም አካባቢ ከሚኖሩ ወልደ ሥላሴ ከሚባሉ የብ ሉይ መምህር ዘንድ ትርጓሜ ዳዊት፣ መጻሕፍተ ሰሎሞንና ትንቢተ ኢሳይያስን ሲቀጽሉ ቆይተው በግንቦት ወር ፲፱፻፰ ዓ.ም ተመልሰው ወደ ትውልድ አገራቸው ሄዱ:: ወደ አገራቸው እንደተመለሱ ትም ህርታቸውን በመቀጠል እዚያው ዲማ ከመምህር ወልደ ጊዮርጊስና ከመምህር እንግዳሸት ዘንድ ቅኔ እና ልዩ ልዩ መጻሕፍትን ቀጸሉ::

ትምህርታቸው በአካባቢያቸው ባሉት ሊቃውንት ብቻ እንዲወሰን አልፈለጉም:: በሌሎቹም የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገራት ካሉት ታላላቅ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ በመሔድ ትምህርታቸውን በመ ቅሰም ዕውቀታቸውን አሰፉ:: በፊት መሪጌታ በኋላ አለቃ ክፍሌ ደር ሰህ ከሚባሉ ዓይነ ሥውር ሊቅ ጋር በመሆን በ፲፱፻፲ ዓ.ም ወደ ደሴ ሄዱ:: ደሴ ከመልአከ ገነት አፈ ወርቅ ፍትሐ ነገሥትን እንዲሁም ከመምህር አካለ ወልድ በሩ ሜዳ /የቀለም ቀንድ/ ዘንድ አዲሳትንና መጻሕፍተ ሊቃውንትን ተማሩ::

በዚያን ጊዜ መሳፍንትና መኳንንቱ የነገሥታቱንና የአባቶቻቸውን ሥርዓት በመከተል ሊቃውንቱን እየፈለጉ በፀቢይ ጾም የዳዊትን፣ በሰ ሙነ ሕማማት የመጻሕፍተ ኪዳንን፣ በጾም ፍልሰታ የውዳሴ ማርያ ምንና የቅዳሴ ማርያምን ትርጓሜዎች ይሰሙ ነበር:: መልአከ ብርሃን



www.ethiopianorthodox.org

አድማሱም ውዳሴ ማርያምንና ቅዳሴ ማርያምን ትርጓሜ በጾመ ፍልሰታ ለራስ ሀብተ ማርያም ለማስማት ተመርጠው ሄዱ:: ራስ ሀብተ ማርያምም ትሰማሥታቸውን፣ ትኅትናውንና ችሎታቸውን በማየት ሙያና ባለሙያ እንዲህ ሲገኝ እጅግ መልካም ነው በማለት ያደንቋቸው ነበር:: ራስ ሀብተ ማርያም በበገና መጸለይ ይወዱ ነበር:: የበገና መዝሙር እንዲያዘጋጁላቸውም መልአከ ብርሃን አድማሱን ጠየቋቸው:: እርሳቸውም የመጀመሪያቸው የሆነውን «የበገና መዝሙር» የተባለ መጽሐፍ ከቅዱሳት መጻሕፍት አውጣጥተው ማዘጋጀት ጀመሩ:: በኋላ ይኸንኑ መጽሐፍ በማስተካከልና በመረጃ ማንጻጸሪያነት የተጠቀሙባቸውን መጻሕፍት ጠቅሰው አስፋፍተው በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም አሳትመውታል::

መልአከ ብርሃን አድማሱ በ፲፱፻፱ ዓ.ም ደሴ የመጡበትን ትምህርት ሲያጠናቅቁ ወደ ጎጃም ተመልሰው ከብሉይ ሊቅ አለቃ ገብረ ኤልያስና ከቅኔው ሊቅ ከመልአከ ሰላም ገብረ ማርያም ደንበጫ ብሉያትን ሲቀጽሉ ቅኔውን ሲያስፋፉ ስውቀታቸውን ሲያሰፉ እስከ ፲፱፻፲፰ ዓ.ም ድረስ ቆዩ:: ከዚያም ወደ ዲማ መጥተው የቅኔ መምህር በመሆን እስከ ፲፱፻፳፬ ዓ.ም ድረስ ሲያስተምሩ ቆይተዋል:: በዚህ ጊዜ መተዳደሪያቸው ልዩ ልዩ መጻሕፍትን በቁም ጽሕፈት፣ በብራና እየጻፉ በመሸጥ ነበር:: እንደ ልጃቸው አቶ ምኅርካ ክርስቶስ አድማሱ ገለጻ ከልጆቻቸው እናት ከወ/ሮ ዓለሚቱ አሸቴ ጋር ትዳር የመሠረቱት በ፲፱፻፲፰ ዓ.ም አካባቢ ነው::

በ፲፱፻፳፭ ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጡ:: በዚያን ጊዜ የመጽሐፈ ግጻዌን ረቂቅ አዘጋጅተው ቀሌምንጦስና መጽሐፈ ኪዳን የተባሉትን መጻሕፍት በብራና ጽፈው መጥተው ነበርና ሁለቱንም መጻሕፍት ብፁዕ አቡነ አብርሃም ገዝተዋቸው ለመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብር ኤል ሰጥተው በዚያ ይገኛሉ:: የግጻዌውን ረቂቅ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አቅርበው ንጉሡም በሊቃውንት ተመርምሮ እንዲታተም እርሳቸውም በቁም ጽሕፈት ቤት እንዲሠሩ አዘዙ:: ይህ መጽሐፈ ግጻዌ በሊቃውንቱ ተመርምሮ ለኅትመት ከቀረበ በኋላ የኢጣሊያ ወረራ





ሥራውን ሁሉ ስለ አሰናከለው ቆይቶ በ፲፱፻፵፭ ዓ.ም ታትሟል:: ከፋሺስት ጣሊያን ወረራ በኋላ መጽሐፉ እንዲታተም ንጉሡ ለመልአከ ብርሃን አድማሱ የጻፉላቸው ደብዳቤ እንዲህ ይላል::

*ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ*
*ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ*
*ለመልአከ ብርሃን አድማሱ*

*እንደምን ሰንብተሃል እኛ በእግዚአብሔር ቸርነት ደኅና ነን:: የጻፍክልን ደብዳቤ ደርሶናል:: የጻፍከውን መጽሐፍ ካየነው በኋላ እንዲታተም በፍጥነት ይዘኸው እንድትመጣ ይሁን:: /መጋቢት ፲፯ ቀን ፲፱፻፵፭ ዓ.ም አዲስ አበባ::/*

የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ትምህርት ቤት ሲከፈት በሊቀ ሊቃውንት ገብረ አብ በኋላ አቡነ ፊልጶስ አማካይነት ከተመረጡት ሊቃውንት አንዱ በመሆን መጋቤ ምሥጢር አድማሱ ተብለው ተሹመዋል:: ይህ መዓርግ ለእሳቸው የመጀመሪያቸው ሲሆን ሹመቱም ገና አዲስ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠ ነበር:: ይህ ሹመት በእንደዚህ ዓይነት አስተዋይ፣ ተመራማሪ፣ ሥራ ወዳድና ሁልጊዜም ተማሪ በሆኑ ሰው መሟሸቱ ከተሿሚው ይልቅ ሹመቱ ዕድለኛ ነበር ይባላል::

በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም በጉጃም ጠቅላይ ግዛት ብቸና ቅዱስ ጊዮርጊስ ሊቀ ጠበብትነት በንጉሠ ነገሥቱ መልካም ፈቃድ ስለ ተሰጣቸው ሊቀ ጠበብት አድማሱ ተብለው ወደ አገራቸው ተመለሱ:: ከ፲፱፻፳፰ ዓ.ም የፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ጊዜ ጀምሮ እስከ ሚያዝያ ወር ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ጣሊያን ተሸንፎ ከኢትዮጵያ እስከ ወጣበት ጊዜ ድረስ በኃዘንና በጸሎት ተወስነው ቅኔ እያስተማሩ እንዲሁም ዲማ ጊዮርጊስ ለተቋቋመው የጀግኖች ማኅበር አባል ሆነው የአርበኝነቱን ሥራ እየሠሩ ቆይተዋል:: ለዚሁም አገልግሎታቸው ከድል በኋላ ባለ ሦስት ዘንባባ ሜዳይ ከንጉሠ ነገሥቱ እጅ ተሸልመዋል::

በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም በብቸና ቅዱስ ጊዮርጊስ ራስ ወርቅ አሠረው መልአከ ብርሃን ተብለው ተሾሙ:: ይሁን እንጂ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ተፈላጊነታቸው እየበዛ ስለሄደ ለተሾሙበት አገር ለብቸና እንደ ራሲ ሰጥተው በአዲስ አበባ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ሲሠሩ ኖረዋል::



www.ethiopianorthodox.org

መልአከ ብርሃን አድማሱ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከራሷ የቤተ ክርስቲያን አባቶችና ሊቃውንት መነኩሳት መካከል ሊቃነ ጳጳሳት ልትሾም ይገባታል፤ መብቷን ማግኘት አለባት፤ የሚለውን አሳብ አቅርበው መከራከራቸው ይታወቃል።

ከዚያም ወዲህ ለቤተ ክህነት አስተዳደር መንፈሳዊ ጉባኤ ሲቋቋም ለአስተዳደር ከተመረጡት የመማክርት አባላት አንዱ ሆነው አገልግለዋል። ቀጥሎም የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የሚመራው በመማክርት መንፈሳዊ ጉባኤ መሆኑ ቀርቶ በሊቀ ብርሃን አድማሱ የታሪክና ድርሰት ክፍል ሹም፣ የሊቃውንት ጉባኤ ፕሬዝዳንት በመሆን አገልግለዋል። መልአከ ብርሃን አድማሱ በሥራቸው ላይ ብቻ የሚወሰኑ አልነበሩም። በተፈጥሮአቸው መወያየትን፣ መመራመርን፣ መጠየቅን፣ ሲጠየቁም በሚገባ ማስረዳትን የሚወዱ ናቸው። ማናቸውንም ዓይነት መጽሐፍ ያነብባሉ። ብዙ መዝናናትና ዕረፍት አይሹም ትርፍ ጊዜ የሚባል የላቸውም። ከሥራ ሰዓት ውጪ ያላቸው የጸሎት ጊዜ፣ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱበት የሚያስቀድሱበት ወይም የሚያገለግሉበት ጊዜ ነው። ከዚህ ወጪ በሚያገኙት ጊዜ ሁሉ ያነብባሉ፤ ይጽፋሉ። በዚህ ጊዜና ሁኔታ ነው «ኩኩሐ ሃይማኖት» የተባለውን የመልስ መጽሐፍ ያሳተሙት።

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም በንጉሠ ነገሥቱ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኛ ሆነው ተሾሙ። በዚህም የመንግሥት ሓላፊነታቸው ወቅት በበጌምድርና በሰሜን፣ በወሎ፣ በትግሬ ጠቅላይ ግዛቶች ተዟዙረው ብዙ የፍርድ ጉዳዮችን ፈጽመዋል። በፍርድ ምርመራ ተመድበው ለብዙዎች አስቸጋሪ የነበሩ ጉዳዮች መፍትሔ እንዲገኝላቸው ማድረጋቸው በብዙዎች ዘንድ ተመስክሯል። በፍርድ ቤት ሲሠሩ ከነበሩበት ወቅት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎታቸውን አልቀነሱም። ከመንግሥታዊ የፍትሕ ሥራቸውና የቤተ ክርስቲያን አገልግሎታቸው ውጪ ጊዜያቸውን በሚገባ ይጠቀሙበት ነበር።

መልአከ ብርሃን አድማሱ በልዩ ልዩ ድርጅቶች፣ በትምህርት ቤቶች፤ በኢትዮጵያ ሬድዮና በብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያዎች





እየተገኙ መንፈሳዊ ትምህርት ይሰጡ ነበር። እንዲሁም ከልዩ ልዩ አቅጣጫ ለሚቀርቡላቸው፤ ሕግና ፍልስፍና፣ እምነትና ምግባር፣ ታሪክ፣ ባህልና ቋንቋ ጠቀስ ለሆኑ ጥያቄዎችም መልስ መስጠት ዋና ተግባራቸው ነበር። «መድሎተ አሚን» የተባለውን መልስ ሰጪ መጽሐፋቸውንም አዘጋጅተው ያሳተሙት በዚሁ ጊዜ ነው።

ከፍርድ ሚኒስቴር የፍርድ ሥራቸው በ፲፱፻፶፱ ዓ.ም በጡረታ ሲገለሉ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አለኝታ ስለነበሩ እንደገና በጠቅላይ ቤተ ክህነት መጻሕፍትን እንዲተረጉሙ፣ እንዲመረምሩና በጠቅላላ በቤተ ክርስቲያን ዐበይት ጉዳዮች ወይም እንቅስቃሴ ላይ ተካፋይ እንዲሆኑ ተደረገ። ይህም ጊዜ ከሃያ ዓመታት በላይ ከየቦታውና ከተለያዩ ሰዎች እየሰበሰቡ በማጠራቀም የደከሙበትን «ዝክረ ሊቃውንት» የተባለውን የሀገራችንን ሊቃውንት /ባለ ቅኔዎች/ ታሪክ የሚያስረዳ መጽሐፍ አዘጋጅቶ ለኅትመት ለማብቃት ምቹ ጊዜ ሆነላቸው። /መጽሐፉን ለኅትመት አዘጋጅተው እርሳቸው ስላረፉ የታተመው ጥቅምት ፮ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ.ም ነው/።

መልአከ ብርሃን ዋናው ሥራቸው በቤተ ክህነት ነበር ቢባልም አንዳንድ ድርጅቶች ስለ ኢትዮጵያ ባህልና ታሪክ ለሚያደርጉት ጥናትና ምርምር የሞያ ድጋፍ ያደርጉላቸው ነበር። ከእነዚህም ውስጥ «የኢትዮጵያ የጥንት ቅርስ ጥበቃ ድርጅት» ባደረገው እንቅስቃሴ በመሳተፍ በጐጃም ጠቅላይ ግዛት በተለያዩ አድባራትና ገዳማት ያሉትን መጻሕፍትና ልዩ ልዩ ቅርሳ ቅርስ ዝርዝር በድርጅቱ ከታሰበው በላይ በተሟላ ሁኔታ አዘጋጅተው አቅርበዋል። የዚህ ዝርዝር ሥራቸው ቅጅ በወቅቱ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናት ክፍል ይባል በነበረው ይገኛል። እንዲሁም የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር በየቤተ ክርስቲያኑ የሚገኙትን መጻሕፍት በማይክሮ ፊልም ለማንሣት ባደረገው ጥረት በጎጃም ጠቅላይ ግዛት ብቻና አውራጃ የሚገኙትን ምርጥና ጥንታውያን መጻሕፍት በማዘጋጀት በድርጅቱ ሥራ ተካፋይ ሆነዋል።

በዕረፍት ጊዜያቸው የሃይማኖት መጻሕፍትን መመርመር፣ የታሪክና ልቦለድ መጻሕፍትን ማንበብ፣ ስለ ሃይማኖት ለጠያቂዎች



www.ethiopianorthodox.org

ማስረዳት ዋና ተግባራቸው እንደሆነ አድርገው ይሠሩበት ነበር። እንደ ምሳሌ በኢትዮጵያ ሬዲዮና በብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያዎች በየጊዜው ያስተላለፉትን ትምህርት ማስታወስ በቂ ነው። «ሐዲስ ሰውነት» የተባለው መጽሐፋቸውም በዐቢይ ጾም ጊዜ በኢትዮጵያ ሬዲዮ የሰጡት ተከታታይ ትምህርት ነው። መልአከ ብርሃን አድማሱ መጻሕፍትን ዝም ብሎ ከመቀበል ይልቅ አስቀድሞ በጥልቀት መመራመርን ይወዱ ነበር። ከመጻሕፍት ውስጥ እልፍ አልፎ በሚገባ ያልተብራሩና ትርጉም ያልተሰጣቸው አነጋገሮች ሲያጋጥሙ በቂ የሆነ ትርጉም ይሰጡ ነበር። ታላቁ ሊቅ አለቃ ኅሩይ ፈንታም መልአከ ብርሃን እንደተረጐመው» እያለ ያስተምሩ እንደነበር የጉባኤው ተካፋይ የነበሩት ሁሉ ምስክሮች ናቸው። መልአከ ብርሃን አድማሱ እስከ ዕድሜያቸው መጨረሻ ድረስ በአካለ ሥጋ እያሉ ዕረፍት አልነበራቸውም። ለዚህ ምስክሩ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጡት የነበረውን «ዝክረ ሊቃውንት» የተባለው መጽሐፋቸው ከፍጻሜ ደርሶ ለማየት በጣም ይጓጉ ነበር። በዚሁ ሥራ ቀን ከሌሊት ይተጉ ነበር። ይህንኑ መጽሐፍ አዘጋጅተው በማሳተም ላይ ሳለ ሥራውን ሳይጨርሱት ቀን ሲሠሩ ውለው ማታ በደረሰባቸው ድንገተኛ ሕመም የአእምሮ ድካም /ስትሮክ/ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ.ም ዐረፉ። የቀብራቸውም ሥነ ሥርዓት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ወዳጅ ዘመዶቻቸው በተገኙበት በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል። መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ከባለቤታቸው ከወ/ሮ ዓለሚቱ አሽቴ ሰባት ልጆች አፍርተዋል።

በቅርብ ያውቋቸው የነበሩ እንደሚናገሩትና በተለያዩ ጊዜያት ስለ እርሳቸው የጻፉ ጽሑፎች እንደሚገልጹት፤ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ ተግባረ ዕድን በጣም የሚወዱ በሌላው ጉልበት በከንቱ ሊጠቀሙ የማይፈቅዱ ታላቅ ሰው ነበሩ። በብዙ ጊዜ ሥራቸው ጽሕፈት ስለሆነ በተለያዩ ጊዜያት ሰማንያ አንድን ቅዱሳት መጻሕፍትን በእጃቸው ጽፈው ጨርሰዋል። «በድካሜ ፍሬ እንድረዳ በማድረጉ ፈጣሪዬን አመሰግነዋለሁ» ይሉ ነበር።

መልአከ ብርሃን አድማሱን በተመለከተ ተጽፈው የታተሙ ጽሑፎች እንደሚገልጹት መልአከ ብርሃን ጠባያቸው ትዕግሥትን የተሞላ





ነበር። ይኸውም በአንድ መልክ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። እኔ ልክበር፣ እኔ ልመስገን፣ እኔ ልናገር፣ እኔ ልቅደም፣ እኔ ልታወቅ፣ እኔ ሙሉ ችሎታና ብቃት አለኝ ማለት በእሳቸው ዘንድ በፍጹም አልነበረም። አይታወቅም። መልአከ ብርሃን አድማሱ መጻሕፍትን በሙሉ መልካቸው ያውቋቸው ስለነበር በንባባቸውም ሆነ በትርጓሜያቸው ተጠይቀው ለመመለስ እና አጥጋቢ ትምህርት ለመስጠት የሚቻላቸው ሰው ነበሩ። እንኳን በቁም ነገሩ ጊዜ በጨዋታው ጊዜም ቢሆን ትምህርታዊነት የሌለው ቃል ከአንደበታቸው አይወጣም።

እርቆ ማስተዋል፣ ጠልቆ መመርመር፣ ለመናገር አለመቸኮል፣ አስተውሎ መናገር፣ እውነትን መድፈር፣ የሰውን ክብር መጠበቅ፣ ሰውና እግዚአብሔርን አጥምሮ መውደድ፣ ሰው ደስ እንዲለው መጣር፣ እግዚአብሔርን መፍራት፣ ሀገርን መውደድ፣ ሰውን አለማሳዘን፣ የሥራ ጊዜን አለማባከን፣ በሥራ አለመለገም፣ ምላስንና ልቡናን መግዛት፣ ሲችሉ እችላለሁ አለማለት፣ መጻሕፍትን የሁልጊዜ ጓደኛ ማድረግ፣ ዓይንንም ልብንም እጅንም ከሥራ አለመለየት፣ ጽኑ ሃይማኖትና ፍጹም ትዕግሥት መልአከ ብርሃን አድማሱ የሚታወቁባቸው ጠባያት ነበሩ።

መልአከ ብርሃን አድማሱ በትርጓሜ መጻሕፍት ቃል በቃል የተቀበሉትን ብቻ ሳይሆን እየመረመሩ እያስተዋሉ የሚያዳብሩ፣ የጐደለውን እየሞሉ የጠመመውን እያቀኑ ያስተምሩ ስለነበረ ትርጓሜያቸው ሁሉ ጣዕምና ምሥጢር የተካከሉት ነበር።

ሰውቀታቸው በእምነት ላይ የተመሠረተ ነበረ። አንድ ጊዜ ልጃቸው በጠና ታሞ ለሞት ይደርሳል። ቤተሰብ ወዳጅ ዘመድ ልቅሶ ጀመረ። ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች የሕፃኑን አስከሬን ወደ መቃብር ለመውሰድ መግነዙን አሰናድተው ሲመጡ መልአከ ብርሃን አድማሱ ሕፃኑን አቅፈው ሲጸልዩ አገኟቸው። ሰዎቹ የሕፃኑን መሞት ባለማወቅ የሚያደርጉ መስሏቸው ያጉረመርሙ ነበር። እሳቸው ግን «ትላንትና በሥጋ ተገልጦ የሰዎችን ልመና ስትቀበል፣ ድውያንን ስትፈውስ፣ ሙታኖቻቸውን ስታስነሣ የነበርክ አንተ ነህ። ዛሬም የእስህ አንተ ነህ። አልተለወጥክም። እኔም ከእነዚያ ባላነሰ እምነት አምንሃለሁ። አሁንም



www.ethiopianorthodox.org

«አዝዝ በቃልከ ይሕየው ወልድየ፤ ልጄ እንዲድን በቃል እዘዝ፤» እያሉ ይጸልዩ ነበር፡፡ ብዙ አልቆየም፡፡ ጸሎታቸው ተሰማ፡፡ እግዚአብሔር ልመናቸውን ተቀብሎ በእቅፋቸው ላይ እንዳለ የሕፃኑ ነፍስ ተመለሰች፡፡ ዓይኑንም ገልጦ ይመለከት ጀመር፡፡ የቤተሰቡም ሀዘን ወደ ደስታ ተመለሰ፡፡ በአካባቢው የተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ የእስልምና እምነት ተከታዮችም ሳይቀሩ የእምነታቸውን ጽናት ተረዱት፡፡ ይህ ሕፃን አድጐ ዛሬ አንቱ የተባለ ትልቅ ሰው ሆኗል፡፡ እኚሁ ልጃቸው አገራቸውንና ወገናቸውን በተማሩ የአካውንቲንግ ሞያ ለረጅም ዘመናት በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡

### ስለ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ
### የሰዎች ምስክርነት

«መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬን የማውቃቸው ሲነገር ከምሰማው ሥራቸውና የጻፏቸውን መጻሕፍት አንብቤ ነው፡፡ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በነበርኩበት ጊዜ እሳቸው በስተእርጅና ዕድሜያቸው ሊመጡ ለጥቂት ቀናት አይቻቸዋለሁ፡፡ ከባለ ቤታቸው ከወ/ሮ ዓለሚቱ እሸቴ /በኋላ እማሆይ ዓለሚቱ/ ጋር ግን በተለያየ ጊዜ ደብረ ሊባኖስ እየመጡ በጣም እንግባባ ነበር፡፡

በአንድ ወቅት እማሆይ ዓለሚቱ ከወንድማቸው ጋር ደብረ ሊባኖስ መጥተው ለስድስት ወራት ያህል ቆይተው ነበር፡፡ በዚያን ወቅት እማሆይ ዓለሚቱ ስለልጃቸው ሲያጫውቱኝ ልጃቸው በሕፃንነቱ ታሞ በሞተ ጊዜ ቤተዘመድ ሁሉ ሲያለቅስ ከእግዚአብሔር ጋር የምነጋገረው አለኝ ብለው ሰውን ሁሉ አስወጡ፡፡ እንባቸው በልጁ አስከሬን ላይ እየተንጠባጠበ ይጸልዩ ነበር፡፡ እኔ አእምሮአቸው የተዛባ መሰለኝ እባካችሁ አስጥሉ እያልኩ እናገር ነበር፡፡ በኋላ ልጁ ዓይኑን ገልጦ ተነሣ፡፡ ልጅን በጸሎታቸው «አዝዝ በቃልከ ይሕየው ወልድየ» እያሉ ከሞት አሥነሥተው እግዚአብሔርን እየመሰገኑ ሰጡኝ» በማለት አጫውተውኛል፡፡

መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ከሊቅነት ጋር ሃይማኖት ያላቸው የጸሎት ሰው ነበሩ፡፡ ታላቅ ምሁር ናቸው፡፡ ጠንካራ እምነት ነበራቸው፡፡»

*ብፁዕ አቡነ ቶማስ*
*የአዊና የመተከል አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ*





«ከመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ጋር የመተዋወቅ ብቻ ሳይሆን አንድ ቤተሰብ ነን፡፡ ከ፲፱፻፴ ዓ.ም ጀምሮ አውቃቸዋለሁ፡፡ የተወለዱትና ያደጉት አገራቸው ምሥራቅ ጐጃም ብቸና አውራጃ ዲማ ጊዮርጊስ ነው፡፡ ወላጆቻቸው አቶ ጀንበሬ አዲሱ እና ወ/ሮ ወለተማርያም ኃይሉ ይባላሉ፡፡ ደግ ቤተሰቦች ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር ሰዎች ነበሩ፡፡

መልአከ ብርሃን ገና በእናታቸው ጀርባ እያሉ አንድ ባሕታዊ መጥቶ «ይሄ ያዘልሽው ልጅ ቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም ነው» ብሎ እንደነገራቸው ይነገራል፡፡ እናታቸውም <እግዚአብሔር ያለው አይቀር> ብለው ስማቸውን <ያለው> አሏቸው፡፡ አባታቸው ደግሞ አድማሱ አሏቸው፡፡ በዚያ ምክንያት ብዙ ጊዜ በትውልድ አገራቸው አካባቢ <ያለው> ነበር የሚባሉት፡፡ አድማሱ የሚለው ስም በኋላ ነው ገኖ ያደገው፡፡

መልአከ ብርሃን ተወልደው ያደጉበት ዲማ ለሥጋዊ ምኞት ያንሰው ይሆናል እንጂ በመንፈሳዊው በኩል ዲማ የተፈለገው ምሁር ሁሉ በየመልኩ ይገኛል፡፡ ከንባብ ጀምሮ እስከ ትርጓሜ መጽሐፍ የተፈለገው መምህር ሁሉ የሚገኝበት መንፈሳዊ አገር ነው፡፡ እዚያ ለተወለዱት ብቻ ሳይሆን ከውጪ ለመጡትም ቢሆን በየዓይነቱ ትልቅ ልግስና አለው፡፡ ታቦቱ ረድኤት አለው፡፡ እዚያ ደጅ የጠና ሁሉ ያገለገለ ሁሉ አያፍርምና ከዚህ ዕድል ውስጥ ነው እንግዲህ መልአከ ብርሃን ያን መንፈሳዊ ሀብት ይዘው ያደጉት፡፡ ከልጅነታቸው ጀምሮ በዲቁናም፣ በመዘምርነትም፣ በቅኔውም፣ በመምህርነትም እግዚአብሔርን እዚያ አገልግለዋል፡፡ ትምህርታቸውም እዚያው ከአባቶቻቸው ያገኙት እንጂ ከውጪ አልሄዱም፡፡

ከዚያ በኋላ ብዙ ጊዜ ከተማ ኖረዋል፡፡ መጀመሪያ ደሴ ንጉሥ ሚካኤል ግቢ ከዚያም ደግሞ ወደ አዲስ አበባ መጥተው መጋቤ ምሥጢር ተብለው በአታ ለማርያም ገዳም አገልግለዋል፡፡ እንደውም ይህን ሹመት አስመልክቶ ሹመቱ እድለኛ ነው፡፡ በእሳቸው ተጀመረ ይባል ነበር፡፡ የመጀመሪያው መጋቤ ምሥጢር እሳቸው ናቸው፡፡ አዲስ አበባ በበአታ ለማርያም ገዳም አራቱ ጉባኤያት ሲሠየም ቅኔ መምህርነቱም የተጀመረው በእሳቸው ነው፡፡ ከጠባያቸው ሙያቸው



www.ethiopianorthodox.org

ከሙያቸው ጠባያቸው ይኸ ይነቀፋል የሚባል ነገር የለባቸውም። የሚያስደንቀው ነገር ይሄ ነው። ቁጣ አያውቁም ከሰው ጋር ሲነጋገሩ በትኅትና በአክብሮት ነው እንጂ ቁጣ የለባቸውም። ተጠይቀው ደግሞ የሚያስረዱት አያጡም። ለተጠየቁት ጥያቄ ሁሉ መልስ አይቸግራቸውም። ሙሉ ሰው ናቸው።

እኔ በ፲፱፻፵ ዓ.ም በጠላት ዘመን አለቃ ማርቆስ ከሚባሉ መምህር ዘንድ ቅኔ ቤት ነበርኩኝ። በዚያን ጊዜም ሆነ ከዚያ በኋላ እያደግሁ ስመጣም ብዙ ጊዜ ጥያቄ የምጠይቀው መልአከ ብርሃንን ነው። እሳቸውም በሚገባ ያስረዱኝና ይከታተሉኝ ነበር። በዚያን ጊዜ የነበረው የዓይነ ሥውሮች ሕይወት ከቤተ ክርስቲያን ከተረፈ ለመና ነው። የቤተ ክርስቲያን ተገኛ ሆኖ መኖር ነው። መልአከ ብርሃን ከቤተ ክርስቲያን እንዳልርቅ ብዙ ጊዜ ይቆጣጠሩኝ ነበር። ይሄ በመሆኑ እንደ አባቴ ነው የማያቸው። በተለይ ለእኔ እዚህ መድረስ የመልአከ ብርሃን አድማሱ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው ማለት ነው።

ጣልያን ከአገር ከወጣ በኋላ በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም አካባቢ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ሊቀ ጠበብት ተብለው ነበር። በኋላ ጎጃም ምሥራቅ ብቸና ጊዮርጊስ መልአከ ብርሃን ተባሉ። በዚህ ምክንያት እየተመላለሱ ሁለቱም ጋ ነበር የሚሠሩት። ብቸናን በእንደራሴ እያስተዳደሩ አዲስ አበባ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የመንፈሳዊ ጉባኤ አባል ነበሩ። ይህ ጉባኤ ሰባ ሊቃውንት የነበሩበት ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ነበር። ይኸ በመሆኑ መልአከ ብርሃንም እየተ መላለሱ ይሠሩ ነበር።

ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብት ራሷን እንድትችል የተደረገውን ክርክር በተመለከተም መልአከ ብርሃን አድማሱ ይጠቀሳሉ። የግብጹ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ በጣሊያን ጊዜ ጥለው ወደ ግብጽ ሄደው ነበር። ከነፃነት በኋላ እንደገና ተመልሰው እንዲመጡ ተደረገ። ተመልሰው ሲመጡ ሊቃውንቱ አንቀበልም አሉ። ጠብ ተነሣ። በዚህ ምክንያት ከዚህ በኋላ እንለያያለን የሚል ነገር መጣ። ሊቃውንቱ ለሁለት ተከፈሉ። ከሁለት ሲከፈል ግማሾቹ እንደቀድሞው በግብጽ ጳጳስ





ይመራ የተቀረው ደግሞ አይሆንም አሉ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራሷን መቻል አለባት የሚል አሳብ መጣ። በዚህ ጊዜ በፍትሐ ነገሥት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከዐዋቂዎቻቸው እንዳይሾሙ ተከልክሏል የሚል ነገር መጣ። ይኸ በሥርዋጽ የገባ ነው እንጂ ዋና ቃል አይደለም። በክርስትና የበላይና የበታች ገዥና ተገዥ የለም። ምንም የሚከለክል ነገር የለም ነው የሚለው። ለካ ያን ጊዜ መልአከ ብርሃን አድማሱ ይሄንን ሃሳብ አቅርበው ነበር። ክርክሩም ቀጥሎ መጀመሪያ ታሪው ሃብቴ የሚባሉ በኋላም መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፡ አሥራተ ካሣ፡ አቡነ ቴዎፍሎስ፣ አቡነ ዮሐንስ፣ ያሉበት ጉባኤ ተፈ ጥሮ ጉዳዩ በክርክር ከቆየ በኋላ ተፈቀደ። ኢትዮጵያ ራሷን እንድ ትችል ሹመቱ ግን ከግብጽ ሆኖ በኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት እንድትመራ የሚል ነበር።

ከመልአከ ብርሃን ጋር አዲስ አበባ ከመጣሁም በኋላ አልተለያየንም። የአንድ አያት ልጆች ሆነን የስጋ ዝምድና ቢኖረንም ከእሳቸው አልለይም ነበር። ጠባያቸው ትዕግሥትን የተሞላ ነበር። ትዕግሥታቸው በአንድ አቅጣጫ የተወሰነ ብቻ አልነበረም። በሁሉም ዘንድ በሁሉም አቅጣጫ ነው። መልአከ ብርሃን ቁጣ አይወዱም በጣም ነፃ ሰው ናቸው። ደግነት አላቸው። ሆኖ ከተገኘ እሳቸው ጋር የሚነቀፍ የለም። ሆኖ መገኘት ብቻ ነው። ካልሆነ ደግሞ መቀበልም የለም። ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ልጅ ነው አዋቂ ነው፥ ድሃ ነው ሃብታም ነው፣ ባለ ሥልጣን ነው ተራ ሰው ነው በእርሳቸው ዘንድ ምንም ልዩነት የለም።

በተለይ ለእኔ እንደአባቴም እንደ መምህሬም ነበሩ። ያልገባኝን ነገር ሁሉ የምጠይቀው እሳቸውን ነው። ያን ጊዜ ታዲያ ሀገር የጋራ ነው ሃይማኖት የግል ነው ተብሎ ስለታወጀ ሚሲዮናውያንም ካቶሊካውያኑም ገቡ። የካቶሊክ መንበር ተዘረጋ። የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ተከፈተ። የእስላም መስጊድ በያለበት ተከፈተ። ያ ሁሉ እያደገ ሲመጣ የሃይማኖት ውዥንብር ነበር። በዚህ ምክንያት ብዙ ጥያቄዎች ይነሡ ነበር። እኔም በወቅቱ ከመምህር ፈላታምስ ዘንድ ብሆንም በዘመኑ የነበሩኝን ጥያቄዎች ሁሉ መልአከ ብርሃን ጋር እየሄድኩ ነበር



www.ethiopianorthodox.org

የማጣራው:: በኋላም መምህር ፊላታዎስ ወደ ሃገራቸው ሄደው እዚያው ዐረፉ:: እንግዲህ በጠቅላላው አሳቤ ወደ እርሳቸው ተመለሰ:: በዚህ ምክንያት ከእሳቸው ጋር ነው የምውለው የምጠይቀውም:: መድሉተ አሚን፣ ኑኑሐ ሃይማኖት መጻሕፍታቸውን ሲያዘጋጁ ሁሉ አብሬያቸው ነበርኩ::

መልአከ ብርሃን ካዘጋጇቸው መጻሕፍት በሁሉም ይሄ ከዚህ ይሆናል ይሄ ይቀንሳል የሚል የለኝም:: መጻሕፍቱ ሁሉ የሚነቀስ እንከን የላቸውም:: ከትውልድ ትውልድ እየተላለፉ የሚያገለግሉ የሚያስተምሩ መጻሕፍትን ነው አዘጋጅተው ያረፉት::

መልአከ ብርሃን ከጉያቸው መጽሐፍ አይለይም:: ሲበሉም በአንድ እጃቸው መጽሐፍ ይዘው ነው:: መጽሐፍ አስቀምጠው አይበሉም:: <ኸረ አባክዎ ዓይንዎ ይደክማል ይጐዳል> ሲሏቸው «የተፈጠረው ለዚህ ብሎ ነው:: ለዚህ ካላገለገለ ይፍረጥ እንጂ እኔ ምን አደርገዋለሁ» ይሉ ነበር:: በመጨረሻም ሊቃውንቱ እያለቁ በመሄዳቸው ታሪክም እየጠፋ ስለሄደ የሊቃውንቱን ታሪክ ከሞላ ጐደል የምችለውንና የማውቀውን በጽሑፍ አድርጌ መሄድ አለብኝ ብለው ተነሡ:: በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ነበር የሚደክሙት:: የዚያ ዝግጅት ይመስለኛል በመጨረሻ ጊዜ የጐዳቸው:: በድንገት ታመው በዚያው ቀኑ፤ ዐረፉ::

መልአከ ብርሃን ያነባሉ ይጽፋሉ:: ሁለቱም የእርሳቸው ነው:: የትም ሄዱ እቤትም ገቡ ሥራቸው መጽሐፍ ማንበብ ወይም መጻፍ ነው:: እረፍት የላቸውም:: እኔም በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በታተመው «የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት» በሚለው መጽሐፌ መግቢያው ላይ ያንን መጽሐፍ ለመጻፍ ካነሣሣኝ ምክንያቶች አንዱ ከእሳቸው ጋር በጥብቅ መነጋገሬ ነው ብዬ ያስቀመጥኩት ነገር አለ::

ትምህርትና ሙያ እስከ ዕለተ ሞት አይቋረጥም ይባላል:: በእውነት እኔን ብዙ መምህራን አስተምረውኛል:: ጥሬ ጥሬውን ያስተማሩኝ ልበላቸው:: መቼም ሰብስቦ እቤት ማግባት ብቻ አይደለም:: የገባውን ደግሞ ወደ ሰው ጉሮሮ እንዲደርስ እንዲገባ የሚያደርግ ሥራ ያስጠፈልጋል:: እህሉ አንድ ቤቱ አሥራ ሁለት ይባላል ከኑተረቱ:: የሙያም





ሆነ የትምህርትን ነገር ከሊቃውንቱ በየጊዜው ማስተካከል ያስፈልጋል:: በዚህ ዓይነት ከጠቀሙኝ መምህራን ዋናው መልአከ ብርሃን ናቸው:: የሃይማኖቱን ትምህርት መልኩን ለይተው ጥርት አድርገው ደርዘውን፣ ልዩነቱን፣ አቀራረቡን ሁሉንም ከእርሳቸው ነው ማጥናት የቻልኩት:: ስለ ምሥጢረ ሥላሴ፣ ምሥጢረ ሥጋዌ የሚመስለውን ሁሉ ዝምብዬ በዳሰሳ ያጠናሁትን ለይቼ እንዳውቀው ጣዕሙ እንዲጣፍጠኝ ያደረጉት ኀሊናዬንም እንድገዛ ያደረጉት መልአከ ብርሃን ናቸው::

መልአከ ብርሃን ጠንካራ እምነት ነበራቸው:: ታላቅ መንፈሳዊ የጸሎት ሰው ናቸው:: ምኅርካ ክርስቶስ የሚባለው ልጃቸው ታሞ ሞተ ተብሎ ቤተ ዘመድ ሁሉ ሕዝቡ ተሰብስቦ ሲያለቅስ ለቀብር ሲዘጋጁ እሳቸው በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ስምንት የተጻፈውን እያነበቡ አዝዝ በቃልከ ይሕየው ወልድዬ ልጄ እንዲድን በቃልህ እዘዝ ብለው እንባቸውን ሲረጩት ልጁ ተነሣ ይባላል:: ይኸው ልጅ አሁንም በሕይወት ይገኛል:: ዛሬ ትልቅ ሰው ነው::

ከመልአከ ብርሃን አድማሱ ጋር በአባትነት በመምህርነት ደረጃ ብቻ ሳይሆን በጓደኝነት ደረጃም እንነጋገር ነበር:: አንድ ነገር ሲመጣ ይሄንን እንዴት ታየዋለህ ይሉኛል:: እኔ የምሰጣቸውን አስተያየትና ሃሳብ ካመኑበት ይቀበላሉ:: ልክ ነህ እኔ አሳስቻለሁ ያንተን ተከትዬአለሁ ይላሉ:: ቅርበታችን እስከዚህ ድረስ ነበር:: መኖሪያ ቤታቸው ጉለሌ ራስ ኃይሉ ሠፈር ነበር:: ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥራቸውን ሲሠሩ ይውሉና እኔም እዚያው ውዬ ስንወጣ ጨዋታችን አላልቅልን እያለ ተያይዘን በእግራችን ከጠቅላይ ቤተ ክህነት /አራት ኪሎ/ ጉለሌ ድረስ እንሄድ ነበር:: በእሳቸው ሞት በተለያየ አቅጣጫ ብዙ ጉዳት ደርሶብኛል:: በቤተ ክርስቲያን አንፃር ደግሞ ምን ማለት ይቻላል የማይተካ ሰው ነው የቀረው:: በሕይወቱም ሆነ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቱ ያንን የመሠለ ሰው መተካት አይቻልም:: በአገር አንፃርም ቢሆን ከፍተኛ አገልግሎት አበርክተዋል:: በከፍተኛ ፍርድ ቤት በዳኝነት ይሠሩ ነበር:: በሁሉም አቅጣጫ የተሟላ እኒህን የመሰለ ሰው ከየት ይገኛል::



www.ethiopianorthodox.org

መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ ለቤተ ክርስቲያን በአጠቃላይ ደግሞ ለኢትዮጵያ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ይኸ ነው ተብሎ ተዘርዝሮ የሚዘለቅ አይደለም። ከአንድ ሰው ሕዋሳት ቢጐድል የማይጐዳ የለም። እርግጥ ማባባስ ከመጣ እግዚአብሔርም መምህራኑን ዓይኖች ናችሁ ነው ያላቸው። ዓይን ማጣት ከባድ ነገር ነው። እንደ መልአከ ብርሃን ያሉ ርዕሶችን ማጣት ለቤተ ክርስቲያን ለሃገርም ጉዳቱ ያን ያህል ነው። ጭራሹን ሲታጡ ቀርቶ ደክመው ከቤት ሲውሉ ከሥራ ገበታቸው ሲለዩ እንኳን ይጐዳሉ። መማሩ ብቻ አይደለም። ለትውልድ ጠቃሚ የሆነን ነገር ጽፎ አዘጋጅቶ ማቅረቡ ራሱ ታላቅ ተግባር ነው። በሚፈለገው ጊዜ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ ሁሉ አስፈላጊውን መልስ መስጠት ተቀባይ ማግኘት ይኼ ሁሉ የተሟላለት ሰው ከየትም አይገኝም። መልአከ ብርሃን ይኼ ሁሉ የተሟላላቸው ነበሩ። አስበው ማዘጋጀት የሚችሉ፣ ያዘጋጁትንም ለሰው ማቅረብ የሚችሉ፣ ያቀረቡትም ደግሞ በሰው ፊት ተቀባይነት ያለው ሰው ነበሩ።»

አለቃ አያሌው ታምሩ

«የአባቴን ታሪክ የማስታውሰውን ያህል በጽሑፍ እንዲቀርና ቅርስነት አግኝቶ ለትውልድ እንዲተላለፍ በማድረጉ ላይ የማስታውሰውና የማውቀውን ያህል ለመናገር አጋጣሚውን ማግኘቱ ታላቅ ዕድል ነው። ሲሆን እኛ ራሳችን ተወላጅ ልጆቻቸው የምንደክምበት ጉዳይ ነበር። ግን ያ ሳይሆን ቀርቶ እንደዚህ ዓይነት ለሀገር ለቤተ ክርስቲያን የሚያስብ ማኅበር ሲገኝ ደግሞ እኛ ስለ አባታችን የምናውቀውን ያህል የመግለጽ ግዴታ አለብን። ይህንን ዕድል በማግኘቴም በጣም ደስ ይለኛል።

ምኅርካ ክርስቶስ አድማሱ ጀንበሬ እባላለሁ። መልአከ ብርሃን ሰባት ልጆች አፍርተዋል። እኔ የመጨረሻ ልጃቸው ነኝ። እኔ አባቴ በኖሩበት ሞያ ሳይሆን በተማርኩት የአካውንቲንግ ሙያ ዛሬ በአዲተርነት እያገለገልኩ እገኛለሁ።

መልአከ ብርሃን እኔ ሳውቅ ጀምሮ በቤት ውስጥ በጣም ትዕግሥተኛ ብዙ የማይቆጡ የማይናገሩ ሰው ነበሩ። በተለይ ደግሞ አሁን





ዲሞክራሲ ተብሎ እንደሚጠራው የእኩልነት መንፈስ በቤታችን ውስጥ በጣም የሠረፀ ነበር። የዚህ ምክንያቱ እሳቸው ናቸው። እኛ ልጆቹም ስናድግ በቤት ውስጥ ተጽዕኖ አልነበረብንም። ምናልባት ቁጣ ቢኖርም እንኳን በጊዜው ልንደርስበት የቻልነው ትምህርት ዳዊት፣ ውዳሴ ማርያም የመሰሉትን በምንማርበት ጊዜ እሳቸው የሚሉትን ሳንቀበል ስንቀር ወይም ደግሞ ግድፈት በሚኖርበት ጊዜ ከሚያደርጉት ቁጣ በስተቀር በሌላው ኑሯችንና ሁኔታችን እኔ ሲቆጡ የማስታውስበት ጊዜ የለም። ሌላውም የቤተሰብ አባል የተቆጡበትን ጊዜ የሚያስታውስ አለ ብዬ አላስብም። ሁሉንም በእኩል ሚዛንና መንፈስ የማየት አቀባበል ነበራቸው።

መልአከ ብርሃን አድማሱ በቤተክርስቲያን ሊቅነታቸው አባትነታቸውና በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ያለባቸው ኃላፊነት በቤት ውስጥ የሚፈጥረው የተለየ ተጽዕኖ አልነበረም። ከልጆቻቸውም ሆነ ከቤተሰባቸው አባላት ጋር ቀርበው በነፃነት የመወያየት ችሎታ ያላቸው ነፃ ነበሩ። ይኸንን በሁለት ብከፍለው ጥሩ መልክ ሊኖረው ይችላል።

አንደኛው ጎኝም የብቸና ቅዱስ ጊዮርጊስ መልአከ ብርሃን በነበሩበት በተለይም ቀደም ባለው ጊዜ በ፲፱፻፴፩ ዓ.ም ይመስለኛል /ጊዜውን በትክክል መናገር ባልችልም/ ቤተ ክርስቲያኑን ሲያስተዳድሩ በወቅቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ራሱ በጉልት ገዥነት ደረጃ ስለነበረ ሃያ አራት አገሮች /አጥቢያዎች/ በብቸና መሪነት በተጨማሪ ለአስተዳደሩም ሆነ ለዳኝነቱ የደብሩ አለቃ ሓላፊነት ነበረባቸው። እሳቸውም ይኸንን ሁሉ አጠቃለው ይሠሩ ነበር። በዚያን ጊዜ ሕዝብ ይመለከታቸው የነበረው እንደ ማንኛውም አገረ ገዥ ስለነበረ የውጪው ሰው ጌቶች ነበር የሚላቸው። በቤተሰብም ውስጥ ሌላው ሰው የሚለውን ተከትለን ጌቶች ነበር የምንለው። በዚያን ጊዜ ሰውም ለእሳቸው የነበረው ክብሬታ በጣም ትልቅ ነው። እንደዛሬው የመንግሥት ሥራቸውን የሚያከናውኑበት የተለየ ቢሮ ስላልነበረ ችሎት የሚያስችሉበት ቦታ የተለየ ይሁን እንጂ ቢሯቸው ቤት ውስጥ ነው። በዚያን ወቅት ሁልጊዜም ለአስተዳደር ጉዳይም ሆነ ለዳኝነት ይመጣ የነበረውን ሕዝብ እናይ ነበር። ችሎት በሚያስችሉበት ጊዜ በትንሹ ከሠላሳ እና



www.ethiopianorthodox.org

አርባ ሰው በላይ በግቢው ውስጥ ይኖር ነበር:: ያን ጊዜ ሁሉ ነገር እርካሽ ነው:: እንደልብ ይገኛል:: እዚያ አደባባይ የዋለው ሰው ሁሉ ከእሳቸው ጋር ወደ ቤት ገብቶ ምሳ በልቶ ቡና ጠጥቶ ተጋብዞ ነበር የሚሄደው:: እሳቸው ዘንድ ለአስተዳደራዊም ሆነ ለዳኝነት ጉዳይ የሚመጣው በደጅ ጥናት እንዲንገላታ በፍጹም አይፈልጉም ነበር:: ወዲያውኑ ፍትሕ አግኝቶ ወደ መጣበት እንዲመለስ ያደርጋሉ::

አባታችን ወደ አዲስ አበባ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ተዛውረው በመጡ ጊዜ ብቻና የነበረው ነገር ሁሉ ቤተሰቡን ተከትሎ ወደ አዲስ አበባ አልመጣም:: አብሮ የመጣው ቤተሰባዊው ፍቅርና መተሳሰብ ብቻ ነበር:: በቤት ውስጥ የሚደረገው ነገር ሁሉ በነፃነት ነበር:: ከገደብ የሚወጣ ነገር የለም:: ሁሉም ነገር ሥነ ሥርዓት አለው:: ሁሉ ነገር ሥነ ሥርዓት እስከተከተለ ድረስ በቤተሰቡ ላይ የሚደርስ ተጽዕኖና ገደብ አልነበረም:: እኔ የመጨረሻ ልጅ በመሆኔ በወቅቱ ሕፃን ብሆንም እንኳን ትንሽ ነው ሳይባል ገበታ አብሬያቸው እቀርብ ነበር:: በውይይትም ጊዜ ትንሽ ናቸው፣ ልጆች ናቸው ሳይባል የፈለግነውን ጥያቄ መጠየቅ እንችላለን:: በውይይትም ላይ በነፃነት እንሳተፍ ነበር:: ነፃ የአባትና ልጅ ቤተሰባዊ መቀራረብ ነበረን::

ጸሎት የሚያደርጉት ወንጌል ዘዮሐንስ ነው:: ሁልጊዜም አይቀርም:: ዳዊት አይታጐልም:: ሌሊት ተነሥተውም፣ በመንገድ ሲሄዱም ዳዊት ይደግማሉ:: እና ውዳሴ ማርያም ያደርሳሉ:: ከዚህ በፊት ፋሺስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት በተለይ በጸሎት የተወሰኑበት ጊዜ ነበር:: በመንገድ ላይ ሲሄዱ ሁሉ ዳዊት እየደገሙ ነበር የሚሄዱት:: በዚሁ በጠላት ጊዜ ቅኔ እያስተማሩ ነበር ያሳለፉት:: እኔ የተወለድኩበት የዘረዘር የምትባል ቦታ አለች:: ከዲማ ወደ የዘረዘር በሚሄዱበት ጊዜ በሁለቱ መካከል ላይ ገድ የምትባል ሸጥ አለች:: እዚያ ሽፍቶች መንገደኛ እየጠበቁ ይዘርፋሉ:: ሌሳም ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳሉ:: አንድ የገቢያ ቀን በዚያ መንገድ ብቻቸውን ሲሄዱ ሽፍቶች እየጠበቁ ይዘርፋሉ:: በመንገድ ላይ አንዲት ሴት ከኋላቸው መጥታ እባክህ ከአንተ ጋር ልሂድ ትላቸዋለች:: እኔስ እንደአንችው ባዶ እጄን አይደለሁም ወይ ከምን አስጥልሻለሁ ይሏታል:: ሴትዮዋም ከአንተ ጋ ብሄድ ይሻለኛል በማለት አብራቸው መጓዝ ቀጠለች:: እሳቸው እንደተለመደው ዳዊት እየደገሙ ነው የሚጓዙት:: ከሴትዮዋ ጋር አብረው ሲሄዱ ከፊታቸው ይጓዙ የነበሩትን ነጋዴዎች ሽፍቶች አስቀመው ሲዘርፏቸው ይደርሳሉ:: እነዚያ ሽፍቶች ነጋዴዎቹን እየቀሙ በነበሩበት ጊዜ መልአከ ብርሃንን ያዩዋቸዋል:: ወዲያውኑ መጣብን ብለው ሽፍቶቹ የሚቀሙትን ትተው እየተሯሯጡ ወደ ጫካ ገቡ:: እሳቸውም ከሴትዮዋ ጋር በሰላም አለፉ:: ኃይላቸው ጠባቂያቸው ጸሎታቸው እንደነበረ ብዙዎች ይናገራሉ::

በጣልያን ጊዜ አገራቸው ዲማ ሄደው በኃዘንና በጸሎት ተወስነው ቅኔ እያስተማሩ በኖሩበት ጊዜ በብቻና አድባራት ሁሉ ምሕላ በማስያዝ ቆይተዋል:: ከብቶች ጥጃ ከላሚ እየተለያዩ ሕዝቡ እየተሰበሰበ በጾም በጸሎት ስለ አገር ነፃነት አምርረው ያለቅሱ ነበር:: በዚህም ጣልያን በተለይ በብቻና አውራጃ ብዙ ጊዜ የሽፍታ አገር ነው በአውሮፕላን ይደብደብ እየተባለ በእግዚአብሔር ጥበቃ ሳይፈጸም ቀርቷል:: የእምነታቸውን ጽናት አስመልክቶ እኔ ልጃቸው ብሆንም ብዙዎቹ በሥራም ሆነ በተለያየ ምክንያት የሚያውቋቸው ሁሉ ብዙ ይናገራሉ:: ለምሳሌ እኔ በወቅቱ ባላስታውሰውም በኋላ ሲነገር እንደ ምንሰማው የአራት ዓመት ልጅ እያለሁ /፲፱፻፴፫ ዓ.ም ይመስለኛል/:: በጠና ታመምኩ:: ታምሜ በነበረበት ወቅት እናቴም ሆነች ሌሎች ዘመድ ወዳጆቻችን ሁሉ ተስፋ በመቁረጥ በየጊዜው ሞተ ይሉ ነበር:: አንድ ቀን የባሰ ሁኔታ ተፈጠረ:: እንደነገሩኝ በዚያን ጊዜ እኔን ይዘው ከፊታቸው የጌታችንን ሥነ ስቅለት አድርገው ወንጌሉን ከደገሙ በኋላ እጅግ በጣም እንደሚቀርቡትና አጠገባቸው እንዳለ ሰው ንግግር ነበር የሚያደርጉት:: <እንዴ... ሃይማኖት ያለው ይድናል ብለሃል:: የዚያን የመቶ አለቃውን ልጅ እምነት ስለነበረው ነው ያዳንከው:: እኔስ እምነት አለኝ አይደለም ወይ....በምን ምክንያት ነው የእኔን ልጅ የምትገድለው?> ከእምነታቸው ጥንካሬ የተነሣ እንደዚህ ነበር ንግግራቸው:: በዚያን ጊዜ እዚያ ብቻና ግዛት እስላሞችም ይገኛሉ::



www.ethiopianorthodox.org

ብዙ እስላሞች ነበሩ። እንግዲህ በዚያን ጊዜ መልአከ ብርሃን የብቸና ሹም በመሆናቸው የሹም ልጅ ታመመ፤ ሞተ ሲባል ብዙ ሰው ወደ ቤት ይሰበሰባል። እስላሞቹም ሊጠይቁ መጥተው ነበር። እሳቸ ውም በጸሎታቸው <እነዚህ እኰ እስላሞች ናቸው። አንተን ልጄን ታድንልኛለህ ብዬ በፊታቸው ለምኜሃለሁ እና እነሱ ፊት እንዴት ታሳፍረኛለህ?> ነበር የሚሉት። የእናቴ አባት ደግሞ ቄስ ነበሩ። በኋላ በምንኩስና ሕይወት የኖሩ ደግ ሰው ነበሩ። በዚያን ጊዜ እሳቸው ስለነበሩ አባቴን <ለምንድነው እግዚአብሔርን የምታስጨንቀው እሱ ሠራው የሠራውን ይውሰድ ለምን ታስቸግረዋለህ?> እያሉ በአንድ ወገን ይናገሯቸው ነበር። ከዚያ በኋላ እንደነገሩን ሁለት ጊዜ ሞተህ ነበር ነው የሚሉኝ። በእሳቸው ጸሎት ተነሣሁኝ።

ይኸ ሁኔታ በተፈጸመ ጊዜ መልአከ ብርሃን በብቸና ይሾማሉ። እርግጥ ብቸና ይወለዱሉ። ነገር ግን ተወልደው ያደጉት ዲማ ስለነበረ የዲማ ሰው ተብለው ነው በብቸና የሚታወቁት። ስለዚህ የብቸና ሰዎች እያሉ ከዲማ መጥቶ እንዴት ተሾመብን የሚል በወቅቱ የአካ ባቢው ሰዎች ቅሬታ ነበራቸው። እዚህ ላይ መቼም ሰዎች ነንና ሰዎቹ <ይኸ ደብተራ በድብትርናው ነው ይሄን ሹመት ያገኘው> እያሉ ያሟቸው ነበር። በኋላ የእኔን ከሞትኩ በኋላ በእሳቸው ጸሎት መነ ሣቴን እዚያው አይተው የእምነታቸውን ጥንካሬ ካረጋገጡ በኋላ <ተሳ ስተናል እኚህ ሰው ለካ ጻድቅ ኖረዋል> በማለት ተናገሩ። ሕዝቡም ከዚያ በኋላ በአክብሮት ይመለከታቸው ነበር። እኔንም አሁንም ድረስ ያን ጊዜ የነበሩ ሰዎች ባገኙኝ ቁጥር ሞቶ የተነሣው ልጅ ነው የሚሉኝ።

አባቴ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ ጊዜያቸው ሁሉ ከሥራቸው ጋር በማንበብና በመጻፍ የተጣበበና የተያዘ ነበር። የሥነ ጽሑፍ ስሜቱ አደረብኝ የሚሉት ከጠላት /የጣልያን ወረራ/ በፊት እሳቸው የሚ ያውቋቸው ሙዱ የሚባሉ ሰው ነበሩ። እኚህ ሰው ጋዜጣ ላይ ጽፈው ስማቸውን አነበብኩ አሉ። <እሱ መጻፍ ከቻለ እኔስ ለምን መጻፍ አልችልም?> የሚለው ሃሳብ ያደረብኝ ያን ጊዜ ነው ይሉ ነበር።





በማንበብ በኩል መጽሐፍ አይመርጡም። የሃይማኖት መጽሐፍ ያዘወት ራሉ። የታሪክ መጻሕፍት፣ አልፎ አልፎ የሰዎች ግለ ታሪክ (Bibliography) እና ልቦለድ መጻሕፍት ማንበብ ይወዳሉ።

መልአከ ብርሃን አዲስ አበባ በነበርንበት ጊዜ ዕረፍት ብለው የተቀመጡበት ጊዜ ትዝ አይለኝም። ፍርድ ቤት በሚሠሩበትም ጊዜ ሆነ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሲሠሩ ጠዋት መሥሪያ ቤት ይመጣሉ፤ ሥራ ውለው ወደቢታቸው ይመለሳሉ። ምሣ ወይም ራት ዘጠኝ ወይም አሥር ሰዓት ላይ ከበሉ በኋላ ወደ ጽሕፈት ጠረጴዛቸው ሄደው ይቀ መጣሉ። ከዚያ በኋላ መኝታ ነው። ምንጊዜም እረፍት አልነበራቸ ውም። እና በጣም ያነቡና ይጽፉ ነበር። መጻሕፍቶቻቸውንም ያዘጋጁ ት በዚህ ሁኔታ ነው። ብዙ ሥራዎቻቸው በጠቅላይ ቤተ ክህነት ይገኛሉ።

አንድ መሠረታዊ የሆነ አሳብ ነበራቸው። ቤተ ክርስቲያንን የሚ መለከት ነገር ከሆነ በጣም ክብር የሚሰጡትና የሚያስቡለት ጉዳይ ነበር። ራሳቸውን አሳልፈው የሚሰጡለት ነገር ነበር። እና ካዘጋጁቸው ውስጥ ለምሳሌ ልቡል ሣህለሥላሴ በሚያገቡበት ጊዜ የተክሊል ድር ሰት ተፈለገ። ከዚያም እሳቸው ሥርዓተ ተክሊልን በጥሩ ሁኔታ አዘጋ ጅተው አቀረቡ። ስሙም በቤተ ክርስቲያኒቷ እንጂ በራሳቸው ስም እንዲሆን አይፈልጉም ነበር። ብዙ ከማንበባቸው የተነሣ ነው ቤተ ክርስቲያንን በመንቀፍና የሃይማኖት ኑፋቄን የሚመለከቱ መጽሐፎችን የሚያገኙት። በዚህም ምክንያት መልስ ሰጪ የሆኑ መጻሕፍትን ለማ ዘጋጀት ችለዋል።

አባቴ በዲያሎግ /ውይይት/ ያምናሉ። ይኸ እምነቴ ነው መደረግ አለበት አይሉም። እሳቸው እንደነገሩኝ ማስታወቂያ ሚኒስቴር የሚ ሠሩ አንድ የቲዮሎጂ ዶክተር ካቶሊክ ነበሩ። ይተዋወቁ ስለነበረ ውይ ይት /ዲያሎግ/ እንዲያደርጉ ጠይቀዋቸው ሰውየው ሳይቀበሏቸው ቀር ተዋል። እኔ ልጅ ሆኜ በ፲፱፻፵፭ ዓ.ም ይመስለኛል። በኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ በዐቢይ ጾም ማታ ማታ ያስተምሩ ነበር። ያን ጊዜ መሣ ሪያው /ቴክኖሎጂው/ ኋላ ቀር በመሆኑ በየቀኑ ማታ ማታ ራሳቸው



www.ethiopianorthodox.org

በአካል ሬዲዮ ጣቢያው ድረስ እየሄዱ ከዚያው ነበር የሚተላለፈው። እኔም አብሬአቸው ስለምሄድ ጨርሰው እስከሚወጡ ድረስ በጨለማው ውጪ ጠብቄአቸው ከዚያ በኋላ ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ጉለሌ እቤታችን ድረስ በእግራችን እንሄድ ነበር። በዚህ ዓይነት የሰጡትን ትምህርት አሰባስበው ከአዘጋጁት በኋላ «ሐዲስ ሰውነት» ብለው በመጽሐፍ አሳተሙት። ከዚያ በኋላም እንደእነ «መድሎተ እሚን»፣ «ኲኲሐ ሃይማኖት» ያሉትን መጻሕፍት ጽፈ ዋል። በመጨረሻው ዘመናቸው «ዝክረ ሊቃውንት» የተባለውን መጽሐፍ በሚያዘጋጁበት ጊዜ በጣም ይጓጉ ነበር። የኢትዮጵያ ሊቃውንት ታሪክና ሥራ ተቀብሮ መቅረት የለበትም። እያሉ ያስቡ ነበር። የሊቃውንቱን ታሪክና ሥራ ማሰባሰቡን የጀመሩት ከብዙ ጊዜያት በፊት ነው። የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ በሆኑበት ጊዜ በየአገሩ ሲዞሩ ዕድል አጋጠማቸውና የሚያገኟቸውን ሰዎች ሁሉ አምጡልኝ እያሉ ታሪካቸውን ሲያሰባስቡ ቆዩ። በዚህ ሁኔታ ዝክረ ሊቃውንትን አዘጋጁ። የመጀመሪያው ቅጽ /ቮሊ. ዩም/ ሊያልቅ ሲል እሳቸው ዐረፉ።

በዚያን ጊዜ አቡነ ቴዎፍሎስ ነበሩ። እኔን አስጠርተው መጽሐፉ የሚቀረው ዝግጅት ካለ እንዲያልቅና እንዲታተም ብለው አዘዙ። በአንድ ጥራዝ አለቀ። ከዚያ በኋላ አቡነ ቴዎፍሎስ <የሚቀጥለውም የመጽሐፉ ክፍል ተዳፍኖ መቅረት የለበትም ረቂቁን አምጥተህ ለሊቃውንት ጉባኤ ስጥ> ብለውኝ ረቂቁን ወስጄ አስረከብኩ። በመካከሉ በተፈጠሩ ችግሮች የመንግሥት ለውጥ አብዮት መጣ። አቡነ ቴዎፍሉስም ታሠሩ ለሞት በቁ። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሳይታተም ጊዜው አለፈ። በመጨረሻው ከብዙ ጊዜ በኋላ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚገኘው የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም በአነስተኛ ቅጂ /ኮፒ/ አሳተመው። ለሕዝብ የተዳረሰ ግን አይመስለኝም።

መልአከ ብርሃን በሚጽፉበት ጊዜ እንግዲህ ሥራቸው በቤተ ክህነት ስለነበረ ገቢያቸውም ውስን ነበር። የምንኖርበትም ቤት ያን ያህል የሚያወላዳ ባለ መሆኑ የራሳቸው ጥናት ክፍል ወይም ጽ/ቤት በቤታቸው አልነበራቸውም። የሚጽፉትም ሆነ የሚያነቡት በሳሎን





ውስጥ ነው። የቤተሰብ ቤት ስለሆነ ሳሎን ያለውም ሰው ያወራል። ሥራውን ይሠራል። እሳቸው ዝም ብለው ሥራቸውን ይሠራሉ። ስለ ቦታ አይጨነቁም ነበር።

መልአከ ብርሃን ለቤተ ክርስቲያን መብት በየአጋጣሚው ከመታገል ወደ ኋላ ያሉበት ጊዜ የለም። እኔ እንኳን ሕፃን ብሆንም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ሊቃነ ጳጳሳት መሾም አለባት በሚለው ክርክር ጊዜ የጎጃምን ሊቃውንት ወክለው ወደ አዲስ አበባ የመጡት ታላቅ ወንድሜን አስከትለው ነበር። ከዚያ በኋላ ሲያወሩ እንደሰማሁት በጣም ትልቅ ክርክር ነበር። በዚያን ጊዜ እጨጌው እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ነበሩ። እሳቸው እንኳን ሳይቀሩ አሳቡን ተቃውመው ነበር። ነገር ግን በኋላ ፓትርያርክ የሆኑት ራሳቸው እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ /ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ/ ናቸው። በዚያን ጊዜ ብዙ አባቶች ተቃውመዋል። ኢትዮጵያ የራስዋ ሊቀ ጳጳስ ይኑራት ማለትን ሃይማኖት እንደማፋለስ አድርገው ይቆጥሩት ነበር። ብዙ ትግል ተደርጎ ይኸው ፍሬው ለዚህ በቃ። ከእሱ በኋላ ደግሞ በ፲፱፻፶ዎቹ ውስጥ ፕሮቴስታንቶች የብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያ እናቋቁም ብለው መንግሥትን ጠየቁ። ጉዳዩም ወደ ቤተ ክህነት ተመራ። ጉዳዩ ለቤተ ክህነት እንደቀረበ በወቅቱ የነበሩ አባቶች ሁሉ በቁጣ ተቃወሙ። ወዲያውኑ ስብሰባ ተቀመጡ። በስብሰባው ላይ መልአከ ብርሃን ይኸ ሬድዮ ጣቢያ ይፈቀድላቸውና ይከፈት። ግን ለእኛም የአየር ጊዜ ይስጠንና እናስተምር። እነሱ አንድ ነገር ቢሉ እኛም በጥሩ ሁኔታ መልስ መስጠት ነው በማለት ተከራከሩ። በመጨረሻ ሃሳቡ ለንጉሠ ነገሥቱ ቀርቦ ሬዲዮ ጣቢያው ሲከፈት የአየር ጊዜም ለቤተ ክርስቲያን ተሰጠ። በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተምሮ ማስተማር በሚል ትምህርተ ወንጌል በዚሁ የአየር ጊዜ ማስተማር የተጀመረው ያኔ ነው። መልአከ ብርሃንም በዚሁ ሬዲዮ ፕሮቴስታንቶቹ የሚያስተላልፉትን እሳቸው በጥሩ ሁኔታ መልስ እየሰጡ በማስተማር ብዙ ጊዜ አገልግለዋል። እንደውም በዚሁ በፕሮቴስታንቶቹ ሬዲዮ ጣቢያ በብሥራተ ወንጌል ከተለያዩ አቅጣጫዎች እጅግ ብዙ ጥያቄዎች



www.ethiopianorthodox.org

እየቀረቡላቸው የተሟላ መልስ በመስጠት ሰፊ ማብራሪያ በማቅረብ በራሳቸው በፕሮቴስታንቶቹ ሬዲዮ ጣቢያ ተጠቅመው ከፍተኛ ሥራ ሠርተውበታል። በሚገባ አስተምረውበታል።

መልአከ ብርሃን በጣም ትዕግሥተኛ ነበሩ። የሚናደዱበትን ጊዜ ወይም ተበሳጭተው አይቼ አላውቅም። ይኽ ጠባያቸው ከልጅነታቸው ጀምሮ በወጣትነታቸውም የነበረ ነው ይባላል። የሚያስቆጣ ነገር ቢያጋጥማቸውም ስሜታዊ ሆነው ወዲያውኑ የሚወስዱት እርምጃ አልነበረም። አንድ እርምጃ ለመውሰድም ሆነ ለመወሰን በጣም ዝግተኛ ነበሩ። እስከ ዕድሜያቸው መጨረሻ ድረስ ይሠሩ ነበር። ያነቡ ይጽፉ መጻሕፍትን ያዘጋጁ ነበር። በመጨረሻው የታመሙ ዕለት እንኳን ቀን ሲሠሩ ውለው «ዝክረ ሊቃውንት» የተባለውን መጽሐፍ በትኩረት ሲያዘጋጁ ውለው ሌሊት ስድስት ሰዓት አካባቢ ነው በድንገት /ስትሮክ/ የሞቱት። መልአከ ብርሃን የመጠቀ አስተሳሰብ ነበራቸው።

በጣሊያን ጊዜ ይመስለኛል። በዲማ በጣም የታወቁ አባ እውነቴ የሚባሉ መነኩሴ ነበሩ። ዲማ ንዋያተ ቅድሳት የሚቀመጡበት ዋሻ ነበር። መነኩሴውም በዚያ ዋሻ ነበር የሚኖሩት። አንድ ቀን አባቴ

ነርሳቸው ዘንድ ሄደው በነበረበት ወቅት... <ይሄ የአውሮፕላን ሥራ የጥበብ ይመስልሃል ወይስ የሰይጣን?> ብለው ጠየቋቸው። መልአከ ብርሃንም <የኔታ ይኼስ የጥበብ ይመስለኛል፥ ለምሳሌ ቶፋ /የሸክላ ድስት/ ውኃ ይጣድበታል። መግላሊት /ክዳን/ ከላይ አለው። ውኃው በሚፈላበት ጊዜ መግላሊቱን ወደ ላይ ያነሣዋል። ከዚያ ጋር ተዛምዶ ያለው ይመስለኛል።> ብለው መለሱላቸው። መነኩሴውም እግዚአብሔር ይስጥህ ልጄ ተባረክ ብለው እንደመረቋቸው ይናገራሉ። ምክንያቱም ከዚያ በፊት ሌሎችን ካህናት ሄደው ይኽንኑ ሲጠይቋቸው «የኔታ ይኸማ የሰይጣን ሥራ ነው» ብለው ይመልሱላቸው ነበር። እና ብዙ ጊዜ አንድን የተለየ ወይም አዲስ ነገር ዝም ብለው አይቀበሉም። ይመራመራሉ። አመለካከታቸውም የቀደመ ነው።

መልአከ ብርሃን በዚያን ጊዜ ሁሉንም ተምረዋል። ነገር ግን አውቃለሁ ብለው አይቀመጡም። ቅኔውን በልጅነታቸው ተምረዋል።





ከተለያዩ መምህራን ቀጽለዋል። መጻሕፍቱን ተምረዋል። ሌሎቹንም የቤተ ክርስቲያኒቷን ትምህርት ተምረዋል። ትምህርታቸው ግን ማብቂያ የለውም ነበር። በዚያን ጊዜ በትልቅ የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነትና ሥራ ላይ እያሉ ሊቅ ሆነው በሊቃውንቱ ዘንድ እየሄዱ ይጠይቁ ይመራመሩ ነበር።

እኔ የመጨረሻ ልጃቸው ብሆንም ቀደም ባሉት ጊዜያት አባታችን መልአከ ብርሃን ባለቤታቸውን /እናታችንን/ በተለይም ነፍሰ ጡር በሚሆኑበት ጊዜ እግራቸውን የሚያጥቧቸው እሳቸው ነበሩ። ለባለቤታቸው የሚያደርጉት አክብሮትና ክብካቤ ለእኛም ለልጆቻቸው ታላቅ ትምህርት ሆኖናል።

*ምኀርካ ክርስቶስ አድማሱ*

ከሞት የተነሣው ልጃቸው

ምሕርካ ክርስቶስ ማለት «የክርስቶስ ምርኮ» ማለት ነው

*ምንጭ፦ ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ታኅሣሥ ፲፱፻፺፩ ዓ.ም*

ምንጭ፦

⇒ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፣ ዝክረ ሊቃውንት ፲፱፻፹፫ ዓ.ም፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ
⇒ የክቡር መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ የ40 ቀን መታሰቢያ መጽሔት፣ ጳጉሜ ፫ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ
⇒ «ዜና ቤተ ክርስቲያን » ሐምሌ ፲፱፻፺፪ ዓ.ም



www.ethiopianorthodox.org

# መምህር ገብረ ሕይወት ሰይፉ

/፲፰፻፺፱ – ፲፱፻፺፯/



*«የኢትዮጵያ ሰው የቀደሙት አባቶች ያቆዩትን ትምህርት አጥብቆ መያዝ አለበት»*

ለሰባ፯ አምስት ዓመታት ያህል በቤተ ክርስቲያን ትምህርት በየ ጉባኤ ቤቱ አሳልፈዋል:: ከዚያም ከስልሣ ዓመታት በላይ አስተምረዋል:: በዚህ የረጂም ዘመን የመምህርነት ጊዜያቸው ሁሉ ጉባኤያ ቸው እንደደመቀ ቆይቷል:: ዛሬ በዕድሜ ብዛት እርጅና ቢታገላ ቸውም እጃቸውን አልሰጡትም:: በደብረ ጽጌ ቅድስት ማርያም ገዳም የመጻሕፍቱ ሊቅ አልጋ ላይ ሆነው ደቀመዛሙርቶቻቸውን ያስተምሩ ነበር:: ከሌሎችም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ምእመናን የሚቀርቡ ላቸውን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፤ ያብራራሉ፤ ያስረዳሉ::

መምህር ገብረ ሕይወት ሰይፉ የተወለዱት ጳጉሜ ፩ ቀን ፲፰፻ ፺፱ ዓ.ም በድሮው ጎንደር ክፍለ ሀገር በጠለምት አውራጃ ልዩ ስሟ ብልብላ ማርያም ከምትባል ደብር ነው:: ወላጆቻቸው አቶ እንግዳ ወርቅ ወንድአፍራሽ እና ወይዘሮ የተመኙ ፋንታዬ ይባላሉ::





በሕፃንነታቸው ትምህርታቸውን የጀመሩት እዚያው በሰሜን አጽገባ ጊዮርጊስ በሚባል አጥቢያ ነው:: በዚያ አባ ወልደኪሮስ ከተባሉ መምህር ዘንድ ከፊደል ንባብ ጀምሮ እስከ ቅዳሴ ድረስ ተማሩ:: ከዚ ያም እልፍ ብለው ጃንአሞራ ከሚባል ቦታ ከመሪጌታ ይትባረክ ዘንድ ምዕራፍና ጾመድጓ ተምረዋል:: እንደገና ወደ ጠለምት ተመልሰው ሰገነት ማርያም በምትባል ደብር ከመምህር /አለቃ/ ብርሃኑ ቅኔ ተማሩ:: ቀጥሎም አለቃ ወልደ ኪዳን ከሚባሉ መም ህር ዘንድ ቅኔውን አስፋፍተዋል::

በወቅቱ የጎጃምና በጌምድር ሊቀጳጳስ ከነበሩት ከብፁዕ አቡነ አብር ሃም መዓርገ ዲቁና ተቀብለዋል:: የመጻሕፍቱ ሊቅ /መምህር/ ገብረ ሕይወት ዲቁናቸውን ከተቀበሉ በኋላ በትውልድ አካባቢያቸው ለመቆየት አልፈለጉም::

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርቷ ተዝቆ የማያልቅ ማዕዷ ሰፊ ነው:: መምህር ገብረ ሕይወት ከሰፊው የትምህርት ማዕዷ በሰፊው ለመቋደስ ሊቃውንቱን ፍለጋ ከትውልድ አካባቢያቸው ርቀው ሔዱ:: ከአለቃ ቀለመ ወርቅ ውዳሴ ማርያምንና ቅዳሴ ማርያምን፣ ከአለቃ /ሊቁ/ ቀጸላ ወንጌልን ተማሩ::

ጣልያን ኢትዮጵያን ከመውረሩ በፊትና በወረረችበት ጊዜ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ ትምህርታቸውን ቀጥለዋል:: ስመ ጥር ከሆኑት ከመምህር ሰይፈ ሥላሴ ሐዲሳትን በሚገባ ተማሩ:: መምህር ገብረ ሕ ይወት የሚጠሩትም በእኚሁ መምህራቸው ስም ነው:: መምህራቸው አዲስ አበባ መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል በነበሩበት ጊዜም ከእሳቸው አልተለዩም:: ከመምህር ገብረ እግዚአብሔርም ዘንድ ሙሉ ሐዲሳትን ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል:: አቡሻህርን ከዶክተር አለቃ አየለ ዘንድ ጠንቅቀዋል:: ከዚያም በኋላ በመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ሐዲሱን እያስተማሩ መጻሕፍተ ብሉያትን ከታላቁ ሊቅ ከመምህር ፊላታዎስና ከመጋቤ ምሥጢር ጌራ ወርቅ አጠናቀዋል::



www.ethiopianorthodox.org

መምህር ገብረ ሕይወት አዲስ አበባ በማስተማር ላይ እንዳሉ በ፲፱፻፴፯ ዓ.ም ለጸበል ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በሄዱበት በዚያው ቆይተው ከአለቃ /አባ/ ይትባረክ ዘንድ የደብረ ዓባይን ቅዳሴ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል፡፡ ከደብረ ሊባኖስ ገዳም ተመልሰው ከመጋቤ ሐዲስ ወልደ ሚካኤልና ከአቡነ ዮሐንስ ፍትሐ ነገሥትን፣ ከሊቀ ሊቃውንት ሞገስ ሃይማኖተ አበውን ተምረው ምስጢሩን በማገናዘብ ጠንቅቀው ተረድተዋል፡፡

መምህር ገብረ ሕይወት ሰይፉ ጉባኤያቸውን በተባሕትዎ ለማስተማር ስለመረጡ ደብረ ሐዊ ገዳም በመግባት ሥርዓተ ምንኩስናን ከመምህር ገብረ ሥላሴ መንርገ ቅስናን ከብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ከዚያም ቁምስናን ከብፁዕ አቡነ እንድርያስና ከብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ተቀብለዋል፡፡

ከ፲፱፻፴፰ ዓ.ም ጀምሮ ማስተማሩን የጀመሩት መምህር ገብረ ሕይወት በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት በአታ በሚገኘው ትምህርት ቤት በሐዲስና በፍትሐ ነገሥት መምህርነት ተመድበው ለዘጠኝ ዓመታት አስተምረዋል፡፡ በዚህም መጋቤ ሐዲስ ተብለዋል፡፡ ከ፲፱፻፶፪ ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ደግሞ በሰሜን ሸዋ ሰላሌ ሃገረ ስብከት በሚገኘው ደብረ ጽጌ ቅድስት ማርያም ገዳም ሳይታክቱ አልጋም ላይ ሆነው መጻሕፍትን በማስተማር ቆይተዋል፡፡

እኚህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ በትጋት ባስተማሩባቸው ረጅም ዘመናት ብዙዎችን ጳጳሳትና ታላላቅ መምህራንን አስተምረው ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አበርክተዋል፡፡

ከሊቃነ ጳጳሳቱ መካከል፡ ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ፡ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል፥ ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ፣ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል፥ ብፁዕ አቡነ ኒቆዲሞስ፥ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ/ካልዕ/፣ ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ፣ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ፣ ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ ይገኙበታል፡፡

ከመምህር ገብረ ሕይወት ዘንድ ተምረው ከወጡት ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መምህራን መካከልም፡ አለቃ ልሳነ ወርቅ /የቅድስት ሥላሴ መምህር/፣ መምህር ዐሐይ፥ መምህር ክንፈ ርግብ፣ መምህር ሐዲስ፣ አለቃ ሐረገ ወይን፣ አለቃ ዓምደ ጽዮን፣ መሪጌታ





አድማሱ፥ መምህር ገብረ ጻድቅ፣ አለቃ ገብረ ጻድቅ፣ መሪጌታ አክሊሉ፣ አለቃ ሲራክ፣ መምህር ሚናስ፣ መምህር ተድላ፣ መሪጌታ ሣህለ ማርያም፣ አባ ገብረ ጻድቅ፣ መምህር ገብረ ማርያም፣ መምህር እሸቴ፣ መምህር ጽጌ፣ መምህር ዜና ደገፋው፣ መምህር ጥበቡ ወ/ማርያም፣ አባ ላዕከ ማርያም፥ አባ አፈ ወርቅ ዘነበ፥ መሪጌታ ቀለመወርቅ ገብረ ኢየሱስ፡ መምህር ልቡል ያሬድ፣ አባ መስፍን፣ መምህር ቃለ አብ፡ መምህር ዘገብርኤል፣ መሪጌታ ስብሐት መኮንን፣ አለቃ ተሰማ፣ አባ ዘሚካኤል፣ መሪጌታ ገብረ ሥላሴ፣ አባ ጽጌ ብርሃን፣ መሪጌታ ቃለ ጽድቅ፣ አባ ኃይለ ጊዮርጊስ ፣ መሪጌታ ዘውዱ ተፈራ፣ ቄስ አዘነ፣ መሪጌታ ይትባረክ፣ ኢጋፋሪ ሐዋዝ፣ መሪጌታ መርዓዊ፥ መሪጌታ ሀቢይ፣ መሪጌታ ገብርኤል፣ መሪጌታ ዘውግ፥ መሪጌታ ገብረ እግዚአብሔር ኃይሉ፣ መሪጌታ ይኄይስ ተመስገን፣ መሪ ጌታ ገብረ ኢየሱስ ካሣ፣ መሪጌታ ኃይለ ጊዮርጊስ፥ መሪጌታ ልሳነወርቅ ደሳለኝ ይገኙበታል፡፡

አባ ገብረ ሕይወት ሰይፉ በማኅበረ መነኮሳቱ ፈቃድ የደብረ ጽጌ ማርያም ገዳም ኃላፊ በመሆንም ገዳሙን አስ[illegible]ረዋል፡፡

ከእርጅና ጋር ሕመም ቢጫጫናቸውም ብርቱ ነበሩ፡፡ በወ[illegible]ቱ እንደበታቸውም ጥርት ያለ ነው፡፡ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ተጠይቀው የሰጧቸውን መልሶች እንደሚከተለው ይታወሳሉ፡፡

በዚህ በእርጅና ዘመናቸው ያስተምሩ እንደሆነ ሲጠየቁ «ኃይለ ቃል እየመረጥኩኝ አስተምራለሁ፡፡ ወንጌሉን፣ ጳውሎስን ግብረ ሐዋርያትን አጥኑ እያልኩኝ አስተምራለሁ፡፡ ቅዳሜ ቅዳሜ እዚያ መማሪያ ቦታ አዳራሽ እዚያ ውስጥ ሆኜ እሑድ እሑድ የሚቀደሰውን ቅዳሴና ወንጌሉን ቀድሜ አስተምራለሁ፡፡ ሐዋርያውን፣ ግብረ ሐዋርያትን፣ ትርጓሜውን እናስጠናለን፡፡ ሰብከቱን፣ ዳዊቱን የሚቀድሱትን ካህናት እናስተምራቸዋለን፡፡ እንዲህ እያደረጋችሁ እያስተማራችሁ ምእመናንን እንድታሰናብቱ እያልን ቅዳሜ ቅዳሜ ስሞኑኞችን ሰብስበን እናስተምራቸው ነበር፡፡ አሁን ከጊዜ በኋላ ጥያቄ መመለስ ነው እንጂ ለማስተማር ብዙም አልቻልኩም፡፡ ልጆቼ እየመጡ ጥያቄ ይጠይቁኛል፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ያንን ጥያቄ እመልስላቸዋለሁ:: አሁን ትምህርቱ ኀቡአትን ኪዳኑን ተርጉምልን እያሉ እተረጉምላቸዋለሁ፣ አስተምራቸዋለሁ፤ ያሉት አይረሳም::

አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ትርጓሜ መማር የግድ ያስፈልገዋል ብለው ያምናሉ? ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ የሚከተለው ነው:: ከሆነማ መጽሐፉ የሚለው አንድ ካህን ሙሉ ሐዲሳቱን ማወቅ ይገባዋል ይላል:: በአሁን ጊዜ ባይሆን ወንጌሉን እንኳን አራቱን ወንጌል ማወቅ አለበት:: ይህን ሳያውቅ እንዳይቀድስ ነው የሚከለከል:: ቅዳሴውም ይናገራል:: ፍትሐ ነገሥት ይናገራል:: በዲድስቅልያ ላይ ይናገራል:: ሐዋርያትም ያን ወስነዋል:: እና በኢትዮጵያችን ሰው ጠንክሮ አይማርም እንጂ ትምህርቱ የሚያስፈልጋቸው ለቀሳውስት ነው::

ከፍ ያለ ዕውቀት ቀሳውስቱ እንዲኖራቸው ነበር የሚታዘዘው:: ዛሬ ግን በሀገራችን ቀሳውስቱ እምብዛም አይማሩም:: ድጓውን፣ ቅኔውን፣ ዝማሬ መዋሥዕት፣ አቋቋምን ከፍ ያለ ትምህርት የሚማሩ ደብተሮች ናቸው:: የቀሳውስት መምህር እነሱ ናቸው:: እነዛ ደብተሮቹ ቅዳሴ የማይቀድሱ ሰዎች የቀሳውስት መምህራን ናቸው:: በኢትዮጵያ ኪዳኑንም፣ መስተብቁዑንም፣ ሊጦኑንም እንዲህ አድርጉ እያሉ የሚነግሯቸው እነሱ ናቸው:: ነገር ግን መሆን የሚገባው ዋና መምህር መሆን የሚገባቸው ቀሳውስት ናቸው:: እንዲውም ምእመናን ጥያቄ ሲያቀርቡ መልስ መስጠት የማይችሉ ካህናት በየቦታው እየበረከቱ ነው ይባላል::

በየጊዜው ቀደም ቀደም ያሉ ሰዎች መምህራንም በያሉበት ያስተምሩ ነበር:: ይልቁንም ይህ ችግር የመጣው ከግራኝ ወዲህ ነው:: ግራኝ አሥራ አምስት ዓመት ሙሉ ሀገሩን አጠፋው፣ ቤተ ክርስቲያኅን አቃጠለ፤ ካህኑን ሁሉ ገደለ:: ከዚህ በኋላ እነ ዐፄ ገላውዴዎስ፣ እነ ዐፄ ሚናስ ቤተ ክርስቲያንን ሠሩና ለጊዜው አገልግሎቱ እንዳይታጐል እያሉ ግብረ ዲቁና እየተማሩ ቀሳውስቱ መቀደስ ጀመሩ:: እና በዚያ ጊዜ ብዙ ትምህርት ተማር እንዳይባል፣ ትምህርቱ ቃለ እግዚአብሔሩ በሰፊው ስለሌለ ቤተ ክርስቲያን ሲዘጋ ስለሆነ ቅዳሴው እንዳይታጐልና ሕዝቡ ክርስትና እንዲኖሩ በማለት ያኔ ግብረ ዲቁና እና ቅስና አስተምረው ቶሎ ቶሎ እንዲቀድሱ አደረጉ:: ሁሉም ትንሽ





ግብረ ዲቁና እየተማረ መቀደስ መጣ:: ከፍ ያለ ትምህርት መስፋፋቱ ቀረ:: በኋላም በዚህ ዓይነት ልማድ ሆኖ መጥቷል::

ትምህርት ያስፈልጋል:: ያኔ በማስተምርበት ጊዜ መቼም ቃለ እግዚአብሔርን አውጥቼ ይኸውና ካህናትም እንዲህ ያለ ትምህርት ያስፈልጋችኋል፤ ይሄ ትምህርት እንዲህ ያለ ነው እያልኩ ለካህኑ አስተምራለሁ:: በኢትዮጵያ ደግሞ ክርስቲያኑ ስሙ ነው ክርስቲያን የሚባል እንጂ፣ ክርስቲያንነቱ የጸና አይደለም:: በልማድ ነው ያለው:: ምክንያቱም ምንድነው ክርስቲያን የሚባል ክርስትና ከተነሳ ጀምሮ አድጎ በሚያገባበት ጊዜ በተክሊል አግብቶ ሥጋውን ደሙን እየተቀበለ መኖር አለበት:: ድንገት ኃጢአት ሠርቶ ወይንም ቢሰነካከል እንኳ ንስሐ ገብቶ ሰው ሥጋውን ደሙን መቀበል ነው እንጂ ሥጋውን ደሙን የማይቀበል የኢትዮጵያ ሰው ግን ብቻ ክርስትና ተነስቷል በልጅነቱ እንጂ ከዚህ በኋላ አጥፍቶ ሲያበቃ ተመልሶ ንስሐ አይገባም:: እንደውም ሥጋውን ደሙን የሚቀበል ሰው የለም፣ ካህናቱ ሲቀድሱ ይኖራሉ እንጂ አሁንማ ሰው ሥጋውን ደሙን የሚቀበል አይገኝም::

ይህን ትምህርት በብዙ ዓይነት አስተምረናል ተቀባይ አላገኘንም:: ሰው ሁሉ ያውቃል ትምህርቱን ይሰማል:: አንድ ሰው ሰባት ጊዜም ቢሆን እየወደቀ በንስሐ እየተነሣ ሥጋውን ደሙን መቀበል አለበት እንጂ አንዴ ኃጢአት ሠርቻለሁ ብሎ አንዴ እንደራቀ መቅረት የለበትም:: ምእመናኑን ለምን እንደዚህ ትሆናላችሁ እያልን ብናስተምራቸው ብንላቸው አይሰሙም:: ያው መቼም ሕዝቡ ልማድ አድርጎታል:: ብቻ ክርስቲያን ነኝ እያለ ያወራል:: በቅዳሴ ላይ ፃኡ ሲባሉ ሥጋውን ደሙን የማይቀበለው ሰው ሁሳ በሙሉ ነው መውጣት ያለበት:: አያስቀድስም:: ወንጌሉ እስኪነበብ ድረስ አስቀድሶ ፃኡ ሲባል ሥጋውን ደሙን የማይቀበል ሰው ሁሉ መውጣት ነው ያለበት:: ልማድ የለምና አይወጣም:: ዝም ብሎ ያስቀድሳል እንጂ ፃኡ ዜማው ትዜማለች እንጂ ዜማ ሆኖ ይቀራል እንጂ የሚወጣ የለም:: «ፃኡ ንዑስ ክርስቲያን፣ የክርስቲያን ታናናሾች ሥጋውን ደሙን የማትቀበሉ ሁሉ ውጡ» ተብሎ ነው የሚታወጅ::



www.ethiopianorthodox.org

አንድ ጊዜ የግብጽ ፓትርያርክ አቡነ ቄርሎስ የሚባሉ መጥተው ነበር። በኢታ ቀደሱና ለሰው ሁሉ በሉ ሥጋውን ደሙን ይቀበል አሉ። አይ አይቀበልም አሏቸው። እንግዲያውስ ለምን አስቀደሱ? ሰው ልማድ የለውም አሏቸው። እንግዲያው ለምን ያስቀድሳል ፃኡ ሲባል መውጣት አለበት እንጂ ሙሉ ቅዳሴውን ማስቀደስ የለበትም። ምን ሲል ተቀመጠ በማለት ተናገሩ። ሌላ ጊዜ እናስተምራቸዋለን አባታችን ያልተለመደ ነውና ያንን የቀረበልዎትን ያቀብሉ አሏቸው። የሚል መልስ ሰጥተው ነበር።

*አንዳንድ ምእመናን በልጅነታቸው ሲያስቀድሱ ሲቆርቡ ቆይተው ካደጉ በኋላ ይተዋሉ፤ ለምንድነው የማትቆርቡት፣ በተክሊል የማታገቡት ሲባሉ አይፈቀድም። ቅስፈት ልታስቀስፉን ነው የሚሉም አሉና እርስዎ ምን ይመክሯቸዋል? በማለት ለተጠየቁት ደግሞ፤* እራሳቸው የፍራቻ ምክንያት ያደረጉት ነው። አንድ ክርስቲያን ከሥጋውና ከደሙ መለየት የለበትም። ቀድሞ በተክሊል ተጋቡ ሲባሉ ወላጆቻቸው ደግሞ አይሆንም እኛ ልጃችን አትችልም ይሉ ነበር። ድሮ ተክሊል አድርጎ ሥጋውን ደሙን መቀበል ነበር እንጂ እንደዚህ ዝም ብሎ የሚሄድ አልነበረም። ነገር ግን ሥጋውን ደሙን ዝም ብላችሁ ተክሊል አድርሳችሁ ባትቀበሉም ግዴለም ተብሎ የተጀመረበት ጊዜ አለ። አዲስ አበባ ይህ የተጀመረ ቅድስት ማርያም ነው። ማነው የፊታውራሪ በየነ ልጅ ጸጋዬ የሚባል ሰው የራስ ጌታ ቸውን ልጅ ሲያገባ ሥጋውን ደሙን ሳያቀብሉ ይህን ተክሊሉን ብቻ አድርሰው ሰደዷቸው። ከዛ በኋላ በተለይ አዲስ አበባ እንዲህ ከሆነ ምን አለበት ተብሎ ልማድ ሆነ።

በቃ ይሄን ተክሊሉን እንደቆብ የፎቶ ግራፍ መነሻ አድርገው እስካሁን ድረስ ሥጋውን ደሙን መቀበል ቀርቶ ነበር። አሁን ደግሞ ተከልክሏል ቆርበው በተክሊል ያገባሉ ሲሉ እሰማለሁኝ።

ለአቅመ አዳም ወይም ለአቅመ ሔዋን ስትደርሱ ቁርባኑን ተውት የሚል መጽሐፋዊ ቃል በጭራሽ የለም። አይገኝም። ራሳቸው ምእመናን ይተውታል እንጂ ሰው ሁሉ በልጅነቱ ክርስትና ተነሥቶ





ሥጋውን ደሙን ሲቀበል ከኖረ በኋላ አካለ መጠን ሲያደርስ እንደልቡ ነው። ያፈርስና ዝም ብሎ ትቶ ክርስቲያን ነኝ እያለ ይኖራል። እንጂ ስታድጉ አፍርሱ የሚል ነገር እንዴት ተብሎ ይደረጋል። ይልቁኑ ያጸናል እንጂ እንዴት ይፈርሳል። ተክሊል አድርጎ ሥጋ ወደሙን መቀበል ነው እንጂ ሌላ ነገር አልታዘዘም። ይህን የሚያዙ ካሉ ክርስትና አልገባቸው ማለትኮ ነው።» በማለት እንደመለሱ ይታወሳል።

የመጽሐፍ መምህር ከመሆናቸው ጋር በማያያዝ በጊዜያችን መናፍቃን በቀላል ቋንቋ በማለት አባዝተው መጻሕፍትን እያሠራጩ መሆኑንና እንደውም በመጽሐፍ ቅዱስ «ኢትዮጵያ» የሚለው ቃል እየተለወጠ «ሱዳን» በሚል ስለመተካቱ ሲነገር በታላቅ ቁጭት የሚከተለውን ብለው ነበር።

ነቢያት የተናገሩት፣ ሐዋርያት ያስተማሩት በቀጥታ ይተረጎማል እንጂ ቃሉ አይለወጥም። ሊቃውንት የጻፉትም እንደዚሁ። ሐዋርያት እንዲያውም አራቱ ወንጌል ቃሉ እንዳይሰረዝ አምኒዮስ አውሳብዮስ የሚባሉ ሊቃውንት አንዳንድ ቃሉን ዘሩን ቆጥረው ዘጠኝ ሺሕ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ነው ብለዋል። የወንጌሉን ቃል ብቻ። ሌሎች እንዳያበላሹ በእንዲህ ያለ ቆጥረው መሥመሩን፣ ሐሳቡን፣ ምዕራፉን ጽፈውት ይገኛል። እና ቃሉ ለምን ይለወጣል? መቼም ሰው በገንዘብ እየተለወጠ የመጣውን ሁሉ ይቀበላል። የኢትዮጵያ ሰው የቀደሙት አበዎች ያቆዩትን ትም ህርት አጥብቆ መያዝ አለበት።

ሱዳን አሉት? ምን አገናኝቶት። እንደውም ሱዳን የኢትዮጵያ ግዛት የነበረ አገር ነው። የእኛ ግዛት ነበረ እንጂ እኛ ለእነሱ ልንገዛ አንችልም። መቼም ኢትዮጲስ የካም ሰጣ ነች። ኢትዮጲስ የሚባል የካም ልጅ መጥቶ ነው ያቀናው። ከዛ በኋላ ደግሞ የሴም ልጆች የሕርቃ ልጆች አቅንተዋታል ነው የሚባለው። ስለዚህ ሱዳን የእኛ ግዛት የነበረ ነው እንጂ ምን ሱዳን ያሰኘዋል። በዚህ ዓይነትማ ወደፊትም የበለጠ ጥፋት እንዳይሠራ ትርጉም እንዳይዛባ ሊቃውንት፣ መምህራኑ፣ ጳጳሳቱ ተሰብስበው ኃይለ ቃሉን አወጣጥተው ባጭሩ ለሕዝቡ የሚገባ ነገር መወሰን አለባቸው።



www.ethiopianorthodox.org

የኔታ በአሁኑ ጊዜ ግእዝ ሞቷል፡ አገልግሎት አይሰጥም ስለሚሉ ሰዎችና ግእዝ የአዳም ቋንቋ ስለመሆኑ ተጠይቀው እንደሚከተለው መልስ ሰጥተውበታል:: ሞቷል? የኢትዮጵያ መጻሕፍት በሙሉ በግእዝ ነው ተጽፈው የሚገኙት:: በአማርኛ የተጻፈው በአዲስ አበባ ዛሬ እንጂ በየታሳሳቱ አድባራትና ገዳማት ብትሄዱ በግእዙ የተጻፈ እንዳለ ይገኛል:: መቼ ይሞታል:: ዛሬ ቅኔ የሚማር ሰው የለም:: አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ተጠናች ያችን እየወራ በዛ ምክንያት ሐዲሳትን ትቶታል:: መቼስ የኢትዮጵያ ቋንቋችን ግእዝ ነበረ፡ ግእዝ ነው ቋንቋችን:: አማርኛው በኋላ ጊዜ በዐፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ነው የተነሣው ተብሎ ይነገራል:: በእርሳቸው ጊዜ ነው የተነገረው ይባላል እንጂ ግእዝ ነው ቋንቋችን የነበረ:: ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከአሁን ድረስ አለ:: ሰው ሁሉ ግእዝ መማር ሲገባው ግእዝ የሚማር የለም:: ያው የቅኔ ተማሪዎች አልፈው አልፈው እየሄዱ ይማራሉ:: ሌላው ሰውም አይሰማውም:: ትግሬም ግእዝ ይናገራል:: በትምህርት ስለማይቃና እንደው ወደ ጉሮሮው እየሄደ አያስተካክለውም:: አሁንም ሆነ ወደፊት ቤተ ክርስቲያን ግእዝን እየተገለገለችበት እንዴት ይሞታል::

መጀመሪያ ዓለም የተፈጠረበት ቋንቋው ዕብራይስጥ ነው የሚባለው:: የሁሉ ቋንቋ ዕብራይስጥ ነበር:: ነገር ግን ባቢሎን በሚባል አገር አንድ ናምሩድ የሚባል የካም ልጅ ያንጊዜ ንጉሥ ከዚያ ላይ ሆኖ የውኃ ፏፏቴ እየሰደደ ዘመዶቻችንን ያጠፋው አምላክ ይኸው ላችሁ ግንብ ሠርተን ወጥተን እንገለዋለን ብለው ባቢሎን ከሚባል ላይ ግንብ ሠሩ:: ግንብ ሲሠሩ አርባ አምስት ሺህ የሚሆን አቀበት ከወጡ በኋላ ሥላሴ አይተው ሰዎች ኃጢአት እንዳይበዛ ባቸውና ከፈጣሪያቸው ተጣልተው ሳይለያዩ እኒህ ሰዎች እንዲህ ያለውን ሥራ መሥራት የጀመሩ በቋንቋ አንድ ስለሆኑ አይደለ ለምን? ኑ በቋንቋ እንለያያቸው አሉና ሰባ አንድ ቋንቋ አመጡባቸው:: በዚያን ጊዜ ቀድሞ የሚያውቁት ቋንቋ ጠፋባቸው:: ተለያዩና ግንብ የሚገነቡት <ድንጋይ አምጣ> ሲለው ጭቃ ያመጣለታል:: <ጭቃ አምጣ> ሲለው





ድንጋይ ያመጣለታል:: አልሳካላቸው አለ:: በቋንቋ ተለያዩ:: ሰባ አንዱን ቋንቋ ለሦስቱ ነገድ ተካፍለውታል:: ለነገደ ሴም አሥራ አምስት፣ ነገደ ያፌት ሠላሳ ሁለት፣ ለነገደ ካም ሃያ አምስት ተካፍለውታል ይባላል:: በዚያን ጊዜ ነው እንግዲህ ግእዝ የሚባለው የተጠገኘው:: ናምሩድ የሚባል የካም የልጅ ልጅ ነው:: ሙሴ እንኳን ምን አለው እንደ ናምሩድ ያለ አርበኛ የለም ነው ያለው::» ሲሉ መልስ ሰጥተዋል::

ሌላው የማይረሳው ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትርጓሜ ቤቶች ተጠይቀው የሰጡት መልስ ነው::

መቼም አንድ ምስጢር ሆኖ ሳለ፣ አንዳንድ ሰው መለያየት አይቀርም:: ትንሽ ትንሽ ነው የሚለያየው፤ መቼም የሐዲሳቱን አንድ መምህር ናቸው ያስተማሩት ጐንደር ላይ መምህር ወልደ አብ ወልደ ሚካኤል የሚባሉ አሥራ ሰባት ሰዎች አስተምረዋል:: ከእነዚህ ከአሥራ ሰባቱ መምህራን ግማሾቹን ሱዳን አርዷቸዋል /ደርቡሾች/ ይባላል:: የተረፉት ስድስቱ የርሳቸው ተማሪዎች

፩ኛ. አለቃ ካሣዬ ይባላሉ:: በዚህ በደሴ ግድሞሽ፣ ግሽን ግድሞሽ እንአለቃ መንክር የሚባሉትን ያስተማሩ ናቸው::

፪ኛ. በትግሬ ቁህ በሚባል ገዳም ያስተማሩ መምህር ወልደ ሩፋኤል የሚባሉ የሳይንት ሰው ነበሩ::

፫ኛ. በሰሜን በደሴ ማርያም አለቃ ገብረ ማርያም የሚባሉ አስተምረዋል::

፬ኛ. መምህር ወልደ ሚካኤል ዜና ማርቆስ በሩ ሂደው አስተምረዋል::

፭ኛ. መምህር ወልደ ጊዮርጊስ የሚባሉ እንጦጦ ራጉኤል ሆነው ሃምሳ ዓመት አስተምረዋል::

፮ኛ. አለቃ ኀሩይ የሚባሉ የእነ ሊቀ ሊቃውንት መሐሪ መምህር ነበሩ:: በኋላ ቤተ መንግሥት የሚባለው ጃንሆይ እልፍኝ ቤት ነበር የሚኖሩት:: የአለቃ አየለ መምህር ናቸው:: እነዚህ ስድስቱ ናቸው የመጻሕፍት ቤት መሠረቶች::

የእነዚህ መምህራቸው ወልደ አብ ወልደ ሚካኤል ይባላሉ:: ያስተማሩት ጐንደር ግምጃ ቤት ሁነው ነው:: ያስተማሩበት ዘመን



www.ethiopianorthodox.org

ሱዳን መጥቶ ጉንደርን ባቃጠለበት ጊዜ ነው:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው:: ይኸው ነው እንግዲህ:: እና እነዚያ ያልኳችሁ ሰዎች የርሳቸው ተማሪዎች ናቸው:: ወልደ አብ የሚባሉ የመንዝ ሰው ነበሩ:: እሳቸው አራቱን ጉባኤ አስተምረዋል ጉንደር ላይ:: ሰውዬው የአራት መቶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ካህናት ነበሩ:: እያ በሉ እያጠጡ ብሉዩን፣ ሐዲሱን፣ ዚቁን፣ መጽሐፈ መነኩሳትን አስ ተምረዋል::

ከእርሳቸው በፊት ትርጓሜ አለ:: እንዲህ አድርጉ እንደሳቸው ሰብስቦ ያስተማረ ግን የለም::

ከላይ ከተጠቀሱት ጉዳዮች ሌላ የኔታ ስለ ቅባቶች ትምህርት እንዲህ ይሉ ነበር::

ወልድ በተ ፀነሰ ጊዜ ይሄውና አርባ ቀን ሲሆነው ከመንፈስ ቅዱስ ተወልዶ የባሕርይ ልጅ ሆነ እያሉ ይቀልዳሉ:: እኛ ግን እሱ የባሕርይ አምላክ ነው:: የተዋሐደውን የለበሰውን ሥጋ ራሱ አከበረው እንጂ መንፈስ ቅዱስን አከባሪ አይሻም፤ ራሱ የተዋሐደውን ሥጋ በተዋሕዶ አከበረ እንጂ በቅባት አልከበረም እንላለን:: እነሱ በቅባት ከበረ ይላሉ:: እዎ ካልተመለሱ መለየት አለባቸው::

ታዲያ የነሱ አንድ መምህራቸው ኤውስጣቴዎስ ይባላል:: ሳንኳ ጊ ዮርጊስ የሚባል የሜጫ ሰው ነው:: ምን ይላሉ:: ታላቁ ኤውስጣቴዎስ ሃይማኖታቸው ጸጋ፣ ቅባት ነው እያሉ ያስወራሉ:: አውቀው ነው እንጂ የራሳቸው መምህር መምህራኑ ስሙን አውጥተውለታል:: መና ፍቅ ኤውስጣቴዎስ ቆረንጭ ተክለ ሃይማኖት ይሏቸዋል:: ያንን የጸጋ ውን መምህር ቆረንጭ ተክለሃይማኖት የቅባቱን ጋዝዖ ኤውስጣቴዎስ ብለውታል:: እና እነሱ ካፈርኩ አይመልሰኝ ብለው ይለፋሉ እንጂ ቃሉ ትንሽ ነገር ነው:: ይህ መርጡለ ማርያም ብዙው የተዋሕዶ ሀገር ነበር:: ዛሬ መምህራኑ አልቀዋል:: እነ መምህር ፊላታዎስ፣ እነ ቄስ ገበዝ ደሳለኝ፣ እነ መምህር ዘውዱ የሚባሉ የተዋሕዶ ታላላቅ መም ህራን ነበሩ ሞተዋል::





በመምህርነታቸውና በብፅዕናቸው ስለሚታወቁት ተማሪያቸው አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ማንነት የተናገሩት ደግሞ የሚከተለው ነበር::

አቡነ ጎርጎርዮስ ከሁሉ ሰው በላይ ንባብ አዋቂ ናቸው:: መቼም ትርጓሜውን በአንድ ጊዜ ግልጽ ነው የሚያደርጉት:: ባሕታዊ ነበሩ:: ያን ጊዜ መቼስ ልብሳቸው ቆዳ ነው:: ባሕታዊ ሆነው ነበር የሚኖሩ:: ሦስት ዓመት ከዚህ ሃገር ተቀምጠው በሦስት ዓመት ሐዲሳትን በሙሉ ተምረው ፈጽመውታል:: በኋላ እኔ ዘንድ ቆጭ ደብሉ ወይ ደግሞ ደብረ ሊባኖስ ይቀመጡ አልኳቸው:: መምህር ወልደ ሚካኤል እኚህ ሰው እዚህ ቢቀመጡልን እንደዚህ ዓይነት ሰው እንዴት ይሄዳል ብለው ይፈልጓቸው ነበር:: አልተቀመጡላቸውም እንጂ::

እነዚህን ሁሉ ሊቃነ ጳጳሳት ያፈሩ፣ እጅግ በርካታ ታላላቅ መምህራንን ያወጡ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ይህን ቃለመጠይቅ ባደረጉበት ወቅት በዕድሜ ዘመናቸው ፍጻሜ ዓይናቸው ደክሞ፤ ክንዳቸው ዝሎ፣ ጉልበታቸው ልሞ አልጋ ላይ ውለዋል::

ይሁም ሆኖ እርጅና፣ ጤና ማጣት፣ የጉልበታቸው መድከምና የአቅማቸው ማነስ ከስልሣ ዓመታት በላይ የዘለቁበትን አገልግሎት ከማ ስተማር ሥራቸው አላገዳቸውም:: ብርቱ ናቸው:: ተስፋቸውና የእም ነታቸው ጥንካሬ እንዳለ ነበር:: ለቤተ ክርስቲያን ያላቸው ምኞት የማ ስተማር ፍላጐትና ዓላማቸው ለሥራ ታጥቆ እንደተነሣ አፍላ ወጣት ትኩስ ነው፤ ጎና አልተነካም ነበር::

አልጋቸው ላይ ሆነው እርጅና ታግሶ ባሳሸነፈው ጥርት ባለ አን ደበታቸው ከመምህራንና ደቀ መዛሙርት ለሚመጣ ጥያቄ መልስ ይሰጣሉ፤ ያብራራሉ፣ ያስረዳሉ:: የመጻሕፍት ቤት ተማሪዎቻቸውን ወኪል መምህር አስቀምጠው ያስተምራሉ:: ጉባኤያቸው እንደ ደመቀ ነበር:: የሰውቀታቸውን አድማስ የዕድሜ ብዛት ግርጃ ሆኖ አልከለከ ለውም:: ከሰባና ሰማንያ ዓመታት በፊት የሆነን ነገር አስታውሶ ለመ ግለጽ መምህር ገብረ ሕይወትን እርጅና አላገዳቸውም:: የማስታወስ ችሎታቸው እንዳለ ነበር::



www.ethiopianorthodox.org

እኚህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ የወር ደመወዛቸው ብር ሁለት መቶ ብቻ ነው። ሌላ ተጨማሪ መተዳደሪያ የሚሆን ገቢ የላቸውም። ለምግባቸው፣ ለልብሳቸውና ለሌሎችም አስፈላጊ ጉዳዮች የወጪ ቋታቸው ይችው የወር ደመወዛቸው ነች። ከዚችው ላይ ተማሪዎቻቸውን ለሚያስተምሩ ወኪል መምህራቸው ይደጉማሉ። ሲታመሙ ለመታከሚያና ለመድኃኒት መግዣ ያወጣሉ። ምግባቸውን ለሚያሰና ዱላቸው ልብሶቻቸውን ለሚያጥቡላቸው ወጪ ሆኖ የሚከፈለው ከዚሁ በወር ከሚያገኙት በጣም አነስተኛ ክፍያ ነበር።

እንዲህም ሆኖ ግን ሐሳባቸው ትኩረታቸው ጨዋታቸው ሁሉ ስለ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ነው።

መምህር ገብረ ሕይወት ሰይፉ ጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ዐረፉ። ሥርዓተ ቀብራቸውም ብፁዕ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖትን ጨምሮ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት ጥር ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተፈጽሟል።

*<u>ምንጭ</u>፡- ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ሰኔ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም*





# መምህር ጥበቡ አስናቀ

/፲፱፻፲፩ - ፲፱፻፺፯/

## እስራት እና እሳት ያልበገራቸው መምህር

*በተሰብ ያሬድ ገ/መድኅን*



*«የተማርኩት በእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ ነው»*

መምህር ጥበቡ አስናቀ ሃብተ ሚካኤል የተወለዱት ታኅሣሥ ፲፫ ቀን ፲፱፻፲፩ ዓ.ም በወቅቱ መንዝ አውራጃ /ሰሜን ሸዋ/ ልዩ ስሙ ግሺ በተባለ ቦታ ነው። ወላጆቻቸው ሻለቃ አስናቀ ሀብተ ሚካኤል እና ወ/ሮ ልኬለሽ አስምሬ ይባላሉ።

የመምህር ጥበቡ ወላጆች በተለይም አባታቸው በቤተ መንግሥት በአገር አስተዳደር ሥራ የኖሩ በመሆናቸው ልጃቸውም እንደሳቸው በቤተ መንግሥት እንዲሠሩ ነበር የሚፈልጉት። ፈቃደ እግዚአብሔር ደግሞ ሌላ ሆነ።

መምህር ጥበቡ አስናቀ ስለ አጠቃላይ ሕይወታቸው በራሳቸው የቀረበውን ገለጻ እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል።



www.ethiopianorthodox.org

እኚህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ የወር ደመወዛቸው ብር ሁለት መቶ ብቻ ነው:: ሌላ ተጨማሪ መተዳደሪያ የሚሆን ገቢ የላቸውም:: ለምግባቸው፣ ለልብሳቸውና ለሌሎችም አስፈላጊ ጉዳዮች የወጪ ቋታቸው ይችው የወር ደመወዛቸው ነች:: ከዚችው ላይ ተማሪዎቻቸውን ለሚያስተምሩ ወኪል መምህራቸው ይደጉማሉ:: ሲታመሙ ለመታከሚያና ለመድኃኒት መግዣ ያወጣሉ:: ምግባቸውን ለሚያበስና ዱላቸው ልብሶቻቸውን ለሚያጥቡላቸው ወጪ ሆኖ የሚከፈለው ከዚሁ በወር ከሚያገኙት በጣም አነስተኛ ክፍያ ነበር::

እንዲህም ሆኖ ግን ሐሳባቸው ትኩረታቸው ጨዋታቸው ሁሉ ስለ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ነው::

መምህር ገብረ ሕይወት ሰይፉ ጥር ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ዐረፉ:: ሥርዓተ ቀብራቸውም ብፁዕ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖትን ጨምሮ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት ጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተፈጽሟል::

__ምንጭ__:- *ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ሰኔ ፲፱፻፺፫ ዓ.ም*





# መምህር ጥበቡ አስናቀ

/፲፱፻፲፩ – ፲፱፻፺፯/

## እስራት እና እሳት ያልበገራቸው መምህር

*በቀሲስ ያሬድ ገ/መድኅን*



*«የተማርኩት በእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ ነው»*

መምህር ጥበቡ አስናቀ ሃብተ ሚካኤል የተወለዱት ታኅሣሥ ፲፫ ቀን ፲፱፻፲፩ ዓ.ም በወቅቱ መንዝ አውራጃ /ሰሜን ሸዋ/ ልዩ ስሙ ግሼ በተባለ ቦታ ነው:: ወላጆቻቸው ሻለቃ አስናቀ ሀብተ ሚካኤል እና ወ/ሮ ልኬለሽ አስምሬ ይባላሉ::

የመምህር ጥበቡ ወላጆች በተለይም አባታቸው በቤተ መንግሥት በአገር አስተዳደር ሥራ የኖሩ በመሆናቸው ልጃቸውም እንደሳቸው በቤተ መንግሥት እንዲሠሩ ነበር የሚፈልጉት:: ፈቃደ እግዚአብሔር ደግሞ ሌላ ሆነ::

መምህር ጥበቡ አስናቀ ስለ አጠቃላይ ሕይወታቸው በራሳቸው የቀረበውን ገለጻ እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል::



www.ethiopianorthodox.org

## የትምህርት ጅማሬ

«እኔ ወደ አብነት ት/ቤት የገባሁበት ምክንያት በእግዚአብሔር ፍቅር ነው እንጂ ቤተሰቦቼ መርተውኝ ወይም አስገድደውኝ አይደለም። ቤተሰቦቼ ወደ ትምህርት ቤት እንዳልሔድ ሦስት አራት ጊዜ አስረው ከቤት አስቀርተውኛል። ወደ ቤተ መንግሥት እንጂ ወደ አብነት ት/ቤት እንድሔድ አይፈቅዱልኝም ነበር። ምክንያቱም ትውልዳችን አባቴም ሆነ ዘመዶቻችን የሚያገለግሉት በቤተ መንግሥት ስለሆነ፣ እኔም በቤተ መንግሥት አገልግዬ ለመሾም እንጂ ትምህርት ለመማር አይፈቅዱም ነበር።

እኔ ግን ከልጅነቴ ጀምሮ ሐሳቤና ምኞቴ ሁሉ ይህንን ትምህርት ለመማር ነው። ፊደልና ንባብ ብቻ ስቆጥር ከቤተሰቦቼ እስከ አሥራ አምስት ዓመቴ ድረስ ቆይቻለሁ። ይኸውም ቤተሰቦቼ እንዳልማር እየከለከሉኝ፣ ሥራ እያሠሩኝ፣ ከብት እያስጠበቁኝ ነው። ከዚያ በኋላ አሥራ አምስት ዓመት ሲሞላኝ ከቤተሰቦቼ ጠፍቼ ለመማር ሔድኩ።

በአሥራ አምስት ዓመቴ ከቤተሰቦቼ ተለይቼ በወሎና ግሼ መካከል አርበንታይ ሚካኤል ከሚባል ደብር አለቃ ደስታ ከሚባሉ የሰድሜ ባዕለጸጋ ከሆኑ ታላቅ መምህር ዘንድ ንባብ፣ ዳዊት፣ ሰዓታት፣ ጸሎት ተማርኩ። ከዚያ ደሴ ሐይቅ እስጢፋኖስ አካባቢ መድኃኔዓለም ደብር ከአለቃ ገብረ ሕይወት ዘንድ ጾመ ድጓ ምዕራፍ ለሦስት ዓመታት፣ ከዚያ ቀጥሎ ላስታ ላሊበላ ከአለቃ ምሕረቱ የአቋቋምና ቅኔ መመህር ዘንድ ቅኔ ተማርኩ። እዚያው ዓመደ ወርቅ ቂርቆስ አጠገብ ከአለቃ ብሉይ ውቤ ቅኔ፣ ቅዳሴ ማርያም፣ ዳዊት፣ እንዲሁም በዚያው አካባቢ አለቃ አወቀ ከሚባሉ መምህር ቅኔ ከነአገባቡ ተምሬ አስመስክሬ ያለሁ። ሰሜን ጎንደር አውራጃ ቅዱስ ያሬድ ተሰወረበት ከሚባልበት አጠገብ የድጓና አቋቋም መምህርት ከሆኑት ከመምህር ኃይሉ ዘንድ ሐዲሳት፣ ሦስት ዓመት ከዚያ ተመልሼ ቂርቆስ ዓመደ ወርቅ አካባቢ ከአለቃ ታምራት ዘንድ አምስት ዓመት አቋቋም ዝማሬ መዋሥዕት ተምሬአለሁ።





## እየተማሩ ማስተማር

ከዚያ ተነሥቼ በጌምድር በመሔድ መካነ ኢየሱስ ከሚገኙት ከታላቁ ሊቃ ከመምህር ገብረ ጊዮርጊስ ፍትሐ ነገሥትና ቅኔ ሦስት ዓመት ተምሬያለሁ። በእነዚህ በምንማርባቸው ወራት ቤቴ ሦስት ጊዜ ተቃጥሏል። ሁለት ጊዜ ሲቃጠል መጻሕፍቶቼ ድነውልኝ ነበር። በሦስተኛው ጊዜ ግን መካነ ኢየሱስ ሳለሁ ዓመት ሙሉ በእጄ የጻፍኩት ፍትሐ ነገሥት ትርጓሜ፣ የሐዲሳቱም ትርጓሜ መጽሐፍ ሌሎችም መጽሐፎቼ፣ የጽሕፈት መሣሪያዎቼ፣ የማስቀጽባቸው ተማሪዎች መሣሪያዎች ሁሉ ተቃጥለውብኛል። በዚህ ጊዜ የመምህራችን ቤት በተማሪዎች መኖሪያ ቤት መካከል ነበር። ጠዋት ጠዋት መምህራችን ጉባኤ አያስታጉሉም። የብዙ ተማሪዎች ቤት ሲቃጠል በመካከል የነበረውን የመምህራችንን ቤት እሳት ምንም ሳይነካው አልፎ የዕቃ ቤቱን አቃጥሎታል። ይህ የማይረሳኝ የተማሪነት ዘመኔ ተአምራት ነው። በሕይወቴ ብዙ ችግር ገጥሞኛል። ገንዘብ ቸግሮኛል። ታምሜ ጤና አጥቼ ተቸግሬአለሁ። ሆኖም በጣም ያዘንኩበት መጻሕፍቴ በተቃጠሉብኝ ጊዜ ነው።

ዮሐንስ በበረሃ እናቱ ኤልሳቤጥ ሞታበት ብቻውን ተቀምጦ ሳለ እንዳገኘው ኃዘን ያለ ኀዘን ነው ያገኘኝ። ከዚያ ከበጌምድር ወደ ደሴ ሔጄ እንደገና ገንዘብና ደብተር ሰብስቤ ተመልሼ መካነ ኢየሱስ ሔድኩና ፍትሐ ነገሥት ትርጓሜን መጻፍ ጀመርኩ። ሰዎቹ በጣም ተደነቁ። ያንን የመምህሬን መጽሐፍ እየገለበጥኩ በምጽፍበት ጊዜ ሌሊት ይጽፋል ተብሎ ለመምህር ተነገራቸው። መምህሬም መጽሐፉን ወሰዱብኝ። አዘንኩ። እንደገና ወደ ገጠር ወጥቼ መጽሐፍ ስፈልግ ከእኛ ጋራ የተማረ አንድ መምህር ታሞ ደብረ ታቦር ሐኪም ቤት ገብቶ ነበር። መጽሐፉ ከእርሱ ዘንድ መኖሩን አውቀዋለሁና ወንድሜ ፍትሐ ነገሥቴ ተቃጥሎብኛል፤ የአንተን ስጠኝ ልጻፍበት ብዬ ጠየኩት። እሱም አይ እኔ ከሞትኩ በኋላ ነው እንጂ ዓይኔ እያየ አልሰጥዎትም አለኝና ተመለስኩ።



www.ethiopianorthodox.org

በዚያ በበጌ ምድር አካባቢ ሕዝቡ ተሰብስቦ እንዳስተምር ጠይቀውኝ ተቀጥሬ ማስተማር ጀመርኩ:: ያን ጊዜ ያንን መጽሐፍ ሳጠያይቅ አገኘሁትና ጽሑፉን በሰኔ ሚካኤል ጀምሬ የኅዳር ሚካኤል ዕለት ጨረስኩት::

ከዚህ በኋላ ጎንደር ሔድኩ:: ጊዜው ከቃና ዘገሊላ በኋላ በጥር ወር ውስጥ ነበር:: ተማሪዎቼን የጻፍኩትን ፍትሐ ነገሥቴን አሸክሜ ጎንደር ገብቼ ባደርኩበት ሌሊት በሕልሜ «ሽምብራ እሸት በእጄ ይዤ ሕዝቡ ሁሉ እየተሻማ ሲበላት» አየሁ:: ያየሁትን ሀልም እንግዲህ ይቺን ሐዲሴን ሊቃውንት ሊማሯት ነው ብዬ ራሴ ፈታሁት:: ወዲያው ዘጠኝ ሊቃውንት ሁሉም የአቋቋም፣ የድጓ፣ የቅኔ መምህራን ናቸው፤ ከእኔ ዘንድ ገብተው ወንጌል መማር ጀመሩ:: ወንበር የዘረጋሁት ጎንደር በብይ እግዚእ ኪዳነ ምሕረት ደብር ነው::

እኔም እያስተማርኩ ከአለቃ ወልደ ሰንበት ዳዊትና ፍትሐ ነገሥት ለሁለተኛ ጊዜ ተማርኩ:: ሐዲሳቱን እያስተማርኩ ግምጃ ቤት ከመምህር ክፍሌ ዘንድ እንደገና ሐዲሳቱን ከልሼ አዘጋጅቼ ከእሳቸው የምስክር ደብዳቤዬን ተቀበልኩና የአራቱ ጉባኤያት መምህር ከሆኑት ከአለቃ አየለ ዘንድ ገባሁ:: ከእሳቸው ዘንድ ብሉያቱን በሚገባ ተምሬ በመምህርነት ተመረቅሁ::

ከዚያ በኋላ የሔድኩት ዋልድባ ነው:: ዋልድባ ዳልሻ ኪዳነ ምሕረት በመምህር ወልደ ትንሣኤ እጅ ምንኩስና ተቀበልኩና ከዚያ ተመልሼ ጎንደር አባጃሌ ተክለ ሃይማኖት ተቀምጬ ሐዲሳቱን እያስተማርኩ፣ መድኃኔዓለም እየተመላለስኩ ብሉያቱን አኼድ ነበር:: ሆኖም ከመነኮስኩ በኋላ ከከተማ መቀመጥ የሚሆን አይደለምና ዋልድባ ገዳም ተመልሼ ሔድኩ:: በገዳሙ ብሉያትና ሐዲሳቱን የሚማርልኝ ባጣሁ ጊዜ ከገዳሙ ደብዳቤ ተጽፈልኝና ደብረ ዓባይ ሔድኩ:: እዚያ እንደደረስኩ ከአድራሾቹ ወንበር ባይኖራቸውም መምህራን ናቸው፣ ከእነሱ መጀመሪያ ቅዳሴውን በግእዝ ስድስት ጊዜ ዘለቅሁትና ዘሩን ከንጉባኡ ከነዜማው ያዝኩት:: ከዚያም ከመምህር ገብሬ ኪዳን የቅዳሴ መምህሩ ዘንድ ገብቼ ሦስት ጊዜ በዕዝልም በግእዝም ዘልቄ አዘጋጀሁና





እዚያው ማስተማር ጀመርኩ:: ከደብረ ዓባይ አስመስክሬ በመምህርነት ከተመረቅሁ በኋላ ተመልሼ ዋልድባ ዳልሻ ኪዳነ ምሕረት ቅዳሴ ብቻ ሦስት ዓመት አስተማርኩ:: በአራተኛው ዓመት ላይ ታመምኩና ወደ አዲስ አበበ መጥቼ ጥር ፩ ቀን ፲፱፻፶፭ ዓ.ም ከቅዱስ ፓትርያርኩ ግቢ ገባሁ:: በቅዱስ ፓትርያርኩ /ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ/ ፈቃድ ታክሜ እዚያው እንድቀር ተደረገ::

## ሰፊው የመምህርነት ዘመን

አዲስ አበባ በቅዱስ ፓትርያርኩ ግቢ ባዐቢይ ጾም መጽሐፈ ኢሳይያስ፣ መዝሙር ዳዊት፣ ወንጌል ሳስተምር ቆየሁ:: በዓመቱ ቀጨኔ መድኃኔዓለም መጻሕፍተ ብሉያት፣ ሐዲሳትና ፍትሐ ነገሥት እንዳስተምር በ፲፱፻፶፮ ዓ.ም ተመደብኩ:: ሹመት የሚባል ነገር አልፈልግም ብዬ ለቅዱስ ፓትርያርኩ ተናግሬ ነበር:: ሹመት የማይፈልጉ ከሆነ ተብሎ በ፲፱፻፶፱ ዓ.ም በንጉሠ ነገሥት ሀዒ ኃይለ ሥላሴ ትእዛዝ በደብዳቤ ደብረ ሊባኖስ ገዳም መጥቼ እስከ ዛሬ /፲፱፻፶፰/ ድረስ መጻሕፍተ ብሉያቱን፣ ሐዲሳቱን፣ ፍትሐ ነገሥቱን እንዲሁም ቅዳሴውን በትርጓሜ እያስተማርኩ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ደቀ መዛሙርት አውጥቻለሁ:: ወንበር ተክዬ ማስተማር የጀመርኩት በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ነው:: በጠቅላላ ሃምሳ ሦስት ዓመት በመምህርነት ቆይቻለሁ:: ማስተማር ከሁሉ በላይ መሆኑን ማንም ያውቀዋል:: መምህርነት ከሥራ ሁሉ የበለጠ በዓለም የተወደደ ተግባር ነው::

## ፈተናና ጽናት

በተማሪነትም ሆነ በማስተምርበት ዘመን የገጠመኝ ፈተና ብዙ ነው:: ምክንያቱም እኔ የምኖረው በብሕትውና ነው:: እንደገለጽኩትና መጀመሪያ ትምህርት ለመማር ስሔድ ቤተሰቦቼ ተቃውመውአስረውኛል:: እኛ ሐሳባችን ልጃችን ለቤተ መንግሥት ሥራ እንጂ ለቤተ ክህነት አይደለም በማለት ወደ ትምህርቱ እንዳልገባ ይከለክሉኝ ነበር:: የተማርኩት በእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

ትምህርት ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ መምህር እስከምሆንበት ድረስ የገጠመኝ ብዙ ፈተና አለ። ከልጅነቴ ጀምሮ ምኞቴ መማርና መምህር መሆን ይሁን እንጂ በልቡናዬ ይወጣና ይወርድ የነበረው ሐሳቤ ሁሉ ምናኔ ነው። ስማርም ሆነ ሳስተምር ዘወትር የማስበው ወደ እግዚአብሔር መሆንን ነው። ዘላለማዊውን የማያልፈውን ዓለም መንግሥት ሰማያትን ብቻ ነበር የማስበው። አባቶቼ የሠሩትን ሥራ፣ አባቶቼ የገቡበትን ቦታ ነው እንጂ የዚህን ዓለም ተድላና ደስታ ምንም አላስብም። ደስ አያሰኘኝም ነበር።

በትምህርት ቤት ሳለሁ ምናናን እወድና እፈልግ ስለነበር ተባሕትዎ እይዝ ነበር። አስቀድሜ በጠቀስኩት ጎንደር በሰሜን አውራጃ ሳለሁ በሰሜን ቆላ አንድ የበቃ ባሕታዊ ነበር። እሱ ዘንድ ሔጄ አባክህን የምዘጋበት ሱባኤ የምይዝበት ቦታ ስጠኝ አልኩት። ወቅቱ ፍልሰታ ነውና እሺ አለኝ። ይዞኝ ሔዶ በገደል መካከል ባለ ዋሻ ውስጥ አስገብቶ አስቀመጠኝ። በቀን አንድ ጊዜ ማታ በአሥራ ሁለት ሰዓት ምግብ በመዳፌ ልክ የምትሆን ቂጣ ውኃ በትንሽ ቀርቀሮ ያመጣል። እሷን እየተመገብኩ ስጸልይ ስወድቅ ስነሣ በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት ቆየሁ። አንድ ቀን እንደዚሁ የብራና ድርሳነ ሚካኤል ዘርግቼ ስደግም ጥቁር እባብ መጣና መካከሉ ላይ ተጋደመበት። እንዴት ላድርገው? እንዳልነካው ነገር ሊመጣ ነው። እሱን ትቼ ያለ ማቋረጥ በቃሌ መልክአ ሚካኤል እደግም ጀመር። ዓይኔን ከለል አድርጌ ስደግም ቆየሁና ገለጥ ባደርገው እባቡ ጠፍቷል። በዚህ ሱባኤ ሌላም መከራ አግኝቶኛል።

ሱባኤው ሊፈጸም በአሥራ አምስተኛው ቀን እዚያው ዋሻ ውስጥ እንደ ፈረስ ግልቢያ ኮቴ ድምጽ እያሰማ መጣና የዋሻውን መግቢያ በር ግጥም አድርጎ ያዘው። ያን ጊዜ በጣም ደነገጥኩ። ሰውነቴን ላብ አሰመጠኝ። የማደርገው ነገር ቸገረኝ። በቃሌ እየደገምኩ እንዳልጸልይ አንደበቴን ያዘው። ከንባብ ስግደት እንደሚበልጥ አውቃለሁና ያለማቋረጥ ቶሎ ቶሎ ስሰግድ እልም ብሎ ጠፋ፤ ሔደ። በማግሥቱ ያ ባሕታዊ ወደ እኔ መጣና «እንዴት አደርክ? ዛሬ ሌሊት መጥቼ ነበር።



ፍሬ ሊቃውንት

አይዞህ እንዳትፈራ» አለኝ። ወዲያው ተደወለ። ሌሊት ሔጄ ዋዜማ ቆሜ አደርኩ። ቀኑን ውዬ ከቅዳሴ በኋላ እጅግ በጣም አመመኝ። እዚያ ባሕታዊ ቤት ሔጄ ወደቅሁ። ወደላይም ወደታችም የሚለኝ ደም ነው። አሥራ አምስት ቀን ባሕታዊው ጠበል እያጠመቀ አስታመመኝ። በመጨረሻው ሰውነቴ መለስ አለልኝና ተሻለኝ። እኔም ባሕታዊውን ሐሳቤ ሁሉ ምነና ነው ስለው፤ አንተ ሥራህ ‘ማስተማር ብቻ ነው በሰላም ሒድ በማለት አሰናበቱኝና በጌምድር ሔጄ ማስተማር ቀጠልኩ። ስለዚህ ምነናውንም ሆነ መምህርነቱን በብዙ ድካም በሱባኤ ነው ያገኘሁት። በሕይወቴ ሁሉ የሚያጋጥመኝ ችግር የፈተና መሆኑን አውቄ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ እንጂ አልተሳቀቅኩም። ለቁም ነገር የሚበቃ ሰው ፈተና እንደሚያጋጥመው አውቃለሁ። ታዲያ እግዚአብሔርም በቸርነቱ ፈተናውን እያሳለፈልኝ ለመምህርነት አብቅቶ ይኸን ያህል ዘመን ለማስተማር ቻልኩ። በማለት ረጅሙን የሕይወት ዘመን ባጭሩ አቅርበውታል።

መምህር ጥበቡ አስናቀ ዲቁና አዲስ አበባ ቅድስት ማርያም ከግብጻዊው ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ፤ ቅስና አክሱም ብፁዕ አቡነ ማቃርዮስ ከሚባሉ ጳጳስ፤ ምንኩስና ዋልድባ ጻልሻ ኪዳነ ምሕረት ከመምህር ወልደ ትንሣኤ፤ ቁምስና አዲስ አበባ ከአቡነ ባስልዮስ ተቀብለዋል።

በረዥም የመምህርነት ዘመናቸው ያፈሯቸውን ደቀመዛሙርት ብዛት ያስታውሷቸው እንደሆን ጠይቀናቸው ቆጥሬ የማልዘልቃቸው እጅግ ብዙ ደቀመዛሙርት አፍርቻለሁ። ሁሉም ለቁምነገር ለመምህርነት ለከፍተኛ ደረጃ የበቁ ናቸው። ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ፣ አቡነ እንድርያስ፣ ብፁዕ አቡነ ዕንባቆም /ጳባቴ ተክለ ሐዋርያት/፣ ብፁዕ አቡነ ቀሌምንጦስ /ጸባቴ ክፍለ ዮሐንስ/ ሁሉ ከእኔ ዘንድ ተምረዋል አሉ።

መምህር ጥበቡ በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ መጽሐፍ ቅዱስ እየታተመ እንደሚሠራጭና የተወሰኑትን በተማሪዎቻቸውና አንዳንድ ምእመናን አማካኝነት አምጥተው መመልከታቸውን ይገልጻሉ። የሚያገኟቸው



www.ethiopianorthodox.org

የትርጓሜ መምህራንም ትርጉማቸውና መልእክታቸው እየተዛባ የተዘጋጁ የመጽሐፍ ቅዱስ ኅትመቶችን ተመልክተው ቅሬታቸውን እንደገለጹላቸው ይናገራሉ። ይኸንኑ አስመልክቶ የሰጡት ሐሳብ እንደሚከተለው ቀርቧል።

## የተዛቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ኅትመቶች

«ገንዘብ ስላላቸው ሕዝቡ በቀላሉ እንዲረዳው እያሉ አማርኛውን /ቋንቋውን/ እንዲገነዘበው ብለው ስሙን መጽሐፍ ቅዱስ በማለት እየሳተሙ ያሠራጫሉ አንድ አይደለም። ሁሉም ሃይማኖቱ በየራሱ ሆነ። ሁሉም መምህር ነኝ ባይ ሆነ። መጽሐፍ ቅዱሱም ቋንቋው ተበላሸ። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ነው። ብሉይና ሐዲስ ነው። ሆኖም በቀላሉ እያሉ የሚያሳትሙት ቋንቋው የቀና አይደለም። ከአማርኛው መጥፋት የተነሣ ብዙ ሰዎች ተበላሽተዋል። ወደተሳሳተ መንገድ ገብተዋጠል። እግዚአብሔር ወልድ አማላጅ ነው የተባለው በዚሁ መጽሐፍ ቅዱስ በተባለው የተዛባ መጽሐፍ የተነሣ ነው። ታዲያ ይኸ መጽሐፍ ቅዱስ ይባላል? «እግዚአብሔር ወልድ አማላጃችን ነው። ያማልደናል፣ የሱስዬ» እያሉ የተነሡት በዚሁ የተዛባ ቋንቋና የተሳሳተ ትርጓሜ ነው። ድሮ እነ ንስጥሮስ፣ እነ አርዮስ፣ እነ ሰባልዮስ፣ እነ አርጌንስ፣ እነመቃርስ፣ እነ መቅዶንዮስ ... ይህ ሁሉ መናፍቃን ተመግዘው የተለዩት በመጽሐፍ ቅዱስ ነበር። እነዚህን ሁሉ ሐዋርያት እግዚአብሔር ስላደረባቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ነው እያሳመኑና እየረቱ የለዩዋቸው።

አሁን ግን ከጊዜ ብዛት የተነሣ ሁሉም ልቅ ሆነ። ትርጓሜውን ሁሉም እንደፈለገው ይተረጉመዋል። ጥንቃቄ የለም። ለዚህ መፍትሔው መጽሐፍ ቅዱስ እንደገና መታረም አለበት። የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት ሊቃውንቱ ተመርጠው ጥርት አድርገው ማረም አለባቸው። እንደ ማኅበረ ሐዋርያት ያለ ጥርት ያለ መጽሐፍ ቅዱስ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። እንደዚያ ከሆነ ለሰውም ለንባብ ይመቻል። የመናፍቃንን በር ይዘጋል።

ዛሬ ብቻ አይደለም። ጥንትም መናፍቃን ይነሣሉ። በትክክለኛው ትምህርት በጻኛ ፊት በክርክር ተረትተው ይወገዛሉ። ዛሬ ግን





የሚከሰስም የለ። በሃይማኖት የሚዳኝም የለ። ክርክርም የለም። ስለዚህ ሁሉም ሥልጣንኑ ብሎ የሃይማኖት አባት ነኝ ይላል። ዛሬ አንድ ሰው ተነሥቶ ሃይማኖት ቢያወጣ የሚከለክለው የለም። ይኸ ሁሉ ነገር መጽሐፍ ቅዱስ ነው እየተባለ ለሚወጣው የተዛባ መጽሐፍ መሠራጨትና መስፋፋት ምክንያት ነው።

## ገድላትና ተአምራት

ገድላትና ተአምራት ችግር አለባቸው፣ በውስጣቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይስማማ የተጋነነ ነገር አለ፣ ተአምራት ውስጥም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጋጩ ሐሳቦች አሉበት የሚሉ እንዳሉ ሰምቻለሁ። በእኔ በኩል መናፍቃን ይህንን የሚሉ ጻድቃን ሰማዕታትን የማይወዱ ስለሆነ ነው።

የጻድቃን የሰማዕታት እንኳን ገድሉ ጠበሉ ዓለምን እየቀደሰ ነው። ገድል ዓለምን የፈወሰ ነው። ርኩስ መንፈሱ ሁሉ እየወጣ የሚሔደው፣ ድውይ የሚፈወሰው ገድሉ ሲነበብ ነው። የሚያጠራጥር አይደለም። በተግባር የሚታይ ነው። ግብረ ሐዋርያት ምንድነው? ገድል አይደለም እንዴ?

ጻድቃን ሰማዕታት ገድላቸውና ጠበላቸው መጠኑ መድኃኒቱ በዓለም ይታወቃል። አያጠራጥርም። በዚህም በየቦታው ያለው ጠበል፣ ገድላቸው በዓይን የሚታይ ምስክር ነው። መናፍቃን የሚሉት ፈጠራ ነው። በአካል የሚታየውን ፈውስ በማየት ለምን አያምኑም? ለተንኮል ነው እንጂ። እነሱ የሚሉትን መስማት አያስፈልግም።

ገድል የቅዱሳንን ተጋድሎ፣ ቃል ኪዳናቸውን፣ ተአምራታቸውን የሚነግረን የሚያስተምረን ነው። እግዚአብሔር ለአባቶቻችን ቅዱሳን የሰጣቸው ጸጋ ታሪካቸውን ይገልጻል። ይኸ ደግሞ ለትውልድ መማሪያ ምሳሌ ይሆናል። በቀናው መንገድ የሚመራ ነው።

መምህር ጥበቡ ቀድሞ በትምህርት ከዚያም ለረጅም ዘመን በማስተማር በትርጓሜ የሚያውቋትን ኢየሩሳሌም በአካል ከዚያው ድረስ ሔደው አይተዋታል። በመጽሐፍ ቅዱስ በትርጓሜ የሚያውቋትን ኢየሩሳሌምንና ዙሪያዋን በዓይናቸው ሲያዩ ቀድሞ በትምህርት የሚያውቁትና



www.ethiopianorthodox.org

በቦታው ተገኝተው የተመለከቱት ነገር ተገናኘልዎ? ወይስ የተለየ ነገር ገጠመዎ? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት የማይረሳ መልስ ቀጣዩ ነበር። «የተለያየ ነገር የለም። ሁሉም አንድ ነው። ያየሁት ቀድሞ እንደሰማሁት እንደማውቀው ነው የተሰማኝ። ያየሁት ሁሉ አገሮቹ፣ በመጽሐፍ የተጻፈው ታሪኩ ሁሉ እንዳለ አግኝቼዋለሁ። አስቤበት ሥራዬ ብዬ የሔድኩበት ስለሆነ ሁሉን እየሆርኩ ተመል ክቻለሁ። አብረን ከሔድነው ውስጥ ኤማሁስ ማንም የወጣ የለም። እኛ ብቻ ነን የወጣነው። ሃምሳ ደረጃ አለው። የተጻፈው ሁሉ እንዳለ ይገኛል። ኢየሩሳሌም ሔጄ ሁሉንም ካየሁ በኋላ እኔ የማመሰግነው ሠ ራተኞቹን ነው። ያንን ሁሉ ሳይቃውሱ... ጌታ ያስተማረበት፣ የተቀመ ጠበት፣ የተጸነሰበት፣ የተወለደበት፣ የተጠመቀበት፣ የተገነዘበት፣ የተ ቀበረበት፣ መከራ የተቀበለበት፣ የተነ ሣበት፣ ያረገበት ይኸንን ሁሉ በሚገባ ለመጪው ትውልድ አዘጋጅተው ማኖራቸው እጅግ ያስደንቃል።

በመጽሐፍ ቅዱስ በትርጓሜ ቤት የማውቀውን ሁሉ ኢየሩሳሌም በሔድኩ ጊዜ እንዳሉ አግኝቻቸዋለሁ። በቃና ዘገሊላ የተደረገውን ድን ጋዮችን አገኘኋቸው። ዮርዳኖስን አገኘሁት። ጨሌው ባሕርን፣ ናዝ ሬትን፣ ገሊላን ጌታ ያስተማረባቸውን ሁሉ ምንም የቀረኝ የለም። እን ዳለ አግኝቼዋለሁ። በኢየሩሳለሌም የእኛ ገዳማት የሚገኙት አባቶች መነኰሳትም ስለ ኢየሩሳሌምም ሆነ ስለ አኗኗራቸው በሚገባ ነግረው ኛል። ጽፈውም ሰጥተውኛል። ገዳሙ የተቀደሰ የጸሎት ቦታ ነው፣ ነበር ያሉት።

መምህር ጥበቡ አስናቀ ባደረባቸው ሕመም በተወለዱ በሰማንያ ሰባት ዓመታቸው ሚያዚያ ፲ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ዐረፉ። የቀብር ሥነ ሥርዓታቸውም ሚያዚያ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተፈጽሟል።

*ምንጭ፦ ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ታኅሣሥ ፲፱፻፺፩ ዓ.ም*





# ሊቀ ምሁራን ሙሉ ገላው

/፲፱፻፬ - ፲፱፻፺፩/

*በአሥራት ከበደ*



*«ድጓ በመላው ዓለም አስደናቂ ሆኖ የሚያኮራን የቤተ ክርስቲያን ብቸኛ ሀብት ነው»*

ሊቀ ምሁራን ሙሉ ገላው ትውልዳቸው በደቡብ ጎንደር ሀረገ ስብከት ጋይንት ቤተ ልሔም ነው። ወላጆቻቸው አባ ገብረ ትርፌ እና ወ/ሮ ብሬቱ ተገኝ ይባላሉ። በ፲፱፻፬ ዓ.ም የተወለዱት ሊቀ ምሁራን ሙሉ ገላው በሰባት ዓመታቸው የአባ ታቸው አጐት መሪጌታ ቦጋለ ከተባሉ መምህር ዘንድ ትምህር ታቸውን ጀመሩ። ዳዊት ከደ ገሙ በኋላ ጾመ ድጓ ቅድስት ቤተ ልሔም ካሉ መምህራን ድጓ አድራሾች ተማሩ። ድጓ ትምህርታቸውን ከጀመሩ በኋላ ምንዖ ሙኃ ሚካኤል አለቃ አስካል ጉበዜ ከተባሉ የቅኔ መምህር ዘንድ ሄደው ሁለት ዓመት ተኩል ተምረው አጠናቀቁ። እንደገና ቤተልሔም ተመ ልሰው ድጓ ትምህርት ቤት ከመሪጌታ ሄኖክ ዘንድ ትምህርታቸውን ቀጠሉ። ከዚያም ጎጃም መሪጌታ መንክር ዘንድ ድጓ አንድ ዓመት ከመንፈቅ፣ ከመሪጌታ ዘርዓ ዳዊት ዘለለ እና ከተለያዩ መምህራን ዘንድ ሲማሩ ከቆዩ በኋላ በ፲፱፻፲፱ ዓ.ም. ተመልሰው ወደ ቤተልሔም ሄዱ። ከ፲፱፻፲፱-፲፱፻፳ ዓ.ም. ቤተልሔም ድጓ እየተማሩና እያገለገሉ ቆይተው ብራና ፍቀው ቀለም በጥብጠው በብራናው በዋናው የምሥ ክሩ ድጓ ትክክል ራሳቸው ጽፈው ጨርሰው በ፲፱፻፳ ዓ.ም. ተመረቁ። ከ፲፱፻፳፪ ዓ.ም. እስከ ፲፱፻፶፩ ዓ.ም. ድረስ የጋይንት አውራጃ ቤተ ክህነት ሊቀ ካህናት ሆነው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ተሾመው



www.ethiopianorthodox.org

ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ከ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. ጀምሮ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ወደ ቤተልሔም ቅድስት ማርያም ተዛውረው በደብሩ አስተዳዳሪነትና መምህርነት አገልግለዋል። ሊቀ ምሁራን ሙሉ ገላው ስለ ቤተልሔም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያንና ትምህርት ቤት ከተናገሩት የተወሰደው እንደሚከተለው ቀርቧል።

## ቤተልሔም የድጓው ዩኒቨርሲቲ

### *ቤተልሔም ቅድስት ማርያም*

ቤተልሔም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በ፫፻፲፭ ዓ.ም. አካባቢ በአክሱም የነገሡት አብርሃና አጽብሃ እንደሠሯት ይነገራል። ይህች ቤተ ክርስቲያን የምትገኘው በደቡብ ጎንደር ሃገረ ስብከት የታች ጋይንት ወረዳ ከተማ ከሆነችው አርብ ገበያ ሰሜናዊ ምዕራብ አቅጣጫ ነው። ከደብረ ታቦር ከተማ ፩፻፴፮ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች። እስከ ቅድስት ቤተልሔም ማርያም ቤተ ክርስቲያን ድረስ የመኪና መንገድ ቢኖርም የትራንስፖርት አገልግሎት ግን አይገኝም። ስለዚህ በበቅሎ ወይም በፈረስ አለበለዚያም በእግር መጓዝ የግድ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ቤተልሔም ተብላ ከመሰየሟ በፊት አብርሃና አጽብሃ አቤጌቴም የሚል ስም ሰጥተዋት ነበር። ከዚያ ቀጥሎም በዚያው ዘመን ቋንቋ ገንቢያ በመባል ትጠራ ነበር። ትርጉሙም ግንብ ማለት ነው። ከዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ግን ቅድስት ቤተልሔም ተብላለች። በሰሜን አፋርጅኝ፣ በደቡብ በጌምድር፣ በምሥራቅ በልል ኤፍራታ የሚባሉ ተራሮች የተከበበችው ታሪካዊ የቤተ ክርስቲያንና የአገር ቅርስ በደጋውና በቆላው መለያያ ድንበር በረባዳው ቦታ ላይ የምትገኝ ስትሆን ወይና ደጋማ የአየር ጠባይ አላት ።

ቤተልሔም ቅድስት ማርያም የድጓ ምስክር ቦታ ለመሆን የቻለችበትን ምክንያት ሊቀምሁራን ሙሉ ገላው እንዲህ ይገልጹታል። ዛሬ ለመላው ኢትዮጵያ የድጓ ምስክር የሆነው ቤተልሔም በዐፄ ሠርጸ ድንግል ዘመን ነው። የቤተልሔም ዜማ ራሱን የቻለ ነው። ሌሎች ዜማዎች አሉ። በፊት በተለያዩ ደብሮች ለየራሳቸው ነበር። ዜማውም





ቢሆን ወሰን የለውም። አሜብር ማለት ቆሜ የሚባል አለ። አሁን ግን ያሁሉ ቀርቷል። እያጸጸ ሄዷል። በጠቅላላው ዛሬ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትቀደሰውና የምትወደሰው ወይም ደግሞ ማኅሌቱ የሚካሄደው በቤተልሔም ዜማ ነው።

ታሪኩ እንዲህ ነው። ግራኝ አሕመድ አብዛኛውን የኢትዮጵያን ግዛት በመውረር አብያተ ክርስቲያናትን በማቃጠል ቅርሶችን በመዝረፍና በማጥፋት ሊቃውንቱን ሁሉ በጨፈጨፈ ጊዜ ቅድስት ቤተልሔም ምንም ዓይነት ጉዳት አልደረሰባትም። ይኸም በእግዚአብሔር ተአምራት የሆነ ነገር ነው።

ግራኝ አሕመድ ቤተ ክርስቲያን አቃጥሎ ለማጥፋት ከፍተኛ ጥረት አድርጉ ብዙ ደክሞ አልተሳካለትም። ከርቀት ከጋራ ላይ ሆኖ ሲመለከታት ከታች ቁልጭ ብላ ትታየዋለች። ሊያቃጥላት ሲመጣ ትሰወርበታለች። ታሪኩ «ደመና ብሩህ ከለላ ለቅድስት ቤተልሔም» ይላል። ግራኝ «የጨረር» ከሚባለው በአካባቢው ከሚገኝ ጋራ ላይ ሆኖ ቁልቁል ያያትና ወደታች ወርዶ ወደ ቤተ ክርስቲያት ሲጠጋ በደመና ተሸፍና ሐረግ ለብሳ ትጠፋበታለች። ሰባት ጊዜ ያህል እየወረደ እየጠወጣ ሞክሮ ከብዙ ችግርና ድካም በኋላ በቤተክርስቲያን አካባቢ ሲደርስ ጨለማ ዓይኑን ጋርዶታል። በሁኔታው ተስፋ ቆርጦ ተመልሶ ወደ ተራራው ወጣ። ያን ጊዜ ቤተ ክርስቲያኗ ታየችው። ሌሎቹን አብያተ ክርስቲያናት አቃጥዬ ጨርሼ ስመለስ ቤተልሔምን አቃጥላታለሁ በማለት ትቶ ሄደ። ነገር ግን በሄደበት ቦታ ባደረገው ጦርነት ደንቀዝ ላይ በመሞቱ አልተመለሰም።

በዚህ ምክንያት ግራኝ ቤተ ክርስቲያን ማቃጠል ባለመቻሉ ቤተ ልሔም «የግራኝ እመቤት» ትባላለች። እንግዲህ ግራኝ ቤተ ልሔምን ለማቃጠል በአካባቢው በሚደርስበት ጊዜ በዚያን ወቅት የቤተ ልሔም አለቃና መምህር የነበሩት ግራኝ መጥቶ ቤተ ክርስቲያን ቢያቃጥል መጽሐፍም አብሮ ይቃጠላል ብለው ፀማሰብ የድጓውን መጽሐፍ ወስደው ቀብረው ደብቀውት ነበር ይባላል። መጽሐፉን የቀበሩበት ቦታም ከቤተ ክርስቲያኑ በስተ ምሥራቅ በኩል ባለው ዋሻ ውስጥ



www.ethiopianorthodox.org

ነው። መምህሩ መጽሐፉን ሰው አግኝቶ እንዳይወስደው ወይም ጉዳት እንዳይደርስበት ለመጠበቅ ወይም ለማረጋገጥ በቀን ውስጥ ብዙ ጊዜ እየተመላለሱ በማየት ያረጋግጡ ነበር። የመምህሩ ሳይሰለቹ መመላለስ ያስገረማቸው የአካባቢው ሰዎች መምህሩን «አይሰለችም ወይ?» በማለታቸው የተነሣ ዋሻውም «አይሰለች» ተብሎ ይጠራል። መምህሩ ግራኝ መሞቱን ሰምተው ሀገሪቱም ሰላም እንደሆነች ካረጋገጡ በኋላ መጽሐፉን ከደበቁበት ዋሻ አውጥተው ወደ ቦታው መለሱት።

ከዚያ ሁሉ የግራኝ አሕመድ ጥፋት በኋላ ዐፄ ሠረጸ ድንግል መል ሰው ለማቋቋም ሲሉ ከሞት የተረፉትን ሊቃውንት ማሰባሰብ ጀመሩ። በዚህ ጊዜ ተጠርተው ነበር። ሊቃውንቱ በቃለ እግዚአብሔር በዚያው በዜማው አልስማማ ብለው ይከራከሩ ይጣሉ ጀመር። ነገሩ መፍትሔ ስለጠፋለት ጉዳዩን እንዲያውቁት ከንጉሡ ዘንድ ቀረበ። መምህራኑ በዜማው ምክንያት መጣላታቸው ተነገራቸው። ንጉሡም ሊቃውንቱ መረጃ እንዳላቸው ጠየቁ። ሌሎቹ መረጃ የለንም ሲሉ መራሔ ዘቤተልሔም ልሳነ ዕፍረት አባቶው የተናገሩት ትክክል መሆኑ መረጃ አለኝ ሲሉ አስታወቁ። አለኝ የሚሉትንም መረጃ ይዘው እንዲቀርቡ ታዘው ተደብቆ የቆየውን የድጓ መጽሐፍ ይዘው ንጉሡ ዘንድ ቀረቡ። ሌሎቹ ሊቃውንት የሚያቀርቡት መረጃ አልነ በራቸውም። የቤተልሔሙ መምህር የኢትዮጵያ ሊቃውንት በተሰበሰ ቡት መጽሐፉን ዘርግተው አስረዱ። ንጉሡ ዐፄ ሠርጸ ድንግልም በመረጃው መሠረት የመምህሩን ንግግር አደነቁ። «በቃል ያለ ይረሳል በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል» ስለዚህ አንተ /ሊቁ ልሳነ ዕፍረትን/ የኢትዮጵያ የድጓ ምስክር አገሪቱም /ቤተልሔም/ የድጓ ማስመስከሪያ እንድትሆን ሲሉ አዋጅ አወጁ። ቅድስት ቤተልሔ ምም ከዐፄ ሠረጸ ድንግል ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የድጓ ምስክር ሆና ሊቃውንትን እያፈራች እስከ ዛሬ ታበረክታለች።

ድጓን ቅዱስ ያሬድ ከብሉይና ከሐዲስ ከሊቃውንት እያውጣጣ የደረሰው ነው እንጂ እንዲሁ ልቦለድ ድርሰት አይደለም። ቅዱስ ያሬድ ሁሉን ነገር አጠናቆ መጽሐፉን ከጻፈ በኋላ ሲወርድ ሲዋረድ





ሊቃውንቱ እያሻሻሉ ሲጽፉት ቆይተዋል። ቢሆንም ግን ዜማው ይለይ እንጂ ይዘቱም ሆነ መልእክቱ አንድ ነው። ትምህርቱ በጣም ሰፊና ጠለቅ ያለ ነው። ምክንያቱም አንድ ሰው ሙያውን ለመያዝ ልብን አስፈቶ በትዕግስትና በጥንካሬ አጠናቆ መማር አለበት። በአማርኛው ድጓ /በማላላት/ ይባላል። በድሮ ጊዜ «ደጓ» ማለት ለሰውነት ድጋፍ የሚሰጥ ማለት ነው። የቤተ ክርስቲያን መታጠቂያ /መገልገያ/ ማለት ነው። ወይንም ድጓ ቀለም ሰብስቦ ስለሚገኝ ነው። ጠቅላላ ከዓመት እስከ ዓመት ያለውን ስማዕታትን የሚያወሳ መዝሙር ማለት ነው። ጌታዩ እንግዳ መጽሐፍ ጥበብና ብርሃነ ዓለም በመባል የሚታወቁ የድጓ ዓይነቶች አሉ። የተጻፉበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር ብዙ ልዩነት የላቸውም። የድጓ መዝሙር ሦስት ዜማዎች ሲኖሩት እነሱም ግእዝ፣ አራራይ፣ እዝል ተብለው ይታወቃሉ። እንደሚነገረው ቅዱስ ያሬድ ድጓን የደረሰው አክሱም በኋላም ሰሜን /ጎንደር/ ውስጥ እያስተማረ እዚያው ተሰወረ ይባላል።

አንድ የድጓ ተመራቂ ወደ ትምህርት ቤቱ ለመግባት መመዘኛው ምን እንደሆነ ሲያስረዱ፣ ተማሪው በሚመጣበት ጊዜ በቅድሚያ ችሎታው ይመዘናል። በመጀመሪያ ከአስተማሪው መሪጌታ ወደ እኛ /ቤተልሔም/ ሲላክ የድጓ ትምህርቱን ማጠናቀቁ በመሸኛ ደብዳቤ ይገለጻል። ከዚያም በኋላ ቤተልሔም መጥቶ ከተቀበልነው በኋላ ተራ ወንበር ይሰጠዋል። እየተማረ እንዳለ ሊቃውንቱ በተሰበሰቡበት ድጓ ይሰጠውና ብቻውን እንዲያሄድ ይታዘዛል። ያለ ምስክሩ የተሰበሰቡት ሊቃውንት በዝምታ ያዳምጣሉ። ከዚያ መካከል ብቻውን ሲያሄድ የሚያጠፋ ከሆነ መምህሩም ሆነ ሊቃውንቱ ያስወጡታል። ከወንበሩ ወይም ከተሰጠው መድረክ ላይ እንዲወርድ ይደረጋል። በዚያ መካከል አጥና ይባላል። አጥንቶ አሻሽሎ ደግሞ እንደገና ይቀርባል። እረፍት የለም። ወንበር ተተከለ አልተተከለ የለም። ያለማቋረጥ መቀጸል ነው። ቤተልሔም በትምህርት ሁለት ዓመት ከሞላቸው ከቆዩትና ከቀደሙት ካጠኑት ሰዎች ወይም መጽሐፋቸውን ካረሙት እየጠየቀ ይረዳል፣ ያስተካክላል። በሚገባ ያጠናል። ከዚያ በኋላ ትምህርቱን



www.ethiopianorthodox.org

ያጠናቅቃል ማለት ነው። ተመራቂው ፈተናውን የሚፈተነው በሊቃውንት መካከል ነው። የሚዘጋጅለትን ፈተና የሚፈተነው በተራ ወንበር ላይ ነው። ወንበር ተክሎ ጉባኤ ዘርግቶ ለማስተማር ገና አልተመረቀምና ባለወንበር አይደለም። በዚህ ዓይነት አንድ ተመራቂ ለተራ ወንበር መድረክ ተሰጥቶት ለመፈተን ከተማሪው ብዛት የተነሣ በሦስትና በአራት ወር ተራው ይደርሰዋል። በዚያ በተራው ተፈትኖ ከወደቀ እንደገና አጥንቶ አሻሽሎ በሌላ ተራ ተመልሶ እንዲቀርብ ይደረጋል። በዚህ ሁኔታ ቀደም ብሎ በውጭ በሚገባ አጥንቶ ወደ ቤተልሔም የመጣ ጉበዝ ተማሪ ከሆነ በቤተልሔም ቆይታ ተምሮ ለመመረቅ ሁለት ዓመት ይበቃዋል። ድጓ በዓመት አንድ ጊዜ ይዘለቃል። ስለዚህም ጉበዝ ከሆነ በሁለት ዓመት ሁለት ጊዜ ይዘልቃል። በተረፈ ግን ለመመረቅ ደንቡ /ሕጉ/ የሚለው በሁለት ዓመት ከመንፈቅ ነው።

ተማሪው ሲመረቅ የሚሰጠው ማረጋገጫ በአሁኑ ጊዜ ተመራቂው በማተሚያ ቤተ ታትሞ ተዘጋጅቶ የሚገኘውን ድጓ መጽሐፍ ይዞ ይቀርባል። ያንን ያርማል። ከታረመና ከተጠናቀቀ በኋላ በሊቃውንቱ ይረጋገጣል። ከዚያም በመጽሐፉ መጀመሪያ፣ መጨረሻና በኅዳጉ ላይ የምሥክር መምህሩ ማኅተም ይደረግለታል። ሁለተኛ ደግሞ ተመራቂዎቹ የሚዘጋጅላቸው ጽሑፍ አለ። ቃለ በረከት ይባላል። የሚሰጣቸው ቃለበረከት /ደብዳቤ/ ለመጡበት ሀገረ ስብከት ለደብራቸው የሚሄድ ነው። የቃለበረከቱ መልእክት እገሌ የተባለው ከአጥቢያችሁ የመጣው ተማሪ በቤተልሔም የድጓ ትምህርቱን አጠናቆና ፈተናውን አልፎ ስለመመረቁ ይገልጽና ጉባኤ ዘርግቶ ለማስተማር የሚችል መሆኑን በማረጋገጥ የመጣበት ደብር /አጥቢያ/ እንዲቀበለው የሚገልጽ ነው። ሦስተኛና ዋናው በማተሚያ ቤት ታትሞ የተዘጋጀ ምስክር ወረቀት የተመራቂው ፎቶግራፍ ተደርጐ በማኅተም ተረጋግጦ ይሰጣቸዋል።

የቅድስት ቤተልሔም ታላቅ መንፈሳዊ ጉባኤ ምስክር ቦታ የመላ ኢትዮጵያ ሊቃውንት መፍለቂያ መሆኑ ይታወቃል። በዚያ በሓላፊነት





ማስተማር ከጀመርኩበት እስከ አሁን ድረስ ሁለት መቶ አስራ አምስት ሊቃውንት የድጓ መምህራን ተመርቀው በመላ ኢትዮጵያ ወንበር ዘርግተው እያስተማሩ ይገኛሉ። ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹም እዚያ ቤተልሔም የሚያገለግሉና የሚያስተምሩ አሉ። መምህር ሙሉ ገላው ባሉበት ወቅት በመማር በወንበር የሚገኙት የድጓ አድራሾች ሰማንያ ናቸው።

የተማሪዎቹ ቁጥር ካለፉት ዓመታት እየጨመረ ነው እንጂ እየቀነሰ የሄደበት ጊዜ የለም። ትምህርቱ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጠቃሚ ነው። ያለ ድጓ መምህር ቤተ ክርስቲያን ጾመድጓ ሌላው መቆም አይችልም። ከባለሙያው ከድጓ መምህሩ ሌላ ሌላው አይቆምም። ቤተልሔም ያስመሰከሩ ከሆነ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ቦታ አያጡም የድጓ ተመራቂዎቹ ደመወዝ ተቆር ጠላቸው ይቀጠራሉ። ስለዚህ ሙያው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ተፈላጊ በመሆኑ የድጓ ተማሪውም ቁጥር ከዓመት ዓመት እየጨመረ ነው።

ዛሬ ቤተልሔም በከፍተኛ ችግርና በአሳዛኝ ሁኔታ ላይ ይገኛል። በዚያ የሚገኙ ታላላቅ የኢትዮጵያ ሊቃውንት በአሁኑ ጊዜ መጠለያ ቤት የላቸውም። የመማሪያ አዳራሹ በ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት በነበሩበት ጊዜ አራት ሺ ብር ሰጥተው የተሠራው ነበር። ያንንም ነፋስ ገነጣጥሎ ጥሎት ቤት የለም። ሊቃውን ቱንም ሆነ ተማሪዎቹን ረሃብ እየተፈታተናቸው ነው። የሚበሉት እየጠፋ ውኃ ጠጥተው የሚያድሩበት ጊዜ ይበዛል። ትንሽ ትንሽ አዲስ አበባ እየመጣን ከበጐ አድራጊዎች ከምናገኘው እርዳታ በስተቀር ሊቃውንቱ ቋሚ መተዳደሪያ ገቢ የላቸውም። የድጓ ተማሪዎችም ቀለብ የላቸውም። ቀደም ባለው ጊዜ በበጎ አድራጊዎች የተተከለ ወፍጮ ነበር። ከዚያ በሚገኘው ገቢ ሊቃውንቱ ይረዱበት ነበር። ዛሬ ወፍጮው በአገልግሎት ብዛት አርጅቶ ተበላሽቶ ከቆመ ቆይቷል። የሊቃውንቱም ርዳታ ቀርታለች። የድጓ ትምህርት ቤቱ በቅድስት ቤተልሔም ቤተ ክርስቲያን ሥር ነው። የቤተ ክርስቲያኑ ገቢ እጅግ በጣም አነስተኛ በመሆኑ ለአገልጋይ ካህናቱም በቂ አይደለም። አገሩ አካባቢው በድርቅ



www.ethiopianorthodox.org

የተጉዳ ስለሆነ ካህናቱም በችግር ላይ ይገኛሉ። የትምህርት ቤቱ ሊቃውንትም ከቤተ ክርስቲያኑ ገቢ የሚረዱበት ሁኔታ የለም።

ተማሪዎቹ የመጡበት ሥራቸው ዓላማቸው ስለሆነ ምንም ዓይነት ችግር ቢያጋጥማቸው የከፋ ረሃብም ቢሆን ችግሩን ተቋቁመው በጽናትና በትዕግስት ይማራሉ እንጂ ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደ የመጡበት እስከመሄድ የደረሱ ተማሪዎች እስከአሁን የሉም።

የአብነት ትምህርቱን ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ የሚቻለው፣ በእውነቱ ከሆነ የትም ቢሆን ሊቃውንቱን ባሉበት ቦታ ለኑሮአቸውም ሆነ ለሚያስተምሩት የሚያስፈልጋቸው ነገር ሲሟላላቸው ተገቢው እንክብካቤ ሲደረግላቸው ነው። እንግዲህ የድጓ መጽሐፍ የተገኘው ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት በሊቁ በልሳነ ዕፍረት ነው። እርሱ ይኸንን ታላቅ መጽሐፍ አጥፍቶት ቢሆን ኖሮ ዛሬም አይገኝም ቀረ ነበር የሚባለው። አንዱ የድጓ መጽሐፍ ተቀብሮ ከተደበቀበት ከቃጠሎ ድኖ በመገኘቱ ዛሬ በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ተስፋፍቶ ሊገኝ ችሏል። ምክንያቱም የተመለከተ /ምልክት ያለው/ ድጓ ያ ብቻ ስለነበር ነው። ለምሳሌ ቅዱስ ያሬድ የጻፈው ድጓ ምልክት የለውም። ስለዚህ ይኸ የምስክሩ ድጓ ምልክት አለው። ያንን ጠብቆ ይዞ በመገኘቱ ይኸው ለዛሬው ትውልድ ሊደርስ ችሏል። እንደገና ደግሞ የቤተክርቲያን መምህራኑን መርዳት ያስፈልጋል። ከዚህ ቀደም የመምህሩ ማደሪያ ብቻ አራት መቶ ቀላድ መሬት ነበረው። ይኸ በመሬት አዋጅ ምክንያት ቀርቷል። መምህሩም ከፍተኛ ደመወዝ ነበራቸው፣ ቀርቷል። ከዚያ በኋላ ቅድስት ቤተልሔም ምንም ዓይነት ገቢ የላትም። ትምህርት ቤቱም እንዲሁ ምንም ዓይነት የነበረው ደመወዝ ካለፈው መንግሥት ጊዜ ጀምሮ ተቋርጦ ቀርቷል። የትምህርት ቤቱም ሆነ ሊቃውንቱና ተማሪዎቹ ምንም ገቢ የላቸውም።

ስለዚህ ቤተክርስቲያን ሊቃውንቱን መንከባከብ ለትምህርት ቤቱም መማሪያ ክፍሎች እና ዕቃዎች በማሟላት ቤተልሔም የድጓ ማስመስከሪያን ጠብቆ ለትውልድ ማቆየት አለባት። ይኸን የመሰለ ታላቅ ሙያ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በሌላው ዓለም ጭራሽ የለም።





በመላው ዓለም አስደናቂ ሆኖ የሚያኮራን የቤተ ክርስቲያናችን ብቸኛ ሃብት ነው። ስለዚህ ይህ ታላቅ ሙያ ትምህርትና ታሪክ እንዳይጠፋ ምእመናን የቅድስት ቤተልሔም ድጓ ምስክር ቦታን ጠብቆ ለማቆየት ትምህርት ቤቱንና ታሪካዊ ቤተ ክርስቲያን መንከባከብ በሚቻላቸው ሁሉ መርዳት ይገባቸዋል። ሊቃውንቱን መደገፍ ተማሪዎቹን በሚያስፈልጋቸው ሁሉ መርዳትና ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል። ይኸ የቤተ ክርስቲያንም ሆነ የአገር አደራ ነው። ዜማው ቅርሱ እንዳይጠፋ ተጠበቆ መቆየት አለበት። ምእመናን ልጆቻቸው የአብነት ትምህርቱንም እንዲማሩ ማሳወቅ ማበረታታት አለባቸው። ሊቃውንቱም ተምረው ከወጡ በኋላ ከሀገረ ስብከትም ሆነ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሊቃውንቱን ተቀብለው ቦታ በመስጠት ለኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን በማሟላት እንዲያስተምሩ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ አለባቸው። ሊቃውንቱም ትምህርቱን በማስተማር ተተኪዎቻቸውን ማፍራት አለባቸው። ሊቃውንቱን በአጥቢያቸው እንዲያስተምሩ የሚያስፈልጋቸውን ከሚሉላቸው ከቦታ ቦታ እየለቀቁ እንዳይሄዱ ማድረግ ይቻላል። ድጓቸውንም እያጠፉ ተማሪ እየበተኑ እንዳይሄዱም መቆጣጠር ይቻላል። ብዙ ጊዜ ሊቃውንቱ እየለቀቁ ወደ ከተማ የሚወጡት የሚቀበላቸው የሚደግፉ ቸው በማጣት ነው። እነዚህን መምህራን ደመወዛቸውን ያሉበት ደብር ሊከፍላቸው ይችላል። አቅም ባይኖረው እንኳን የሕዝቡን ልጆች የሚያስተምሩ ስለሆነ ሕዝቡ የሚቻለውን ያህል የአቅሙን እያወጣ አሰባስቦ እንዲደጉማቸው ለማድረግ ማስተባበር ነው። በዚህ ሁኔታ መምህራኑ ባሉበት እንዲቆዩ ማድረግ ይቻላል። የአብነት ትምህርቱንም ጠብቆ ለትውልድ ለማቆየት ይረዳል።

ከመጀመሪያው እሳቸው እስካሉበት ድረስ ያሉትን የድጓ መምህራኑን /አባቶችን/ ሲዘረዝሩ ከቅዱስ ያሬድ ይጀምራሉ። ሳዊሮስ፣ ስንድሮስ፣ አንዲሮስ፣ ብልዳዶስ፥ ኬፋ፣ ገብሩ፣ ጌራወርቅ፣ አባጊዮርጊስ፣ ልሳነ ዕፍረት፥ ዕንቆ ባሕርይ አስተማሩ። ግራኝ አብያተ ክርስቲያናቱንና መጻሕፍቱን አቃጥሎና አጥፍቶ ሊቃውንቱን ፈጅቶ ከዚያ የጥፋት ዘመን በኋላ ልሳነ ዕፍረት የድጓ መጽሐፉን አግኝቶ ቅድስት ቤተልሔም



www.ethiopianorthodox.org

የድጓ ምስክር ቦታ ሆና በዓዋጅ ጸናች። ከዚያ ልሳነ ዕፍረት፣ ቃለ አብ፣ ዕጨጌ ቃለ አዋዲ፣ ሕንፃ ሃይማኖት፣ ተጠምቀ መድኅን፣ እሸቴ ወልደ ገብርኤል፣ ሕንፃ ሃይማኖት፣ ወልደ መለኮት፣ ሠርፀ ድንግል፣ መምህር ክንፈ ሚካኤል፣ ገብረ እግዚአ ብሔር ደርሶ፣ መምህር መርሻ ወልደ ማርያም ገብረ መድኅን፣ አለቃ አምሳሉ መርሻ ስብሐተ ማርያም፣ ሊቀ ምሁራን ጥበቡ መንግሥቱ ተክለ ማርያም ናቸው።

ከላይ የተጠቀሰውን የቤተልሔም አጠቃላይ ሁኔታ የተረኩት ሊቀ ምሁራን ሙሉ ገሳው ከሊቀ ምሁራን ጥበቡ መንግሥቱ ተክለ ማርያም ቀጥሎ የነበሩት ሊቅ ሲሆኑ በደረሰባቸው የራስ ላይ የነርቭ ሕመም ምክንያት አዲስ አበባ ሐያት ሆስፒታል ሲታከሙ ቆይተው ጥር ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም በተወለዱ በሰልሣ ስምንት ዓመታቸው ዐርፈዋል። አስከሬናቸው ወደ ተወለዱበትና ሲያገለግሉበት ወደ ቆዩባት ቅድስት ቤተ ልሔም ቤተ ክርስቲያን ተወስዶ ወዳጅ ዘመዶቻቸውና ደቀ መዛሙርቶቻቸው በተገኙበት የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት የካቲት ፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ተፈጽሟል።

*ምንጭ፡- ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ መጋቢት ፲፱፻፺፰ ዓ.ም*





# ፍቅር

*በግርማ ወ/ሩፋኤል*

«እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን ዐውቀናል እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል።» ፩ዮሐ.፫፥፲፮

በዓለማችን ላይ በተለያዩ አጋጣሚዎች ታላላቅ የኪነጥበብ ሰዎች የታወቁ ፈላስፎች ስለፍቅር ብዙ ብለዋል። ይሁን እንጂ የእውነተኛውን ፍቅር ምንነቱን የገለጹት፣ በተግባርም ያዋሉት በጣም ጥቂቶች ናቸው። እውነተኛ ፍቅር ብዙ ስለተጻፈበት ወይም ተደጋግሞ ስለተነገረ ከሰው ልቡና አይገባም። እውነተኛ ፍቅር ከእግዚአብሔር የሚገኝ የተለየ ጸጋና የክርስትና ሃይማኖትም መሠረት ነው። «ወዳጆች ሆይ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሆነ።» የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደ እግዚአብሔርንም ስለሚያውቅ እርስበርሳችን እንዋደድ» ፩ዮሐ.፬፥፯፣ ሮሜ. ፰፥፳፰።

የሰው ልጆች በሃይማኖት ጸንተው በአገልግሎትም ተጠምደው ቢኖሩ ከዚያም አልፈው ንብረታቸውን ለነዳያን እየሰጡና እየመጸወቱ መሳ ሕይወታቸውን ቢያሳልፉ ቢጾሙ ቢጸልዩ ቢሰግዱ የሕግጋት ማሠሪያ የሆነውን ፍቅርን ካልያዙ ከንቱ ነው። ፩.ቆሮ.፲፫፥፩-፫። ፍቅር ከሌለ ሰላም የለም። ፍቅር የሌለው ሰው ተስፋ ቢስ ነው። ራሱን ይጠላል። ቅናትና ምቀኝነትን ተመልቶ የሌሎችንም ሰላም ይነሣል። ኃጢአትን ያለ ይሉኝታና ያለገደብ ይፈጽማል። ሸንጋይና በመጨረሻም ሃይማኖት የለሽ ይሆናል። መዝ.፲፬ በአንጻሩ ፍቅር ካለ የጎደለው ይሞላል፣ የጠመመው ይቃናል፣ መራራው ይጣፍጣል፣ ጥቂቱም ይበዛል። «ፍቅር የኃጢአትን ብዛብ ይሸፍናልና» ፩ጴጥ.፬፥፰፣ ማቴ.፲፬፥፲፱-፳፮፣ ምሳ.፲፯፥፱።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለደቀመዛሙርቱ አደራውንና ትእዛዙን በሚሰጥበት ጊዜ «እኔ እንደወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት።» በማለት ፍቅርን ምሳሌ ሆኖ አስተምሯል። ዮሐ.፲፭፥፲፪። ለዚህ ነው ፍቅርን ሐዋርያት



www.ethiopianorthodox.org

የትምርታቸው መጀመሪያና ማሣረጊያ ያደረጉት፣ ሊቃውንትም በመጸሕፍታቸው ሰፊ ዓምድ የሰጡት፣ መዘምራን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው የዘመሩት።

## ማንን ነው የምናፈቅረው?

ክርስቲያን እውነተኛ ፍቅር ሊኖረው ይገባል። የሚያመልከው የፍቅርን አምላክ ነውና። ይህም እውነተኛ ፍቅር ሁለት ዘርፎች አሉት።

«ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም አሳብህ ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች እርስዋም፡- ባልንጀራህን እንደነፍስህ ውደድ የምትለው ናት። ኦሪትና ነቢያት በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ጸኑ።» ማቴ.፳፪፥፴፯-፵።

## ፍቅረ እግዚአብሔር

«ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም አሳብህ ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ማቴ.፳፪፥፴፯። የሰው ልጅ ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ ባለውለታነቱን በውቆ ይወደው ያመልከው ያመሰግነው ክብሩንም ዘወትር ይናገር ዘንድ ያስፈልጋል። ፍቅረ እግዚአብሔር እግዚአብሔርንና የእርሱ የሆነውን ሁሉ በመውደድም ይገለጣል።

### ሀ. ትእዛዛቱን በመጠበቅ

«... ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤» ዮሐ.፲፬፥፳፩።

«የሚወደኝ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።» ብሎ በፍቅር የጠራን አምላክ «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» ብሎ ሕጉን በፍቅር አስቀመጠልን። ማር.፰፥፴፬፣ ዮሐ.፲፬፥፲፭ ሥጋውን ቆርሶ ደሙንም አፍስሶ በሞቱ ፍቅርን አስተማረን። ይህንን ፍጹም ፍቅሩን አስበን ስለምንወደው እንታዘዛለን። ስለዚህ ለክርስቲያኖች የተሠጠን የሐዲስ ኪዳን ሕግ የፍቅር ሕግ ነው። ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ «ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው፤» ያለው ሮሜ.፲፫፥፲። በመሆኑም ፍቅረ እግዚአብሔር ፈቃዱን በመፈጸማችን ትዕዛዛቱን በመጠበቃችንና





ለእርሱም ከእውነት በመገዛታችን ይገለጻል። «ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና። ፩ዮሐ.፭፥፫።

### ለ. ቅዱሳኑን በመውደድ

«... እግዚአብሔርን ስንወድ ትእዛዛቱንም ስናደርግ የእግዚአብሔርን ልጆች እንድንወድ በዚህ እናውቃን።» ፩ዮሐ.፭፥፪።

ፍቅረ ቅዱሳን ለምእመናንን ሁሉ የተሰጠ ታላቅ ጸጋ ነው። በመሆኑም ኦርቶዶክሳውያን እግዚአብሔር ለወደዳቸውና ላከበራቸው ቅዱሳን የተለየ ፍቅር አለን። ሮሜ.፰፥፴። ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ብለው ለጽድቅ የተሰደዱትን ነቢያት ቃሉን በዓለም ሁሉ ዞረው ያስተማሩትን ሐዋርያት በስሙ መከራ የተቀበሉትንና ደማቸውን ያፈሰሱትን ሰማዕታት በሕይወት ዘመናቸው በተጋድሎ የኖሩትን ጻድቃን አገልጋዮቹን መላእክት መውደድ እግዚአብሔርን መውደድ ነው። ስለዚህም ኦርቶዶክሳውያን ቅዱሳንን እናከብራቸዋለን፣ ዘወትርም ስማቸውን እየጠራን በአማላጅነታቸው እንማጸናለን። ይህም እውነተኛ ፍቅር ምድራውያንን ከሰማያውያን ጋር ያገናዝበናል። በኋላም አንድ ያደርገናል። ይህ ፍቅር ነው ጌታችን በቤተልሔም ሲወለድ ሰዎችንና ሰማያውያን መላእክትን አንድ ዓይነት ዝማሬ ያዘመራቸው፣ አንድ ዓይነትም ምሥጋና እንዲያቀርቡ ያደረጋቸው። ሉቃ.፪፥፲፫።

### ሐ. የአገር ፍቅር

አገራችን ኢትዮጵያን የምንወዳት ወንዝ ተራሮችዋ ልምላሜዋ የተለየ በመሆኑ አይደለም። ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ ሕገ ኦሪትን ቀድማ የተቀበለች በሕገ ወንጌልም የጸናች ታቦተ ጽዮንን እና ግማደ መስቀሉን ስለያዘች ቅዱሳን በኪደተ እግራቸው የባረኳት ለእመቤታችንም በአሥራትነት የተሰጠች የቃል ኪዳን ሀገር ስለሆነች ነው። በመሆኑም የአገር ፍቅር ከፍቅረ እግዚአብሔርና ከቅዱሳን ፍቅር ጋር ይገናኛል። አባቶቻችን ይህ ፍቅር ኖሯቸው ነው ነፃነቷንና አንድነቷን አስከብረው ያቆዩልን። በሰላምና በነፃነት የሚኖሩበት አገር ከሌለ እግዚአብሔርን በነፃነት ማምለክ ለእርሱም መገዛት አይቻልም። በመሆኑም ክርስቲያን



www.ethiopianorthodox.org

አገሩን ሊያፈቅር ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ነው ቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር ስለ አገር ፍቅር የምታስተምረው፣ ስለ አገር ሰላምም የምትጸልየው፡፡

ኢትዮጵያውያን ይህ ፍቅር በልቦናቸው ስላለ በየትኛውም ዓለም ቢጓዙ ወገናቸውን የሚወዱ በራሳቸው ስም የሚጠሩ በራሳቸው ትውፊትና ሃይማኖት የሚመሩ ናቸው፡፡ ዛሬ መናፍቃን የሚሯሯጡት በእውነት ወንጌልን ሊሰብኩን ሳይሆን ለዚህች የቅዱሳን ሀገር ለሆነች አገራችን ያለንን ፍቅር ለማጥፋት እና ግድየለሾች እንድንሆን ለማድረግ ነው፡፡ ወንጌልን መስበክ እውነተኛ ዓላማቸው ቢሆንማ ኖሮ በአገራቸው ወንጀልን፣ ዝሙትን፣ የእፅ ሱሰኝነትን...መቆጣጠር ተስኗቸውና ስንቱስ ወገናቸው ወንጌል ጠምቶት አልነበር?!

## ፍቅረ ቢጽ

«... ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርን የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን፤» ፩ዮሐ.፬፥፳-፳፩፡፡

ፍቅረ ቢጽ /ባልንጀራን መውደድ/ ማለት በሥላሴ አርአያ የተፈጠረን የሰውን ልጅ ሁሉ በሰውነቱ መውደድ ማለት ነው፡፡ ክርስቲያን የሰውን ክፉ ምግባሩን ይጠላል እንጂ ሰውየውን ስለ ሰውነቱ አይጠላም፡፡ በመሆኑም ክርስቲያን አብሮት ካለው ባልንጀራው ወይም ወንድሙ ጀምሮ ለነፍስ እስከሚፈልገው ጠላቱ ድረስ ሊወደው ይገባል፡፡ ይህ ማለት ግን በሃይማኖት ከማይመስለንና የቤተ ክርስቲያን ጠላት ከሆነው ጋር እንተባበር፣ አንድ እንሁን ማለት አይደለም፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ፍቅር ሳይሆን ሞኝነት ነው፡፡ ይህንንም «በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖር ሰው አምላክ የለውም በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት፡፡ ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት፤ ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና» በማለት ሐዋርያው በሚገባ ገልጾልናል፡፡ ፪ዮሐ.፲ ይህንን ባለመረዳትም ነው ብዙዎች በሃይማኖት ከማይመስሏቸው ጋር አጉል ወዳጅነት ፈጥረው በመጨረሻ የካዱት፤ ከፍቅረ





እግዚአብሔርም የተለዩት፡፡ በመሆኑም በፍቅረ ቢጽ ጠላትን እስከ መውደድ መድረስ ማለት ሃይማኖትን የሚያስክድ ከፍቅረ እግዚአብሔርም የሚለይ ይሁን ማለት አይደለም፡፡ ፍቅረ ቢጽ የሚገለጠው በሃይማኖት ነውና! ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስም «ሞት ቢሆን ሕይወትም ቢሆን መላእክትም ቢሆኑ ግዛትም ቢሆን ኃይላትም ቢሆኑ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ፤» ያለው፡፡ ሮሜ.፰፥፴፰-፴፱፡፡ ስለዚህ በሃይማኖት ከማይመስሉን ከቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ጋር /በጋብቻ፣ በዝምድና፣ በጓደኝነት፣ ወዘተ .../ መወዳጀትና የጥፋታቸው ተባባሪ መሆን ፍቅረ ቢጽ ሊሆን አይችልም፡፡ «ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ ጽድቅ ከአመጻ ጋር ምን ተካፋይነት አለው? ፪ቆሮ.፮፥፲፬»፡፡

ይሁን እንጂ ለእንደዚህ ዓይነቱ ሰውም ሆነ በጊዜያዊ ግጭት የተጣሉት ሰው ቢኖር ከጥፋቱ ሳይተባበሩ ቢቸገር በመርዳት በቀል ሳይዙ በጸሎት በማሰብ ፍቅርን መግለጽ ያስፈልጋል፡፡ «... ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው ቢጠማ አጠጣው» ሮሜ.፲፪፥፳፡፡ ይህንንም ዮሴፍ በጠላትነት ለሸጡት ወንድሞቹ ቅዱስ እስጢፋኖስም በድንጋይ ለወገሩት ወገኖቹ ይቅርታ በማድረግ ፈጽመውታል፡፡ ዘፍ.፵፭፥፩-፲፭፤ የሐዋ.፯፥፷፡፡ እና ቅድስት ክርስቶስ ሠምራም ጠላትን በጸሎት በማሰብ በግብር አውለውታል፡፡

ዛሬ ብዙዎች ስለ ፍቅረ ቢጽ ሲናገሩ እንጂ በተግባር ሲያውሉት አይታይም፡፡ ከቤተሰባቸው ጀምሮ ሰላም የላቸውም፣ እንዳቸው ሌላውን በክፉት ዓይን ያያሉ፤ ከጐረቤቶቻቸው ጋር ስምምነት የላቸውም፤ በሥራ ቦታ እርስ በርሳቸው ይቀናናሉ ይጨቃጨቃሉ ነገር ግን ስለ ፍቅር ይሰብካሉ፡፡ ፍቅር አላቸው የሚባሉትም ፍቅራቸው የታይታና ውጭአዊ ነው፡፡ አንዳንዶችም ወረተኞች ናቸው፤ ፍቅራቸው ጊዜአዊና የአንድ ሰሞን ብቻ ያውም በጥቅም ላይ የተመሠረተ፡፡ ነገር ግን እውነተኛ ፍቅር በቃላት ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም፤ ራስን ለሌላው አሳልፎ እስከ መስጠት የሚያደርስና በተግባር የሚገለጥ እንጂ! «... በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት እንዋደድ፤» ፩ዮሐ.፫፥፲፰



www.ethiopianorthodox.org

## ፍቅረ ቢጽ በተግባር እንዴት ይገለጻል?

### *ሀ/ በመርዳት*

ፍቅረ ቢጽ የተራበን በማብላት የተጠማን በማጠጣት፣ የታረዘን በማልበስ፣ ያዘነን በማጽናናት፣ የታመመን በማከምና በማሳከም፣ ... ይገለጻል። ይህ በፍኖተ ኢያሪኮ በጹላ ተቀጥቅጦ የወደቀውን መንገደኛ እንድናስታውስ ያደርገናል። ይህ ሰው ቀና አድርጎ ውኃ የሚያጠጣው ቁስሉን የሚያክምለት እውነተኛ ወዳጅ ይሻ ነበር። ብዙዎች ከንፈራቸውን መጠውለታል። ፈሪሳውያንም እያዩ አልፈውታል። ሣምራዊው ግን ደረሰለት፤ ተቀጥቅጦ የወደቀውንና የተሰቃየውን መንገደኛ እስነሥቶ ቁስሉን አከመለት። የሚያስፈልገውን ሁሉ አድርጎ ፍቅሩን ገለጠለት። እውነተኛ ወዳጁም ሆነ። ሉቃ.፲፥፳፱-፴፯። እውነተኛ ፍቅር እንደዚህ በተግባር የሚገለጥ እንጂ በመመቸትና ባለመመቸት፣ በማግኘትና በማጣት ተወስኖ በቃላት የሚቀር አይደለም።

እንዲሁም ክርስቲያን ቤተሰቡን ሊረዳ ላሳደጉት ወላጆቹ መልካም ነገር ሊያደርግ ያስፈልጋል። ይህንን ሳይፈጽም ለተቸገሩት ሁሉ ሲመጸውት ቢውል ፍቅሩን ገልጧል ማለት አይቻልም። «ነገር ግን ለእርሱ ስለ ሆኑት ይልቁንም ስለቤተሰቦቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው፤» ፩ጢሞ.፭፥፰።

### *ለ. በኀዳጌ በቀልነት*

ክርስቲያን በተለያዩ አጋጣሚዎች ከሰው ጋር ሊጋጭ ይችላል። ይሁን እንጂ ቂም ሊይዝና ሊበቀል አይገባም። «... በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙአችሁን መርቁ ለሚጠሉአችሁ መልካም አድርጉ ስለ ሚያሳድዷችሁ ጸልዩ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና።» ማቴ.፭፥፵፬-፵፭። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለጠላት መልካም ማድረግ እንደሚገባ ከገለጸ በኋላ «ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ» በማለት ኀደጌ በቀል መሆን እንደሚገባ ተናግሯል። ሮሜ.፲፪፥፳። ስለዚህ ፍቅረ ቢጽ በቀል ሳይዙ ለጠላት መልካም በማድረግና በጸሎት በማሰብ ሊገለጽ ይገባል።



ፍሬ ሊቃውንት

### *ሐ. በማስተማር*

እውነተኛ ፍቅር ገንዘብን በማውጣት እንዲሁም በጉልበትና በዕውቀትም ይገለጣል። ፍቅር ያላቸው ገንዘባቸውን በመስጠት የተቀሩትም በጉልበታቸው ሲረዱ መምህራንም ደግሞ ዕውቀታቸውን በማካፈል ይገልጡታል። ኃጢአተኛውና እውነተኛው መንገድ የጠፋው ቃለ እግዚአብሔርን ሰምቶ በንስሐ እንዲመለስ ማይምነትና ድንቁርና እንዲጠፋ ማስተማር ፍቅረ ቢጽ ነው።

ከዚህም ሌላ «ፍቅር ይታገሳል ቸርነትንም ያደርጋል፣ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፣ አይታበይም፣ የማይገባውን አያደርግም የራሱንም አይፈልግም አይበሳጭም በደልን አይቆጥርም ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመጻ ደስ አይለውም፣ ሁሉን ይታገሳል ሁሉን ያምናል ሁሉን ተስፋ ያደርጋል በሁሉ ይጸናል፤» ፩ቆሮ.፲፫፥፬-፯።

በአጠቃላይ እውነተኛ ፍቅር የሃይማኖት ዋልታ የምግባራት ራስ ነው። ያለ ፍቅር ሃይማኖተኛ መሆን ለእግዚአብሔር መገዛትም አይቻልምና! ፍቅር የተለያዩትን የሚያዋሕድ የተራራቁትን የሚያቀራርብ የጥልን ግድግዳ አፍርሶ ሰላምን የሚያነጽ የሕይወት መሠረት ነው። ሊላው ይቅርና አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው «ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት» ብሎ እንደተናገረው አምላካችንን ከሰማያዊው ዙፋን ያወረደው፣ እስከሞትም ያደረሰው ፍቅር ነው። «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከመስጠት ድረስ ዓለሙን ወድዶታልና፤» ዮሐ.፫፥፲፮

እንግዲህ አምላካችንን እስከ ሞት ያደረሰውን ፍቅሩንና ለእኛ ያደረገልንን ውለታውን እያሰብን ለሕጉ በፍቅር ተገዝተን እርስበርሳችን» እየተዋደድን ለሰማያዊ መንግሥት እንድንበቃ የእርሱ የአምላካችን ፈቃድ የቅዱሳን አማላጅነት አይለየን።



www.ethiopianorthodox.org

## «ሰው ዝም ብሎ የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ ቢያደርግ መልካም ነው::» /ሰቆ.ኤር.፫÷፳፮/

*ቀሲስ ያሬድ ገ/መድኅን*

በመከራ ዘመን ለእስራኤል ልጆች የተነገረ ቃል ነው:: ተናጋሪው ነቢዩ ኤርምያስ ነበር:: ነቢዩ ከእግዚአብሔር ፈቃድና ሐሳብ ውጭ በመሆናቸው ለመከራ የተጋለጡ በምርኮ ምክንያት በባዕድ ሀገር የሚሰቃዩ ወገኖቹን የፈጣሪን ምሕረት በዝምታ ጠብቀ ይላቸዋል:: በራሳቸው ጥበብ ምርኮን እናስወግድ ብለው አላስፈላጊ ሰማዕትነት ውስጥ እንዳይገቡ ከዚያ ይልቅ እግዚአብሔር የሚሠራውን በዝምታ እንዲጠብቁ ይመክራቸዋል::

ዝምታ አስፈላጊ ነው:: የፈጣሪያችሁን ምሕረት ተስፋ እያደረጋችሁ በዝምታ ጠብቁ የተባለውም ለዚህ ነው:: በመሠረቱ «ዝምታ» ስንል ዓይነቱ ብዙ ነው:: ለምሳሌ ሲናገሩን ሲተቹን ... ሰምቶ መልስ አለመስጠት ዝምታ ነው:: መንፈሳዊ ሰው ሰምቶ ማሳለፍ ስላለበት ነቃፊዎች ቢመጡበት ተናግረው የሚያናግሩ ቢቀርቡት በዚህ የዝምታ ዓይነት /መልስ ባለመስጠት/ ድል ይነሳቸዋል:: ጌታችን በስቅለቱ ወቅት አይሁድ ሲሰድቡት በዝምታ ሲሰማቸው የምናየው ለዚህ ነው:: ይህ ዝምታ ግን ሁልጊዜ ላይሠራ ይችላል:: አንዳንዴ አስፈላጊ የማይሆንበት ጊዜ አለ:: ሃይማኖትን የሚደፍር፣ በሕልውና ላይ የሚነግ ትህትናን እንደ ስንፍና የሚቆጥር ሲኖር በመጠኑም ቢሆን መናገር ያስፈልጋል:: ነቢዩ ኢሳይያስ «ስለ ጽዮን ዝም አልልም» ይለናል:: ኢሳ.፷፪÷፩:: የእናታችን የጽዮንን ክብር የሚያቃልሉትን በዝምታ ማሳለፍ አልችልም:: ክብሯን እየመሰከርኩ መልስ እሰጣቸ ዋለሁ ሲል ነው:: አባ እንጦንስ በዘመኑ ከበዓቱ ወጥቶ አያውቅም:: መናፍቃን በቤተ ክርስቲያን ላይ ሲነሡ ግን ሃይማኖትን ለመመስከር መናፍቃንን ለማሳፈር ይወጣ ነበር:: ምክንያቱም ወቅቱ በዝምታ የሚታለፍ ስላል ነበረ ነው:: ከዚህ ውጭ በራስ ህልውና ላይ ሲመጡ መብትን ሲነጠቁም መናገር የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ:: አባ አጋቶን ድንጋይ ጎርሶ





የኖረ አባት ነው:: ድንጋይ ከጎረስ በኋላ ተናግሮ አያውቅም:: ሰይጣንም ብዙ ጊዜ እየመጣ ይሰድበው እርሱም ሰምቶ እንዳልሰማ ሆኖ ያሳልፍ ነበር:: አንድ ቀን ግን «መናፍቅ አንተ» ብሎ ስለሰደበው ይህንን ሰምቶ ማሳለፍ አልቻለም:: ስለዚህ ድንጋዩን እንሥቶ «መናፍቅ»ንን አይደለሁም ብሎ መለሰ:: ሆኖም መብት ሳይጣስ ሃይማኖታዊ በሆነ ጉዳይ ላይ ሳይሆን በተገኘው ሁሉ ግን መናገር አይገባም::

የሰው ልጅ በድርጊቱ የሚናገርበት ወይም ዝም የሚልበት ወቅት አለ:: ለምሳሌ አንድ ሰው ፈጣሪው ሁሉን እንደሚያደርግለት አስቦ አንተ ታውቃለህ በማለት ለፈጣሪው ሁሉን ቢሰጥ ይህ ዝምታ ነው:: ማድረግ የሚገባውን አድርጎ ከዚህ በላይ የአንተ ፈንታ አይደለም፡ ያሰብኩትን አስፈጽመኝ ብሎ ውጤቱን ለአምላኩ ቢተው ይህ ዝምታ ነው:: በተቃራኒው ደግሞ ያሰብኩት ካልተሳካ ብሎ ቢጨነቅ ሐሳብ ቢያበዛ ከዝምታ ውጭ መሆኑ ነው:: የድርጊት ዝምታ የሚባለው መታገሥ ልቅደም አለማለት ነው::

ከላይ ባየነው ምስራፍ የተጠቀሰውም ይህ ነው:: ሰው ዝም ብሎ እግዚአብሔርን ተስፋ ያድርግ ያለው በትዕግሥት ሆኖ መንግሥቱን ለእግዚአብሔር አደራ ሰጥቶ ሳይጨነቅ ሐሳብ ሳያበዛ በተስፋ ይጠብቅ ሲል ነው::

ነቢዩ እንዳለው የሰው ልጅ ሲቸገር ሲጎሳቆል ሲራብ ሲጠማ ራሱን ሁሉን ማድረግ ለሚችል ፈጣሪ ሰጥቶ መታገሥ አለበት:: አለበለዚያ ግን የፈጣሪውን ቸርነት ተስፋ ማድረግ ትቶ በራሱ ጥበብ ለመጓዝ ቢሞክር ሕይወት በራሱ ውስብስብ ይሆንበታል:: ነገሮች ከቁጥጥሩ ውጭ ሆነው ይበላሹበታል:: ጌታችን «ከእናንተ ተጨንቆ ከቁመቱ ላይ አንድ ክንድ የሚጨምር ማን ነው» /ማቴ.፮÷፳፯/ እንዳለ ሰው በገዛ አካሉ ላይ የሚሆነውን እንኳን መቆጣጠር የማይችልበት ወቅት አለ:: ስለዚህ ሁል ጊዜ ራሱንም ሆነ በዙሪያው ያለውን ለፈጣሪው መስጠትና መታገሥ ይገባዋል::

አንዳንድ ጊዜ ውስጣችን ሰላም ሲያጣ ያሰብነው አልሳካ ሲለን የእግዚአብሔርን ቸርነት እንረሳለን:: ትላንት አብሮን የነበረውን ዛሬም



www.ethiopianorthodox.org

አብሮን ያለውን ነገም ረጅሙን ጉዞ የሚያስጉዘንን አምላክ እንዘነጋለን። በራሳችን ጥበብ የምናመጣው ያለ ይመስል ችግሮችን ለመፍታት ብቻችንን ተነሥተን ያለ የሌለ ኃይላችንን እንጠቀማለን። እግዚአብሔርን ትተን በራሳችን እንሮጣለን። ግን ሁሉም እንዳሰብነው አይሆንም። እርሱ በወሰነው ሰዓትና ወቅት ካልሆነ በእኛ ሐሳብ የሚሆን ስለሌለ የሩጫችን ፍጻሜ በተነሣንበት ቦታ መልሰን ማረፍ ይሆናል። ስለዚህ የሰው ልጅ ሁል ጊዜ እግዚአብሔርን እየጠበቀ በተስፋ ቢጸናና በትዕግሥት መጨረሻውን ቢመለከት መልካም ነው።

አባታችን አዳም ከገነት ሲወጣ ያጣትን ርስት ለማግኘት ብዙ እንደጣረ መጻሕፍት ይነግሩናል። ደሙን ከእህል ጋር ለውሶ እስከ ማቅረብ ደርሶ ነበር። ግን ይህንን ሁሉ ቢያደርግም ገነትን ማግኘት አልቻለም። እርሱ ባሰበው ወቅትና ጊዜ ወደ ቦታው አልተመለሰም። በዚህ ፈንታ ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ተገባለት። ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በኋላ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ተባለ። ይህንን የተስፋ ቃል የሰማው አዳም አልተከራከረም። አንተ ፭ሺ፭፻ ዘመን ብትልም እስከዚያው እኔ በራሴ እሞክራለሁ በሦስተኛውና አራተኛው ሺህም ልገባ እችላለሁ አላለም። ከዚህ ይልቅ ሲያል ሆኖ የተገባለት ቃል ኪዳን እስኪፈጸም መጠባበቅ ጀመረ። በእርሱ ሩጫና ጥበብ የማያመጣው ስለሌለ የአምላኩን ቸርነት እየጠበቀ ቆየ። እግዚአብሔር ትዕግሥቱን አይቶ ደረሰለት። በወሰነለት ጊዜና ሰዓት ከሞት አዳነው።

በእኛም ሕይወት ያጣነውን የምናገኝበት ያሰብነው የሚሳካበት ጊዜ አለ። ለዚህ ግን በትዕግሥት መጠበቅ ይገባናል። አዳምን ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በኋላ ያዳነ ፈጣሪ እንደማይረሳን አስበን መታገሥ ይኖርብናል። ዝምታ የተባለው ይህ ነው። አንተ ሁሉን ማድረግ ትችላለህ ብሎ ለፈጣሪ መስጠት፣ የአምላክን መለኮታዊ ጥበብ በትዕግሥት መጠበቅ።

አረጋዊው ስምዖን የጌታችንን መወለድ ሳያይ እንደማይሞት ተነገረው። ሉቃ.፪፥፳፮። ጊዜው ደርሶ የፈጣሪውን ልደት እስኪመለከት





፫፻ ዘመን ኖረ። እርጅና እየተጫነው ሰውነቱ እየደከመ ቢሄድም ሁሉን በትዕግሥት ጠበቀ። እግዚአብሔር የገባለት ቃል ኪዳን ነበርና ይኸው እስኪፈጸም ቆየ። እኔም እርጅና ተጫነኝ አንተም ዘገየህ አላለም። አንተ የምትቆይ ከሆነ እኔን ውሰደኝ ብሎ አለመነም። ሁሉን በጊዜው የሚፈጽም አምላክ በጊዜው እንደሚያሳየው አምኖ ጸና። በዚህ የተነሣ በእርጅናው ወራት ከቤተ መቅደስ ሲወጣ የተሰጠው ቃል ኪዳን ተፈጸመለት። ጌታችንን በእናቱ እቅፍ ሆኖ አየ። ከዚህ በኋላ ነው «ዓይኖቼ ማዳንህን አይተዋል፤ እንግዲህ እንደ ቃልህ ባሪያህን ታሰናብተዋለህ» ያለው። /ሉቃ.፪፥፴/።

ዓይኖቻችን የእግዚአብሔርን ማዳን የማያዩበት በሰላም ግቡ የምን ባልበት ጊዜ አለ። የጎበጠ ሲቀና የተበላሸ ሲስተካከል የጠፋ ሲመለስ... የምናይበት ጊዜ አለ። ቢዘገይም እግዚአብሔር ሊሠራው ያሰበው ሁሉ አንድ ቀን ይከናወናል። የቤተሰባችን የራሳችንና የቤተ ክርስቲያን ችግርና ጭንቀት ተወግዶ የምናይበት ጊዜ ይኖራል። ይህን ወቅት መቼም ይሁን መች የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እኛ እንደስምዖን ዓይኖቻችን ማዳኑን የሚያዩበት ጊዜ በትዕግሥት /በዝምታ/ መጠበቅ ነው ድርሻችን።

አባታችን አብርሃም ዘሩ እንደ ምድር አሸዋ እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደሚበዛ ተነገረው። /ዘፍ.፲፭፥፭/። ይህን ቃል ከሰማ በኋላ ግን ተፈተነ። ልጅ ሳይወልድ ለብዙ ዘመን ኖረ። እርሱም ሚስቱም እስኪያረጁ ድረስ ፍሬ አልባ ሆነው ቆዩ። እንዲያውም ሣራ ልጅ መውለድ አትችልም የሚባልበት የእርጅና ደረጃ ደረሰች። በሴቶች ያለ ልማድ ከሰውነቷ ቀረ። ይህ ሁሉ ሲሆን ለምን ብለው አልተቃወሙም። በመጨረሻ እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገለጠለት። ሚስቱ ሣራ ፀንሳ ወንድ ልጅ እንደምትወልድ፣ ማኅፀኗን አለምልሞ ዘር እንደሚሰጣት ነገረው።

የእኛም ሕይወት እንዲሁ ነው። ነገሮች ሁሉ ተበላሹ ባልንበት ወቅት ባላሰብነው ጊዜና ሰዓት እግዚአብሔር ሥራ ይጀምርና ችግራችንን ይፈታል። አብርሃምን ከርሞ የልጅ አባት ትሆናለህ እንዳለው



www.ethiopianorthodox.org

እኛንም ከርሞ ይህን ታገኛለህ እንዲህ ትሆናለህ ይለናል:: ያጣነው ጽናት ከሆነ ጽናት፣ ትዕግሥት ከሆነ ትዕግሥት፣ ዕውቀት ከሆነ ዕውቀት፣ ፍቅር ከሆነ ፍቅር ያድለናል:: ሌላም ምድራዊ ሥጋዊ ችግር ካለብን ያንን ሰጥቶ ያስደስተናል፣ ሥራ ላጣነው ሥራ፣ ትዳር ለሌለው ትዳር፣ ቤት ለምናስብ ቤት የሚሰጥበት ጊዜ አለው:: እንደ አብርሃም እኛም ተፈጸመ የምንልበት ጊዜ መድረሱ አይቀርም:: ለዚህ ግን ዝምታ ያስፈልጋል:: ጊዜ ሁሉ ያንተ ነው ለእኔ የመሸ የምለው ወቅት ለአንተ ጠዋት ነው:: እኔ ተፈጸመ የምለው ጊዜ ላንተ መነሻ መጀመሪያ ነው ብሎ መታገሥ:: ነቢዩ በዝምታ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርጉ የሚለንም ለዚህ ነው::

ነቢይቱ ሐና ከነገደ አሴር የተወለደች የፋኑኤል ልጅ ነበረች:: ሉቃ.፪+፴፮:: ይህች ሴት አሥራ አምስት ዓመት በድንግልና ከኖረች በኋላ ባል አግብታ ሰባት ዓመት ቆየች:: ከዚያም ከባሏ ተፋታ ሰማንያ አራት ዓመት በቤተ መቅደስ እያገለገለች ኖረች:: በአጠቃላይ መቶ ስድስት ዓመት እስኪሆናት ከቤተ መቅደሱ ሳትርቅ ትንቢት እየተናገረች በጾምና በጸሎት ተጠምዳ የጌታችንን መምጣት እየጠበቀች ኖረች:: በመጨረሻም ጌታችን ሲወለድ ተነሥታ ለሕዝቡ ሁሉ መስከረች:: የተወለደው ሕፃን የዓለሙ መድኃኒት እንደሆነ ነገረች:: ከቤተ መቅደስ ባለመራቋ ይህንን ሁሉ ዘመን በመታገስ የምትጠብቀውን ሁሉ ለማየት በቃች:: ትንቢቷ ሠመረላት:: አስቀድማ የተናገረችለት እርሱ መሆኑን አሳይታ አለፈች::

እኛም እንደ ነቢይት ሐና ነገ ይሆናል ብለን የምናስባቸው ብዙ ጉዳዮች አሉ:: በቤተ ክርስቲያን አካባቢ እንዲከሰቱ የምንመኛቸው ምኞቶች አሉ:: ለምሳሌ ሰው ሁሉ ንስሐ ቢገባ፣ ቆራቢ ቢሆን፣ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ቢመለስ ምኞታችን ይሆናል:: ሰንበት ት/ቤቶች ሁሉ ጽናት ያለው መንፈሳዊ ወጣት ቢያፈሩ አንድ ዓይነት የዕድገት ደረጃ ይዘው ቢራመዱ ብለን እናስብ ይሆናል:: ጉባኤያት እየሰፉ የአብነት ት/ቤቶች ችግራቸው ተወግዶ ከአሁኑ በበለጠ ተማሪ ሲሰበሰብባቸው ማየትም እንሻ ይሆናል:: ይህንን ያሰብነውን በዓይናችን ለማየት ግን ትዕግሥት ሊኖረን ይገባል:: እንደ ነቢይት ሐና ነገን ለእግዚአብሔር





ሰጥቶ ወገብን ታጥቆ ማገልገል ያስፈልጋል:: እግዚአብሔር አንድ ቀን ሐሳባችንን አሳክቶ እንደሚያሳየን ምኞታችንን ፈጽሞ እንደሚያስደስተን በማመን በዝምታ መጓዝ ይኖርብናል:: ነገን በተስፋ ከጠበቅነው ብሩህ ሆኖ እንደሚገለጥ ማመን ይጠበናል::

ጻድቁ ኢዮብ ልጆቹን ሀብቱን በአንድ ወቅት አጣ:: /መጽሐፈ ኢዮብ ፩ እና ፪/:: እግዚአብሔርን ካድ ብላ ሚስቱ እስክትፈትነው ድረስ ተቸገረ:: ሰውነቱም ተገልብጦ በቁስል ተመታበት:: ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ያጣውን እያሰበ አልተማረረም:: ይልቁን እግዚአብሔር ነገ እንደሚገለጥለት የነሣውን ሰጥቶ ሊያስደስተውም እንደሚችል እያሰበ በትዕግሥት ጠበቀ:: በዙሪያው ያለው ፈተና የሰዎች ጉትጎታ ሳይረብሸው በዝምታ ቆየ:: ስለዚህም ፈጣሪው ትዕግሥቱን ተመልክቶ የወሰደበትን ሁሉ መለሰለት:: የቀደመ ሀብቱን ጸጋውን አጎናጸፈው፤ ልጆችንም ሰጠው::

ዛሬም ቀድሞ የነበረንን ያጣን መንፈሳዊ ጥንካሬያችን ተሰርቆ ጽናታችን ጠፍቶ ታሪክ ተራኪ ሆነን የቀረን እንኖራለን:: ድሮ እኮ አባቶቻችን ቀድስ ነበር:: ያን ጊዜ አጸለይ ነበረ:: መንፈሳዊ ሕይወቴ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ነበረ በማለት ብቻ የምንናገር የትላንቱን ከማሰብ ውጭ ዛሬ የምንለው የሌለን ውሉ እንደጠፋበት ቋጠሮ መንፈሳዊ ሕይወታችን የተናጋብን እንጠፋም:: እንዲህ የሆንን እግዚአብሔር ወደ ቀደመ ቦታችን እንዲመልሰን ማጉረምረም ሳይሆን መታገሥ ይገባናል:: ስለማይፈልገኝ ተወኝ:: ጽናት ላጣ መንፈሳዊ ጥንካሬ ሲለየኝ ዐይቶ እንዳላየ ሆነ ብለን የወሰደብንን ጸጋ እያሰብን ከማጉረምረም ነገ የቀድሞው ሀብታችን እንደሚመለስ ተስፋ አናድርግ:: ሳንማረር ፈጣሪን ደጅ እንጥና፤ አቤቱ መሬት መሆኔን አስብ የበደልኩትን በደል ሳትመለከት ወደ ትላንትና ጽናት ወደ መጀመሪያው መንፈሳዊ ሕይወት መልሰኝ እንበለው:: የኢዮብን ትዕግሥት አይቶ የወሰደበትን ሁሉ እንደመለሰለት እኛም ከታገሥን የተነጠቅነውን ሁሉ መልሰን እናገኛለን:: ነገ እንደ ትላንቱ ብሩህ ዘመን ሆኖ ይገለጥልናል:: ለሁሉም ግን በዝምታ /በትዕግሥት/ ፈጣሪን ደጅ መጥናት ያስፈልጋል:: ችግርን መከራን በጸጋ ተቀብለን እርሱን ተስፋ በማድረግ በትዕግሥት /በዝምታ/ ለመጽናት እንድንበቃ ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን::



www.ethiopianorthodox.org

## «የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ» ዘጸ.፫፥፯

*በቀሲስ ደጀኔ ሽፈራው*

ይህን ቃል የተናገረው እግዚአብሔር ነው። ሕዝቤ የተባሉት እስራ ኤል ዘሥጋ ሲሆኑ ቃሉ የተነገረበት ቦታ ደግሞ ደብረ ሲና ነው። ይህ ተራራ የሚገኘው ከግብጽ በስተምሥራቅ ነው ቃሉን የተናገረውም ሰው ሙሴ ነው። ሙሴ በእግዚአብሔር ጥበብ በፈርዖን ቤተ መንግሥት ያደገ ቢሆንም የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እንቢ ብሎ ከግብጽ ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ ባለጠግነት መሆኑን አስቦ፣ ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መርጦ የተሰደደ ሰው ነበረ። ዕብ.፲፩፥፳፭።

በምድያም ምድር እረኝነት ተቀጥሮ የዮቶርን በጎች በሲና ተራራ ላይ ሲጠብቅ እግዚአብሔር በእሳት ነበልባል ምሳሌ ከዕፀ ጳጦስ ተዋሕዶ ተገለጠለት። እሳቱ ሐመልማሏን ሳያቃጥላት ሐመልማሏ እሳቱን ሳታጠፋው አየ። ተደንቆ ወደ ምሥጢረ ተዋሕዶው በቀረበ ጊዜ የእግዚአ ብሔርን ድምፅ ሰማ። የቆመበትም ሥፍራ ቅዱስ በመሆኑ ጫማውን እንዲያወልቅ ተነገረው። የተነገረውንም ፈጸመ። እግዚአብሔርን ያይ ዘንድ ፈርቶ ፊቱን ሸፈነ።

እግዚአብሔርም ከአስገባሪዎቻቸው የተነሣ የሚጮሁትን የሕዝቡን ጩኸት ሰምቶ መከራቸውን በእውነት አይቶ ስቃያቸውንም ዐውቆ ከግብጻውያን እጅ አድኖ ማርና ወተት ወደምታፈስሰው አገር ወደ ሰፊይቱና ወደ መልካሚቱ ምድር ወደ ምድረ ከነዓን ያወጣቸው ዘንድ እንደወደደ ለወዳጁ ለሙሴ ነገረው። እንደተናገረውም ከግብጽ በተአ ምራት አውጥቶአቸው ከነዓንን በማውረስ ቃሉን ፈጸመ።

ግብጽ የሲኦል፣ ከነዓን የገነት፣ ዕፀ ጳጦስ የድንግል ማርያም፣ እሳት የመለኮት፣ ደብረ ሲና የቤተ ክርስቲያን፣ ሙሴ የካህናት፣ በትሩ የመስቀል፣ በጐች የምእመናን ምሳሌዎች ናቸው። በረሀብ ምክንያት ወደ ግብጽ የተሰደዱ እሥራኤል ዘሥጋ በግብጻውያን እጅ ተይዘው እንደተቀጠቀጡ፣ በኃጢአት ምክንያት ወደ ሲኦል ተሰድደው የነበሩ





ነፍሳትም በመከራ ተይዘው በአግረ አጋንንት ተረግጠው ይኖሩ ነበር። ያኔ እነዚያን ለማዳን በእሳት ምሳሌ ወርዶ እንደታየ ከግብጽ አውጥቶ ከነዓንን አውርሶ እንዳዳናቸው በሲኦል የነበሩትንም ነፍሳት ከመከራ ከጩኸት ከስቃይ ለማዳን ከሰማይ ወረደ። ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷም ነፍስ ነሥቶ ተወለደ። ሰው ሆነ። በመስቀል ላይም ስለ እኛ ብሎ ሥጋውን ቆረሰ። ደሙን አፈሰሰ። በአካለ ሥጋ ወደ መቃብር ወርዶ ሙስና መቃብርን አጠፋ። በአካለ ነፍስም ወደ ሲኦል ወርዶ ነፍሳትን አወጣቸው ወደ ገነትም አስገባቸው።

እንግዲህ እሱ እንዲህ አድርጐ ከሲኦል ካወጣን በኋላ ለምንድነው ወደ ሲኦል የምንጓዘው? በደልን መፈጸም በኃጢአት መመላለስ ወደ ሲኦል መጓዝ ነው። ምናልባት የተያያዝነው መንገድ ቅን ሊመስለን ይችላል። የእግዚአብሔር ቃል ግን «ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው።» ይለናል። ምሳ.፲፬፥፲፪። ዛሬም መከራ፣ ጩኸትና ስቃይ አለ። በዓለማችን በመከራ ማዕበል የማ ይንገላታ ሰው የለም። ለመሆኑ መከራ ለምን ይመጣል? መከራስ ጥሩ ነው ወይስ መጥፎ? በእንዴት ያለ የመከራ ጊዜስ ነው እግዚአብሔር በፍቅር የሚያየን?

፩. መከራ የኃጢአት ውጤት ሊሆን ይችላል። እኛ ፈቃደ እግዚአ ብሔርን ትተን በፈቃደ ሥጋ ስንመራ መከራ ይመጣል። የሥጋ ምኞ ታችንን እና የዐይን አምሮታችንን ብቻ ለመፈጸም ስንሮጥ በመከራ ወጥመድ እንያዛለን። ጣዖትን ለማምለክ፣ ለሟርት፣ ለጥል፣ ለክርክር፣ ለቅንዓት፣ ለቁጣ፣ ለአድመኝነት፣ ለመለያየት፣ ለመናፍቅነት፣ ለመግ ደል፣ ለስካር፣ ለዘፈንና ይህንን ሁሉ ለመሰለው ስንጣደፍ መከራ ይመ ጣብናል። እንደሥራችንም ይከፈለናል። የምናጭደውም ያንኑ የዘራ ነውን ነው። ሞትን ወይም ሕይወትን «በገዛ ሥጋው የሚዘራ ከሥጋ መበስበስን ያጭዳልና። በመንፈስ ግን የሚዘራ ከመንፈስ የዘላለምን ሕይ ወት ያጭዳል።» ገላ.፮፥፰።

፪. መከራ፣ ሰዎች ከክፋታቸው እንዲመለሱ የእግዚአብሔር ቅጣት ሊሆን ይችላል። ብዙውን ጊዜ ሰዎች በክፋት እየባሰን ስንሔድ እንጂ



www.ethiopianorthodox.org

ስንመለስ አንታይም። መልካሙን ትተን የምንጓዘው በክፉ መንገድ ነው። መንገዱም ሰፊ ስለሆነ ለጊዜው ለጉዞ አያስቸግረንም። እንኳን ለወገኖቻችን ለራሳችንም ቢሆን ክፉዎች ነን። እግዚአብሔር ግን ደግ ስለሆነ ስለሚወደንም በክፋት ወደ ጥፋት ስንሮጥ ዝም ብሎ አይመለከተንም። በመከራ አለንጋ እየገረፈ እየገሠፀ ይመልሰናል። እኛም በመከራው ሳንመረር ለጥቅማችን መሆኑን ዐውቀን ከክፋት ወደ በጎነት እንመለስ። አባታችን ስለሆነ ከቤት ወጥተን በዚያው ጠፍተን እንዳንቀር በመከራ ቀጥቶ በደሙ ወደ መሠረታት ቤቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንድንመለስ ይፈልጋል። «ልጄ ሆይ የእግዚአብሔርን ተግሳፅ አትናቅ በገሠፀህም ጊዜ አትመረር። እግዚአብሔር የወደደውን ይገሥፃልና። አባት የሚወደውን ልጁን እንደሚገሥፅ።» ምሳ.፫፥፲፪

፫. መከራ፣ ሰዎች የሚፈተኑበት የሚጸኑበትም ነው። ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን እውነተኞች ክርስቲያኖችም በመከራ እሳት ይፈተናሉ። ረሀቡን፣ ጥማቱን፣ መራቆቱን፣ ስደቱን፣ እሳቱን ስለቱን ሁሉንም ነገር ታግሰው በመከራ መካከል ጸንተው ይቆማሉ። በዐለት ላይ እንደተመሠረተው ቤት አይወድቁም። የመከራው ዝናብ አያደክማቸውም። ጐርፉ አይጠራርጋቸውም። ነፋሱም አያንሳፍፋቸውም። በመከራውም ብቻ አይደለም። በዚህ ዓለም ያለው ደስታው፣ ሀብቱ፣ ሥልጣኑ ይኸን የመሳሰለውም ሁሉ አይችላቸውም። በጊዜውም ያለጊዜውም ጸንተው ይገኛሉ። እኛስ? የጣለን ምንድነው? ለምንስ መጽናት አልቻልንም? ብለን ራሳችንን የምንጠይቀው ዛሬ ነው። ነገ የእኛ አይደለምና። የእኛ ችግር በቃሉ አለመታነጻችን ነው። በቃሉ ብንታነጽ ኖሮ በእምነት ቆመን በምግባር ጸንተን እንገኝ ነበረ። ከእንግዲህ ራሳችንን እናስተካክል። በዓለሙ ሐሰት በነገሠበት ዘመን ስለ እውነት በመመስከር የሚመጣብንን መከራ በትዕግሥት እንቀበል። በመከራችን እንመካ እንጂ አንፈር በመከራ ጊዜ ሰዎች ባያዩንም እግዚአብሔር በእውነት ያየናል። «ነገር ግን መከራ ትዕግሥትን ትዕግሥትም ፈተናን፣ ፈተናም ተስፋን፣ እንዲያደርግ እያወቅን በመከራችን ደግሞ እንመካለን።» ሮሜ.፭፥፫። መከራን በትዕግሥት መቀበል ክርስቶስን መምሰል ነው። በእምነት የምንቀበለው መከራ ትዕግሥተኞች እንደሚያደርገን እንወቅ። እስከመጨረሻው የታገሠ እርሱ ይድናልና በትዕግሥታችሁ ብዛት ነፍሳችሁን ታድናላችሁ የተባለውም የሚፈጸመው በመከራ ነው። በመሆኑም በመከራ ጊዜ ጸንቶ መገኘት ይገባናል።

፬. በእምነት፤ በመከራ መካከል ማለፍ ለክብር ነው። በመከራ የተፈተነ እምነታችን ያስከብረናል። ያስመሰግነናል። ለጸጋም ያበቃናል። በመከራ ጊዜ በሐዘን ብንጨበጥም ለጥቂት ጊዜ ነው። ነገር ግን በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ የሚከብር የተፈተነ እምነታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ ለምስጋናና ለክብር ለሙገሴም ይገኝ ዘንድ አሁን ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል።» ፩ጴጥ.፩፥፯።

፭. መከራ፣ ሰዎች በይበልጥ እግዚአብሔርን እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል። እኛ ምድራውያን በዚህ ዓለም ሳለን ሁሉ ነገር ሲሟላልን በጥበባችን በጉልበታችን እና በሀብታችን የሆነ እየመሰለን በራሳችን መመካት እንጀምርና ወደ ስህተት እናመራለን። ሐሰት መናገር፣ ማጭበርበር ብልህነት ይመስለናል። ዝሙት፣ ርኵሰት ሳይሆን ቅድስና ይመስለናል። ነፍስ መግደል እንደ ኃጢአት ሳይሆን እንደ ጽድቅ ይታየል። ነውርን እንደ ክብር እንቆጥራለን። ሕጉን መጣስ ትእዛዙን ማፍረስ ድንቁርና ሳይሆን ዕውቀት ነው ወደማለት እናዘነብላለን። በዚህ ጊዜ የገዛ ሥራችን መከራን ጐትቶ ያመጣብናል እግዚአብሔርም አቅማችንን ዐውቀን እጅ እስክንሰጥ ዝም ይለናል።

እኛም መከራው ያስተምረንና እግዚአብሔርን ዐውቀን ሕጉን ወደ መፈጸም ትእዛዙን ወደ መጠበቅ እንመለሳለን። መጀመሪያም ቢሆን ሳንጨነቅ መሳታችን ትዝ ይለናል። «እኔ ሳልጨነቅ ሳትሁ አሁን ግን ቃልህን ጠበቅሁ» መዝ.፻፲፰፥፷፯

፮. መከራ፣ ግብዞችን ከእግዚአብሔር ያርቃቸዋል። ያልሆኑት ወይም የማያውቁትን ለመምሰል መመጻደቅ ግብዝነት ነው። እምነትና ምግባር ሳይኖር ከእግዚአብሔር በራቀ ልብ በሰው ፊት ራስን ጻድቅ ማድረግ ግብዝነት ነው። ጸሐፎችና ፈሪሳውያን ግብዞች ነበሩ። ግብዞች





www.ethiopianorthodox.org

በመከራ ጊዜ ይክዳሉ በክህደት ሲወድቁም አወዳደቃቸው የከፋ ይሆናል። እኛስ ግብዞች አይደለንም ወይ? ክህደት ሲባል በቃል ብቻ አይደለም። ክፉ መሥራትም ክህደት ነው ከዚህም ሁሉ ጋር ግብዞች በመሆናችን ጥቂት መከራ መታገሥ እየቃተን በአሳብ በቃልና በሥራ ከእግዚአብሔር ርቀናል። «በጭንጫ ላይ የተዘራውም ይህ ቃሉን ሰምቶ ወዲያው በደስታ የሚቀበለው ነው። ነገር ግን ለጊዜው ነው እንጂ በእርሱ ሥር የለውም። በቃሉ ምክንያትም መከራ ወይም ስደት በሆን ጊዜ ወዲያው ይሰናከላል።» ማቴ.፲፫÷፳።

፯. መከራ ለእውነተኞች ይጠቅማል። በእውነተኞች ላይ መከራ የሚመጣባቸው ለበጐ እንጂ ለክፉ አይደለም። በመከራ መካከል ካለፉ በኋላ ክብራቸው ይገለጣል። ጽናታቸው ይታወቃል። እኛ ግን መከራ በመጣ ጊዜ እንደነግጣለን። መከራ ሁሉ ለክፉ እየመሰለን እንማረራለን። ተሉም ተስፋ እንቆርጣለን። የሚታደገንም እንደሌለን እንጨነቃለን። እንዲህ መሆን ግን አይገባም። እውነትን ይዘን ስለ እውነት በምንመሰክርበት ጊዜ የሚመጣውን መከራ ሁሉ ለበጐ እና ለጥቅማችን እንደሆነ በማመን በጸጋ መቀበል አለብን። «እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጐ እንዲደረግ እናውቃለን።» ሮሜ.፰+፳፰።

፰. መከራ፣ ወደ ክብር ይመራል። ክርስቶስን ለመከተል ወይም በመከራው እርሱን ለመምሰል የምንፈልግ ከሆን ሰውነታችንን ለመከራ አሳልፈን ሰጥተን ጨክነን ነፍሳችን ከሥጋችን የሚለይበትን መከራ እንኳ ቢሆን መቀበል አለብን። በዚህም የዘላለምን ክብር እናገኛለን። ነገር ግን ወደ ዘላለም ክብር የሚመራንን ጥቂት መከራ ጨክነን መቀበል አቅቶን ብንሸሽ የዘላለም መከራ ይመጣብናል። «እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ። መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ። ... ስለ እኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያገኛታል።» ማቴ.፲፮÷፳፬። መስቀልን መሸከም ማለት መከራን መታገሥ ማለት ነው።

፱. ምእመናን መከራን በደስታ ሊቀበሉ ይገባቸዋል። ቅዱሳን የተለያየ ጸዋትወ መከራ ሲቀበሉ አንድም ቀን አዝነው አያውቁም ነበር።





እንዲያውም መከራን ይናፍቁ ነበረ። እሳቱ ስለቱ ደስታቸው ነበር። እኛንስ የሚያስደስተን ምንድነው? ብዙዎቻችን የሚያስደስተን የሥጋ ፍላጐታችን የዐይን አምሮታችን ሲሟላ ነው። ከዚህም በላይ በወገኖቻቸው ላይ ግፍ በመፈጸም በመግደል በሐሰት በመክሰስና በመወንጀል ደሀ በመበደልና ፍርድ በማዳደል የምንደሰትም አለን። የክርስቶስ የሆኑ ሁሉ ግን ደስ የሚላቸው ስለ እውነት ብለው መከራን ሲቀበሉ ብቻ ነው። «ሐዋርያትንም ወደ እነርሱ ጠርተው ገረፏቸው በኢየሱስም ስም እንዳይናገሩ አዝዘው ፈቱአቸው እነርሱም ስለስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለ ተቆጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ።» የሐዋ.፭+፵፩። «ወንድሞቼ ሆይ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ በውቃችሁ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት» ያዕ.፩+፪።

፲. በመከራ ጊዜ ድንቅ ነገር እንደመጣ መደነቅ አይገባም። ብዙዎች መከራ ሲመጣብን እንደ ድንቅ ነገር ቆጥረን እንረበሻለን። በሁሉ እግዚአብሔርን ማመስገን ሲገባን እናማርራለን። ቀኑን በትካዜ እናሳልፋለን። ሌሊቱን ደግሞ በአሳብ ውጣ ውረድ ያለ እንቅልፍ እናድራለን። ሰው የሚባል ነገር ያስጠላናል። አካባቢያችን ያስጠላናል፡ ራሳችንንም ያስጠላናል። ተስፋም እንቆርጣለን። ክርስቲያን ግን በእምነት ቆሞ በምግባር ጸንቶ ነፍስን ከሥጋ የሚለይ አሰቃቂ መከራ ቢመጣ እንኳ አይደነቅም። እንግዲህ ክርስቲያኖች ከሆንን ሃይማኖት እንደሌለው ሰው ነፍስ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም ክፉ አድራጊ በመሆን ወይም በሌሎች ሥጋውያን ጉዳዮች በመግባት መከራ እንቀበል ዘንድ አይገባንም። ክርስቲያኖች በመሆን መከራን ብንቀበል ግን ስለዚህ ጸጋው እግዚአብሔርን እናመስግን እንጂ አንፈር። አንሸማቀቅ።

«ወዳጆች ሆይ በእናንተ መካከል እንደ እሳት ሊፈትናችሁ ስለሚሆነው መከራ ድንቅ ነገር እንደመጣባችሁ አትደነቁ። ነገር ግን ክብሩ ሲገለጥ ደግሞ ሐሴት እያደረጋችሁ ደስ እንዲላችሁ በክርስቶስ መከራ በምትካፈሉበት ልክ ደስ ይበላችሁ። በክርስቶስም ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ» ፩ኛጴጥ.፬÷፲፪



www.ethiopianorthodox.org

፲፩. መከራ ከፍጹምነት መዓርግ ያደርሳል:: ሰው ታግሦ ስለ እውነት በእውነት ጥቂት መከራ ከተቀበለ የጠራው የመረጠውና የጋበዘው እግዚአብሔር በመከራ ጊዜ ካጸናው በኋላ ከፍጹምነት ያደርሰዋል:: ዋናው ነገር የምንቀበለው መከራ ለጥቂት ጊዜ መሆኑ ነው:: የጠራን አምላክ የጸጋ ሁሉ አምላክ ስለሆነ ጸጋውን ያድለናል:: ያጽናናል:: ያበረታናልም:: «በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል:: ያጸናችኋልም ያበረታችሁማል::» ፩ኛ.ጴጥ.፭÷፲::

፲፪. ወደዓለም መጨረሻ ከፍ ያለ መከራ አለ:: ጌታችን በማቴዎስ ፳፬ ላይ የተናገረው ሁሉ እየተፈጸመ ነው: አሁን የምንገኘውም በዋዜማው ላይ ነው:: ጦርን የጦርን ወሬ እየሰማን ነው:: ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ተነሥቷል:: ራብ ቸነፈርና የምድር መናወጥ በየሥፍራው እየሆነ ነው:: ወገን ወገኑን ለመከራ አሳልፎ እየሰጠ እየገደለም ነው: በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ቸርነት ስለማይለየን ቅዱሳን መላእክት በተራዳኢነት ይቆሙልናል:: «በዚያም ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደ እርሱ ያለ ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል» ዳን.፲፪÷፩::

፲፫. በመከራ ጊዜ እግዚአብሔር ያድነናል:: ሠለስቱ ደቂቅን ከእሳት፣ ዳንኤልን ከአፈ አናብስት፣ ሶስናን ከዕደ ረበናት ያዳነ አምላክ እኛንም ያድነናል:: እግዚአብሔር ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ የሚያድን አምላክ ነውና:: «ከሰማይ ልኮ አዳነኝ» ማለት መዝ.፶፯÷፫:: ረድኤቱን ልኮ አንድም ልጁን ልኮ አንድም መልአኩን ልኮ አዳነኝ ማለት ነው:: እግዚአብሔር በመከራዬ ቀን ደረሰልኝ:: እግዚአብሔር ግን ደጋፊዬ ሆነ ወደ ሰፊ ስፍራም አወጣኝ:: ወድዶኛልና አዳነኝ:: ፪ሳሙ.፳፪÷፲፰

ወጥኖቼ እስተውሉ እኛ መከራ የምንቀበለው ነገ በገሃነመ እሳት ሳይሆን ዛሬ በምድር ሳለን መሆን አለበት:: ይቺ ዓለም እውነት በሐሰት ማዕበል የምትንገላታበት ስለሆነች እውነትን ይዘን ከእውነት ጋራ በመንገላታት መከራን እንቀበል ዘንድ ይገባናል:: እንዲህ ከሆነ እውነት





ስለማትወድቅ አንወድቅም:: ስለማትጠፋም አንጠፋም:: ይህ ሳይሆን ቀርቶ ከሐሰተኞች ጋር ብንሰለፍ ፍጻሜያችን አያምርም:: እግዚአብሔር ገጹ መዓቱን ያዞርብናል» የእግዚአብሔር ፊት ክፉን በሚያደርጉ ላይ ነውና» መዝ.፴፫÷፲፮

ስለዚህ ዛሬውኑ እግዚአብሔርን እንፈልገው:: እርሱም ይመልስልናል:: ከመከራችንም ሁሉ ያድነናል:: መዝ.33ማ.4:: ችግረኞች ስለሆን እንጮኽ እግዚአብሔርም ጩኸታችንን ሰምቶ ስቃያችንንም ዐውቆ መከራችንንም በእውነት አይቶ ያድነናል:: «ይህ ችግረኛው ጮኸ እግዚአብሔርም ሰማው:: ከመከራውም ሁሉ አዳነው» መዝ.፴፫÷፮:: የእምነት፣ የምግባር፣ የሰላምና የፍቅር ችግር ያለብን ሁሉ ዛሬውኑ እንጩኽ እርሱ ይሰጠናል:: ሙሴ ከግብጽ ወደ ምሥራቅ ቢጓዝ በደብረ ሲና እግዚአብሔር ተገለጠለት:: ከወገኖቹ ጋር መከራ መቀበልን መርጦ ነበርና:: እርሱንም ወገኖቹንም ያድን ዘንድ እግዚአብሔር ወረደ::

እኛም ከእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ጋር መከራ መቀበልን እንምረጥ:: ኃጢአትንና በደልን ትተን አማናዊነት ደብረ ሲና ወደ ሆነች ቤተ ክርስቲያን እንጓዝ ወደ ምሥራቅም ዞረን እንጸልይ:: ምሥራቅ እመቤታችን ናትና አማልጂን እንበል:: ሥጋውንና ደሙንም እንቀበል:: ፈጣሪያችን ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ያድነናል:: የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን፤ አሜን::



www.ethiopianorthodox.org

# ምጽዋት

*በቀሲስ ያሬድ ኀ/መድኅን*

ምጽዋት ከርኅራኄ ወገን የምትሆን የመንፈስ ፍሬ ናት። ይህም ሰው ምጽዋቱን ለሚሹት ሰዎች ወጥቶ ወርዶ በድካሙ በወዙ ባገኘው ገንዘብ የሚያደርገው ርኅራኄ ነው። የተራበውን ቆርሶ ማብላት የተጠማውን ማጠጣት፣ የታረዘውን ማልበስ ነው። በአጠቃላይ በፍጹም ርኅራኄ የባሰባቸውን፣ ቀን የጐደለባቸውን ነዳያንን ማሰብ ነው። ጠቢቡ ሰሎሞን «ርኅሩኅ የተባረከ ይሆናል፣ ከእንጀራው ለድሀ ሰጥቶአልና።» ያለው ለዚህ ነው። ምሳ.፳፪÷፱ በአጠቃላይ ምጽዋት ማለት ሀብትን ብልና ዝገት በማያጠፉት ሌቦችም ግድግዳውን ምሰው ግምቡንም አፍርሰው በማይወስዱበት ሥፍራ በሰማያዊ መዝገብ ማከማቸት ነው። ማቴ.፮÷፳። አንድም በበረከት ለማጨድ በበረከት መዝራት ነው። ፪ኛቆሮ.፱÷፮። አንድም እግዚአብሔርን ማክበር ነው። ምሳ.፲፬÷፴፩።

ምጽዋት የሚመጸወተው ከአሥሩ እጅ ለእግዚአብሔር አሥራት /አንድ አሥረኛውን/ ካወጣን በኋላ ከሚቀረው ከዘጠኙ ላይ ነው። ከዚህ ውጭ አሥራት አጠራቅሞ ለነዳያን መመጽወት ትክክል አይደለም። ምክንያቱም አሥራት የእግዚአብሔር ድርሻ ስለሆነ መስጠት የሚገባው ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ነውና። ደግሞም የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ገንዘብ ላይ ሥልጣን የለውም። በመሆኑም «የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር የቄሳርንም ለቄሳር» እንደተባለ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ካስረከቡ በኋላ ከሚቀረውና ለእኛ ከተፈቀደው ላይ ቀንሶ መመጽወት የሚገባው በወዙ ካገኘው እንጂ ሰርቆና ቀምቶ፣ ዋሽቶና አጭበርብሮ ካመጣው፣ በኃጢአትና በበደል ካጠራቀመው አይደለም። ስለሆነም እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር አምላክ እንደሰጠው በረከት መጠን እንደችሎታው መስጠት አለበት። ዘዳ.፲፮÷፲፯ ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው ወንድሙም የሚያስፈልገውን ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ ውስጥ ሊኖር አይችልም። ምክንያቱም ክርስትና ማለት በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት መዋደድ አይደለምና። ፩ኛዮሐ.፫÷፲፰



www.ethiopianorthodox.org



ምጽዋት የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው። በመሆኑም ጸጸትና ቁጭት የሌለበት ንጹሕ ምጽዋት ለነዳያን መስጠት ይገባል። ምክንያቱም እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ ለነዳያን አለመመጽወት ኃጢአት ነውና። ይኸንን በተመለከተም «አምላክህም እግዚአብሔር በሰጠህ በአገርህ ደጅ ውስጥ ከሚኖሩ ወንድሞችህ አንዱ ቢደኸይ፣ ልብህን አታጽና በድሀው ወንድምህ ላይ እጅህን አትጨብጥ። ነገር ግን እጅህን ለእርሱ ክፈት፤ ... ለድሀውም ወንድምህ አንዳች የማትሰጥ እንዳትሆን፣ ዓይንህም በእርሱ ላይ ክፉ እንዳይሆን እርሱም ወደ እግዚአብሔር በአንተ ላይ እንዳይጮኽ፣ ኃጢአትም እንዳይሆንብህ ተጠንቀቅ። እጅህን በምትጥልበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ስለዚህ በሥራህ ሁሉ ይባርክሃልና ፈጽመህ ስጠው፣ በሰጠኸውም ጊዜ በልብህ አትጸጸት። ድሆች ከምድሪቱ ላይ አያልቁምና፣ ስለዚህ እኔ፡ በአገርህ ውስጥ ላለው ድሀ ለተቸገረም ወንድምህ እጅህን ትከፍታለህ ብዬ አዝዝሃለሁ።» ተብሏል። ዘዳ.፲፭÷፯-፲፩ በተጨማሪም ለጠላትም ቢሆን መመጽወት እንደሚገባ ታዝዟል። ይህም «ጠላትህ ቢራብ አብላው ቢጠማ አጠጣው። ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሳት ፍህም ትከምራለህና» ተብሎ ተነግሯል። ምሳ.፳፭÷፳፩፣ ሮሜ.፲፪÷፳። ትርጉሙም ምጽዋቱን በትኅትና ቢቀበል ራሱን በኀፍረት እንዲደፋ እንዲጸጸት ታደርገዋለህ ነገር ግን «እየጠላሁት የመጸወተኝ ቢፈራኝ እንጂ ነው፤» ቢል በገሃነመ እሳት ታስፈርድበታለህ ማለት ነው።

ምጽዋት በማናቸውም መንገድ ከነዳያኑ ብድራትን ሳይሹ የሚፈጸም መሆን አለበት። ብድራቱን የሚከፍል እግዚአብሔር ስለሆነ ከነዳያኑ ከ«እግዚአብሔር ይስጥህ» በላይ ምንም ዓይነት ነገር መጠበቅ አይገባም። ለዚህም ነው ጌታችን «ምሳ ወይም እራት ባረግህ ጊዜ፣ እነርሱ ደግሞ በተራቸው ምናልባት እንዳይጠሩህ ብድራትም እንዳይመልሱልህ ወዳጆችህንና ወንድሞችህን ዘመዶችህንም ባለጠጎች ጐረቤቶችህንም አትጥራ። ነገር ግን ግብዣ ባደረግህ ጊዜ ድሆችንና ጉንድሾችን አንካሶችንም ዕውሮችንም ጥራ፤ የሚመልሱት ብድራት የላቸውምና ብፁዕ ትሆናለህ፤ በጻድቃን ትንሣኤ ይመለስልሃልና።» ያለው።

ሉቃ.፲፬÷፲፪-፲፬ የጻድቃን ትንሣኤ የተባለችው ዕለተ ምጽአት ናት። በዕለተ ምጽአት ጌታችን በጐቹን ከፍየሎቹ እንደሚለይ እረኛ ጻድቃንን ለይቶ በቀኙ ያቆማቸዋል፤ ጻድቃንን በምሥጋና ቃል «እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ። ተርቤ አብልታችሁኛልና ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፣ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፣ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና።» ይላቸዋል። እነርሱም «ጌታ ሆይ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለ በስንህ? ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን?» ይሉታል። እርሱ መልሶ «እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ከወንድሞቼ /ከድሆች/ ለአንዱ ስላደረጋችሁ ለእኔ አደረጋችሁት» ይላቸዋል። ኃጥአንን ግን በወቀሳ ቃል «ይኸንን ሁሉ አላደረጋችሁል ኝምና እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመልእክተኞቹ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ሂዱ» ይላቸዋል። እነርሱም በተራቸው «መቼ አይተንህ አላደረግንልህም?» ይሉታል። እርሱም መልሶ «እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም» ብሎ ይመልስላቸዋል። ማቴ.፳፭÷፴፩-፵፮። ስለሆነም ምጽዋትን እንዲሁ በልግስና መስጠት ያስፈልጋል።

የሚመጸውት ሰው ዋጋው በምድር እንዳይቀርበት ውዳሴ ከንቱን መሸሽ አለበት። ምክንያቱም ውዳሴ ከንቱ ሰሚያዊ ዋጋን ያስጥልና። ስለዚህም ጌታችን ሲናገር «ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፤ ያለዚያ በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም። እንግዲህ ምጽዋት ስታደርግ ግብዞች በሰው ዘንድ ሊከበሩ በምኩራብ በመንገድም እንደሚያደርጉ በፊትህ መለከት አታስነፋ፤ እውነት እላችኋለሁ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን በቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ያስረክብሃል» ብሏል። ማቴ.፮÷፩-፬። እዚህ ላይ ምኩራብና መንገድ የተጠቀሰው በቤተ ክርስቲያንና በጉዳና





መርዳት አይገባም ለማለት አይደለም። ጌታችን እነዚህን የጠቀሰው ግብዞች ሰዎች እንዲያዩአቸውና እንዲያመሰግኗቸው ሰዎችን ሰብስበው ቀን ቀጥረው በተመሳቀለ ጉዳና በአደባባይና በምኩራብ «አቦ አቦ» እየ ተባሉ ይመጸውቱ ስለነበር «እንዲህ አታድርጉ፣ ውዳሴ ከንቱ ፈል ጋችሁ የምትሠሩት ሥራ አይኑር፤» ሲላቸው ነው። «ቀኝህ የምትሠራ ውን ግራህ አትወቅ፤» ያለው ደግሞ «ሚስትህ ልጆችህና ቤተሰቦችህ አይ ወቁ፤» ሲል ነው። ምክንያቱም በእምነት ካልጸኑ በስተቀር ያሳንፉታልና። እርሱ ልመጽውት ሲል ሚስት፡ «አይሆንም ንብረቱ የጋራችን ነው፤» ትለዋለችና፤ ልጆችም «ዛሬ መጽውተህ ጨርሰህ ነገ ምን ልን ወርስ ነው? ይሉታልና፤ ዘመድ አዝማዶቹ ደግሞ «የጌታችን ወርቁ ለዝና፣ ልብሱ ለእርዝና፣ እህሉ ለቀጠና፤» እያሉ ያዳክሙታልና በእምነት ከጸኑ ግን «አነስ ጨምር» ይሉታል እንጂ «በዛ ቀንስ» አይሉትም።

እንዲህም ሲባል ምጽዋት መስጠት የሚገባው በስውር ብቻ ነው ማለት አይደለም። በግልጥም ይሰጣል። ምክንያቱም ከቤተ ክርስቲያን ደጅ ወድቀው በየጉዳናው ዳር ተኰራምተው በቤታችንም ደጃፍ ቆመው ስመ እግዚአብሔርንና ስመ ቅዱሳንን እየጠሩ ሲማጸኑን ዝም ብሎ ማለፍ አይገባምና። ይኸንን በተመለከተ ጌታችንና አምላካችን መድኃ ኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ለሚለምንህ ስጥ፤» ብሏል ማቴ.፭÷፵፪። ዋናው ነገር ሰውነታችን እንዳይገበዝ ልቡናችንንም ውዳሴ ከንቱን እንዳ ይፈልግ በትኅትና መጋረጃ ውስጥ መሰወር ነው። ሲያመሰግኑንም «አይ ገባኝም» እያልን በውስጥ መቃወም ነው። ምጽዋት መስጠት የሚገባ ውም በእግዚአብሔር በእመቤታችንና በቅዱሳን ስም ነው። ፩ኛቆሮ.፲÷፴፩፣ ቆላ.፫÷፲፯፣ ማቴ.፲÷፵-፵፪።

ምጽዋት ዝም ተብሎ በግብር ይውጣ ወይም በዘፈቀደ የሚሰጥ አይደለም። ዓላማ አለው። ዓላማውም ነዳያንን ከችግር ማላቀቅ ነው። ነገር ግን ያ ሰው ሲጋራ እንደሚያጤስበት ጫት እንደሚቅምበት፣ ጠጥቶ እንደሚሰክርበት በዝሙት ቤተ መቅደስ ሰውነቱን እንደሚያረክስበት እያወቅን የምንሰጥ ከሆነ በደል ነው። ሳናውቅ ከሆነ ግን በደሉ በራሱ ላይ ይሆናል። ስለዚህ ስንመጸውት የዚያን ሰው የችግር ቀዳዳ በመጠኑም ቢሆን ለመድፈን በማሰብ መሆን አለበት።



www.ethiopianorthodox.org

ምጽዋት መመጽወት ያለባቸው ባዕለጸጎች ብቻ አይደሉም:: ድሆችም ከእነርሱ ለሚያንሱት ያላቸውን መመጽወት አለባቸው:: ምክንያቱም የምጽዋት ትንሽ የለውምና:: ለምሳሌ በወንጌል እንደተጻፈው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሙዳየ ምጽዋት አንጻር ተቀምጦ ሕዝቡ በሙዳየ ምጽዋቱ ውስጥ ገንዘብ እንዴት እንደሚጥሉ ሲያይ ብዙ ባለጠጎች ብዙ ይጥሉ ነበር፤ አንዲትም ድሀ መበለት መጥታ አንድ ሳንቲም የሚያህሉ ሁለት ናስ ጣለች:: ደቀመዛሙርቱንም ጠርቶ «እውነት እላችኋለሁ በመዝገብ ውስጥ ከሚጥሉት ሁሉ ይልቅ ይህች ድሀ መበለት አብልጣ ጣለች፤ ሁሉ ከትርፋቸው ጥለዋልና ይህች ግን ከጉድለትዋ የነበራትን ሁሉ ትዳርዋን ሁሉ ጣለች፣» ብሏቸዋል:: ማር.፲፪÷፵፩-፵፬:: በሌላ በኩልም ድሆች ፍቅራቸውን ምክራቸውንና ጉልበታቸውን መመጽወት ይችላሉ:: ባለጸጎች ደግሞ እንዲያውም አምስትና አሥር ሣንቲም መጣል ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ ድሆች ለዘለቄታው ከችግር የሚላቀቁበትንና ራሳቸውን ችለው በሁለት እግር የሚቆሙበትን መንገድ መፈለግ አለባቸው:: አለበለዚያ «የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁና በመጠን ኖራችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ የምታገኙትን ጸጋ ፈጽማችሁ ተስፋ አድርጉ የተባለውን ቃል ዘንግተን እኛ ከመጠን በላይ እየኖርን ድሆቹ ግን ከመጠን በታች የሆነ አሳዛኝ ኑሮ ሲኖሩ እያየን ዝም ማለት በደል ነው::» ፩ኛጴጥ.፩÷፲፫ እነርሱ ቆሎ እንኳ አርሮባቸው እያየን እኛ ግን በውስኪ የምንራጭ ከሆነ ግፍ ነው:: እነርሱ እንጀታቸው ታጥፎ በረሃብ አለንጋ እየተገረፉ እኛ ግን ተርፎን የምንደፋ ከሆነ የበደል በደል የግፍ ግፍ ነው:: በዚህም ምክንያት ድሆች ወደ እግዚአብሔር ይጮኻሉ:: ዘጸ.፲፮÷፱:: እግዚአብሔርም ጩኸታቸውን ይሰማል:: መዝ.፴፫÷፮፤ ለምሳሌ ነዌ የተባለው ባዕለጸጋ ወደ ሲዖል ተጥሎ የተሰቃየው ከደጃፉ ላይ ወድቆ የነበረውን ድሀ አልዓዛርን ባለመጉብኘቱ ነው:: አልዓዛር ከባዕለጸጋው ደጅ ወድቆ ከማዕዱ ከሚወድቀው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር:: ውሾች እንኳ መጥተው ቁስሉቹን ይልሱ ነበር:: በሞተ ጊዜ ግን እንደ ድሮው ውሾች ሳይሆኑ ቅዱሳን መላእክት ከበቡት፥ ወደ ሰማይም አሳርገው በአብርሃም ቀኝ አስቀመጡት:: ሉቃ.፲፮÷፲፱-፴፩::





ባዕለጸግነት ጌታ በወንጌል በምሳሌ እንዳስተማረው በድሆች ላይ መጋቢ ሆኖ መሾም ነው:: ሿሚውም እግዚአብሔር ነው:: በመሆኑም የሹመቱን ዓላማ በማወቅ ድሆችን መመገብ ያስፈልጋል፡ ከሁሉም በላይ ድሆች ፍቅርን ይሻሉ:: ይህ ካልሆነ ግን ድሆች መጋቢዎቻቸውን ይከስሳሉ:: እግዚአብሔርም መጋቢዎችን ይጠይቃቸዋል «ይህ የምሰማባችሁ ነገር ምንድር ነው? ወደፊት ለእኔ መጋቢ ልትሆኑ አትችሉምና የመጋቢነታችሁን ሂሳብ አስረክቡኝ፤» ይላቸዋል:: ሉቃ.፲፮÷፩-፱ «እናንተ ባለጠጎች፣ ስለሚደርስባችሁ ጭንቅ ዋይ ዋይ እያላችሁ አልቅሱ:: ሀብታችሁ ተበላሽቶአል ልብሳችሁም በብል ተበልቶአል:: ወርቃችሁም ብራችሁም ዝጎአል ዝገቱም ምስክር ይሆንባችኋል፡ ሥጋችሁንም እንደ እሳት ይበላል፤» እያለ ይወቅሳቸዋል:: ያዕ.፭÷፩-፫:: በመጨረሻም «እናንተ ሰነፎች በዚች ሌሊት ነፍሳችሁን ከእናንተ ሊወስዱአት ይፈልጓታል፤ ይህስ የሰበሰባችሁት ለማን ይሆናል? ለራሳቸው ገንዘብ የሚያከማቹ በእግዚአብሔር ዘንድም ባለጠጎች ያልሆኑ እንዲህ ናቸው» ብሎ ይፈርድባቸዋል:: ሉቃ.፲፪÷፳-፳፩::

ማንኛውም ሰው እግዚአብሔር ከሰጠው ጸጋ በፍቅረ ቢጽ ላይ ተመሥርቶ በፈሪሃ እግዚአብሔር የሚመጸውተው እምነት ሲኖረው ነው፡ በመሆኑም ከሁሉ አስቀድሞ በእምነት መታነጽና ማደግ ያስፈልጋል:: ፩ኛቆሮ.፲፮÷፲፫ ምክንያቱም የበጎ ምግባር ሁሉ መሠረት እምነት ነውና:: እግዚአብሔርም ደስ የሚለው መንፈሳዊ ሥራ ሁሉ በእምነት ሲፈጸም ነውና ዕብ.፲፩÷፮:: አለበለዚያ አሕዛብ ከሚያደርጉት ምንም ልዩነት አይኖረውም፤» ማቴ.፳÷፵፮-፵፯::

በእምነት የሚፈጸም ምጽዋት ሁሉ ዋጋ አለው:: ዋጋውም ሰማያዊ ነው:: ማቴ.፳፭÷፴፬፣ ሉቃ.፲፬÷፲፬ በምድርም ቢሆን ለደጋጎች በረከት ይትረፈረፍላቸዋል:: ይኸንን በተመለከተ ጠቢቡ ሰሎሞን «ያለውን የሚበትን ሰው አለ ይጨመርለታልም:: ያለቅጥ የሚነፍግም ሰው አለ ይደኸያልም:: ለድሀ የሚሰጥ አያጣም፤» ብሏል:: ምሳ.፲፩÷፳፬፣ ምሳ.፳፰÷፳፯:: ነቢዩ ዳዊትም «ለችግረኛና ለምስኪን የሚያስብ ምስጉን ነው፤ እግዚአብሔር ከክፉ ቀን ያድነዋል:: እግዚአብሔር ይጠብቀዋል ሕያውም



www.ethiopianorthodox.org

ያደርገዋል በጠላቶቹም እጅ አያሳልፈውም:: እግዚአብሔር በደዌው አልጋ ሳለ ይረዳዋል፤ መኝታውን ሁሉ በበሽታው ጊዜ ያነጥፍለታል::» ብሏል:: መዝ.፵፩÷፩-፫:: በመሆኑም በፍጹም እምነት ከእግዚአብሔር የሚገኘውን የተትረፈረፈ በረከትና በኋላም የምትወረ ሰውን የማታልፍ የእግዚአብሔር መንግሥት በማሰብና ተስፋ በማድ ረግ እጅን ለም ጽዋት መዘርጋት ይገባል:: ምክንያቱም ምጽዋት ከጸሎት ጋር ቅድመ እግዚአብሔር ይደርሳልና:: የእግዚአብሔር መልአክ ቆርኔሌዎስን «ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን ዐረገ፤» ያለው ለዚህ ነው:: የሐዋ.፲÷፬::

እንግዲህ «የሰማይ አባታችሁ ርኅሩኅ እንደሆነ ርኅሩሆች ሁኑ፤» እንደተባለ በርኅራኄ በመመጽወት ፈጣሪያችንን እግዚአብሔርን በመ ልክ ብቻ ሳይሆን በግብር ልንመስለው ይገባል:: ሉቃ.፮÷፴፮:: እግዚ አብሔርም ከመሥዋዕት ይልቅ ርኅራኄን ይወዳል:: ሆሴ.፮÷፮፤ በአጠ ቃላይ ምጽዋት አበው እንደሚያመሠጥሩት:

- ⇒ ለአምላክ የሚያበድሯት ብድራት ናት፤
- ⇒ ወደ አምላክ የሚነግዷት የታመነችና ትርፍ ያላት ንግድ ናት፤
- ⇒ ወዶ እስኪያስነሣት ድረስ ብልህ ሰው ከፈጣሪው ከእግዚአ ብሔር ዘንድ የሚያኖራት አደራ ናት፤
- ⇒ በጐ ሥራን ሁሉ ንጹሕ የምታደርግ ናት፤
- ⇒ ኀልፈት ጥፋት የሌለባት ሰማያዊ ድልብ ናት፤
- ⇒ እግዚአብሔር ከርሠ ነዳያንን መቅደስ አድርጎ የሚቀበላት መብዓ ናት
- ⇒ የአምስቱ ትጉኃን ቆነጃጅት መብራት ናት፤ ማቴ.፳፭÷፯
- ⇒ የቅዱሳን ትጋት ናት፤ ገላ.፪÷፲

የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን::





## «የተባረክሽ ነሽ» ሉቃ.፩÷፴፱-፵፮

በቀሲስ ደጀኔ ሺፈራው

ሰማያዊ ንጉሥ ውበቷን /ንጽሕናዋን ቅድስናዋን/ የወደደላት ማደ ሪያው /እናት/ ትሆነው ዘንድ የመረጣት ለዘለዓለም ማረፊያው እንድ ትሆን የወሰነላት መንፈስ ቅዱስ ያጸናት ወልድ ያደረባት ኃይለ ልዑል የጸለለባት እመቤት ቅድስት ድንግል ማርያም «እንደ ቃልህ ይሁን ልኝ» ብላ ብሥራተ ገብርኤልን ከተቀበለች በኋላ በዚያ በብርድ እና በውርጭ ወራት ወደ ተራራማው አገር ወደ ይሁዳ ከተማ ፈጥና ወጣች:: ይሁዳ በደቡብ ከነዓን ያለ አገር ነው:: የእሥራኤል ልጆች ከባቢሎን ምርኮ ተመልሰው ወደ አገራቸው ሲመጡ አብዛኞቹ ከይሁዳ ወገን ስለሆኑ በከነዓን አገር የተቀመጡበት ሥፍራ ይሁዳ ተባለ:: ሰዎ ቹም አይሁድ ተባሉ:: ሕዝ.፳፰÷፳፫:: ይሁዳ ከታላቁ ባሕር እስከ ጨው ባሕር ከኢዮጴ ከተማ እስከጋዛ ይደርሳል::

እመቤታችን ወደ ዘካርያስ ቤት ገብታ ኤልሳቤጥን ተሳለመቻት:: ኤልሳቤጥ ለእመቤታችን አክስቷ ናት:: ዘመዷ መሆኗንም ቅዱስ ገብር ኤል ተናግሯል:: ዘካርያስና ኤልሳቤጥ በጌታ ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየሔዱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ:: ሉቃ.፩÷፮-፴፮::

ኤልሳቤጥ በእመቤታችን በመጐብኘቷ ድንቅ ነገር ተደረገላት የድንግል ማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በማኅፀንዋ ውስጥ ዘለለ:: «አንፈ ርዓፀ እጓል በውስተ ከርሣ» የሚለውን ቅዱስ ያሬድ «ዮሐንስ ሰገደ ውስተ ከርሠ እሙ» ዮሐንስ በእናቱ ማኅፀን ሳለ ሰገደ ብሎ ተርጉሞ ታል:: በኤልሳቤጥ መንፈስ ቅዱስ ሞላባት ምሥጢርም ገለጠላት በታላቅ ድምፅም እየጮኸች ድንግል ማርያምን እንድታመሰግን አደረ ጋት:: በሰድሜዋ ብታረጅም በመንፈስ ቅዱስ ታድሳ አመሰገነቻት::

ምስጋናዋም ከሰማያዊው መልአክ ከቅዱስ ገብርኤል ጋር ተመሳሰለ አንድ ሆነ «አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ የማኅፀንሽም ፍሬ አምላክ ወልደ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ የተባረከ ነው» አለች:: ከዚ ህም አከታትላ የትሕትናን ነገር ተናገረች:: የጌታዬ እናት ወደ እኔ



www.ethiopianorthodox.org

ትመጪ ዘንድ አይገባኝም በማለት የራሷን ታናሽነት የእመቤታችንን ታላቅነት መሰከረች። ይህ ታናሽነት እና ታላቅነት በዕድሜ ሳይሆን በክብር ነው። በዕድሜማ ኤልሳቤጥ አረጅታለች። ሉቃ.፩÷፵፭ ኤልሳቤጥ እንደገለጠችው በጌታ /በአምላክ/ እናትነቷ ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች ናት በክብርም የሚተካከላት የለም ምስጋናዋ በሰማይም በምድርም የመላ መሆኑ በዚህ ታወቀ። ከሰማያውያን ቅዱስ ገብርኤል ከምድራውያን ኤልሳቤጥ በአንድ ቃል አመስግነዋታልና።

ኤልሳቤጥ በእመቤታችን ምክንያት የተደረገላትን ተአምር አልሸሸገችም ያደረባት መንፈስ ቅዱስ የእመቤታችንን ነገር የሚሸሽግ ሳይሆን የሚገልጥ ነው። ዳሩ መንፈስ ቅዱስ የሞላባት እመቤታችን ስለቀረበቻትና ስለተሳለመቻት አይደል፤ ድንግል ማርያም እንደማናቸውም ሴቶች እንደ አይደለች ከሴቶች ሁሉ ተለይታ እንደተባረከች ከተለዩ የተለየች እንደሆነች የማኅፀኗም ፍሬ ቡሩክ አምላክ መሆኑን መንፈስ ቅዱስ አስተማራት። «ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት» በማለት በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል አንደበት የተነገረው አስቀድሞም በቅዱሳን ነቢያት በግልጥም በምሳሌም ለእመቤታችን ሲነገር የኖረው ቃለ እግዚአብሔር በእውነት እየተፈጸመ መሆኑን መንፈስ ቅዱስ አፏን ከፍቶ ፊቷን ጸፈቶ አናገራት። የአምላክ እናት የመሆኗን ነገር፡ መሰከረች።

ለእመቤታችን ከሠራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር የተነገረላት ቃል እጅግ የበዛ ነው። «ዘምሩ ለእግዚአብሔር ዘየኀድር ውስተ ጽዮን፤ ጽዮን ለሚያድር ለእግዚአብሔር ዘምሩ» መዝ.፱÷፲፩ «ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም ዝየ አኀድር እስመ ኀረይክዋ፤ ይቺ የዘለዓለም ማረፊያዬ ናት መርጫታለሁና፤ በዚች አድራለሁ።» መዝ.፩፻፴፩÷፲፬ ተብሎ በቅዱስ ዳዊት ተነግሮ የነበረ ቃል ፍጻሜውን አገኘ። እግዚአብሔር ወልድ እግዚአብሔር ቃል ጽዮን ተብሎ ትንቢት በተነገረላት በድንግል ማርያም ማኅፀን አደረ። ምሥጢሩም በመንፈስ ቅዱስ ለኤልሳቤጥ ተገለጠ። ጽዮን ማለት በትርጉሙ አምባ መጠጊያ ማለት ነው። አማናዊት ጽዮን እመቤታችንም በአማላጅነትዋ ለምእመናን አምባ መጠጊያ





በመሆን ተሰፋቸው ናት። «ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች።» ኢሳ.፯÷፲፬ ተብሎ በኢሳይያስ የተነገረላት ቃል በእግዚአብሔር ይፈጸማልና አምላክን በድንግልና ፀነሰች አምላክንም በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ በማኅፀነ ድንግል አደረ። ቡሩክ አምላክ በማኅፀኗ አድሮ ቡርክት ትባል ዘንድ ወደደ ፈቀደ እርሱ በሰማይ በምድር ቡሩክ እንደሆነ እርሷም በሰማይ በምድር ቡርክት ሆነች፤ እሱ በሰማይ በምድር ምስጉን እንደሆነ የወደዳት የመረጣትና ያደረባት እናቱም በሰማይ በምድር ተመሰገነች።

ኤልሳቤጥ እንደተናገረችው አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና እንደምትወልድ በመልአኩ አንደበት የተነገረላትን የሚፈጸመውን የእግዚአብሔርን ቃል በፍጹም እምነት የተቀበለች እመቤት እውነትም ብፅዕት ናት። እግዚአብሔር ተናግሮ የሚያስቀር አምላክ አይደለምና፤ «እኔ እግዚአብሔር ነኝ እናገራለሁ የምናገረውም ቃል ይፈጸማል ደግሞም አይዘገይም።» በማለት አረጋግጦልናል። ሕዝ.፲፪÷፳፭። በኢሳይያስ አድሮ «... ከአፌ የሚወጣ ቃል እንዲሁ ነው የምለውን ያደርጋል። የላክሁትንም ይፈጽማል ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም።» ሲል መናገሩ ለዚሁ ነው። ኢሳ.፶፭÷፲፩።

ጠቢቡ ሰሎሞን በመኃ.፮÷፲ ላይ «ርግቤ አንዲት ናት። መደምደሚያዬም አንዲት ናት። ለወለደቻት የተመረጠች ናት ልጆችም ባዩአት ጊዜ አመሰገኑአት ንግሥታትና ዕቁባትም ምስጋና ሰጡአት። ይህች ማን ናት? እንደ ማለዳ ብርሃን የምትጐበኝ እንደጨረቃ የተዋበች እንደ ፀሐይ የጠራች እንደ ኮከብም ጦር የምታስፈራ፤ «ብሎ የተናገረላት የዋሂት ርግብ እመቤታችን በሁሉ የተመሰገነች ናት። ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ስትመሰገን ትኖራለች። የቤተ ክርስቲያን ሊቅ አባ ጊዮርጊስ «ውድስት አንቲ በአፈ ነቢያት ወሰብሕት በሐዋርያት» በማለት እመቤታችንን በነቢያትም በሐዋርያትም አፍ የተመሰገንሽ ነሽ ብሎላታል። ነቢያት ትንቢት የተናገሩለትን ሐዋርያት ወንጌል ያስተማሩለትን ሰማዕታት በስሙ የተጋደሉለትን ጻድቃን [illegible]



www.ethiopianorthodox.org

የተለዩለትን ኪሩቤል መንበሩን የተሸከሙለትን ሱራፌል ያለ እረፍት የሚያመሰግኑትን መላእክት ለተልእኮ የሚፋጠኑለትን አምላክ በማኅፀንዋ ተሸክማላቸዋለችና ሁሉም በአንድ ቃል ያመሰግኗታል:: መላእክት እኅታችን ጻድቃን እመቤታችን ሰማዕታት እናታችን ምእመናን መመኪያ ዘውዳችን ጥንተ መድኃኒታችን ይሏታል:: የምድረ ባለጠጎች አሕዛብ በፊቷ ይማልላሉ» መዝ.፵፬÷፪::

እኛም ከሰማይ ቅዱስ ገብርኤልን ከምድር ኤልሳቤጥን አብነት መንፈስ ቅዱስን ምስክር አድርገን «ስብሐት ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ አምላክን የወለደች ለእመቤታችን ለድንግል ማርያም ምስጋና ይገባል:: እውነት ነው ምስጋና ይገባል» እያልን እናመሰግናታለን:: አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው ቅዱስ ኤፍሬም በውዳሴው አባ ጊዮርጊስ በድርሰቱ እንዳመሰገኗት በአባቶች ፈንታ የተወለድንላት ልጆቿም የጌታን እናት ከማመስገን ቸል አንልም:: በመዝሙራችንም ሆነ በቅዳሴአችን ከስመ ሥላሴ ቀጥለን የምንዘምረው የእመቤታችንን ምስጋና ነው: እንኳን የአምላክ እናት «በክፉዎች ምክር ያልሔደ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ ሰው ምስጉን ነው:: መዝ.፩÷፩:: እግዚአብሔርን የሚፈራ ትእዛዙንም እጅግ የሚወድ ሰው ምስጉን ነው:: መዝ.፩፻፲፩÷፩:: በመንገዳቸው ንጹሐን የሆኑ በእግዚአብሔርም ሕግ የሚሔዱ ምስጉኖች ናቸው:: ምስክሩን የሚፈልጉ በፍጹም ልብ የሚሹት ምስጉኖች ናቸው:: መዝ.፩፻፲፰÷፩:: እንግዲህ እነዚህ ሁሉ የአምላክ አገልጋዮች ምስጉኖች ከሆኑ አገልጋይነትን ከአምላክ እናትነት ጋር አስተባብራ የተገኘች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ምስጋናዋ ከሁሉ ከፍ ያለ ነው::

በዘመናችን የእውነት መንፈስ ከሰዎች በመለየቱ እንጂ ሁሉም በአንድ ቃል እንደ ኤልሳቤጥ በመንፈስ ተሞልተው እመቤታችንን የጌታችንን እናት በመሰገኑአት ነበር:: ሰው ሥጋዊ ደማዊ ሲሆን ማለትም ለሥጋ ምኞቱ ለዓይን አምሮቱ ሲገዛ የእግዚአብሔር መንፈስ ለዘለዓለሙ ይለየዋል:: ዘፍ.፮+፫::





ድንግል ማርያምን የባረከና ያስባረከ እግዚአብሔር ነው:: ከእግዚአብሔር የሆነ ሁሉ ደግሞ «ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ::» እያለ ያመሰግናታል:: ከፍጡራን ወገን ከማንም አያወዳድራትም:: አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው «በመኑ ወበአምሳለ መኑ ናስተማስለኪ በማንና በምን ምሳሌ እንመስልሻለን» ያለው ወዶ አይደለም:: እግዚአብሔር ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት ያላት አማናዊት ጽዮን ድንግል ማርያም ለዘለዓለሙ የተባረከች መሆኗን ሁሉ ማወቅ አለበት:: ይህ ዕውቀት የሚገኘው በመንፈስ ቅዱስ ነው::

እመቤታችንን የሚባርኩ ሁሉ ቡሩካን ይሆናሉ ለዚህም የአበ ብዙኅን የአብርሃም ሕይወት ትልቅ ትምህርት ይሆነናል:: «እግዚአብሔር አብራምን አለው:: ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ:: እባርክሃለሁ ስምህንም አከብረዋለሁ:: ለበረከትም ሁን የሚባርኩህንም እባርካለሁ:: የሚረግሙህንም እረግማለሁ::» ዘፍ.፲፪÷፩:: ከዚህ የምንማረው እግዚአብሔር የባረከውን ስሙንም ያከበረውን ለበረከትም ያደረገውን አብርሃምን የሚባርክ ሰው ቡሩክ የሚረግም ደግሞ ርጉም እንደሚሆን ነው::

እመቤታችንም አባቷ ዳዊት በመንፈስ በመዝ.፵፬÷፲ ላይ «ልጄ ሆይ ስሚ እዪ ጆሮሽንም አዘንብዪ ወገንሽንም ያባትሽንም ቤት እርሺ ንጉሥ ውበትሽን ወድዶአልና» ባለው መሠረት ገና በሦስት ዓመቷ ከቤተሰቦቿ ተለይታ ለቤተ መቅደስ ተሰጥታ መላእክት እያረጋጓት ሰማያዊ ምግብ እየተመገበች በቤተ መቅደስ አሥራ ሁለት ዓመት ኖራለች:: ብሥራተ ገብርኤልን እንደሰማች የበረከተ ሥጋ ወነፍስ ማደሪያ ሆነች:: እግዚአብሔር አስቀድሞ የመረጣት ምርጫና የባረካት በረከት በቅዱስ ገብርኤልና በኤልሳቤጥ ምስጋና ተገለጠ:: ይፋ ሆነ:: እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ መንፈስ ቅዱስ ኤልሳቤጥን ገፋፍቶ የምስጋናዋ በር ተከፈተ እንግዲህ ሁለቱ በገቡበት የምስጋና በር ገብቶ ከምስጋናው አጻራሽ እሷን ማመስገን ይገባል::

አብርሃምን ለበረከት ሁን «ያለ አምላክ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ እንድታስጥ ድንግል ማርያምን መረጠ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን



www.ethiopianorthodox.org

የምታሰጭ የጌታችን እናት ሆይ እውነትም የተባረክሽ ነሽ» እንበላት:: የአብርሃምን ስም ያከበረ አምላክ የእናቱንም ስም አክብሯል:: ስለዚህ በስሟም ጭምር እንማፀናለን:: ስምዋን መማለጃ እናደርጋለን:: «በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ ስለማርያም ብለህ ክርስቶስ ሆይ ማረን::» በእንተ ማርያም ወላዲትከ ሥረይ ኃጢአተ ሕዝብከ ስለ እናትህ ስለ ማርያም ብለህ የሕዝብህን ኃጢአት ይቅር በል» እንላለን::

«የሚባርኩህን እባርካለሁ የሚረግሙህንም እረግማለሁ» ብሎ ለአብርሃም ቃል ኪዳን የገባ አምላክ እመቤታችንን እንደ ቅዱስ ገብር ኤልና ኤልሳቤጥ የምንባርካትን ሁሉ ይባርከናል:: ለእሷ ለባሕርይዋ የማይስማማ ትምህርት እያስተማርን የምንረግማትም ከሆነ ርጉማን እንሆናለን:: እንግዲህ ከበረከትና ከርግማን ከሞትና ከሕይወት እንም ረጥ በኢየሱስ ክርስቶስ ክርስቲያን ተብለን የተጠራን ሁሉ ምርጫችን በረከትና ሕይወት እንደሚሆን አልጠራጠርም:: እንዲህ ካልሆነ ግን በስሙ እየተጠራን ገና ክርስትናው እንዳልገባን ያመለክታል:: ይሄም ብቻ አይደለም እንደ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላክን አይ ደለንም:: እንደ ኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ አላደረብንም ማለት ነው::

ጌታን በማኅፀኗ ተሸክማ ወደ ኤልሳቤጥ ቤት የገባች እናት ዛሬም የጌታን ቸርነት ይዛ ወደ ቤታችን ለመግባት ፈቃደኛ ናት:: እኛ ግን በራሳችንን አንዝጋባት:: ለኤልሳቤጥ የተደረገላት እንዲደረግልን ከፈለ ግን በራችንን ክፍት እናድርግ ለእኛም እመቤታችን ድምፅዋን ታሰ ማናለች:: በዚህን ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆነ ደስታ በውስጣችን ይላወሳል:: ሕይወታችን በመንፈሳዊ ደስታ ይሞላል:: በሐዘን መከራ መት በጭንቅ መወጠር ይቀርልናል:: ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ ጌታንም እመቤታችንንም እንዳመሰገነች ጌታን ከእናቱ ጋር የምናመሰግን እንሆናለን:: ምናልባት አንዳንዶች እሷን ስናመሰግን የጌታን ምስጋና ወደ ጎን የተውን ሊመስላቸው ይችላል::

ይህ ግን ትልቅ ስህተት ነው:: እኛ ከፈጣሪያችን ከኢየሱስ ክርስ ቶስ ማንንም አናስቀድምም:: መጀመሪያ ጌታን ቀጥለን እመቤታችንን እናመሰግናለን:: ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ጌታን አመስግና እመቤታ ችንን ወይም እመቤታችንን አመስግና ጌታን አልተወችም:: እኛም





እንዲሁ ነን:: እንግዲህ እግዚአብሔር የባረካትንና ያስባረካትን እመ ቤት ትርጓሜያቸው ባልገባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እየተሰናከሉ የሚራገሙ ሁሉ ሊመለሱ ይገባቸዋል የዘለዓለም ድንግል በሆነች የጌታ እናት ላይ የማይገባ ነገር መናገር እርግማን ነውና:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔ ር የባረካትን ይረግም ዘንድ ለማንም ሥልጣን አልተሰጠ ውም:: እሷ የአምላክ ዙፋን ናት በመሆኑም በአምላክ ዙፋን ላይ ሰውን ለማስቀ መጥ የሚጥሩ ርጉማን ዛሬም ስላሉ «ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ::» ወደሚለው ዘለዓለማዊ ቃል ሊመለሱ ይገባቸዋል::

በለዓም እግዚአብሔር የባረከውን ሕዝብ ለመርገም በባላቅ ጥሪ ሲጓዝ የእግዚአብሔር መልአክ ተቃወመው:: እንዲያውም በሰው አን ደበት የገሰፀችህ አህያህ ሦስት ጊዜ ከፊቴ ፈቀቅ ባትል ኖሮ አሁን አንተን በገደልኩህ ነበር አለው:: በመጨረሻም የምናገርህን ቃል ብቻ ትናገራለህ ሲል አስጠንቀቀው:: በለዓምም ከባላቅ ጋር ከተገናኘ በኋላ «ባላቅና ያዕቆብን ርገምልኝ:: ና እሥራኤልን ተጣላልኝ ብሎ ጠራኝ:: እኔ ግን እግዚአብሔር ያልረገመውን እንዴት እረግማለሁ? እግዚአ ብሔርስ ያልተጣላውን እንዴት እጣላለሁ» ብሎ ተናገረ ባላቅ በለዓምን «ያደረግህብኝ ምንድር ነው? ጠማቶቼን ትረግምልኝ ዘንድ ጠራሁህ:: እነሆም ፈጽመህ ባረክሃቸው አለው:: እርሱም መልሶ በውኑ እግዚአ ብሔር በአፌ ያደረገውን እናገር ዘንድ አልጠነቀቅምን አለው:: «ዳግ መኛም» እነሆ ለመባረክ ትእዛዝን ተቀብያለሁ:: እርሱ ባርኮአል:: እመልሰውም ዘንድ አልችልም» አለ:: ባላቅም በለዓምን «ከቶ አትርገ ማቸው ከቶም አትባርካቸው::» አለው:: በለዓምም መልሶ ባላቅን «እግዚአብሔር የተናገረውን ሁሉ አደርጋለሁ ብዬ አልተናገርሁምን?» አለው ሦስተኛም «ያዕቆብ ሆይ ድንኳኖችህ እሥራኤል ሆይ ማደሪያ ዎችህ ምንኛ ያምራሉ... የሚመርቅህ ሁሉ የተመረቀ ይሁን:: የሚረግ ምህም ሁሉ የተረገመ ይሁን::» በማለቱ ባላቅ ተበሳጨ በለዓምም ባላ ቅን «በቤትህ የሞላው ብርና ወርቅ ቢሰጠኝ መልካሙን ወይም ክፉ ውን ከልቤ ለማድረግ የእግዚአብሔርን ቃል እተላለፍ ዘንድ አይቻለኝም



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር የተናገረውን እርሱን እናገራለሁ:: ብዬ ለላክሃቸው መልእክተኞችህ አልተናገርኋቸውምን?» አለው፣ በመጨረሻም «አየዋለሁ አሁን ግን አይደለም እመለከተዋለሁ በቅርብ ግን አይደለም:: ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል» ሲል ትንቢት ተናገረ:: ዘኍ.፳፬÷፳፫-፳፬::

ከላይ የተጠቀሰውን ታሪክ ምሳሌ ብናደርግ የሚያስተምረን መሠረታዊ ትምህርት አለ ይኸውም ትናንትም ሆነ ዛሬ በዘመናችን ብዙ ባላቆች እንዳሉ ነው:: ባላቅ ምንም እንኳን የእግዚአብሔርን ስም ቢራገም እግዚአብሔር የባረከውን ሕዝብ ለመርገምና ለማስረገም ሲጣደፍ ተገኝቷል:: ሆኖም አልተሳካለትም:: በለዓምም እግዚአብሔር ያልረገመውን እንዴት እረግማለሁ? ያልተጣለውንስ እንዴት እጣላለሁ ሲል ተጠንቅቆ እግዚአብሔር በአፉ ያኖረለትን የበረከት ቃል ተናገረ እሥራኤልን ባረከ::

እንግዲህ የዛሬ ባላቆች ከዚህ መማር አለባቸው:: እግዚአብሔር የባረካትን ድንግል ማርያምን መርገም የወደዳትን መጣላት አይቻልም:: በለዓም እሥራኤልን ለመባረክ ከባራኪው ከእግዚአብሔር ትእዛዝ እንደ ተቀበለ ቅዱስ ገብርኤል እና ኤልሳቤጥም እግዚአብሔር ቢያዝዛቸው ቃሉንም በአንደበታቸው ቢያኖርላቸው ነው በአንድ ቃል ድንግል ማርያምን ያመሰገኑት:: በለዓም ቡራኬውን ወደ መርገም መለወጥ አይቻለኝም እንዳለ እኛም እግዚአብሔር ለዚህ መርጧታልና ፍቅሯን በጥላቻ የአምላክ እናትነቷን ወደ ሰው እናትነት መለወጥ አይቻለንም:: የሰዎች እምነት መለዋወጥ የዘለዓለም ድንግል እና የአምላክ ብቻ እናት የሆነችውን የድንግል ማርያምን ማንነት አይለውጠውም::

በለዓም ለሦስተኛ ጊዜ በሞዓብ ሜዳ የሰፈረውን ሕዝብ አሻግሮ እያየ የተናገረው፣ «ያዕቆብ ሆይ ድንኳኖችህ እሥራኤል ሆይ ማደሪያዎችህ ምንኛ ያምራሉ:: ... የሚመርቅህ ሁሉ የተመረቀ ይሁን የሚረግምህም ሁሉ የተረገመ ይሁን::» የሚል ነበረ:: ድንቅ ቃል ነው:: በዚህም ምሳሌ ቅዱስ ገብርኤልንና ኤልሳቤጥን ተከትለን የያዕቆብ አምላክ ሆይ ድንኳንህ የእሥራኤል ጌታ ሆይ ድንኳንህ የእሥራኤል ጌታ ሆይ ማደሪያህ ድንግል ማርያም ምንኛ ያማረች የተባረከች ናት እንላለን::





እግዚአብሔር ለአብርሃም አባ ጊዮርጊስ በሰዓታት ድርሰቱ ለእመቤታችን በለዓለም በእግዚአብሔር ቃል ለእሥራኤል እንደተናገሩት፣ እኛም ድንግል ማርያም ሆይ የሚመርቅሽ የተመረቀ የሚረግምሽ ደግሞ የተረገመ ይሁን እንላለን:: መራገማችን ወይም መፍረዳችን አይደለም:: የሚፈርደው ዘለዓለማዊ ቃሉ ነው:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «የሚጥለኝ ቃሌንም የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው:: እኔ የተናገርሁት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል::» ማለቱ ለዚህ ነው:: ዮሐ.፲፪÷፵፰::

በለዓም በመጨረሻ «ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል::» እንዳለ ከያዕቆብ ወገን ከምትሆን ከድንግል ማርያም ሳይከፍት ገብቶ ሳይከፍት ይወጣ ዘንድ ኮከብ የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስ ጊዜውን ሲደርስ በማኅፀነ ድንግል አደረ:: በኤልሳቤጥ አንደበት ቡሩክ ተባለ:: እናቱም ቡርክት ተባለች:: አዎ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ድንግል ማርያም ሆይ የተባረክሽ ነሽ የማኅፀንሽም ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ የተባረከ ነው:: እመቤታችን ሆይ ሥጋውን ደሙን ተቀብለን የዘለዓለም ሕይወት እንድናገኝ የልጅሽ ቸርነት የአንቺ አማላጅነት አይለየን:: አሜን::



www.ethiopianorthodox.org

# «ጸሎትህ ተሰምቶልሃል» ሉቃ.፩÷፲፫

*በዲ/ን ተክለወልድ*

ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ለእግዚአብሔር ስለተፈጠረ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ይፈልጋል:: መገናኛውም ጸሎት ስለ ሆነ ይጸልያል:: ቀደምት አበው /የቀደሙ አባቶች/ ጸሎት በሰቂለ ኅሊና በአንቃዕድዎ ልቡና በሰፊሃ እድ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር እንደሆነ ነግረውናል:: ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የመገናኛ ምልክትና ማጽኛ ነው:: ጸሎት ኅብረትን ምስጋናን ስግደትን ንስሐን ልመናን ምልጃን ያጠቃልላል:: ሰዎች በልዩ ልዩ አቋቋም ቦታና ጊዜ ሊጸልዩ ይችላሉ:: ዋናው ነገር ግን የልብ መሰበር ነው:: ነቢዩ ዳዊት እንዳለ «የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም» መዝ.፶÷፲፯ ቃሉም ትሕትናን ገንዘብ ማድረግ እንዲገባ ያስተምረናል::

በሕይወቱ ውስጥ ጉድለት ያለበት ሰው ሁሉ የጨለመው እንዲበራለት የጠመመው እንዲቃናለት የጠወለገው እንዲለመልምለት የተዘጋው እንዲከፈትለት የዘራው እንዲበቅልለት የተተከለው እንዲጸድቅለት የተወለደው እንዲያድግለት የተበተነው እንዲሰበሰብለት የተሰበሰበውም እንዲባረክለት ልመናውን በጸሎት ለእግዚአብሔር ያቀርባል:: እግዚአብሔርም የልጆቹን ጸሎት በደስታ ይሰማልና ጸሎት ብዙ ኃይል አለው:: ፩ጴጥ.፫÷፲፪፤ ያዕ.፭÷፲፯ ጸሎቱ የተሰማለት ሰው ፈጥኖ ከሐዘኑ ይጽናናል:: ከጭንቀቱ ይረጋጋል:: ከትካዜ ባሕር ይወጣል ከድካሙ ይበረታል::

በትእዛዙና ሕግጋቱ ሲመዘን ያለነቀፋ የሄደና በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ የነበረ ካህን ዘካርያስ በአዲስ ኪዳን ዋዜማ እንደ ካህናት ሥርዓት ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ጽንሐውን ይዞ በሚያጥንበት ጊዜ ከዕጣኑ መሠዊያ በስተቀኝ መልአኩን በማየቱ ደነገጠ፤ ፍርሃትም ወደቀበት:: ሉቃ.፩÷፲፩-፲፫ ተፈጥሮአቸው ከማይጠፋ እሳትና ነፋስ የሆኑ ቅዱሳን መላእክት ኃይላቸው ታላቅ ስለሆነ የሚያስፈሩና የሚያስደነግጥ ግርማ አላቸው:: መዝ.፻፫÷፳፤ ፻፫÷፬:: እንኳን ሰው ምድር በፊታቸው ትንቀጠቀጣለች:: እጅግም የሚያስፈሩ ናቸው:: መልካቸው እንደ መብራት ልብሳቸውም እንደ በረዶ ነጭ ነውና:: ማቴ.፳፰÷፫::

በዚህ ሁኔታ ለዘካርያስ የተገለጠው መልአክ «ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ» ብሎ ካረጋጋው በኋላ ሚስቱ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ስሙም ዮሐንስ እንደሚባል ለዘካርያስም ተድላና ደስታ እንደሚሆንለት በመወለዱም ብዙዎቹ ደስ እንደሚላቸው በጌታ ፊት ታላቅ እንደሚሆን የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ እንደማይጠጣ በእናቱም ማኅፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚቃኝ ከእስራኤልም ልጆች ብዙዎቹን ወደ አምላካቸው እንደሚመልስ የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ እንደሚያሰናዳ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ እንደሚሔድ ለዘካርያስ በዝርዝር ነገረው:: ይህ ሁሉ ሲሆን በዕጣኑ መሥዋዕት ጊዜ በውጭ ይጸልዩ የነበሩት ሕዝብ በዘካርያስ መዘግየት ከመደነቅ በቀር ምንም አላወቁም:: ዘካርያስ «እኔ ሽማግሌ ነኝ ሚስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህን በምን ዐውቃለሁ» በማለቱ መልአኩ መልሶ «እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ እንድናገርህም ይህችንም የምሥራች እንድሰብክልህ ተልኬ ነበር:: እነሆም በጊዜው የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንህ ዲዳ ትሆናለህ መናገርም አትችልም» ስለአለው ወዲያው ዲዳ ሆነ:: ከመቅደስም በወጣ ጊዜ ሊመናገር ባለመቻሉ ሕዝቡ ራእይ እንዳየ አስተዋሉ:: እግዚአብሔር ለወዳጆቹ በራእይ ይገለጣልና በሕልምም ያነጋግራቸዋልና:: ዘኍል.፲፪÷፮:: ሉቃ.፩÷፲፫-፳፫::

በብሉይ ኪዳን ታሪክ ነቢዩ ዳንኤል በኡባል ወንዝ መካከል ቅዱስ ገብርኤልን ጤግሮስ በተባለው በታላቁ ወንዝ አጠገብ በፍታ የለበሰውንም ጥሩም የአፌዝን ወርቅ በወገቡ የታጠቀውን አካሉም እንደ ቢረሌ÷ ፊቱም እንደ መብረቅ አግሮቹም እንደ ጋለ ናስ የሚመስለውን የቃሉም ድምፅ እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ የነበረውን መልአክ ባየ ጊዜ እንደ ፈራ እንደተንቀጠቀጠ÷ እንደ ደነገጠ እና እንደሰገደ የዘካርያስም ፍርሃትና ድንጋጤ ከዚሁ እንጻር ነበር:: በዚህም አባቶቹን ነቢያትን መስሎ ተገኝቷል:: ዳን.፲÷፲፮፤ ፲÷፭:: አባቱን የማይመስል ልጅ ግን





www.ethiopianorthodox.org

ዲቃላ ነው:: ዘዳግ.፳፫÷፪:: ዕብ.፲፪÷፳:: ዲቃላ ያይደለ የሕግ ልጅ ዘካርያስ መላእክትን ማክበር እንደ አባቶቹ ገንዘብ አደረገ::

ነቢዩ ዳንኤል በማታ መሥዋዕት ጊዜ ስለራሱና ስለሕዝቡ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ሲጸልይና ሲናዘዝ ጸሎቱ ስለተሰማለት መሥዋዕቱ ስለሠመረለት ቅዱስ ገብርኤል እየበረረ መጥቶ ዳሰሰው÷ አስተማረው÷ ተናገረው:: በአዲስ ኪዳን መግቢያ በር ላይ የነበረውም ጻድቅ ካህን ዘካርያስ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ስለራሱም ሆነ ስለሕዝቡ ሲጸልይና መሥዋዕተ ዕጣን ሲያሳርግ መልአኩ ተገልጦ አነጋገረው:: ዳን.፱÷፳:: ሉቃ.፩÷፲፫:: ዕጣን ጸሎትን የሚያሠምር የመዓዛ መሥዋዕት ነውና:: ራእ.፰÷፫-፬::

ሥጋንና እንጀራን ከመብላት የወይን ጠጅን ከመጠጣትና ዘይትም ከመቀባት ተከልክሎ ሰውነቱን በጾምና በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት አዋርዶ ለነበረው ነቢይ ለዳንኤል መልአከ እግዚአብሔር ተገልጦ የተወደድህ ሰው ዳንኤል ሆይ አትፍራ ልብህ ያስተውል ዘንድ ሰውነትህም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ካደረግህበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ቃልህ ተሰምቶአል:: እኔም ስለቃልህ መጥቻለሁ በማለት ፍርሃትን አርቆ እንዳበሰረው ለዘካርያስም «ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ» ብሎ ጸሎቱ ቅድመ እግዚአብሔር መድረሱን ነገረው:: ዳን.፲÷፲፪:: ሉቃ.፩÷፲፫ በዘመነ ሐዋርያት ለቆርኔሌዎስ «ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን ዐረገ» ተብሎ በመልአክ ቃል እንደተነገረው ማለት ነው:: የሐዋ.፲÷፬::

ባለጠግነቱ ጥበቡና ዕውቀቱ ፍርዱ የማይመረመር ለመንገዱም ፍለጋ የሌለው እግዚአብሔር ለሣራ ካረጀች ካፈጀች በኋላ ይስሐቅን÷ ለመካኒቱ የማኑሄ ሚስት በብሥራተ መልአክ ኃያሉ ሶምሶንን÷ በልጅ ዕጦት ብስጭት ከስታ ጠቁራ ከመብል ከመጠጥም ተከልክላ ለነበረች ለሕልቃና ሚስት ለሐና ነቢዩ ሳሙኤልን እንደሰጠ ለዘካርያስና ለኤልሳቤጥም የሆድ ፍሬ ዋጋ ሊከፍላቸው የልጅ ስጦታ ሊሰጣቸው ፈቀደ:: ዘፍጥ.፲፰+፲፬ መሳ.፲፫+፪:: ፩ሳሙ.፩+፲፱ ሮሜ ፲፩÷፴፫:: ነቢዩ ዳዊት እንዳለው «እነሆ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው የማኅፀንም ፍሬ ዋጋ ናቸው» መዝ.፻፳፯÷፫:: ዘፍጥ.፴÷፪::





ዘካርያስ ሕገ እግዚአብሔርን አክብሮ የመቅደስን አገልግሎት አጽንቶ እምነትን ከምግባር አዋሕዶ በመገኘቱ በፍሬ ምግባር ላይ ፍሬ ማኅፀን እንደሚጨመርለት የሚገልጠውን ቃል ሰማ፤ ይህም በጸጋ ላይ ጸጋ በበረከት ላይ በረከት መሆኑ ነው:: በብሉይ ኪዳን ልጅ አለመውለድ ልዩ ትርጉም ነበረውና የዘካርያስም ኀዘኑ ይኸው ነበረ:: ይሁን እንጂ መልአኩ÷ «ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች:: ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ደስታና ተድላም ይሆንልሃል» አለው:: የያዕቆብ ሚስት ልያ ለባልዋ ደጋግማ ወንዶች ልጆች በመውለድዋ «ደስታ ሆነልኝ ሴቶች ያመሰግኑኛልና» ብላለች:: ዘፍ.፴÷፲፫ ፩ቆሮ.፲፩÷፫::

የይስሐቅ መወለድ የአብርሃምና የሣራ÷ የሶምሶን መወለድ የማኑሄና የሚስቱ÷ የሳሙኤል መወለድ የሕልቃናና የሐና ደስታ ነበረ:: የዮሐንስ ግን ልዩ ነው:: ምክንያቱም ደስታው በወላጆቹ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ለብዙዎች ሰዎች ጭምር እንደሚሆን መነገሩ ነው:: ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬያት አንዱ ደስታ በመሆኑ ዮሐንስን ደስታ ነው ለማለት ይቻላል:: ገላ.፭÷፳፪:: ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ፍሬ ደስታ ዮሐንስን እንዲያፈሩ እግዚአብሔር የተከላቸው ዛፎች ናቸው «መልካም ዛፍ መልካም ፍሬ ያፈራልና» ማቴ.፯÷፲፯ መልካም ዛፍ የደጋግ ሰዎች ቅጠል የሃይማኖታቸው ፍሬ የምግባራቸው ምሳሌ ነው::

የዘካርያስና የብዙዎች ሰዎች ተድላና ደስታ የሚሆን ዮሐንስ ወደፊት ጌታን በማጥመቅ መጥምቀ መለኮት በመሰኘት ታላቅነቱ የሚገለጥ ነውና «በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና» ተባለ:: ይህ ታላቅነት የሚገኘው ራስን በሰውና በፈጣሪ ፊት በትሕትና በማሳነስ ነው:: ማቴ.፳÷፳፮፤ ፳፫÷፲፪ ሉቃ.፳፪÷፳፮:: ያዕ.፩÷፱፤ ፬÷፲:: ምሳ.፳፱÷፳፫:: ከማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ በመሆኑ የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ እንደማይጠጣ ተነገረለት:: ይህ ምልክት በእሥራኤል ዘንድ ልማድ ነበረ:: «ሰው ወይም ሴት ለእግዚአብሔር ራሱን የተለየ ያደርግ ዘንድ የናዝራዊነት ስዕለት ቢሳል ከወይን ጠጅና ከሚያሰክር መጠጥ ራሱን የተለየ ያድርግ» ይላል:: ዘኁ.፮+፪:: ሶምሶን ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ



www.ethiopianorthodox.org

ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ እንደሚሆን ተነግሮለት ነበር:: መሳ.፲፫÷፯:: ዋናው ነገር ለአገልግሎት የተመረጠና የተለየ ሰው መሞላት ያለበት በእግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በወይን ጠጅ አይደለም:: ሉቃ.፳፭÷፴፩:: ሮሜ.፲፫÷፲፫ ኤፌ.፭÷፲፰

ነቢዩ ዳዊትን በእናቱ ማኅፀን ሳለ ሰውሮ ግሩምና ድንቅ ሆኖ እንዲፈጠር ያደረገ፣ ነቢዩ ኤርምያስንም ገና በማኅፀን ሳይፈጥረው ያወቀው በማኅፀንም ሳለ የቀደሰው አምላክ ዮሐንስም በእናቱ ማኅፀን እያለ በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላ እንዲቀደስም ፈቃዱ ሆነ:: መዝ.፩፻፴፰÷፲፫ ኤር.፩÷፭:: ሉቃ.፩÷፲፭:: እግዚአብሔር የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ከወሰናቸው÷ ከጠራቸው÷ ካጸደቃቸውና ካከበራቸው መካከል ታላቁ ዮሐንስ መጥምቀ መለኮት ነው:: ሮሜ.፰÷፳፱:: ጌታም በወንጌል÷ «ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ የለም» ማለቱ ለዚሁ ነው:: ማቴ.፲፩÷፲፩

ዮሐንስ በድንቁርና ጨለማ ያሉትን ወደ ዕውቀት ብርሃን ክርስቶስ እንዲመራ÷ በኃጢአት ያሉትን በንስሐ ወደ ጽድቅ እንዲመልስ÷ በአምልኮተ ጣዖት የተጠመዱትን ፈትቶ ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር እንዲያመጣ የተመረጠ ነውና «ከእሥራኤል ልጆች ብዙዎችን ወደ ጌታ አምላካቸው ይመልሳል» ተባለ:: እሥራኤል አብዛኞቹ በኃጢአትና በበደል ምክንያት ከጌታ ተለይተው ነበርና ነው:: በደል ከእግዚአብሔር ይለያል ኃጢአትም ከእግዚአብሔር ቸርነት ያርቃል:: ይህም ምሕረቱ÷ ቸርነቱ÷ በረከቱ÷ ረድኤቱ÷ ርኅራኄውና ይቅር ባይነቱ ይሰወራል÷ ይርቃል ማለት ነው:: ኢሳ.፶፱÷፪::

በነቢዩ በኢሳይያስ እንደተነገረ ቃለ ዓዋዲ ዮሐንስ ለጽድቅ ምድረ በዳ እና በረሃ የሆነውን የሰው ልቡና ጠርጐ አስተካክሎ ምቹ ጐዳና /ፍኖተ እግዚአብሔር/ እንዲሆን የሚያመቻች÷ በኃጢአት ተሸርሽሮ ሸለቆ÷ በትዕቢት አብጦ ተራራ÷ በክፋት ጸንቶ ጠማማ የሆነውን ልብ የተስተካከለ ትሁትና ቀና አድርጐ መሢሕ ክርስቶስን እንዲቀበል የሚያሰናዳ÷ ነቢዩ ሚልክያስም እንደተናገረ በድንገት ወደ መቅደሱ ለሚመጣ ጌታ መንገድን በፊቱ የሚያስተካክል በመሆኑ የተዘጋጀ





ትን ሕዝብ ለጌታ እንደሚያሰናዳ ተነገረለት:: መንገድ ጠራጊ መባሉም ለዚህ ነው:: ኢሳ.፵÷፫:: ሚል.፫÷፩:: ሉቃ.፩÷፲፯

ጌታ በወንጌል ወደ መንግሥተ ሰማያት እንድትገቡ ታላቅም እንድትሆኑ ተመለሱ እንደ ሕፃናትም ሆናችሁ ራሳችሁን አዋርዱ ባለው መንገድ ዮሐንስ መንግሥተ ሰማያት ወንጌል ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ብሎ የሚሰብክ÷ ብዙዎች በትሕትና ተዋርደው ለክፋት ነገር ሕፃናት እንዲሆኑ የሚመክር÷ እግዚአብሔርን የመፍራት ጥበብ የጐደላቸውን መንግሥቱንና ጽድቁን ወደ መፈለግ ጥበብ የሚመልስ÷ ከኃጢአት አዋቂነት ወደአለማወቅ ሕፃንነት የሚለውጥ በመሆኑ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልሳል ተባለ:: የጻድቃን ጥበባቸው መሠረቱ እግዚአብሔርን ማፍራት ነው:: ምሳ.፩÷፯:: ማቴ.፫÷፩:: ማቴ.፲፰÷፫:: ፩ቆሮ.፲፬+፳:: ፍርሃት ሲባልም መጋቢነቱን÷ ፈጣሪነቱን÷ ጌትነቱን÷ ኃያልነቱን ዐውቆ በመንግሥቱ ሽረት በባህርዩ ሞት የሌለበት ጻድቅ ፈራጅ መሆኑን ማመን ነው::

ሣራ÷ «ካረጀሁ በኋላ በውኑ ፍትወት ይሆንልኛልን? ጌታዬም ፈጽሞ ሸምግሎአል» እንዳለች ዘካርያስም እኔ ሽማግሌ ነኝ÷ ሚስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህን በምን አውቃለሁ? በማለቱ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ይህ ቃሌ እስኪፈጸም ድረስ ዲዳ ትሆናለህ አለው:: ሆኖም ዘካርያስን ተገሠፀ:: «አባት የሚወደውን ልጅ እንደሚገሥፅ እግዚአብሔርም የወደደውን ይገሥፃልና::» ዘፍ.፲፰÷፲፪ ምሳ.፫÷፲፩ ሉቃ.፩+፲፰ ተግሣፁ በዘካርያስ ልብ የተከሰተው ጥርጥር እንዲወገድ ነው:: ሕዝቡ ለከበረ አባታችን ራእይ ተገልጦለት ነው አሉ እንጂ እንደ ደካሞቹ በኃጢአቱ ምክንያት ይሆን? ብለው አልተጠራጠሩም:: ለመፍረድም አልቻሉም:: እርሱም የአገልግሎቱ ወራት እስኪፈጸም ድረስ ከቤተ መቅደስ አልተለየም::

እንግዲህ ከዚህ የምንማረው ምንድነው? እኛስ ጸሎታችን እንዲሰማልን ምን እናድርግ? ከሐዘን ይልቅ ደስታን+ ከጦርነት ይልቅ ሰላምን÷ ከመርዶ ይልቅ የምሥራችን የምንሰማው ምን ስንሆን ነው?



www.ethiopianorthodox.org

ከሥር ጀምሮ ታሪኩን እንደተመለከትነው የሚያስፈልገው ነገር ዘካርያስንና ኤልሳቤጥን ሆኖ መገኘት ነው። ይኸውም በጌታ ሕግጋትና ትእዛዛት መኖር፥ ከቤተ ቤተመቅደስ አለመለየት፥ ከዕጣኑ መሥዋዕት አለመራቅ ነው። ዕጣኑ የዘላለም መሥዋዕት ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና ከቅዱስ ቁርባን አለመለየትን ያመለክታል። ዘካርያስ በቤተ መቅደስ ቢዘገይም ሕዝቡ በትዕግሥት እንደጠበቁት ቅዳሴው ቢረዝምም ካህናቱ ከመቅደስ ወጥተው እስኪያቆርቡን በትዕግሥት መጠባበቅ አለብን። እነዘካርያስ ተስፋ ሳይቆርጡ እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ የሚፈልጉትን ለማግኘት እስኪያረጁ ድረስ እንደጸለዩ እኛም እስከመጨረሻው ተስፋ ሳንቆርጥ እንጸልይ። ስንጸልይም በአጭሩ አራት ነገሮችን እናስተውል።

፩. መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ.፳፩፥፳፪ «አምናችሁም በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ» ባለው መሠረት ያደርጠግልኝ ይሆን? ወይስ አያደርግልኝ ይሆን? እያልን ሳንጠራጠር በእምነት እንጸልይ። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ «ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጐድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን። ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን። የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕር ማዕበል ይመስላልና። ሁለት አሳብ ላለው በመንገዱም ሁሉ ለሚወላውል ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች የሚያገኝ አይምሰለው» በማለት አስተምሮናል። ያዕ.፩፥፭። የጥርጥር ማዕበል በልባችን ውስጥ የተነሣ እንደሆነ ኑሮአችን ሁሉ ማለት ሥጋዊውም ሆነ መንፈሳዊው በሁከት የተሞላ ይሆናል። የምንሻውንም አናገኝም። ይህ እንዳይሆን ነው የእምነት ጸሎት የሚያስፈልገው። እንዲያውም እግዚአብሔር የነገሩትን የማይረሳ የለመኑትን የማይነሳ አምላክ ነውና «የጸለያችሁትንና የለመ ናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ ይሆንላችሁማል» ትዕግሥቱ ካለ መቼም ይሁን መች አያስቀርባችሁም ማለት ነው። ማር.፲፩፥፳፫።

፪. የምንለምነውን እንወቅ። የዘብዴዎስ ልጆች እናት ሳታውቀው ለልጆቿ መከራና ሞተ እንደለመነች ጌታም «የምትለምኑትን አታውቁም»





እንዳላት እኛም አለማመኑን አጥተንበት ጌታ ጨክነብኝ ስንል እንዳንገኝ ምን እንደምንለምንና ለምን እንደምንለምን ማወቅ አለብን። የሚቀረውን ርስት ምድራዊ ሳይሆን ርስት ዘላለማዊ መንግሥቱን፥ የሚጠፋ ሀብትን ሳይሆን የማይጠፋ ሀብተ መንፈስ ቅዱስን፥ ሥጋዊ መብልን መጠጥን ሳይሆን መንፈሳዊውን ሥጋ ወደሙን እንለምን ይሰጠናል። «ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል» ተብለናልና። ማቴ.፮፥፴፫። መንግሥቱን ሲል ሃይማኖትን ጽድቁን ሲል ምግባርን ነው።

«የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ ከመጐምጀትም ሁሉ ተጠበቁ» መባሉ ለዚህ ነው። ሉቃ.፲፪፥፲፫

፫. እንደ ፈቃዱ እንጸልይ። ሐዋርያው ዮሐንስ፡ «በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው። እንደፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል የምንጠለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመንነውን ልመና እንደተቀበልን እናውቃለን» ባለው መሠረት የእርሱ ፈቃድ መንፈሳዊውን ነገር እንድንለምነው ነው። ፩ዮሐ.፭፥፲፬ የሚቱን ሞት አይፈቅድምና ከዘላለም ሞት አድነን ብለን እንለምነው። ሕዝ.፲፰፥፴፪ ለዚህም ከኃጢአት መመለስ በደልን ማራቅ ተገቢ ነው።

፬. በጸሎታችን ኃጢአታችንን እንናዘዝ «ቀም ይሆ ጸሎት ሳል ይሆ ስርቆት» አይሆንምና አስቀድመን በሕይወታችን ውስጥ ያቄምነውን ኃጢአት በንስሐ ማስወገድ ይገባናል። በተቋረጠ መስመር ስልክ መደወልና በኃጢአት ሆኖ መጸለይ አንድ ነው። ነቢዩ ኢሳይያስ፥ «የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም። ጆሮውም ከመስማት አልደነቆረችም። ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች። እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል» ብሎናል። ኢሳ.፶፱፥፩። ስለዚህ ራስህን ለካህን አሳይ ባለው መንገድ ኃጢአታችንን ተናዝዘን በንስሐ ታጥበንና ነጽተን እንጸልይ። አበው «ልብስ ሲያድፍ በውሃ፥ ሰውነት ሲያድፍ በንስሐ ይነጻል» ይላሉ።

ያን ጊዜ በምድር የታሰረው በሰማይ የታሰረ ይሆናል። ካህናቱ ይቅር ሲሉን በእርሱ ዘንድም ይቅር እንባላለን። ማቴ.፰፥፬። ማቴ.፲፮፥፲፱፤



www.ethiopianorthodox.org

ማቴ.፲፰÷፲፰ ዮሐ.፳÷፳፫:: ከሁሉም አስቀድመን ግን የሰማዩ አባታችን ይቅር ይለን ዘንድ የበደሉንን ሁሉ ከልብ ይቅር ማለት አለብን:: ማር.፲፩÷፳፮:: «ሲበድሉ ማሩኝ ሲበደሉ ይቅርታ የክርስቲያንነት ምልክት ነውና::»

መቼም ሁላችንም በዚህ የምንመራ ከሆነ ጸሎታችን ተሰምቶ ከማኀፀን የተባረከ ልጅ ከሜዳ የተባረከ ፍሬ እናገኛለን:: የሰማዩ አባታችን እንኳን ለምንነው ሳንለምነው የሚያስፈልገንን የሚያውቅ ነው:: ማቴ.፮÷፰ በኤርምያስ አድሮ÷ «ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ ዐውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም:: እናንተም ትጠሩኛላችሁ:: ሄዳችሁም ወደ እኔ ትጸልያላችሁ:: እኔም እሰማችኋለሁ:: እናንተ ትሹኛላችሁ በፍጹም ልባችሁ ከሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ ከእናንተም እግዚአብሔር አነጋግሮታል:: ዘፍ.፲፭÷፩-፳፩:: ስሙ በተለወጠለትና አብርሃም በተባለ ጊዜ ከእግዚአብሔር ተነጋግሯል:: ዘፍ.፲፯÷፩:: በመምሬ የአድባር ዛፍ ሥር እንግዶችን ለመቀበል በመጠባበቅ ላይ እያለ አንድነቱን ሦስትነቱን በገለጠለት ጊዜ እግዚአብሔር አነጋገረው:: ዘፍ.፲፰÷፩-፪:: ሣራ ልጅ እንደምትወልድ ተስፋ በተሰጣት ጊዜ እግዚአብሔር አነጋገረው:: ዘፍ.፲፰÷፲፩-፲፭ ስለሰዶምና ገሞራ ብዙ ጊዜ ከፈጣሪው ጋር ተነጋገረ:: ዘፍ.፲፰÷፳፪ እስከ ፍጻሜ:: ልጁ ይስሐቅን እንዲሠዋለት በጠየቀው ጊዜ እግዚአብሔር አነጋግሮታል:: ዘፍ.፳፪÷፩-፲፰

አብርሃም ከማንም በላይ ያለ ሕግ ቅንና ደግ ሆኖ በመገኘቱ ከፈጣሪው ጋራም እውነተኛ በሆነ ፍቅሩና በጽኑ እምነቱ በመተዋወቁ ንግግሩ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ኑሮው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ነበር:: ሕይወቱን ሁሉ በድንኳን ውስጥ በመኖር ያሳለፈው አብርሃም በዘሩ ምድር እንደምትሞላ ተነግሮታል:: እርሱ እግዚአብሔር በተለየ ነገር የመረጠው÷ ለድንቅ ክብር ያኖረው÷ ማንም ለማያውቀው ምሥጢር የፈጠረው ሰው ነው:: በብሉይ ኪዳን ዘመን በነበሩት አበው ሁሉ ዘንድ ምሳሌነቱ ሲነገር የነበረ የዓለም ሁሉ መመኪያና ተስፋ ነበር::



www.ethiopianorthodox.org



ከዘሩ የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ እንዲወለድ የእግዚአብሔር ፈቃድ በመሆኑ በዘሩ ዓለም ሁሉ እንደሚባረክ ተነግሮለታል:: ይህም ተስፋ ተፈጽሟል:: «ይታደሷል እንጂ ይታገሷል?» ይሉታል እንዲህ ነው::

ቤሉዲስ ኪዳንም ለእግዚአብሔር መታዘዙ ዮሐ.፰÷፴፱-፵:: ዕብ.፲፩÷፲፯-፲፱ ያዕ.፪÷፳፩-፳፬:: በሃይማኖቱ የምእመናን ሁሉ አባት መባሉ፣ በክርስቶስ አምነው ዘለዓለማዊ ሕይወት ለሚያገኙት የሰው ልጆች ምሳሌ መሆኑ፣ ሮሜ.፬÷፩-፫:: ገላ.፫÷፮-፯:: ያመኑና ምግባርን የሠሩ ሁሉ የአብርሃም የግብር ልጆች መሆናቸው፣ ሮሜ ፬÷፲፩-፲፪ ሮሜ፱÷፯-፰:: ገላ.፫÷፯-፱፥፳፱:: ስለዚህ ጻድቅ ሰው ጎልተው የተነገሩ ማስረጃዎች ናቸው::

የጻድቁ የአብርሃም ሕይወት በንጽሕናና በቅንነት መኖር ሳይታሰብ እግዚአብሔር ብቻ በሚያውቀው ጥበብ ከአምላክ ጋር የሚያነጋግር መሆኑን ያስተምረናል:: እርሱ በየዋህነት በነበረው መመሳለስ የእግዚአብሔርን ጥሪ ለመስማት ከእግዚአብሔርም ጋር ደጋግሞ ቃል በቃል ለመነጋገር በቅቷል:: ይህን የእግዚአብሔርን የጥሪ ቃል ለመስማት በሃይማኖት መዘጋጀት፣ እግዚአብሔርም ሲጣራ አቤት በሚል ከሁሉ በላይ ለእግዚአብሔርና ለጥሪው ቃል ለመታዘዝ በቅንና ታዛዥ ልቡና ዝግጁ መሆንን ያስተምረናል::

እግዚአብሔር ሲጣራ አባቴ÷ እናቴ÷ ዘመዶቼ÷ ሀገሬ ሳይል ለተጠሩበት የሕይወት ጎዳና ቆርጦና አምኖ መሔድን÷ ሳያመነቱና ሳይጠራጠሩ ማመንን÷ በሁሉም ሥፍራ በሁሉም ጊዜ እግዚአብሔርን ብቻ ዘመድና ረዳት አድርጎ እግዚአብሔርም የሰጠው ሁሉ ነገር መሆኑን አውቆ የትእዛዛቱ ፈጻሚ መሆንን ያስተምረናል::

የክርስቲያኖች ሕይወት እግዚአብሔር የሚጎበኘው÷ የሚያነጋግረው÷ የሚመራው÷ የሚባርከው ሊሆን ያስፈልጋል:: እንደ አብርሃም ያለ ሃይማኖት ነው የእግዚአብሔርን ድምፅ ወደ ሰው ሊያመጣው የሚችለው:: መጠራትም የማቻለው ለመጠራት በሚያበቃ ሕይወት የተገኙ እንደ ሆነ ነው:: ያለበለዚያ ባዶ ሆኖ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርና

የእግዚአብሔር በረከት የሚገኝበትን ጥሪ መስማት አይቻልም። በሥጋ ከሥጋ ለሆነ ነገርና ከምድር የሚገኘውን ክብር፥ ተድላ ደስታ ብቻ ተስፋ አድርጎ የሚኖርና ሐሳቡ ሁሉ በምድር የሆነ ሰው ለእግዚአብሔር ሊሆን አይችልም። በምድር ያለው ማንነቱ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ላይ የሰለጠነበት ማንም ቢሆን የሥጋውን ምኞትና ምድራዊ ፍላጎቱን ማሸነፍ ካልተቻለ የእግዚአብሔርን የጥሪ ቃል ለመስማት አይችልም። የእግዚአብሔርን የጥሪ ቃል ለመስማት እንደአብርሃም መለወጥና እግዚአብሔር ደስ በሚሰኝበት ሕይወት መመላለስ ያስፈልጋል። ኑሮውን በድንኳን ውስጥ በመንገድ ዳር አድርጎ የሚያልፍ የሚያገድመውን እያስተናገደ ይኖር የነበረው አብርሃም ውስጣዊ ማንነቱን ለውጦ የሃይማኖትና የምግባር ሰው ስለነበረ ሥላሴን ማስተናገዱን፣ ቃል በቃል ከፈጣሪው ጋር መነጋገሩን ስናስተውል ምንኛ የእግዚአብሔር ሰው እንደነበር እንገነዘባለን።

አብርሃም እግዚአብሔር ሲጠራው አምኖ ከሀገሩ ወጣ፤ ከወገኖቹም ተለየ አምላኩን ፍለጋ፥ በረከት ፍለጋ። አዎን፥ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ለጣዖት አምልኮ ተገዝቶ በኃጢአት ይኖርባት የነበረችውን ሀገር እግዚአብሔር በሰጠው ከፈጣሪው ጋር እየተነጋገረ በሚኖርባት ሀገረ ሕይወት ለውጦ፥ በሥጋ የወለዱትን እናትና አባቱን ብቻ ሳይሆን በአምልኮ እናት አባት የሆኑትን ጣዖታት ሁሉ ጥሎ ወደኋላም ዞሮ ሳያያቸው ሀገሩን ከነዓን እናት አባቱን እግዚአብሔር አድርጎ ከምድረ ካራን ወጣ። ይህ ነው እንግዲህ በእውነት የእግዚአብሔር ሰው የሚባለው፤ የበረከት ጥሪ ከሁሉ በላይ የሆኑትን በሃይማኖት የማያልፈውን ተስፋ ገንዘብ አድርጎ በሕይወቱ የሰለጠኑትን የሥጋ ገመዶችና የፍላጎት ማነቆዎች በጥሶ ለእግዚአብሔር ለመሆን በእግዚአብሔር ለመኖር ራስን ለውጦ መሔድ። ለዚህ ነው ከዘሩ የተገኘው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት «ብፁዕ ሕዝብ ዘእግዚአብሔር አምላኩ፣ እግዚአብሔር አምላኩ የሚሆን ሕዝብ ንዑድ ክቡር ነው» በማለት የተነበየልን። መዝ.፴፪÷፲፪





ዓለማችን አብርሃምን የመሰሉ ቀደምት አባቶችን ያላፈራችውን ያህል ሁሉን ትተው እግዚአብሔርን ብለው የሚመንኑ ቅዱሳን ያል ተፈጠሩባትን ያህል ዛሬ ደግ ሰው አጥታ የሥጋ ፍላጎት እያቃጠላት ትገኛለች። ያኔ የነበረው እግዚአብሔር ዛሬም አለ ወደፊትም ደግሞ ይኖራል። ዛሬ የታጣው እንደ አብርሃም ያለ ሃይማኖት እንደ ይስሐቅ ያለ ትሕትና እንደ ኢዮብ ያለ ትዕግሥት ነው። ከዚህም የተነሣ የሰዎች የመጀመሪያው ሐሳባቸው ሥጋዊ፥ መሬታዊ፥ በመሆኑ ራሳቸውን ወስነው ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ሕይወታቸውን ባለመለወጣቸው ዳግማዊ አብርሃም የሚሆኑ የሉም።

የዛሬው ሰው አካል ባልነሱና ባልገዘፉ በረቂቃን የፍላጎትና የምኞት ጣዖታት አምልኮ የተያዘ በመሆኑና ከእነዚህ ተላቅቆ እግዚአብሔር ወደሚኖርባት ወደመረጣት አማናዊቱ ከነዓን ቤተ ክርስቲያን እንዲሔድ የቀረበለትን የሐዲስ ዘመን ወንጌላዊ ጥሪ ለመቀበል የተዘጋጀ ባለመሆኑ፥ ያልበሰለ ጥሬ፥ ያልታደሰ አሮጌ ልብ ስላለው ደግ ሰው፥ አብርሃምን የመሰለ ሰው ማግኘት ከባድ ነው። በዘመናችን ላለ ሰው ዓለምንና ምናምንቴ ንብረቷን ጥሎ እግዚአብሔርን ፍለጋ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር መሔድ ድንቁርና ስለሚመስለው ጥበብ በሚመስል የአላዋቂነትና የድንቁርና ባሕር ውስጥ ተዘፍቆ ከፈጣሪው እጅግ ርቆ ይገኛል።

በዚህች ለጊዜው ብቻ ተውባ በምታስደስት ነገር ግን ከመቅፅበት በምታልፍ ምናምንቴ ዓለም ለዘለዓለም መኖርና መደሰት የማይቻል መሆኑን ዐውቆ የዓለማት ሁሉ ጌታ በሆነው በእግዚአብሔር እግርሥር ራስን ማስገዛት እንደሚገባ፥ በዚህ ዓለም የሚኖረው ኑሮ ጊዜያዊ መሆኑንና በኋላ በፍርድ ቀን ከእግዚአብሔር ፊት እንደሚቆም ላላወቀው የዘመናችን «ባለጥበበ» ትውልድ መንገሩና ማስተማሩ ሓላፊነት ነው።

በነገራችን ላይ ክርስትና ለዓለም ከተገለጸ ሁለት ሺህ ዓመት ሊሞላው ነው። ታዲያ የሰው ልጆች እውነተኛ ክርስቲያኖች ሆነው የሚገኙት መቼ ይሆን? እናስብበት።



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ዘመንስ አብርሃም አባታችን እያልን የምንናገር ክርስቲያን ነን የምንል እኛ ለመሆኑ ከአብርሃም ጋር ምን መመሳሰል አለን? በስም ብቻ በመመካት የአብርሃም ልጆች ነን ያሉ አይሁድ የተነገራቸውን ወቀሳ አስተውለን የስም ብቻ ክርስቲያኖች መሆናችንን በመረዳት ማንነታችንን መለወጥ እንደሚገባን ልናውቅ ጊዜው ዛሬ ነው:: የክርስቲያናዊ ሕይወት ሰዎች÷ የሃይማኖትና የምግባር ሰዎች ዳግማዊ አብርሃም እንድንሆን ሀገራችን ከሆነች በኃጢአት ከምንኖርባት ዓለም እንውጣ:: ከተዛመድናቸውና እናት አባት አድርገን ከተገዛንላቸው ፈቃዳተ ዓለምና ግብረ ኃጣውዕ እንለይ:: ያን ጊዜ እግዚአብሔር ይጠራናል:: በቃሉም ያነጋግረናል:: ከዓለም ባሕር ያልወጣ÷ ከኃጢአት ያልተለየ÷ ረቂቃኑን የምኞት ጣዖታት ከነዝግንትሉ ከልቡናው አውጥቶ ያልጣለ÷ ውስጣዊ ማንነቱን ያልቀየረ እርሱ ለእግዚአብሔር ሊሆን እግዚአብሔርን ለማነጋገር አይችልም:: ስለዚህ እኛነታችንን በእግዚአብሔር ቃል መስታወትነት መመልከትና አብርሃምን መሆን ያስፈልገናል::

አብርሃምን የሆንን እንደሆነ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው:: እግዚአብሔር ለእኛ ይቆማል:: የተስፋ ሀገራችን ወደ ሆነች ሰማያዊት ምድር እንገባ ዘንድ ይባርከናል:: ለትውልዱ ምሳሌ ሆኖ ዘወትር የሚነገርለት የአብርሃም ሕይወት የተለወጠ በመሆኑ ነው የተባረከው የተቀደሰው:: ያላየውን የእግዚአብሔርን ድምፅ ብቻ ሰምቶ ሀገርን÷ ወገንን ትቶ ወደማያውቃት ሀገር በተስፋ መሔድ የቱን ያህል የጸና እምነት እንደሆነ ስናስተውል ደንዳናውና ዓለት ልቡናችን ምን ያህል እንደ ሚያስቸግረን ስንመረምር የአብርሃምና የእኛ ሕይወት አብዝቶ መራራቁን እናውቃለን::

ስለዚህ ሕይወታችንን መመርመር÷ ድካማችንን ከእኛ ማስወገድ ኃጢአታችንን ከእኛ ማውለቅ መጣል÷ ዓለም ሀገራችንን መናቅ በታደሰ በተለወጠ ሕይወት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ያስፈልጋል:: እስከመቼ በኃጢአት ታመን፣ ከፈጣሪአችን በረከት ርቀን÷ ለፈቃደ ሥጋ ጣዖታችን ዕጣን ስናጥን እንኖራለን? ያለፈው የድካምና



www.ethiopianorthodox.org



የኃጢአት ኑሮ ሁሉ ትተነው ውስጣችንንም ሁሉናችንንም ለውጠን በንስሐ ታጥበን በሕገ እግዚአብሔር በመኳዝ ሕይወት ለሚገኝበት የክርስትና ማንተም ለሥጋውና ለደሙ ታዳሚዎች በመሆን÷ የመምሰል የነበረውን በእውነት በክርስትና ሕይወት በመተካት በእግዚአብሔር ቤትና በፊቱ በበረከት የምንኖር መሆን ይገባናል:: የተለወጥን እንደ ሆን አምላካችን «የሚባርኩህን እባርካለሁ ... ለበረከትም ሁን÷» ይለናል::

ለበረከት እንድንበቃ እግዚአብሔር በቸርነቱ የአብርሃምን ሃይማኖት ይግለጥልን:: ወላዲተ አምላክ በአማላጅነት ቅዱሳን በረድኤት መላእክት በጥበቃ ከሁላችን ጋር ይሁኑ አሜን::

*ወይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዊነ*

# የሚጐድለን ምንድነው?

*በቀሲስ ደጀኔ ሺፈራው*

ብዙዎች በመንፈሳዊ ሕይወታችን ምን እንደጐደለን አስበን አናውቅም:: በፈቃደ ሥጋ ስለምንመራ ለጊዜው የሚታየን ፍትወተ ሥጋችንና የግይን አምሮታችን አለመሟላቱ ብቻ ነው:: ሀብት፣ ቤት፣ ንብረት፣ ትዳር፣ የሥጋ ዘመድ መኪና ሥልጣን ወዘተ ስለሌለን በጠቅላላው በዓለም ያለውን አላፊውን ነገር ሁሉ በማጣታችን ባዶነት የሚሰማን ሰዎች ጥቂቶች አይደለንም:: ኑሮአችን ከእጅ ወደ አፍ ከሆነው ጀምሮ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እስካላቸው ሰዎች ድረስ ከተራው ሰው እስከ ትልቁ ባለሥልጣን ሁላችንም የምናጾምጠው ሥጋችንን ነው:: የሚታየንም በሥጋ የጐደለንን ነገር ብቻ ነው:: ይህንንም ለማሟላት የማንወጣው ዳገት የማንወርደው ቁልቁለት የለንም:: የቀን እረፍት የሌሊት እንቅልፍ እናጣለን:: በዚህም ምክንያት ማንኛውንም ወንጀል ከመፈጸም ወደ ኋላ አንመለስም:: ወደ ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት ጣዖትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንአት፣ ቁጣ፣ አድመኛነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ እና ዘፋኝነት እናመራለን:: ገላ.፭፥፲፱:: ውጤቱም የዘላለም መከራ ነው:: ምክንያቱም «በሥጋው የሚዘራ መበስበስን ያጭዳልና» ገላ.፮፥፰:: እንደ ሥጋ ፈቃድ መኖር ሞት ነውና ሮሜ.፰፥፲፪ እንደ ሥጋ ፈቃድ በመኖር በሚመጣ ጠንቅ የእግዚአብሔር ቁጣ በማይታዘዙ ልጆች ላይ ይመጣልና ቆላ.፫፥፭-፮::

አንድ ሀብታም ወጣት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀርቦ ጌታ ሆይ የዘረዘርክልኝን ትእዛዛትማ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁ:: ደግሞስ የሚጐድለኝ ምንድር ነው ሲል ጠየቀ:: ኢየሱስም እንዲት ቀርታሃለች ፍጹም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ:: መጥተህም ተከተለኝ አለው:: ወጣቱ ባለጸጋ ግን ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ብዙ ንብረት ስለነበረው እያዘነ ተመለሰ ማቴ.፲፱፥፲፮-፳፪:: ይህ ወጣት በሕይወቱ የጐደለው ነገር እንዲሟላለት ተው የተባለውን ነገር መተው አልቻለም:: ከእግዚአብሔር የቁጣ ቀን የሚያድነውን ብርና ወርቅ ወዶ በሕይወት ጉዳና መንዝ አቃተው:: ሶፎ.፩፥፲፰

የራሱን ኑሮ ከወንድሙ ምድራዊ ኑሮ ጋር እያነፃፀረ ባዶነት ይሰማው የነበረ አንድ ሰው በወንድሙ አላፊ ጠፊ ሀብት ቀንቶ መምህር ሆይ ርስቱን ከእኔ ጋር እንዲካፈል ለወንድሜ ንገረው ሲል ኢየሱስ ክርስቶስን ጠየቀ:: ኢየሱስም አመጣጡን ያውቅ ስለነበር ለተከተሉት ሁሉ በአንድነት የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ ከመጐምጀትም ተጠበቁ አላቸው:: ይህ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ብዙ የጐደለው ነገር እያለ የተመለከተው የሥጋውን ነው:: ሰማያዊ ክብር ጐድሎት ሳለ የሚያስበው ምድራዊ ክብርን ብቻ ነበር:: ሉ.ቃ.፲፪፥፲፫

ንጉሡ ሳኦልን ነቢዩ ሳሙኤል እግዚአብሔር ከአማሌቃውያን ምርኮ አትንካ ብሎሃል ቢለው ሀብቱ የሚጐድልበት፣ የተባለውን ትቶ ምርኮውን ቢሰበስብ ደግሞ የሚያተርፍ መሰለው:: በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ናቀው:: ፩ኛ ሳሙ.፲፮፥፲፬ ርኩስ መንፈስ ተቆራኝቶት የሚሰቃይ ሆነ:: መንግሥቱንና ክብሩን አጣ አተርፍ ባይ አጉዳይ ይሏል ይኼ ነው::

የአልዓዛር እኅት ማርታ የማዕድ ቤት ሥራዋን ለጊዜው ትታ ከኢየሱስ እግር ሥር ተቀምጣ እንደ እኅቷ እንደማርያም መማርን እንደ ጉድለት በመቁጠሯ «ማርታ ማርታ በብዙ ነገር ትጨነቂያለሽ:: ትታወኪማለሽ የሚያስፈልገው ጥቂት ወይም አንድ ነገር ነው:: ማርያምም መልካሙን ዕድል መርጣለች:: ከእርስዋም አይወሰድባትም» ነው የተባለችው:: ሉ.ቃ.፲፥፴፰-፵፪:: ወጣቱ ዴማስ መንፈሳዊ አባቱን ቅዱስ ጳውሎስን ትቶ ወደ ዓለም የኮበለለው ዓለምን ማጣት እንደ ጉድለት ስለታየው ነው:: ፪ኛ ጢሞ.፬፥፲::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለተከታዮቹ የጐደላቸውን ነገር በየጊዜው ይነግራቸው ነበር:: «አንተ እምነት የጐደለህ ስለምን ተጠራጠርህ::» ማቴ.፲፬ ፴፩:: «እናንተ እምነት የጐደላችሁ ስለምን ትፈራላችሁ»



www.ethiopianorthodox.org

ማቴ.፳፩÷፳፪:: «ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው::» ማቴ.፲፯÷፳:: «እምነት ቢኖራችሁ ባትጠራጠሩም በበለሲቱ እንደሆነባት ብቻ አታደርጉም::» ማቴ.፳፩÷፳፩:: እነርሱም ጉድለታቸውን በውቀው ጌታ ሆይ እምነት ጨምርልን ብለውታል::

በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የመረጣቸው ኢያሌ ሰዎች የጉደላ ቸውን ነገር እያስተዋሉ ፈጣሪያቸውን ይለምኑ ነበር:: ነቢዩ ዳዊት «አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ» ሲል ለምኗል:: ምክንያቱም ንጹሕ ልብ ከሌለው እግዚአብሔርን ማየት እንደማይችል ስለሚያውቅ ነው:: እግዚአብሔርን ማየት የሚችሉ ልበ ንጹሐን ብቻ ናቸውና:: ማቴ.፭÷፰:: ጠቢቡ ሰሎሞን እግዚአብሔር ተገልጦለት ልሰጥህ የምትፈ ልገውን ነገር ለምን ቢለው ታናሽነቱን አምኖ፣ ድካሙን አውቆ፣ የጉደለውን አስተውሎ «እኔ መውጫና መግቢያ የማላውቅ ታናሽ ብላቴና ነኝ:: ... ስለዚህም በሕዝብህ ላይ መፍረድ ይችል ዘንድ መልካሙንና ክፉውንም ይለይ ዘንድ ለባርያህ አስተዋይ ልቡና ስጠው:: አለዚያማ በዚህ በታላቅ ሕዝ ብህ ላይ ይፈርድ ዘንድ ማን ይችላል::» ብሏል:: ፩ኛነገ.፫÷፰-፱:: ሰው ከእግዚአብሔር አስተዋይ ልቡና ካልተሰጠው በቀር በዳኝነት ወንበር በተቀመጠ ጊዜ ፍርድ የሚያጓድል ደሀ የሚበድል ነው የሚኾነው::

ሙሴ እግዚአብሔር ወደ ፈርዖን ሊልከው በጠራው ጊዜ «ወደፈ ርዖን የምሔድ የእሥራኤልንም ልጆች ከግብጽ የማወጣ እኔ ማን ነኝ» አለ:: ሒድ ቃሌን ተናገር በተባለም ጊዜ «ጌታ ሆይ እኔ አፌ ኮልታፋ ምላሴም ጸያፍ የሆነ ሰው ነኝ:: ትናንት ከትናንት ወዲያ ባርያህንም ከተናገርኸኝ ጀምሮ አፈ ትብ ሰው አይደለሁም» በማለቱ የጠራው እግዚአብሔር አፍን የፈጠረኩ እኔ ከአፍህ ጋር እሆናለሁ:: አስተምር ኻለሁ:: አለው:: ዘጸ.፫÷፲፩፣ ፬÷፲:: ኤርምያስም ወጣት ሳለ እግዚአ ብሔር ለአሕዛብ ነቢይ አድርጌኻለሁ:: ባለው ጊዜ «ወዮ ጌታ እግዚአ ብሔር እነሆ ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም» በማለቱ እግዚ አብሔር እጁን ዘርግቶ አፉን ዳሰሰ:: ቃሉንም በአፉ አኖረለት:: ኤር.፩÷፬-፲:: ነቢዩ ኢሳይያስም እኔ ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው ነኝ በማለቱ በዕደ ሱራፌል በሰማያዊ እሳት ፍም ተዳስሶ በደሉ ተወገ ደለት:: ከለምፅ ርኩሰት ተቀደሰ:: ኢሳ.፮÷፮::





እኛስ ከየትኛው ወገን ነን አብዛኞቻችን መንፈሳዊ ጉዞ እንጀምርና ዓለምን በመተዋችን የጐደለብን ይመስለናል:: እንደ ሎጥ ሚስትም ወደ ኋላ ስንመለከት እዚያው ቆመን እንቀራለን፤ መንፈሳዊ ጉዞአችን ከመቅጽበት ይገታል:: መንፈሳዊያን የነበርን ተለውጠን ሥጋዊያን፤ አማኞች የነበርን መናፍቃን እንሆናለን:: ዓለምን መመልከት ስንጀምር ለቅዳሴና ለስብከት መትጋታችን ጊዜ እንደማባከን ብዙ ነገርም እንደ ማጣት እየመሰለን ይመጣል:: እንደ ጓደኞቼ ብሯሯጥ ዕድሌን ብሞ ክር ኖሮ ማለት እንጀምራለን:: ወዲያው የጉዞ አቅጣጫችንን ለውጠን በሰፊው ጐዳና መጓዝ እንጀምራለን:: ጠማማው ቀና÷ ጨለማው ብር ሃን÷ መራራው ጣፋጭ፣ ክህደቱ እምነት፣ ጥፋቱ ልማት፣ ገደሉ ሜዳ መስሎ ይታየናል::

በሌላ መልኩ ደግሞ ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ በእግዚአብሔር ቤት ለዘላለም እኖር ዘንድ እሻለሁ:: እንዳለ ወስነን በእግዚአብሔር ቤት መኖር ስንጀምር በአፍአ ያሉ ሰዎች እንደ ሥራ ፈትነት ቆጥረው ያጐደልንና የጐደለብን መስሏቸው «አንተ ደግሞ ለምን ታበዛዋለህ? በልኩ አታደርገውም እንዴ? ምንድነው ሟት ማታ ወደ ቤተ ክርስቲ ያን መሮጥ? ለምን ጾም ታበዛለህ? ለምን ሥራ ፈልገህ አትገባም? ወዘተ ...» እያሉ ያዳክሙናል:: በዚህን ጊዜ ሌሎች የሚጓዙበት ሰፊ ጐዳና ቅን መስላ ትታየናለች:: ለጊዜው ይመስለናል እንጂ «ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው::» ምሳ.፲፬÷፲፪

ምንም እንኳን ዕለት ከዕለት ቃሉን ብንሰማም ሁኔታዎቻችን ግን ቃሉን እንዳልሰማና ተአምራቱን እንዳላየ ሰው ልቡናችን ደንዳና ነው:: መስማት እንሰማለን ነገር ግን አናስተውልም:: ማየትም እናያለን አንመለከትምም:: ጆሮአችን ደንቁሮአል ዓይኖቻችንም ተጨፍነዋል:: ኢሳ.፮÷፱:: ማቴ.፲፫÷፲፬ ዓይነ ልቡና እና እዝነ ልቡና ይጐድለናል::

፩ኛ ከሁሉ በላይ እምነት ይጐድለናል ያለ እምነት ደግሞ እግዚ አብሔርን ማገልገል አይቻልም:: በሕግ በአምልኮት ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሰው አስቀድሞ ሊያምን ይገባል:: አንድ ሰው እግዚአብሔር



www.ethiopianorthodox.org

በሕግ በአምልኮት ለሚሹት ሰዎች የሚሰጣቸው እንዳለ ማመን አለበት ዕብ.፲፩÷፮፣ ኤር.፳፱÷፲፫፣ ሮሜ.፲፬÷፳፫፣ አሞ.፭÷፬፣ ሚል.፫÷፲፬።

እኛ ግን ተጠራጣሪዎች ወላዋዮች ነን በመሆኑም የምናገኘው ነገር የለም ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ «የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕር ማዕበልን ይመስላልና ሁለት አሳብ ላለው በመንገዱም ሁሉ ለሚወላውል ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች እንዲያገኝ አይምሰለው።» ያለው ለዚህ ነው። ያዕ.፩÷፰።

፪ኛ. በጐ ምግባር ይጐድለናል ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ እንዳለ «ሥራ የሌለው እምነት በራሱ የሞተ ነው።» ያዕ.፪÷፲፯ የምንሠራው ለሕይወት ሳይሆን ለሚጠፋ መብል ብቻ ነው ጌታ ያለው «ለሚጠፋ መብል አትሥሩ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ» ነበር። ዮሐ.፮÷፳፯።

፫ኛ. ፍቅር ይጐድለናል ፍቅር ከሌለን እግዚአብሔርን አናውቅም ማለት ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍቅር ነውና። ፩ኛዮሐ.፬÷፰። በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብንናገር ትንቢትም ቢኖረን ምሥጢርንም ሁሉና ዕውቀትን ሁሉ ብናውቅ ተራሮችንም ሁሉ እስክናፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረን ድሆችንም ሁሉ ልንመግብ ያለንን ሁሉ ብናካፍል ሥጋችንንም በእሳት መቃጠል አሳልፈን ብንሰጥ ፍቅር ግን ከሌለን ከንቱ ነን ፩ኛ ቆሮ.፲፫÷፩-፫። ጌታ ግን ያስተማረን «ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙአችሁንም መርቁ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ ስለሚያሳድዷአችሁም ጸልዩ ... የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ። ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ። አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን?» የሚል ነው። ማቴ.፭÷፵፫-፵፰።

፬ኛ. ትሕትና ይጐድለናል፡ በጉዞአችን ሁሉ ከእኔ በላይ ማንም የለም እንላለን፤ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ምንም እንኳን ጉልበታሞች ብንሆንም እንሸነፋለን። ሥልጣን ቢኖረንም እንሻራለን። ብንከብርም እንዋረዳለን፤ ብናገኝም እናጣለን! ከሁሉም በላይ ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍትን መርምሬአለሁ። ንባቡን ከነትርጓሜው ጠንቅቄአለሁ። ከእኔ





በላይ አዋቂ ለአሳር ነው የምንል ከሆነ ፍጻሜአችን መናፍቅነት ነው። ምክንያቱም ዕውቀታችንን በእምነትና በትሕትና ካልያዝነው ይጐዳናል። «እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል። ለትሑታን ግን ጸጋውን ይሰጣልና» ፩ኛጴጥ.፭÷፮። እርሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከቤተልሔም እስከ ቀራንዮ ያስተማረንና ሠርቶ ያሳየን ፍጹም ትሕትናን ነው። «ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ።» ማቴ.፲፩÷፳፱። ያለውን ልንረሳ አይገባም።

፭ኛ. ጽናት ይጐድለናል፡ ቀድሞውንም ቢሆን በቃሉ ላይ የተመሠረተ ሕይወት ስለሌለን የክህደት ነፋስ ሲነፍስ የክህደት ጐርፍ ሲጐርፍ ልክ በአሸዋ ላይ እንደ ተሠራው ቤት እንወድቃለን። አወዳደቃችንም የከፋ ይሆናል። ማቴ.፯÷፳፯። እኛ የተማርነውን ትምህርት የሚቃወም ከመጣ ጽናቱ ስለሌለ ፈጥነን እምነታችንን ሥርዓታችንን እንለውጣለን። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ግን ይህ እንዳይሆን «ነገር ግን ወንድሞች ሆይ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያ የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችሁአለሁ። ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ። እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና በመልካምና በሚያቆላምጥም ንግግር ተንኰል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ።» ሮሜ.፲፮÷፲፯ ዕብ.፲፫÷፰ «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ ለዘላለምም ያው ነው። ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ።» በማለት አስቀድሞ ነግሮናል። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም «በዓመፀኞች ስሕተት ተስባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ» ሲል መክሮናል። ፪ኛጴጥ.፫÷፲፯ በተለይም ይህ ዘመን የተመረጡት እንኳ ጽናት አጥተው የሚስቱበት ዘመን ነው። ማቴ.፳፬÷፳፬።

፮ኛ. ኃጢአትን ሠርተን የመርሳት ጠባይ አለብን። ኃጢአትን እየሠራንም አናስተውልም። ከቁጥር የማይገባ ጽድቃችን እንጂ ከራሳችን ጸጉር የበዛው ኃጢአታችን አይታየንም። ጉዞአችንም ራስን የማጽደቅ ሌላውንም የመኰነን ኑሮ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሕይወት የጸሐፍት



www.ethiopianorthodox.org

ፈሪሳውያን ነው:: በዚህም «እናንተ ዕውሮች መሪዎች ትንኝን የምታጠሩ ግመልንም የምትውጡ ወዮላችሁ... በውጭ ለሰው እንደጻድቃን ትታያላችሁ በውስጣችሁ ግን ግብዝነትና ዓመፀኝነት ሞልቶባችኋል» ተብለው በጌታ ተወቅሰዋል:: ማቴ.፳፫፥፳፬፣ ፳፰:: ምክንያቱም ኃጢአታቸውን አያስተውሉም ነበር:: ነቢዩ ዳዊት ይህን በተመለከተ የተናገረው አለ:: «ስሕተትን ማን ያስተውላታል ከተሰወረ ኃጢአት አንጻኝ የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባርያህን ጠብቅ የዚያን ጊዜ ፍጹም እሆናለሁ ከታላቁም ኃጢአት እነጻለሁ» ብሏል መዝ.፲፰፥፲፪

በጠቅላላው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬያት ተብለው የተዘረዘሩት ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ ደግነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት እነዚህ ሁሉ ይጐድሉናል:: ገላ.፭+፳፭:: ስለዚህ «ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጐድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን ለእርሱም ይሰጠዋል::» ያዕ.፩፥፭:: ምሳ.፪፥፫:: እንደ ተባለ ለሁሉ አምልቶ አስፍቶ አብዝቶ ከሚሰጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንለምን:: እርሱም ለሕይወታችን የሚያስፈልገንን ሁሉ ይሰጠናል:: በእውነት የሚጐድለንን እንድናውቅ የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን፤ አሜን::



www.ethiopianorthodox.org



# «እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው::»

*በቀሲስ ሙሉጌታ ሥዩም*

እግዚአብሔር አስቀድሞ በነቢዩ ኢሳይያስ አንደበት «በተወደደ ሰዓት ሰማሁህ በመዳንም ቀን ረዳሁህ...» ኢሳ.፵፱፥፰:: ብሎ የተናገ ረውን ቃል መሠረት በማድረግ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው ሁለተኛ መልእክቱ ላይ «እነሆ የተወደደ ሰዓት አሁን ነው:: እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው» ፪ቆሮ.፮፥፪:: በማለት ትምህርቱን ይጀምራል::

ሰው የመዳን ቃል ከሰማበት የሕይወት ቃል ከተማረበት ወንጌል ከተሰበከለት ጊዜ ደቂቃና ሰከንድ አንሥቶ የመዳን ቀኑ ለእርሱ እንደ ቀረበ አውቆ በኃጢአት የተጐሳቆለ፥ በክህደት ያደፈ፥ በበደል የረከሰ ሰውነቱን በንስሐ አዘጋጅቶ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመንና ፈቃዱን በመፈጸም መዳን እንዳለበት ያስገነዝባል::

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው ለሰው ልጅ በሕይወቱ ሁለት አማራጮች ብቻ አሉት:: እነርሱም:

፩. በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ ፈቃዱን በመፈጸም መኖርና ኋላም በዘላለማዊ ሕይወት በደስታ እና በክብር መኖር::
፪. የሥጋን ፈቃድ በመፈጸም ከእምነትና ከምግባር ተለይቶ ከሰይጣን ጋር በኃጢአት መኖርና ኋላም በዘላለማዊ ፍርድ ትሉ በማያንቀላፋ እሳቱ በማይጠፋ በገሃነም እሳት በስቃይ መኖር ናቸው::

ይህ የሰው ልጅ በተሰጠው አእምሮ ተጠቅሞ መዳኑን ወይም መጥፋቱን ለይቶ የሚወስንበት ሌላ አማራጭ የሌለው ብቸኛ መንገድ ነው:: ስለዚህም ነው ሰው ለመዳን ምርጫውን ማስተካከል መንገዱንም ማቅናት ስላለበት በዘመነ አሪት እነ ኢያሱ «የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ... እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን::» ኢያ.፳፬፥፲፭ በማለት ያስተማሩት:: በዚሁ ላይ ቅዱስ ዳዊት የመዳን መንገዱ አንድ ብቻ መሆኑንና እርሱም ከሁሉ በላይ የከበረ እንደሆነ በመረዳት ከአምላኩ የሚፈልገው የቱን እንደሆነ ገልጸ አስቀምጧል:: «እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንኩት እርስዋንም እሻለሁ በእግዚአብሔር ቤት ለዘለዓለም እኖር ዘንድ::» መዝ.፳፮፥፬::

ከላይ ለማስቀመጥ እንደተሞከረው የሰው ልጅ ከሁለቱ በአንዱ መንገድ የመሔድ ምርጫ ቢኖረውም ኋላ ግን ፍርድ እንደሚጠብቀው ከቅዱሳት መጻሕፍት እንረዳለን፡፡ ነቢዩ ዳንኤል በትንቢት መጽሐፉ «በምድር ትቢያ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ፥ እኩሌቶቹ ወደዘለዓለም ሕይወት፥ እኩሌቶቹ ወደዘለዓለም እፍረትና ጉስቁልና» ዳን.፲፪፥፪፡፡ በማለት ያስረዳል፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሁሉ ይድኑ ዘንድ ቢሆንም ሞትን ግን ሕግንና ትእዛዝን በመተላለፍ ወደራሱ ያመጣ የሰው ልጅ ነው፡፡ ከጥንቱ ከመሠረቱ የሰው አፈጣጠር ለክብር እንጂ ለሞትና ለውርደት አልነበረም፡፡ ይሁን እንጂ በአዳምና በሔዋን በደል የሰው ልጅ በፍርድ ወድቆ በዲያብሎስ ተረግጦ እንዳይቀር የጠፋትን ሊፈልግ በጨለማ ላሉት ሊያበራ ክርስቶስ በሥጋ ተገለጠ፡፡ ኢሳይያስ በትንቢቱ «በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ፥ በሞት ጥላ አገርም ለሚኖሩ ብርሃን ወጣላቸው፡፡» ኢሳ.፱፥፪፡፡ በማለት አስቀድሞ የተናገረው ቃል በጊዜው ተፈጸመ፡፡ ጌታም በጊዜው በተገለጸ ሰዓት «በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁና፡፡» ዮሐ.፲፪፥፵፮፡፡ ብሎ አስተማረ፡፡ ይህ ሁሉ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ለማዳን ያደረገው በመሆኑ ሁላችን ለመዳን የተዘጋጀን መሆን አለብን፡፡

ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ ስለክርስቶስ ሲመሰክሩና ወንጌልን ሲያስተምሩ አይሁድ በቅናት ተነሣሥተው በወኅኒ አኖሩዋቸው፡፡ በዛም እጃቸው በሰንሰለት ታሥሮ ሳለ በእኩለ ሌሊት በመዝሙር ጌታን ሲያመሰግኑ የወኅኒ ቤቱ መሠረት ተናግቶ የታሠሩበት ሰንሰለት ተበጣጥሶ መስኮቶቹ እና ደጃፎቹ ሁሉ ተከፍተው የወኅኒ ጠባቂው ቢመለከት ጳውሎስና ሲላስ ከእሥር አምልጠው የጠፉ መስሎት ደንግጦ ራሱን ሊያጠፋ ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ተመልክቶ «አይዞህ እራስህን አታጥፋ እኛ ከዚህ አለን» ብሎ ሲመልስለት በሁኔታው ተደንቆ የጠየቀው አንድ ታላቅ ጥያቄ ነበር፡፡ እርሱም በፊታቸው ተደፍቶ «ጌቶቼ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?» ነበር ያለው፡፡ እነርሱም የመለሱለት ቢኖር «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰቦችህ ትድናላችሁ፡፡» ሐዋ.፲፮፥፴-፴፩፡፡





አዎ መዳን ለምንፈልግ ሁሉ መልሱ ይኸው ነው፡፡ እያንዳንዳችን እንድን ዘንድ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ይገባናል፡፡ የወኅኒ ጠባቂውም ወዲያውኑ አምኖ እንደተጠመቀና እንደዳነ ነው የምንረዳው፡፡ ይህ የሚያመለክተን የመዳን ቀናችን ቃሉን የሰማን ዕለት መሆኑን እንድናረጋግጥ በተንኮልና፥ በክፉ ሐሳብ የተጣመመ ልቡናችንን በጽድቅና በፍቅር እንድናቃና ነው፡፡ ስለዚህ በኃጢአት የደነደነ በዓለም የሰመጠ ልብናችንን /ሕይወታችንን/ በጫት፥ በሲጋራ፥ በመጠጥ፥ በዝሙት ወዘተ ... የበለዘ አካላችንን በንስሐ አጥርተን በነፍሳችን የተኛነው በሥጋችን የተጋነው ሁሉ ዛሬ ለመዳን በተራው ለነፍስ ሥራ መንቃት አለብን፡፡ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ «ከእንቅልፍ የምትነሡበት ሰዓት አሁን እንደደረሰ ዘመኑን ሰወቁ ካመንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደእኛ ቀርቧል፡፡ እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ እና ጦር እንልበስ በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ፡፡ በዘፈንና በስካር አይሁን፥ በዝሙትና በመዳራት አይሁን በክርክርና በቅናት አይሁን፥ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ፡፡» ሮሜ.፲፫፥፲፩-፲፬ ይለናል፡፡ እስካሁን ባለ ዘመናችን ሁሉ ለዚህ ዓለም ሥራ ለሥጋችን ሮጠናል፡፡ ያተረፍነው ነገር ቢኖር ግን ችግርና ስቃይ ነው፡፡ አባቶች ሲተርቱ «አትሩጥ አንጋጥ» እንዲሉ በቀረው ዘመናችን ደግሞ ካወቅንበት የዘላለሙን እያሰብን ለነፍሳችን ልንሮጥ ይገባናል፡፡ «በእሽቅድምድም ስፍራ የሚሮጡ ሁሉ እንዲሮጡ ነገር ግን አንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል አታውቁምን እንዲሁ ሁሉ ታገኙ ዘንድ ሩጡ» ፩ቆሮ.፱፥፳፬፡፡ ጳውሎስ ቀጠል አድርጎ «እነርሱ ለሚጠፋውና ለሚያልፈው እንደሚሮጡ የእኛ ሩጫ ግን በማያልፈው ለዘለዓለሙ ክብር እንደሆነ ያብራራል፡፡ እኛ ለመዳን ፈቃደኛ ከሆንን እርሱ ግን ሊያድነን ዝግጁ ነው፡፡ «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝና ለነፍሳችሁም እረፍት ታገኛላችሁ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና» ማቴ.፲፩፥፳፰፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ጌታ በሆሳዕና ዕለት የታመረቸውን አህያ ከነውርንጭላዋ ሂዱና ፈትታችሁ አምጡልኝ ማንም ቢጠይቃችሁ ለጌታ ያስፈልገታል በሉ እንዳለ እኛም ዛሬ ከኃጢአት እስራት ተፈትተን የዓለምን ሸቀጥ አራግፈን የእርሱ ማረፊያ የእርሱ ማደሪያ እንድንሆን ይፈልጋል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአት እሥራት ሊፈታን በፍጹም ፍቅሩ ሊዋጀን መጥቷልና በእርሱ አምነን እንድን ዘንድ ወድዷል። «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን ወዷልና» ዮሐ.፫÷፲፮ በመሆኑም በጌታ ለምናምን በፈቃዱና በሕጉ ልንመላለስ በፍቅሩ ልንተሣሠር የምንፈልግ ሁሉ ጊዜውና ሰዓቱ አሁን ነው። በኋላም አይደለም። ነገና ከነገ ወዲያም አይደለም። ዛሬና አሁን ነው። ስለነገው የምናውቀው ነገር የለምና። ነቅተንና ተዘጋጅተን እንድንኖር ነው ቃሉ የሚያዘን። ለመዳን ቀጠሮ የለምና «ቀኒቱንና ሰዓቱን አታውቁምና እንግዲህ ንቁ።» ማቴ.፳፬÷፴፮ ሐዋ.ሥ.፩÷፯። ብዙ ወገኖቻችን ለመዳን ቀጠሮ ሲያበዙ÷ ሲያመነቱ በሞት ተነጥቀዋል። ለፍርድ ተጋልጠዋል። ዛሬ ለመዳን በእርሱ ብናምን ግን አይፈረድ ብንም። «በእርሱ የሚያምን አይፈረድበትም በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።» ዮሐ.፫÷፲፰ ይለናል። የመዳን ጊዜ አሁን ነው «እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደእርሱ እገባለሁ።» ራእ.፫÷፳ ይላል ጌታ። ስለዚህ ሲጠራን ድምፁን ሰምተን ልንቀርበው÷ ሲያንኳኳ ልንከፍትለት ይገባናል። ኢሳይያስ በትንቢቱ «እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት ቀርቦም ሳለ ጥሩት ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛም ሐሳቡን ይተው» ኢሳ.፶፭÷፮-፯። ይለናል። እኛ ግን በሁለት ልብ ሆነን በሁለት እግራችን እያነከስን የመዳን ቀናችንን ችላ ብለን እንገኛለን። ያለን አማራጭ ግን አንድ ነው እርሱም በክርስቶስ አምነን ፈቃዱንም ፈጽመን መዳን ነው። ዕለቱም ዛሬ ነው። ጌታ ከዓለሙም ከመንፈሳዊውም ሕይወት እየሸቃቀጡ እንዲያው በለብታ የስም ክርስቲያን ብቻ ሆነው መኖር የሚሹትን ሲወቅሥ «በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን ዐውቃለሁ።





በራድ ወይንም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር÷ እንዲሁ ለብ ስላልክ በራድም ትኩስም ስላልሆንክ ከአፌ ልተፋህ ነው።» ራእ.፫÷፲፭ እያለ ያስጠነቅቀናል። ስለዚህ ጊዜዋንና ሰዓቷን መጠቀም ያሻል። ከጌታ አፍ ከመተፋታችን በፊት ለመዳን መፍጠን ይኖርብናል። ሲያንኳኳ መክፈት÷ ሲጠራን መስማት አለብን። የጌታን ጥሪ ቸል አንበል። በሰሜ የሚያፍር እኔም በክብሬ ስመጣ አሳፍረዋ ለሁ ይላልና። ጠቢቡ ሰሎሞን «የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ ደስ አይለኝም የምትላቸው ዓመታት ሳይደርሱ ፀሐይና ብርሃን ጨረቃ እና ከዋክብትም ሳይጨልሙ» መክብብ ፲፪÷፩።

እነዚህን ሁሉ የጌታን ቃል በማመንና በመቀበል ለኃጢአታችን ይቅርታን ከጌታ ለመጠየቅ እንቅረብ። የንስሐ ፍሬ እናድርግ። መንፈሳዊ ዕውቀትን ለማዳበር መጽሐፍ ቅዱስን እናንብብ÷ ወንጌል በሚነገርበት ቦታ በመሔድ ለመማር እንወስን። «እምነት ከመስማት ነው መስማትም የእግዚአብሔርን ቃል ነው።» ሮሜ.፲፥፲፯ ስለሚለን በጸሎትና በጾም ወደጌታ እንቅረብ÷ እንትጋ የመዳን ቀናችን ዛሬ ነውና።



www.ethiopianorthodox.org

# ልጆቻችንን

## እንዴት እናሳድጋቸው?

## ከክፉ ነገርስ እንዴት እንጠብቃቸው?

*በዲ/ን ዶ/ር መስፍን ተገኝ*

ጊዜው ሦስት ወር ያህል ሆኖታል፡፡ አንዲት እናት ሕጻን ሴት ልጅ ይዛ በቤተ ክርስቲያን ደጅ ቆማ ታለቅሳለች፡፡ ልጅቷም ጭምር፡፡ ሁኔታውን ሳይ ምን ዓይነት ችግር ቢያገኛቸው ይሆን ሁለቱም የሚያለቅሱት ብዬ ላነጋግራቸው ቀረብኩኝ፡፡ በተወሰነ ደረጃ ካረጋጋኋቸው በኋላ እናትዬዋ ሕጻኗን ልጇናት ብላ አስተዋወቀችን፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ እናት ከባሏ ከተለያየች /ከተፋታች/ ሁለት ዓመት ሆኗታል፡፡ የዘጠኝ ዓመት ሴት ልጃቸውን የማሳደግን ኃላፊነት የወሰደችው እናት ከቤቷ ተጣልታ ስትወጣ በሠርግ ተሸኝታ ከወጣችበት የእናትና አባቷ ቤት ልጇን ይዛ ተመለሰች፡፡ ቀሪውን ጊዜ አብራ ለመኖር መተዳደሪያዬ ነው የምትለው ሥራ ቢኖራትም ደመወዟ በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ከሦስት ወራት በፊት ይህችን እናት በልጇ ላይ የሚያስደነግጥ ነገር ተፈጽሞ አገኘች፡፡ ሕጻኗ ልጅ በመገደድ ተደፍራለች፡፡ ከደረሰባት ጉዳት ለጊዜው በሕክምና እንድትረዳ ብታደርግም ኅሊናዋ የተጎዳው ሕጻን ግን የባሰ ስውን እየፈራችና እየራቀች መሄዷ እናትየዋን አሳሰባት፡፡ ይህ ብቻም አይደለም ማን ነው የደፈራት የሚለውን መልስ ለማግኘት ልጇን ደጋግማ ጠየቀች፡፡ ሕጻኗ ልጅ ግን ከተናገርሽ እገልሻለሁ ብሎኛል በማለት ማንነቱን አልናገርም አለች፡፡ ከብዙ ውትወታ በኋላ «የደፈራት አጎቷ» /የእናቷ ወንድም/ መሆኑን ነገረቻት፡፡ እናት ይህንን ክፉ ድርጊት የፈጸመው ወንድሟ መሆኑን ስታውቅ በጣም ተጨነቀች፡፡ ለማመንም ተቸገረች፡፡ ከማን ዘንድ ሄዳ ምን መፍትሔ ታግኝ፡፡ ግራ ስለገባት ሥራዋ ማልቀስ ብቻ ሆነ፡፡ ልጅ ከእናቷ መለየት አልቻለችም፡፡ ሌሊት እንቅልፍ አትተኛም፡፡ ወንድ ስታይ ታለቅሳለች ትጮሀለች፡፡ በዚህ የተነሣ ልጅቷ ትምህርቷን አቋረጠች፡፡ ይህች እናት በነገረችኝ ነገር ልቦናዬ አዝኖ ከቤተ





ክርስቲያኑ ግቢ ስወጣ በአስፓልት ጐዳና ዳር የተቀመጡ ዕድሜያቸው በግምት ፲፪ ዓመት የሚሆኑ ስድስት ሕፃናት ክብ ሠርተው ጫት ሲቅሙ ሲጋራ እየተቀባበሉ ሲያጨሱ አየኋቸው፡፡ ለመሆኑ በቤትም ሆነ በውጭ ያሉትን ሕጻናት /ወላጆች/ እንዴት ነው ማሳደግ ያለብን? ከክፉ ነገርስ እንዴት እንጠብቃቸው? የሚል ጥያቄ አደረብኝና ከአንድ ሁለት ይሻላል በማለት ከምዕመናን ጋር መወያየቱን መረጥኩ፡፡

በዚህ ዓለም መልካም እንደሚነገርበት እና እንደሚሠራበት ሁሉ የክፋት ሥራዎችና ንግግሮችም የሞሉበት ነው፡፡ ከእናታቸው ማኅፀን የወጡ ሕጻናትም ዕድገታቸው በጨመረ ጊዜ እነዚህ ሁለት ተቃራኒ ነገሮች ባሉበት ዓለም መኖራቸው የማይቀር ነው፡፡ መልካም ኅሊና እንደያዙ የሚዘልቁት እንዴት ይሆን?

ልጆችን የማሳደግና የመጠበቅን ጉዳይ ስናነሳማ ኅሊናቸው ከክፉ ነገር ተጠብቆ ወደ ኃጢአት ከሚመራና ሥነ ምግባርን በሚያበላሽ ነገር ሳይጐዳ በመንፈሳዊ ትምህርት መመሪያነት የሚያስፈልጋቸውን መሠረታዊ ነገር ሁሉ በማቅረብ የወደፊት የቤተ ክርስቲያን ተረካቢ፣ ለአገርና ለወገን ጠቃሚ እንዲሆኑ ማብቃት መሠታዊ ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ ለልጆች አስተዳደግ ትኩረት የምንሰጥበትን ምክንያት ልንረዳው ያስፈልገናል፡፡

፩ኛ. በአሁኑ ጊዜ በሕጻናት ላይ ከፍተኛ የሥነ ምግባር ውድቀት እያንዣበበ መሆኑን በማየታችን እና በተለያዩ አጋጣሚዎች ሕጻናት ላይ የሚደርሱ በደሎችን /አስገድዶ መደፈር፣ ለተለያዩ ሱሶች መጋለጥ ወዘተ/ ዛሬ የሚገቱበት መንገድ ካልተፈለገ ነገ ትልቅ ማኅበራዊ ቀውስ የሚያመጣ ተግር በመሆኑ፡፡

፪ኛ. ወደፊት ቤተ ክርስቲያንን የሚረከቡ፣ አገርና ወገንን የሚጠቅሙ ተተኪዎችን ለማፍራት በትክክል የሚመራቸው ስለሚያስፈልግ ከአሁኑ በተሻለ መልኩ ትኩረትና እንክብካቤ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ ነው፡፡

ታዲያ ልጆችን ለዚህ ደረጃ ለማብቃት የሚጠይቀው ጥረት በቀላል የሚታይ አይደለም፡፡ ምእመናን በሙሉ ችግሩን በመረዳት እና በመተጋገዝ ከተነሳሱ ግን አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ በዚህም ጽሑፍ ይህንን



www.ethiopianorthodox.org

ጉዳይ ለማንሳት የተፈለገው ከአስተማሪነቱ በተጨማሪ ከምእመናን ጋር ለመወያየት ሲባል ነው::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሕፃናትን ሕይወት በማሳየት አዋቂዎች እንዲመለሱና እነርሱን እንዲመስሉ ያስተምራቸው ነበር:: «ካልተመለሳችሁ እንደ ሕጻናትም ካልሆናችሁ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም» ማቴ.፲፰፥፫:: ሕጻናት ተንኮል በልባቸው የለም:: ስለነገም አይጨነቁም፣ ፍቅራቸውም ከልብ ነው:: በዚህ ዘመናቸው ኅሊናቸው ያገኘውን ሁሉ ሊቀርጽ የሚችል መሆኑም መዘንጋት የለበትም:: በእርግጥም የሕጻናት ኅሊና መልካም እንደሆነ እንዲዘልቅ ከፍተኛ ጥረት የሚያስፈልገው ሲሆን ለዚህ ደግሞ የእግዚአብሔር ረዳትርነት ትልቁን ቦታ የሚይዝ ነው:: ወላጆች በሚያደርጉት እንክብካቤ ላይ እግዚአብሔር ካልተጨመረበት የተጀመረውን ለመጨረስ የተዘራውን ለማጨድ ያስቸግራል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም እየተመላለሰ በሚያስተምርበት ጊዜ ወላጆች ቀርበው ሕጻናት ልጆቻቸውን ባርክልን ይሉት ነበር:: ዛሬም ቢሆን ይህንን ያላስተዋሉ ልጆቻቸው በሊጋ ዕድሜ ሲደርሱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ማምጣት ያልቻሉ ምንም እንኳን አብልተው አጠጥተው፣ ቢያስተምሩም የኋላ ኋላ ግን በልጆቻቸው ተንቀው የወለዱትን እስከ መርገም የደረሱ ወላጆች አሉ::

ነገ ቤተ ክርስቲያንን ተረክቢና ለእግዚአብሔርም ተገዥ የሚሆን ትውልድ ለማትረፍ ዛሬ የወላጆች፣ የኅብረተሰቡ የሁሉም ሐላፊነት ነው:: ዛሬ በእጃችን ላይ ያሉትን ልጆች ስናዛቸው በሚሰሙበት ሰንመራቸው እሺ ብለው በሚከተሉበት ዕድሜያቸው ተጠቅመን በመልካም ጉዳና እንዲጓዙ መቅረጽ ለማንም የማንተወው ኃላፊነት ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ በልጆች ላይ እየደረሰ ያለው ጉዳት እጅግ የሚያሳዝን ነው:: በልጆች ላይ በአስገድዶ መድፈር፣ የሕጻናት ዝሙት፣ የተለያዩ ሱስ ተጠቂነት እና በአጠቃላይ የሥነ ምግባር ውድቀት እየደረሰ ነው:: ችግሩን አውቆ አለመንቀሳቀስ ደግሞ የባሰ ጉዳት ነው:: የልጆችን አስተዳደግ እና ጥበቃ /ከመጥፎ ምግባርና ጉዳት/ ካነሣን የኃላፊነቱን ደረጃ እና ተጽዕኖ የሚያደርጉትን ምክንያቶች በሚከተለው መልኩ ከፍለን እንመልከት::





- ⇒ ቤተሰብ
- ⇒ ኅብረተሰብ /አካባቢ/
- ⇒ ልማድ

## ፩. ቤተሰብ

ዛሬ የምናያቸው አብዛኛዎቹ ማኅበራዊ ችግሮች መነሻቸው ቤተ ሰብ ነው:: «ቤተሰብ ለክፉም ሆነ ለመልካም ነገር መሠረት ነው:: የቤተሰብ ጉዳይ ደግሞ ገና ከአመሰራረቱ ጀምሮ ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባ መሆኑን በማስተማር የተቀደሰ እንዲሆን ቤተ ክርስቲያን ዘወትር ታስተምራለች:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰዎች መካከል ማስተማር ሲጀምር ጋብቻን በመባረክ የመልካም ቤተሰብን መሠረትነት አጠንክሮ ገልጾታል::

እግዚአብሔር እንዳስተማረው የሚገኙ አርአያነታቸው የሚጠቀስ ቤተሰቦች እናትና አባት ቤተ ክርስቲያንን የሚያከብሩ ልጆቻቸውም የቤተ ክርስቲያን ፍቅር ያደረባቸው አሉ:: ነገር ግን አብዛኛው ቤተሰብ በዚህ መልካም መንገድ አለመገኘቱን ስንመለከት ጊዜ ሰጥተን በችግሮቹ ላይ መነጋገሩ መልካም ነው:: ቤተሰብ በምንልበት ጊዜ እናት፣ አባትን ልጆች እንዲሁም አብሮ የሚኖር ዘመዱን ያጠቃልላል:: የሚከተሉትን ምክንያቶች በልጆች አስተዳደግ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ናቸው::

### ፩.፩. የቤተሰቡ የምግባር አርአያነት ችግር

ልጆች ከወላጆቻቸው /ከቤተሰብ/ ጋር አብረው ሲኖሩ ወላጆቻቸው /ቤተሰብ/ የሚያደርገውን ዘወትር ይመለከታሉ:: በእንደበታቸው ለጊዜው ባይናገሩትም በኅሊናቸው መሳላቸው አይቀርም:: ወላጆች ያደረጉትን ለማድረግ የሰሙትን ለመፈጸም ይጓጓሉ:: በእርግጥ ይህንን ያስተዋሉ ወላጆች በልጆቻቸው ፊት ያላቸው ምግባር ወደ መልካም ነገር የሚመራ እንጂ ለክፉው እንዳይሆን ይጠነቀቃሉ:: የሕጻናትን የወደፊት ሕይወት ረስተው እንደፈለጉ ለመሆን የሚነሡ ወላጆች ግን ልጆቻቸውን እየጐዷቸው መሆኑን መዘንጋት አይገባም::



www.ethiopianorthodox.org

ልጆች በምግባር ደክመው /አንሰው/ ሲገኙ መደብደብ ወይም መግረፍ ብቻ መፍትሔ አይሆንም ወላጆች ለዚህ መጥፎ ምግባር ልጄ ምሳሌ ያደረገው እኔን ይሆን? ብለው ራሳቸውን ሊጠይቁ ይገባል። አባቱ ሲጋራ ሲያጨስ ያየ ወይም ሲጋራ ግዛ ተብሎ በተደጋጋሚ የሚላክ ልጅ፣ አባቱ ሰክሮ እየተንገዳገደ ሲመጣ የሚያይ ልጅ፣ እር ሱም ሲያድግ መጠጣትን ማጨስን ቢጀምር አርአያ የሆነው አባቱ ነው። አባቱ አልታወቀውም /አላስተዋለውም/ እንጂ ልጁን ወደ መጥፎ ምግባር መርቶታል። ስለዚህም በልጁ ሕይወት መበላሸት አባት ተጠያቂ ሆነ ማለት ነው። ይህ ደግሞ የኋላ የኋላ በሰውም በእግዚአብሔርም ዘንድ ወቀሳን የኅሊና ጸጸትን ያስከትላል። አባትህን እንዲህ ብለህ ስደበው እናትህን እንዲህ በላት በማለት ስድብንም የሚያስተምሩ ወላጆች አሉ። ታዲያ ወላጆች /ቤተሰብ/ እንዲህ አይነት አስተማሪ ሆነው ከተገኙ ልጆች ቤት ተዘግቶባቸው ግቢ ተከልሎላቸው ተለይተው ቢያድጉም በውጭ ያለውን መጥፎ ምግባር ቤታቸው ዘልቆ ስለገባ መከለልና ዘግቶ መዋል ጥቅም የለሽ መሆኑን ያሳያል።

ልጆች ወላጆቻቸውን /ቤተሰባቸውን የሚንቁበትን ሁኔታም ይታያል። መከባበር የቤቱ ሥርዓት ሆኖ ቢለመድ እናትና አባት ሲከባበሩ ቢታይ ኖሮ ልጆችም ሰው አክባሪ ሆነው ያድጋሉ። ጥሩ ሥነ ምግባርና መከባበር የማይታይባቸው ወላጆች እራሳቸውን ጐድተው መልካም ኅሊና ሥነ ምግባር ሊኖራቸው የሚችሉ ልጆቻቸውን እየጐዱ መሆኑን በመረዳት ጥፋታቸውን ማረም ተገቢ ነው። የመጥፎ ምግባር ምሳሌ የሆኑ ወላጆች ልጆቻቸውን ጠበቁ ማለት አይቻልም። ምክንያቱም ምንም እንኳን ቢያለብሱ፣ ቢያጠጡ፣ ሥጋዊ ትምህርትን ቢያስተምሩ ልጆቻቸው በምግባር ስለወደቁ የኅሊናቸው ጉዳት ከሁሉ ይበልጣልና ነው።

ከእናትና አባት በተጨማሪ እንደ ቤተሰብ ተቆጥረው አብረው የሚኖሩትም የቤተሰብ አባላት ሊያመጡ የሚችለው ተጽዕኖ ሊጤን ይገባል። በመግቢያችን ላይ እንደገለጥነው በአስገድዶ መደፈር ሰለባ የሆነችው ሕፃን የቤተሰቡ አባል በሆነ አጉቷ ነው። ቤተሰብ አድርገን



www.ethiopianorthodox.org



ያስቀመጥናቸው የመጥፎ ምሳሌዎች መምህራን የሚሆኑ ከሆነ አብሮ መቀመጣቸውን እንደ.ት መፍትሔ መስጠት እንደሚገባ ማስተዋል ተገቢ ነው።

## ፩.፪. ወላጆች ለልጆቻቸው የሚያካፍሉት አመለካከት

በተወሰነም ደረጃም ቢሆን። የልጆች የወደፊት ሕይወት በወላጆች አመራር ላይ የተመሠረተ ነው። ልጆች የሚጓዙበትን መንገድ መጠቆም በጥሩም ሆነ በመጥፎ ጐኑ የወደፊቱን ሕይወታቸውን ይወስናል። ዘመናዊነትን ሰበብ በማድረግ ልጆቻቸውን መጠጥ ቤትና ዳንስ ቤት ይዘው እስከመሄድ የደረሱ ወላጆች አሉ።

ልጆችን ወደ ቤተ ክርስቲያን መርቶ ቃለ እግዚአብሔርን እንዲማሩ በመዝሙር ፊንታ እንዲዘምሩ ማድረግ የሚቻለው መልካሙን መንገድ የመረጡና የሚያምኑ ወላጆች ሲገኙ ነው። አንዳንድ ወላጆችም ወደ ቤተ ክርስቲያን ልጆቻቸውን ሲልኩ ከሥጋዊ ትምህርት የሚያደክማቸው የሚመስላቸው ካሉ ይህ እውነት እንዳልሆነ ተረድተው መልካም ነገርን በኅሊናቸው መቅረጽ የሚችሉበትን ዕድሜ እንዳያሳልፉ ሊያስተውሉት ያስፈልጋል። ሕጻናት ቤተ ክርስቲያን ሄደው ዕጣኑን ሲያሸቱ፣ ከበሮውንና ዝማሬውን ሲሰሙ፣ ጠበሉን ሲጠጡ፣ መስቀሉን ሲሳለሙ ብሩህ ኅሊና እያገኙ የቤተ ክርስቲያን ፍቅር እያደረባቸው ያድጋሉ። ልጆቻችንን ወደ ዘፈን እና ቅጥያጣ ዘመናዊነት መርተናቸው ለዘማዊነት፣ ለአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚነትና ሱሰኝነት ቢጋለጡ ልጆቻችንን ወደ ጥፋት ጉዳና እየመራናቸው መሆኑን መረዳት ያስፈል ጋል ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመራቸው ደግሞ እግዚአብሔርን መፍራት እንዲማሩ እየረዳናቸው ነው።

## ፩.፫. በባልና ሚስት መካከል የሚፈጠር ግጭት

ባልና ሚስት ለጥንቃቄ ሲባል በልጆች ፊት ግጭትን /አለመግባባትን/ ማሳየት የለባቸውም። ባልና ሚስትን የሚያነጋግሩ ብዙ ጉዳዮች ቢኖሩም ጊዜያዊ በሆነ ስሜት ተነሣሥተው መጣላት መከራከር ወይንም መደባደባቸው መሰዳደብን ማሳየት የልጆችን ኅሊና ክፉኛ

ይጐዳል። ሲያድጉ እንደነሱ ተመሳሳይ ወይም በአጠቃላይ ደግሞ ትዳ ርን የሚጠሉ ሊሆኑ ይችላሉ። ወላጆች በመካከላቸው ብቻቸውን በሆኑ ጊዜ በመነጋገር ማስተካከል አለባቸው። በልጆች ፊት መታገስ መል ካም ነው።

### ፩.፬. የወላጆች ተለያይቶ መኖር

የወላጆች ተለያይቶ መኖር በልጆች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አለው። ትዳራቸውን አፍርሰው የሚለያዩ ልጆቻቸውንም ነጣጥሉ በመከፋፈል መውሰዱ «ያለ አባት» ወይም «ያለ እናት» ማሳደግ በልጆች ላይ የሚፈጥረው ጉዳት ቀላል አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ልጆች የወላጆቻቸውን ፍቅር እንዳያገኙ ከማድረግ በተጨማሪ እንደኛው ወገን /እናት ስለ አባት ወይም አባት ስለ እናት/ የሚያቀርቡላቸው ምክንያት በኅሊናቸው እንዲቀረጽ የሚያደርጓቸው አመለካከቶች የልጆ ችን የወደፊት ዕድገትና ቤተሰባዊ ፍቅር የሚያበላሽ ነው። ከወላጅ ተለይተው የሚኖሩ ልጆች በእንጀራ አባት እና በእንጀራ እናት ሊ ደርስባቸው የሚችለው ሰቀቀን መልካም ነገርን ሊያስብ የሚችል ኅሊ ቸውን ክፉኛ ይጐዳዋል። በወላጆች መካከል መለያየት ተፈጥሮ የሚያድጉ ሕጻናት ብዙዎቹ ለፍሬ አይበቁም። በእናትና አባታቸው መለያየት ምክንያት ልጆች ከአንዱ ቤት ወደ አንዱ እየተዘዋወርን እንኑር ሲሉ በመካከሉ ብዙ ነገርን ይለምዱና ከቁጥጥር ውጭ ይሆ ናሉ። አስተዳደጋቸውም ብዙ ጊዜ ጉስቁልና የበዛበት ይሆናል። ተቆ ጣጣሪ የሌላቸው መስሎም ሊሰማቸው ይችላል።

### ፩.፭. ከጋብቻ ውጭ የሚወለዱ ልጆች የሚኖራቸው አስተዳደግ

ከጋብቻ ውጭ የሚወለዱ ልጆች ከሌሎቹም ሁሉ የተለየ ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ ይከሰትባቸዋል። ለአንድ ሕጻን /ልጅ/ አባቴ ማን ነው? ወይም እናቴ ማን ናት ለሚለው ጥያቄ መልስ አለማግኘት ከባድ ነው። በኋላም ሲያድግ ሌሎች ሰዎች የሚያደርጉባቸው ተጽዕኖ ቀላል አይሆ ንም። አባታቸው ወይም እናታቸውን አለማወቃቸው ዘወትር ዕረፍት ይነሳቸዋልና። ኅብረተሰቡም ቢሆን ያለ ጋብቻ የተወለዱ ልጆችን





በቀላሉ ያገልላቸዋል። ይህ ልጆችን ወደ መጥፎ ምግባር እንዲጓዙ የሚገፋፋቸው ይሆናል። ያለጋብቻ ልጆችን የሚወልዱ ሰዎች የልጆችን ኅሊና የሚጐዳ ምግባር መፈጸማቸውን ብዙ ተደራራቢ ችግር የሚያ ስከትል መሆኑን በመረዳት ሰዎች በተቀደሰ ጋብቻ ሊገኙ ይገባል።

እንግዲህ ከላይ ለመመልከት እንደሞከርነው በልጆች አስተዳደግ ላይ ተጽዕኖ የሚያስከትሉ ምክንያቶችን በመረዳት ቤተሰብ ምን ማድ ረግ አለበት የሚለውን በመጠኑ ለመጠቆም ነው። የሁሉ ነገር መሠ ረቱ ሃይማኖት ነውና ወላጆች ከልብ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንመለስ። እራሳችንን ተመልክተን የጐደለንን እናስተካክል። ያለንን አመለካከት ከእግዚአብሔር ፊት ሆነን እንመርምረው። ከዚያም ወደ ማስተካከሉ እንምጣ። ትዳራችንም የተቀደሰ እንዲሆን እናድርግ ወላጆች በግልጥ በመነጋገር በመወቃቀስ ሳይሆን በመማማር እስካሁን በልጆቻችን አስ ተዳደግ ላይ ተጽዕኖ ያሳደረውን ድርጊታችንን እንመርምር። በእኛ በኩል ይህንን ካደረግን ልጆቻችንን እየተከታተልን በኅሊናቸው የተቀረ ጸውን ፍላጐትና አመለካከት እናጥናው። እንዴት ወደ ቤተ ክርስቲያን መመለስና ፍቅር ማሳደር እንደምንችል እናስብበት። እኛው ራሳችን ምሳሌ በመሆን አብረናቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን እንውሰዳቸው። በአ ቅማቸውና ሊረዱት በሚችሉት መጠን የክርስቲያናዊ ሕይወትን መል ካምነት እንግለጥላቸው። በልጆቻችን ፊት የምንፈጽመውን በጥንቃቄ እንመልከተው ለዚህም እግዚአብሔር ማስተዋሉን ይስጠን።

### ፪. ኅብረተሰብ

ኅብረተሰብ በልጆች አስተዳደር ላይ የሚኖረውን ሚና ስንመለከት የተያያዙና ተጽዕኖ ሊያመጡ የሚችሉ ጉዳዮችን ከተለያየ አቅጣጫ ሆነን መመልከት ያስፈልጋል። የኅብረተሰቡ አመለካከት የተለያዩ ባሕ ላዊና ሃይማኖታዊ ምክንያቶችን የተከተለ ሊሆን ይችላል። ልጆችም አካባቢያቸውን የመምሰል ሁኔታ ይታይባቸዋል። ይህ ደግሞ በእያንዳ ንዱ አካባቢ ምን አለ ብለን እንድንጠይቅ ያደርገናል። «ልጆች በመ ሰል የዕድሜ ጓደኞቻቸው ላይ የሚፈጥሩት ተጽእኖ አለ፣ ይህም በመ ልካምም ሆነ በመጥፎ ጎኑ የሚታይ ነው። ሥጋዊ ስሙቀት እንዲገበዩ



www.ethiopianorthodox.org

ተብሎ ልጆች የሚላኩባቸው ትምህርትቤቶች አብዛኛዎቹ በመልካም የሥነ ምግባር በታነጹታቸው የሚጠሩ አይደለም፡፡ ሁሉንም መመልከት ባንችልም ዋና ዋና የምንላቸውን ዘርዝረን ለመመልከት እንሞክራለን፡፡

## ፪.፩. ሰዎች ያላቸው አመለካከት

ስለ ልጆች አስተዳደር እንክብካቤ ብዙ ዓይነት ሀሳብና አመለካከቶችን ይሰነዝራሉ፡፡ ይህ አመለካከታቸው በእነርሱ ኅሊና ሃሳብ ብቻ ሆኖ አይቀርም፡፡ በተለያየ ጊዜና ሁኔታም በተግባር ሲንፀባረቅ ይታያል፡፡ ለምሳሌ ያህል አንዳንድ ሰዎች የልጆችን አስተዳደግ ከዕድል ጋር የሚያያዙ አሉ፡፡ ልጅ «በዕድሉ ይደግ» የሚለውን አነጋገር አብዛኛው ሰው የሚቀበለው ቢመስለኝም በዚህ አነጋገር የተጠቃለለው ሀሳብ ግን በሰዎች ኅሊና የሚፈጥረው ግንዛቤ የተለያየ ነው፡፡ በእርግጥ ይህ ዓይነት አመለካከት ለልጆች የሚሰጠውን ትኩረት ይቀንሳል፡፡ የልጆች በዕድል ማደግ ከሚበሉትና ከሚጠጡት ነገር ጋር ብቻ ሳይሆን የት እንደሚያድጉ፣ እንዴት እንደሚያድጉ፣ ማን እንደሚያሳድጋቸው የሚለውን ሀሳብም ያጠቃልላል፡፡ ልጆች በመጥፎ አካባቢ ማደጋቸው በዕድላቸው ነው ከተባለ ይህ አመለካከት ያላቸው ሰዎች ባሉበት ኅብረተሰብ ልጆች በየሜዳው ከቤታቸው ርቀት የሚገባቸውን እንክንካቤ ሳያገኙ ጧት ወጥተው ማታ ቢገቡ እንግዳ ነገር አይሆንም፡፡

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ «እኔ የማደርገው ነገር ሁሉ እኔን ለማስደሰት ነው፤ ሌላውን ሰው ተስማማው አልተስማማው አይመለከተኝም» የሚሉ አሉ፡፡ አንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ስንኖር እኛ የምናደርገው ማንኛውም ነገር ሌላው የኅብረተሰብ ክፍል ላይ በጥሩም ሆነ በመጥፎ ጐኑ ተጽዕኖ ማምጣቱ አይቀርም፡፡ የዚህ ድርጊት ውጤትም በኛ ላይ ብቻ ተወስኖ እንደማይቀር መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ጥሩ ስናደርግ በጥሩ ጐኑ ኅብረተሰቡ ላይ ተጽዕኖ እናሳድራለን፤ መጥፎ ስናደርግ ደግሞ በመጥፎ ጎኑ ተጽእኖ ማሳደራችን አይቀርም፡፡ ይህ ዓይነት አመለካከት ያላቸው ሰዎች ሌሎች ሰዎችን ሲሳደቡ በሕፃናት ፊት ነው፡፡ እነርሱ ስሜታቸውን መግለጻቸው እንጂ ሕፃናትን ስድብ ማስተማራቸውን አያስተውሉትም፡፡ እንደዚሁም የሚያጨሱ፣ የሚቅሙ፣ የሚሰክሩ፣





በዝሙት የሚሰማሩ ሁሉ እኛን ተከተሉን ማለታቸው ነው፡፡ እነርሱ ይደሰቱበት እንጂ በእነርሱ ምክንያት ችግር ውስጥ ሊገቡ የሚችሉትን አይጨነቁላቸውም፡፡

ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ ደግሞ ለሕፃናት እንክብካቤ ማድረግን ኅሊናቸው ፈጽሞ ትቶት ራሳቸውን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚሯሯጡ መናራቸውን ደግሞ ሌላው የብዙ ሰዎች ችግር ነው፡፡ በአንዳንድ ቦታ የምንሰማው ታሪክም ይህንን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ሕፃናትን ጠልፈው በከረሜላ፣ በብስኩት እና በመሳሰሉት አታለው ለዝሙት የሚመኙአቸው የሚደፍሯቸው አሉ፡፡

በቤተሰብ ደረጃ ልጆችን ማሳደግ እንዴት እንደሆነ መሠረቱ የጠፉባቸው አሉ፡፡ አንዳንዶቹ ከመጠን በላይ ልጆችን በማዝናናት ያምናሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ ልጆች ትንሽ ጥፋት ሲያጠፉ አስረው በመግረፍ ያምናሉ፡፡ ልጆችን የተንከባከቡ መስሏቸው ከታሳሳቆች ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነትና አክብሮት በተመለከተ ወሰን /ድንበር/ ጠፍቶባቸው ትናንሾቹ ታላላቆቹን ሲመቱ /ሲደበድቡ/ ሲነሡ ማየት የተለመደ ሆኗል፡፡ ይህ ሁሉ አንድ ወጥ የሆነ ጥቅምና ጉዳቱን ያመዛዘነ የልጆች አስተዳደግ አለመኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡

## ፪.፪. ልጆች የሚያድጉበት አካባቢ

ልጆች የሚያድጉበትን አካባቢ ይመስላሉ፡፡ አካባቢ በልጆች ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ አለና፡፡ ይህ ደግሞ ምን ዓይነት አካባቢ እያሳደግናቸው ነው ምን ዓይነት ትምህርት እና ጥንቃቄ ይፈልጋሉ የሚሉትን ጥያቄዎች እንድናነሳ ያደርገናል፡፡ ለምሳሌ ንግድ አካባቢ የሚያድጉ ሕፃናት በንግድ ቦታ የሚያዩዋቸውን ነገሮች በኅሊናቸው ሊቀረጽ ይችላል፡፡ በንግድ ቦታ ሌቦች አሉ፡፡ ብዙ ውሸቶች ይነገራሉ፡፡ የሁለም ሰው ፍላጎት ገንዘብ ለማግኘት ይሆናል፡፡ በተለያየ ሱስ የተያዙ ሰዎች የሚበዙበት አካባቢም ልጅን ስናሳድግ የግድ ተከትለው የሚመጡ ችግሮች ይኖራሉ፡፡ ይህ ግንዛቤ ካለን ልጆችን የምናሳድግ ግበት አካባቢ የት መሆን እንዳለበት እንወስናለን፡፡ ሁኔታዎች አስገድደውን ችግር ሊፈጠር የሚችልበት አካባቢ እንኳን ቢያድጉ ዘወትር ምን ማስተማር እንዳለብን ቀድመን እንዘጋጃለን፡፡



www.ethiopianorthodox.org

### ፪.፫. ልጆች በልጆች ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ

ሌላው በልጆች አስተዳደግ ላይ ተጽዕኖ የሚያመጣው መሰል ልጆች የሚፈጽሙት ድርጊት ነው:: ልጆች በተፈጥሮ መሰል ጓደኞቻቸው የተናገሩትን ለመናገር የሚያደርጉትን ለመፈጸም ይፈልጋሉ:: ይህ ከመሰሎቻቸው የሚደርስባቸው ተጽእኖ ነው:: «ከአህያ ጋር የዋለች ጊደር...» የሚለው ተረት ትርጉሙም ይህ ነው:: አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸውን ተጨንቀው በሥርዓት እንደ ሚያሳድጉ ሁሉ ሥርዓት የሌላቸው በጣም ብዙ ልጆችም አሉ:: እነዚህ ሁለት የተለያየ መንገድ የተከተሉ ልጆች በመንደር ውስጥ፣ በጨዋታ ጊዜ ትምህርት ቤት ለትምህርት ሲሄዱ፣ እንዲሁም በሌላ አጋጣሚ ሊገናኙ ይችላሉ:: ይህ ዓይነቱ ችግር እንዳይከሰት ልጆችን ከልጆች ለይቶ ማሳደጉ ዘላቂ መፍትሔ አያመጣም ሁሉም ኅብረተሰብ ለመፍትሔው መነሣት ይገባዋል እንጂ»::

### ፪.፬ የሚማሩበት ት/ቤት

በአሁኑ ጊዜ የሚታዩት ትምህርት ቤቶች በከፍተኛ ደረጃ የሥነ ምግባር ችግር ይታይባቸዋል:: አሁን ያሉት ትምህርት ቤቶች ድሮ ከነበሩት በምን ተለዩ ስንል ድሮ ይሰጥ የነበረ አሁን ግን በብዙ ቦታ የቀረ ልጆች ጥሩ ሥነምግባር እንዲኖራቸው የሚረዳ የግብረገብነት ትምህርት አለመሰጠቱ ነው:: ለልጆች ፈሪሃ እግዚአብሔር በልቦናቸው እንዲያድር የሚያደርግ ትምህርት ሊሰጥና በየጊዜው እየተከታተሉ ማስተማር አስፈላጊ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል::

## ለዚህ ሁሉ ችግር መፍትሔው ምን ይሆን?

በመጠኑም ቢሆን የችግሩን አቅጣጫ ከጠቀስን መፍትሔ ሊሆን የሚችለውንም ማሳየት አለብን:: ልጆችን በመንከባከብ ረገድ መጀመሪያ የወላጆች ቀጥሎ የቤተ ዘመድ፣ የጐረቤት እያለ በአካባቢው ያሉ ሰዎች ሁሉ ኃላፊነት መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል:: እኛ ላልወለድነው ልጅ ምን አገባን ማለት የለብንም:: ለልጆች የተስተካከለ ዕድገት የሚያመጣው ለውጥ የሚኖርበትን አቅጣጫ ማሳየት ይገባል:: ልጆችን በመምከር፣ በማስተማር፣ ከዚያም አልፎ የኢኮኖሚ ድጋፍ ማድረግም





በሚያስፈልግበት ጊዜ የሚቻለውን ያህል ማድረግም ይጠበቅብናል:: በየአካባቢው ላለው ችግር ሁሉ መፍትሔ ለመፈለግ መነሣት የሚገባው የአካባቢው ኅብረተሰብ ነው:: በአቅማችን የምንችለውን ለማድረግ መንቀሳቀስ የሁላችንም ድርሻ ይሆናል:: በዚህ ረገድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እና ሰበካ ጉባኤ፣ የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ዕድሮች ማኅበራት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው መንቀሳቀስ ይገባቸዋል:: ችግሩ አሳሳቢ ነው:: ነገ ዛሬ በማለት ቀጠሮ የሚያዝለትም አይደለም:: ስለዚህም ልጆቻችንን በአግባቡ አሳድገን ለፍሬ ለማብቃት:–

### ፩. እንክብካቤና በቂ ክትትል ማድረግ

ምንም እንኳን መልካም ልጅ የእግዚአብሔር ስጦታ ቢሆንም የተሰጣቸውን በአግባቡ ይዞ ለፍሬ ማብቃት ግን የወላጆች ድርሻ ነው:: በመሆኑም ወላጆች ልጆቻቸውን በሚገባ እየተከታተሉ÷ እውነተኛ ፍቅራቸውን እየመገቧቸው ሊያሳድጓቸው ያስፈልጋል:: ምናልባትም የወላጆች ክትትልና ለልጆቻቸው የሚያደርጉት እንክብካቤ÷ እንደየቤተሰቡ የኑሮ ደረጃ ወይም የገቢ መጠን÷ የወላጆች የዕውቀት ደረጃና የሥራ ጠባይ÷ የልጆች ብዛትና የዕድሜ ደረጃ ሊለያይ ይችላል:: ለምሳሌ ብዙ ልጆች ያሉትና አንድ ልጅ ያለው እኩል እየተቆጣጠረ የሚያስፈልገውን እያሟላ ሊያሳድግ አይችልም:: የሥራቸው ጠባይ ብዙ ጊዜያቸውን ከልጆቻቸው ጋር እንዳያሳልፉ የሚያደርጋቸውና ብዙውን ጊዜ ከልጆቻቸው ጋር የሚያሳልፉት እኩል ናቸው ማለትም አይቻል ይሆናል:: እንዲሁም በሞት ወይም በሌላ ምክንያት በአባቱ ወይም በእናቱ እንክብካቤ ብቻ የሚያድግ ልጅና የሁለቱንም ፍቅርና እንክብካቤ እያገኘ የሚያድገው እኩል ላይሆኑ ይችላሉ::

ይሁን እንጂ÷ ምንም በቂ ገንዘብ ወይም ጊዜ ባይኖራቸው÷ የልጆቻቸውም ቁጥር ቢበዛ ወላጆች በሚችሉት መጠን ለልጆቻቸው ትኩረት ሊሰጡና ሊንከባከቧቸው ያስፈልጋል:: ወላጅነት በጊዜና በገንዘብ የሚተመን ሳይሆን ከፍቅር የተነሣ ራስን አሳልፎ እስከመስጠት የሚደርስበት ነው:: ይህ ሲባል ከበቅማችውም በላይ በሆነ መንገድ



www.ethiopianorthodox.org

ቁሳዊውንና ሥጋዊውን ፍላጎታቸውን ሁሉ ይሟላላቸው ማለት አይደለም፤ የእናትነት ወይም የአባትንት ፍቅራቸውን ያሳዩአቸው፥ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ውሏቸውን ጤናቸውን የትምህርታቸውን ሁኔታ ይከታተሏቸው ማለት እንጂ።

## ፬. አርአያ መሆን

ለልጅ በተለይም በሕፃንነቱ ጊዜያት ከወላጆቹ በላይ በዋቂ፥ ትልቅና የተከበረ አይኖርም። ሁሉን ነገር እንደወላጆቹ ቢያደርግ፥ ከወላጆቹ ቢሰማ ይመርጣል። ወላጆቹ ሲያደርጉ ያየውን ወይም በወላጆች የተነገረውን በቀላሉ ይቀበላል። ታዲያ በዚህን ጊዜ ወላጆች በልጆቻቸው ፊት ለሚያደርጉትም ሆነ ለሚናገሩት ነገር ሊጠነቀቁ ያስፈልጋል።

ከዚህ አንፃር አንድ ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ ለልጆቹ አርአያ ሆኖ ማሳደግ ብዙም አይከብደውም። አማትቦና ጸልዮ መመገብን፥ በሰንበትና በበዓላት ቀናት በአንድነት ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ማስቀደስን፥ በሥነ ሥዕል ፊት ቆሞ ጠዋትና ማታ ስብሐተ እግዚአብሔር ማድረስን፥ ለድሆች መመጽወትን፥ እውነተኛ ፍቅሩንና ለሌሎች ያለውን ርኅራኄ እያደረገ ያሳያቸዋል። ልጆችም፥ የቤተ ክርስቲያን እምነቷን ተባብለው፥ ጠበሏን ጠጥተው፥ ዕጣኑ ሽቷቸው፥ ትምህርቷን ተምረው፥ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተቀበሉ ፈሪሐ እግዚአብሔርን ገንዘብ አድርገው ስለሚያድጉ ወላጆቻቸውን መምሰላቸው፥ የወደፊቷ ሀገርና የቤተ ክርስቲያን ተረካቢ መሆናቸው አያጠራጥርም። ለዚህም የነቢዩ ሳሙኤልን እናት ሐናን ምሳሌ ማድረግ ይቻላል። ፩ሳሙ.፳፮፥፳፰።

በተቃራኒው ከኩርንችት በለስ እንደማይለቀሙ ሁሉ፥ ሰላም ከጠፋበት፥ ንዝንዝና ጭቅጭቅ ከነገሠበት፥ የመጠጥና የዕፅ ሱሰኝነት ከተቆጣጠረው ቤተሰብ መልካም ልጅ ለማግኘት ማሰብ ያልዘሩትን ለማጨድ እንደመሞከር ነው።





## ፭. መልካም ሲሠሩ ማበረታታት

ወላጅነት ልጆችን የመጨቆን፥ የመግዛትና የማስጨነቅ ሥልጣን አይደለም። በመሆኑም ልጆችን ባጠፉ ቁጥር መጨቅጨቅና መነዝነዝ አይገባም። ይልቁንም መልካም በሠሩ ቁጥር ማበረታታቱ ይመረጣል። መልካም ሲሠሩ ማሞገስ፣ ሁልጊዜም እንደዚህ እንዲሠሩ ማበረታታት፣ ሲያጠፉ ራሳቸውን እስከማረም ያደርሳቸዋል።

እንዲሁም ጥፋት ከፈጸሙ በኋላ ከመቆጣትና ዱላ ከማንሣት ይልቅ ማድረግ የሚገባቸውን አስቀድሞ ደረጃ በደረጃ መንገር ያስፈልጋል። ማድረግ የሚገባቸውን ቀስ በቀስ እየነገሩ ማሳደግ የተነገራቸውን ነገር አስፈላጊነት አምነውበት እንዲያደርጉና ለሓላፊነትም እንዲበቁ ያደርጋቸዋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «እናንተም አባቶች ሆይ፥ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጓቸው እንጂ አታስቆጡአቸው» በማለት አስገንዝቧል። /ኤፌ.፮፥፬/

ይህ ሲባል ምንም ዓይነት ጥፋት ቢያጠፉ አይቀጡ ማለት አይደለም። አልፎ አልፎ በአካልና በሥነ ልቡናቸው ላይ ጉዳት በማያመጣ መልኩ ወዲያው እንዳጠፉ በመጠኑ መቅጣት አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ በሚጐዳቸው ነገር ከመደብደብ ወይም እየጮኹ ከመቆጣትና የአንድ ጊዜ ጥፋታቸውን ዘወትር እያነሡ ከመውቀስ እንዲሁም ለሌላ ሰው ከመንገር ለተወሰኑ ደቂቃዎች ከጨዋታ መከልከልን የመሰሉ ቅጣቶችን መጠቀሙ ይመረጣል።

## ፮. ከጥፋት መጠበቅ

ሕፃናትን በለጋ ዕድሜአቸው ሊያበላሿቸው ከሚችሉ ነገሮች መጠበቅ ያስፈልጋል። ለምሳሌ፡ በዕድሜአቸው ከማይመጥኗቸው የቴሌቭዥን ፕሮግራሞችና ፊልሞች፣ መጥፎ ጠባይ ካላቸው ጓደኞች ወዘተ ... እንዲርቁ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ ሲባል ምን አልባትም እንዳይመለከቱ መከልከል የበለጠ እንዲጓጉ ስለሚያደርጋቸው በተቻለ መጠን በምክር መልክ መንገሩ ይመረጣል። አልያም ክፉውንና በጎውን እስኪለዩ ድረስ በፊታቸው የማይገቡ ነገሮችን አለማድረግ ለዕድሜአቸው



www.ethiopianorthodox.org

የማይመጥኑ ፊልሞችና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችንም አለማየት፣ በምትኩ ለእነርሱ የሚስማሙ ማለትም ለዕውቀታቸው ለሥነ ምግባራቸው መጉልበት፥ የቤተሰብ ፍቅር እንዲኖራቸው የሚያደርጉአቸውን ነገሮች እንዲመለከቱ የራስን ጥረት ማድረግ ያስፈ ልጋል።

አለበለዚያ ለዕድሜአቸው የማይመጥናቸውንና ለወደፊቱም ሕይወታቸው የማይጠቅማቸውን ሁሉ እያዩ ቢያድጉ ንጹሕ አእምሮአቸውን ለበቀል መርዝ እንደመጋት ነው። ለዚህ አንድ ምሳሌ ማንሣት ይቻላል። እናትና አባቷ በፍቺ የተለያዩና ከአባቷ ጋር የምትኖር አንዲት የስምንት ዓመት ልጅ አባቷ አቤት ውስጥ የወሲብ ቪድዮ ፊልሞችን እየተወ ስለሚሔድ ወጣ ባለ ቁጥር ያን እያየች ሌሊት በሕልሟ እየባነነች እንደተቸገረችና ያየችውንም በተግባር ለመፈጸም እንደተገፋፋች በቅርቡ ከደረሰን ደብዳቤ ለመረዳት ችለ ናል።

ልጅቷ ያየችውን ነገር ምንነት ባትረዳም ለመፈጸም መሞከሯ ምን ያህል ተጽዕኖ እንዳሳደረባት ለመገንዘብ አያዳግትም።

ስለዚህ ሕፃናትን የሚጠቅማቸውን ከማይጠቅማቸው እንለይላቸው ከጥፋትም ልንጠብቃቸው ያስፈልጋል።

እንግዲህ ልጅን ተጣሞ ካደገ በኋላ ማቃናው ጠፍቶ ከመቸገርና በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ «የዛሬ ልጅ» እያሉ ከማውገዝ በአግባቡ ማሳደግ ያስፈልጋል። ለዚህም ለነገው ትውልድ መስተካከል ከዛሬ ወላጆች ከፍተኛ ጥረት ይጠበቃል። የዛሬው ወላጅ መልካም ከሆነ መልካም የሚያፈራበት ራሱን ቀርጾ የማያወጣበት ምንም ምክንያት አይኖርም። ከሁሉ በላይ ደግሞ እግዚአብሔር የተባረከ ልጅ እንዲሰጥ መጸለይ፣ ከቤተ ክርስቲያን ሳይቀር በሰው ፊት ብቻ ሳይሆን* በእግዚአብሔርም ፊት እንዲያድግ ማድረግ ያስፈልጋል። ሉቃ.፪፥፶፪። ያን ጊዜ ነው የሀገርም ሆነ የቤተ ክርስቲያን ተረካቢ መሆን የሚችለው። ገና ዛሬ በልጅነቱ ያላሳወቅነውን ቤተ ክርስቲያንም ሆነ አገር ነገ ተረከብ ማለት ቀንበር እንደመጫን ከባሰም ሽጣት ብሎ አሳልፎ እንደመስጠት ነው።

ስለዚህ ሀገሩንና ቤተ ክርስቲያኑን አፍቃሪ ወላጆቹን አክባሪ ዜጋ ለማፍራት ልጅን በፍቅርና በመልካም አያያዝ፥ ፈሪሐ እግዚአብሔር እንዲያድርበት አድርጎ ማሳደግ ይገባል። ለሁሉም የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል እማላጅነት አይለየን።





# ፍቅር፣ ወጣትነት፣ መንፈሳዊነት

በዲ/ን ኤፍሬም እሸቴ

ብዙ ወጣቶች በጋራ የሚያውቋቸው፣ ዘወትር የሚነጋገሩባቸው፣ ሕይወታቸውን እስከመለወጥ የሚደርሱባቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ከእነዚህም ነገሮች መካከል ከተቃራኒ ጾታ ጋር ያላቸው ግንኙነት አንዱ ነው። ይህ በዕድሜያቸውና በተፈጥሯዊ ለውጣቸው ምክንያት የሚመጣ ጠባይ በመሆኑ ወጣቶቹ መንፈሳውያን ሆኑም አልሆኑ የዚህ ነገር ተጋሪዎች ናቸው። ለዓቅመ ሔዋንና ለዓቅመ አዳም ከደረሱበት ጊዜ አንሥቶ አስተሳሰባቸውና አመለካከታቸው፣ በት/ቤትም ሆነ በሥራ ከሚያገኟቸው በጾታ ተቃራኒዎቻቸው ከሆኑት ጋር ያላቸው ጉድኝት እንደ ሕፃንነቱ ወቅት አይሆንም። ራሳቸውን ይመረምራሉ። እነርሱ ስላልደረሱበት ነገር ለማወቅ ያላቸው ጉጉት ይጨምራል። በሚያነቧቸው መጽሔቶች፣ ጋዜጦች፣ መጻሕፍት፤ በሚመለከቷቸው ፊልሞችና ድራማዎች በየመንገዱ ከሚያዩዋቸው ነገሮች በመነሣት እነርሱም ያንን የሚያደርጉበትን ቀን ይናፍቃሉ። ይህ ናፍቆትና ፍላጎትም ያድግና በተግባር ይተረጎማል። በዚህም ምክንያት የብዙ ወጣቶች ሕይወት ሊበላሽ ይችላል።

በሀገራችንም ሆነ በየሰንበት ት/ቤቶቻችን ወጣቶች ከተቃራኒ ጾታዎች ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባው ግንኙነት ለማወቅ የሚችሉባቸው አጋጣሚዎች ብዙ የሉም። በግልጽ ሊያውቋቸው የሚገቡ ነገሮች በ«ነውርነት» ተሸፍነው ስለሚታለፉ ኋላ ለወጣቶቹ ሕይወት እንቅፋት ይሆናሉ። እስከ ጋብቻቸው ዕለተ ድረስ ራሳቸውን ጠብቀው ለመቆየት፣ ከጋብቻ በፊት በሚፈጸሙ ግንኙነቶች ላለመሰናከል ማወቅ የሚገባቸውን ቁምነገሮች ባለመረዳታቸው ይጎዳሉ። አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከሆነ ብዙ ወጣቶች ቅድመ ጋብቻ በሚፈጠሩ የግብረ ሥጋ ግንኙነቶች የሚመሳለሱ ናቸው። በዚህም ምክንያት የሚከሰቱ የተለያዩ እክሎች አሉ። በበሽታ መጠቃት፣ ያለጊዜና ያለዕድሜ ማርገዝ፣ ያለጊዜው የተረገዘውን ፅንስ ማስወረድ፣ ለማስወረድ በሚደረግ ሙከራም ሕይወትን ማጣት፤ ከትምህርትና ከሥራ መስተጓጐል፤



www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ ሁሉ ነገር በኋላም በመንፈስ ጭንቀት መሰቃየት የጥፋተኝነት ስሜት መሰማት፣ ወዘተ ... ሊጠቀሱ የሚችሉ ችግሮች ናቸው።

በዚህች አጭር ጽሑፍ እነዚህ ሁሉ ችግሮች ይቀረፉ ዘንድ ምን መደረግ አለበት? የሚለውን ጥያቄ መመለስ በጣም አስቸጋሪ ነው። ይሁን እንጂ ትኩረት ከሚሹት ጉዳዮች መካከል አንዱን መዘን እና ውጣ «ፍቅር»።

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ «ፍቅር ምንድነው?» የሚለውን ጥያቄ መመለስ አይደለም። የተቃራኒ ጾታ ፍቅር በተለይም ከወጣትነትና ከመንፈሳዊነት አንጻር ያለውን ገጽታና ሊኖረው የሚገባውን አካሔድ ለመመልከት ይሞክራል።

«ፍቅር» የሚለው ቃል በብዙ ወጣቶች ተወዳጅ ቃል ነው። ከየንግግራቸው ውስጥ አይጠፋም። ቀልዳቸውና ጨዋታቸው ራሱ የሚሟሸው በርሱ ነው። አሁን አሁንማ በጣም የሚወደድ መብልና መጠጥ ሁሉ ላይ «በፍቅር የሚወደድ» የሚል ቅጥያ ይገባለት ይዟል። ይሁን እንጂ የቃሉ ትርጉም ትክክለኛውን ቦታ ባለማግኘቱ ወጣቶቹ ይጎዱበታል። ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመላለሱት ወጣቶችም ምንም እንኳን ዘወትር ቃለ እግዚአብሔር የሚሰሙ፣ መዝሙር የሚያዳምጡ ቢሆኑም ወጣቶች ናቸውና ችግሩ እነርሱንም ይመለከታል። ጊዜ ሰጥቶ ለሚያዳምጣቸው፣ የሚብሰለሰሉበትን ነገር ሊካፈላቸው ፈቃደኛ ለሆነ ሰው የሚያካፍሉት ቁምነገር ነው። በዚህም ምክንያት መንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚበላሽባቸው ወንድሞችና እኅቶች ጥቂቶች አይደሉም። ስለ ዚህ ችግሩ እነርሱንም የሚመለከት መሆኑን መገንዘቡ አስፈላጊ ይሆናል።

በወጣትነት ወቅት በተቃራኒ ጾታዎች መካከል መሳሳብ ይኖራል። መሳሳብ ሁሉ ግን ለትዳር የሚያበቃ፣ መሠረት ያለው፣ በምንም ዓይነት ችግር የማይነዋወጽ፣ በዐለት ላይ የተመሠረተ አይደለም። አብዛኞቹ በጊዜያዊ መቀራረቦች፣ መተያየቶችና «እኔስ ይህንን ለማድረግ ምን ይጎድለኛል?» ከሚሉ የወጣትነት ስሜቶች የሚፈጠሩ ናቸው። በት/ቤት የሚገናኙ፣ በሰፈር የሚተያዩ፣ በመንገድ የሚገናኙ፣ ወዘተ ወጣቶች የሚፈጥሩት መቀራረብና «ወደድኩህ ወደድኩሽ» መባባል ሁሉ የሚዘልቅ ላይሆን ይችላል።





ስለዚህም የወጣቶቹ መቀራረብ፣ «መፈቃቀር» መሠረቱ ምን መሆኑን መረዳት ይሻል። ከዚህም በመነሣት በ«ፍቅር» ስም የሚጀመሩ አንዳንድ ግንኙነቶችን ከሚከተሉት ነጥቦች አንጻር ለመመዘን እንሞክራለን።

## ፩. የግብረ ሥጋ ግንኙነትን መሠረት ያደረገ ፍቅር

የአንዳንድ ሰዎች ፍቅር መታወቂያው ያፈቀሩትን ሰው በሥጋ ለማወቅ የሚደረግ ችኩልነት ነው። ይወቁትም አይወቁትም፣ ያለፈ ታሪኩ ምንም ይሁን ምን፣ ግንኙነታቸው ነገ ችግርን ይዞ ይምጣም አይምጣ የሚያስደስታቸው ካፈቀሩት ሰው ጋር በዝሙት መውደቅ ብቻ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱሳችን የምናገኘው የአምኖንና የትዕማር ታሪክ ለዚህ አብነት መሆን ይችላል። አምኖን ከትዕማር ጋር በፍቅር በመጠመዱ ለመታመም ደርሶ ነበር። ነገር ግን ያለፈቃዷ /በጉልበት/ ክብሯን ካስነሣት በኋላ ፍቅር ድራሹ ጠፋ፣ ይልቁንም የቀደመ ፍቅሩ በጥላቻ ተተካ። ፪ኛሳሙ.፲፫፥፩-፴፱። በእውነት የአምኖን ፍቅር እውነተኛ ፍቅር ነበርን? እውነተኛ ፍቅርስ ከሆነ በቶሎ ወደ ጥላቻ ለመድረስ ያበቃው ምን ነገር ተፈጠረ?

የአምኖን ፍቅር እውነተኛ አልነበረም። የዝሙት ፍላጎት እንጂ። ዛሬም አንዳንድ ወጣቶች በዚህ ዓይነቱ አምኖናዊ ጾር በመነደፋቸው የሌላውን ሕይወት ለማበላሸት ላይ ታች ይላሉ። ምንም የማያውቁ ሴቶችን በማፋጭ አንደበታቸው፣ በፍቅር ስም ይሸነግላሉ። ያታልሏቸዋል፣ በዝሙትም ይጥሏቸዋል። ችግሩ ሲመጣ ግን ጀርባቸውን ይሰጧቸዋል።

መንፈሳውያን ወጣቶችም ይህንን ልናስተውል ይገባል። ስለዚህ የምንወዳቸው ሰዎች ጠባይ በጊዜያዊ የሥጋ ፍላጎት ላይ የተመረከዘ ከሆነ ፍቅራቸው ዘላቂ አለመሆኑን እንገነዘባለን። አበባውን ከቀጠፉ፣ የፈለጉትን ካገኙ በኋላ አምኖናዊ ጠባያቸው ያገረሽባቸዋልና።

## ፪. በጊዜያዊ ጓደኝነት ላይ የተመሠረተ ፍቅር

በተለያዩ አጋጣሚዎች ከሰዎች ጋር መተዋወቅ፣ መግባባት፣ ሐሳብ ለሐሳብ፣ ንግግር ለንግግር መጣጣም ይኖራል። መግባባቶች ሁሉ ግን ወደ ትዳር ለመሔድ የሚያበቁ መሆን የለባቸውም። መጠናናት፣ መለማመድ፣ ፈቃደ እግዚአብሔርን መጠየቅ ይገባል። አንዳንድ ወጣቶች



www.ethiopianorthodox.org

ከመቀራረባቸው ብዛት የሚፈጠርን «ጓደኝነት» ለ«ፍቅር» በመስጠት ይሳሳታሉ:: ለሳምንታትና ለወራት መለያየት እስከነመፈጠራቸው ሊያ ረሳሳቸው እንደሚችል ይዘነጋሉ::

ወጣቶቹ የሚውሉባቸው ቦታዎች፣ የሚሠሯቸው ሥራዎች፣ ት/ቤቶቻቸው፣ በብዛት በጓደኝነት መሰብሰባቸው ለእንደዚህ ዓይነቶቹ መቀራረቦች በር ይከፍታሉ::

ከዚህ አንጻር በጊዜያዊ መቀራረብ ላይ የሚፈጠር «ፍቅር»ን መሠረት ያለው አድርጎ በማየት ነገን አርቆ ከመመልከት መከልከል አይጠገባም:: በዚህ መልኩ ተጀምረው ለሠመረ ትዳር የበቁ ግንኙነቶች የሉም ለማለት ባንችልም በአብዛኛው ሲታዩ ግን መጨረሻቸው ስለማያምር መንፈሳውያን ወጣቶች መጠንቀቅ ይገባቸዋል::

## ፫. በኢኮኖሚያዊና ስሜታዊ መረጋጋት ላይ የተመሠረተ ፍቅር

ከላይ ከተገለጡት ሁለት የፍቅር ዓይነቶች በተለየ መልኩ እንዲህ ዓይነቱ «ፍቅር» የያዛቸው ሰዎች ዓላማቸው ትዳር ላይ ያዘነበለ ነው:: ከወጣትነት የዕድሜ ጣራ ያለፉ፣ ትዳር መያዣ ዕድሜያቸው እያለፈ መምጣቱ የተሰማቸው፣ ቤትና ንብረት መያዝ ልጅ መውለድ እንዳለባቸው የሚሰማቸውና ብዙውንም ጊዜ «ምነው አግባ/ቢ/ እንጂ!» የሚሉ ጉትጎታዎች የበዙባቸው ሰዎች ናቸው:: ጥሩ ገንዘብ፣ ሥራ፣ የዕውቀት ደረጃ አላቸው:: የሚፈልጉት ነገር ሁሉ ቢኖራቸውም የጎደለ ነገር መኖሩ ስለሚሠማቸው ዕረፍት አይኖራቸውም:: ያም የትዳር ጓደኛ ነው:: ስለዚህም ያንን የጎደለ ነገር ለማሟላት ስለሚሹ ያገባሉ:: የሚያገቡት ግን በምድራዊ ጥሪቱ የሚመስላቸውን ነው::

የነዚህ ዓይነት ሰዎች ፍቅር መለኪያው፣ ያላቸው ምድራዊ ሀብትና የዕውቀት ደረጃ በመሆኑ ፍቅሩ መሠረት ያለው ራስን ለሌላው አሳልፎ እስከመስጠት ሊያደርስ የሚችል አይደለም:: አንዳንድ ጊዜም በገንዘብ ምክንያት በሚፈጠሩ አለመግባባቶች የሚበጣበጡ፣ ከትዳር ጓደኛ ውጪ በሚፈጸሙ ውስልትናዎች የተበላሹ ይሆናሉ::

ስለዚህም ያፈቀርንበት፣ ወይም የተፈቀርንበት ምክንያት ከምድራዊ ሀብትና ዕውቀት ውጪ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል::





## ፬. ራስን ለሌላው አሳልፎ በመስጠት ላይ የተመሠረተ ፍቅር

ፍቅር ማለት ለራስ ምንም ሳይሳሱ ራስን ለተወዳጁ አሳልፎ መስጠት፣ ከእኔ ይልቅ የምወደው ሰው ይቅደም ማለት፣ እኔ ቢደረግልኝ የምወደው ነገር ከእኔ በፊት ለምወደው ሰው ይደረግለት ማለት ነው:: የተቃና መንፈሳዊ ትዳር መሠረት የሚሆነው ፍቅር ይህንን ያዘለ ነው:: ነገር ግን «ለምንወደው ሰው ራሳችንን አሳልፈን የምንሰጠው ምን ድረስ ነው?» የሚለው ጥያቄ መመለስ አለበት::

አንዳንድ ወጣቶች የሚመላለሱበት ፍቅር ራስን ለሌላው መሥዋዕት አድርጎ በመስጠት ላይ የተመሠረተ ነው:: የመዋደዳቸው መገለጫው ራሳቸውን ለሚያፈቅሩት ሰው በመስጠት የሚገለጽ ይመስላቸዋል:: ሌሎቹ ደግሞ መፈቀር አለመፈቀራቸውን ለማወቅ ራሳቸው የሚያደርጉትን፣ ሊያደርጉትም የማይፈልጉትን ጥያቄ ይጠይቃሉ:: «የምትወደኝ/ጂኝ/ ከሆነ ... አድርግልኝ/ጊልኝ» ይላሉ:: ይህ ካልደተረገላቸው ያልተፈቀሩ፣ ከተደረገላቸው ደግሞ የተፈቀሩ ይመስላቸዋል:: ይህን ግን የተሳሳተ የፍቅር መንገድ ነው:: እውነተኛ ፍቅር በዚህ አይገለጽም::

የዚህ ፍቅር ተጠቂ የሆኑ ወጣቶች ከአፍቃሪዎቻቸው በሚቀርቡላቸው «የተሳሳቱ የመሥዋዕትነት ጥያቄዎች» ሕይወታቸው ይበላሻል:: ማፍቀራቸውን ለሌላው ወገን በግልጽ ለማሳየት ክብረ ንጽሕናቸውን ቅድመ ጋብቻ የሚያቀርቡ ወጣቶች አያሌ ናቸው:: ይሁን እንጂ ያስቡት ቀርቶ ያሳሰቡት ይተካና የፈለጉት ፍቅር በንቀት፣ በጥላቻ፣ በኩራት ይተካል:: ይህ በወደፊቱ ሕይወታቸው ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ቀላል አይሆንም::

ስለዚህ መንፈሳውያን ወጣቶች ይህንን በመረዳት ቅድመ ጋብቻ የሚቀርቡ አላስፈላጊ «መስዋዕትነቶች»ን መረዳት ይኖርብናል:: በምድር በሥጋችን፣ በሰማይ በነፍሳችን ከሚጎዳ ነገርም ራሳችንን እንጠብቅ::

## ፭. በቅናት የታጠረ ፍቅር

የአንዳንድ ወጣቶች ፍቅር ደግሞ መገለጫው ቅናት ነው:: ይህ ዓይነቱ በቅናት የታጠረ ፍቅር እውነተኛ ባለመሆኑ ለተፈቃሪዎች ሰላም የማይሰጥ ምድራዊ ገሀነም ነው:: «የት ሄድክ/ሽ/፣ የት ነበርክ/ሽ/፣



www.ethiopianorthodox.org

ከነማን ጋር ወጣህ/ሽ/?» ሰዎች ያፈቀሩት ሰው ጥሩ ሲለብስ፣ ሲያምር በት፣ ከሰው ሁሉ ጋር ሲግባባ፣ በሰዎች ሲወደድ፣ በሥራው ከፍ ያለ ደረጃ ሲደርስ አይደሰቱም። የሚያመልጣቸው ይመስላቸዋል። ይጨነቃሉ። ስለዚህም ይቀናሉ። ቅናታቸውም ከፍቅር የመነጨ መሆኑ እንዲታወቅላቸውም ይፈልጋሉ።

የዚህ ዓይነቱ ፍቅር መሠረቱ በአብዛኛው ውጫዊ ተክለ ቁመና /Physical appearance/ ነው። ውስጣዊ ውበት ቦታ የለውም። ታይቶ የሚጠፋ አፍአዊ ነው። ያ አፍአዊ ውበት ሲደበዝዝ ወይም ከዚያ የበለጠ ሲገኝ ይቀራል ይሻራል።

***ማጠቃለያ:*** ወጣትነት የነገው ማንነት መሠረት የሚጣልበት ጊዜ ነው። በወጣትነት የተበላሸን ሕይወት ለማረቅ በጣም አስቸጋሪ ነው። ከነዚህ የወጣቶች ሕይወት ከሚበላሹባቸው ነገሮች መካከል ደግሞ ከተቃራኒ ጾታ ጋር የሚኖረን ፍቅር አንዱ መሆኑን ከላይ ተመልክተናል። ስለዚህም ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን መገንዘብ ይኖርብናል።

በወጣትነት ስሜት የሚመጡ ፍላጎቶችን ሁሉ ማስተናገድ አይገባም። ያለጊዜያቸው ከመጡ ፈተናዎች ናቸውና ልንቃወማቸው ይገባናል። ፲፪ኛን ክፍል ለመጨረስ ያልደረሰ ወጣት በፍቅር ምክንያት ፈተና ቢገጥመው ውድቀቱ ሁለት ነው የሚሆነው። ወደፊት ሊያገኘው የሚችለውን እውነተኛ ፍቅር በጊዜያዊው ምክንያት ያጣል፤ እንደገናም የወደፊት ሕይወቱም ይሰነካከላል።

ከዚህ ሁሉ አስቀድሞ ግን ራሳችንን ለመቻል መጣር፣ ሕይወታችንን በመንፈሳዊ ሕይወት ማጎልመስ ይገባናል። በዚህም ምክንያት ከሚመጡ ክፉ የጎልማሳነት ምኞቶች መራቅ የምንችለው ይህንን ስንረዳ ብቻ ነው። ፪ጢሞ ፪፥፳፪።

በአጠቃላይ በፍቅር ሰበብ የሚመጡብንን ፈተናዎች ለመቋቋም፣ እውነተኛውን ከሐሰቱ ለመለየት እንጣር፤ ፈቃደ እግዚአብሔር ርንም እንጠይቅ። የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



www.ethiopianorthodox.org